

# ወደ ዳነ ልብ የተሸጋገረ ህዝብ

የቤተክርስቲያን ሚና፣ ለፈውስ፣ለይቅርታ እና ለእርቅ

በዶ/ር ሪሃነን ሎይድ

ረዳት ፀሐፊ፡ መጋቢ ጆሴፍ ኒያሙተራ

ወደ ዳነ ልብ የተሸጋገረ ህዝብ

በዘር ግጭት ምክኒያት የመጡ ቁስሎችን መፈወስ

በዶ/ር ሪሃነን ሎይድ

ረዳት ፀሐፊ፡ መጋቢ ጆሴፍ ኒያሙተራ

አምስተኛ ዕትም

መብቱ ሁሉ በህግ የተጠበቀ ነው

የአሳታሚዉ መብት ‘Copyright ©’ እ.አ.አ ሰኔ 2016 በሜርሲ ሚኒስትሪስ ኢንተርናሽናል የተጠበቀ ነዉ

CP 442, 1215 ጄኔቫ 15, ስዊዘርላንድ

ኢሜይል: rhiannon@healingthenations.co.uk

ይህንን የስልጠና መጽሐፍ መመሪያ በግልዎ ለመጠቀም ወይም ለእርቅ የሚደረጉ ሴሚናሮች መጠቀም ሲቻል፤ ትርፍ ለማግኘት መጠቀም ግን የተከለከለ ነዉ። የወሰድናቸዉ ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ከጠቀስናቸዉ ዉጪ ያሉት በሙሉ በዓለም አቀፍ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር “New International Version® NIV®, Copyright ©1973, 1978, 1984” በዞንደርቫል ማተሚያ ቤት ከታተመዉ የወሰድን ሲሆን መብቱ ሁሉ በህግ የተጠበቀ ነዉ።

ይህንን የስልጠና መመሪያ በሌላ ቋንቋ ተርጉሞ ለመጠቀም ከፈለጉ፤ እባክዎ በኢሜል አድራሻዉ መጀመሪያ ያስፈቅዱ።

# ምስጋና

## ይህ መመሪያ እዉን እንዲሆን ግብአቶችን ለሰጡን:

ዋናዉን ጽሁፍ ለመገምገምና ለማሻሻል ሰፊ የሆነ ጊዜያቸዉን የሰዉትን መጋቢ ጆሴፍ ኒያሙትራ (ከሩዋንዳ)፤ ትልቅ ዋጋ ያለዉን አስተዋጽኦ ላበረከቱት መጋቢ አናስታሴ ሳባሙንጉ (ከሩዋንዳ)፤ በአባሪ ዉስጥ የተጻፈዉን እንዲሁም በእጅ የተጻፈዉን ወደ ፈረንሳይኛ ቋንቋ ተርጉማ የፃፈችዉን ካቲ ፈሮሄሊች (ከጄኔቫ)፤ የመጀመሪያዉን እትሜን በማቀናጀትና መመሪያዉ መሠረት እንዲይዝ እንዲሁም ቀጣዩ ህትመት እንዲሳካ በማረም የረዳችኝን ክርስቲን ብሬሰር (ከዩ ኤስ ኤ አሜሪካ፣ ጄኔቫ የነበረች እና ቀድሞ ደግሞ ሩዋንዳ የነበረች)፤ የላቀ ግንዛቤ እንዳገኝ ያገዙኝን ፣ ዲሞክራቲክ ኮንጎ እና ደቡብ አፍሪካ ሀገራት ያሉ የዕርቀ ሰላም ድርጅቶች፤ ብዙ የእርማት ሥራዎችን የረዱኝን ሌስ ሮበርትስ (ከዌልስ) እንዲሁም ማዳ ኤንገልበርት (ከደቡብ አፍሪካ)፤

ከመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የወሰድኳቸዉን ጥቅሶች በትጋት ያዩልኝን በአንታዮች ቤተ ክርስቲያን (ዌልስ) የሚገኙ በርካታ ጓደኞች፤ ድንቅ ስዕሎችን ያዘጋጁልኝ ክርስቲን ጋርቡት፣ ግሪት ከኒግ፣ ጆን ራይት፣ ኢለን ዱሃረና ክሪስ ታይለር፤ ከሥነመለኮት አንጻር የቀደመዉን መመሪያ ለማረምና ቅርጽ ለማስያዝ ሰፊ የሆነ ጊዜ የሰጡኝን ሬቨረንድ ሀይወል ራይስ ኤድዋረድስ (ከዌልስ)፤ይህ የተሻሻለዉ ዕትም ጥሩ ቅርጽ እንዲይዝ የረዱኝን ዋይን ፐላት፣ አንዲ ሊቨርስ እና ዲቪድ ኮልማንን፤ ይህ መመሪያ እንዲዘጋጅ በታማኝነት ሲፀልዩልኝ የነበሩትን ሌራቸር ሚኒሰትሪ፣ ጄኔቫ እና ዓለም ላይ ለሚገኙ ጓደኞቼ ሁሉ ምስጋናዬ የላቀ ነዉ።

# ማዉጫ

**ምስጋና** i

**ማዉጫ** ii

**መግቢያ** 1

የቤት ቅርጽ የያዘዉን ምስል መግለጽ 3

**መሠረትን መጣል** 3

**ግድግዳዉን መገንባት** 4

**ኮርኒሱን ማስገባት** 4

**ጣሪያውን መስራት** 4

**ክፍል አንድ: መሠረትን መጣል** 4

የእግዚአብሔርን የልብ ሀሳብ መረዳት እና መለማመድ 4

**ትምህርት አንድ** 7

**ስለ እርስ በእርስ ግንኙነቶች የእግዚአብሔር የመጀመሪያው ዓላማ** 7

**እግዚአብሔር እኛን ሲፈጥረን የነበረዉን ሃሳብ መረዳት** 7

1) **ሥላሴ -ለግንኙነት ፍጹም የሆነዉ ምሳሌ** 7

**በስላሴዎች መካከል የነበረዉ ህብረት አስደናቂ ከሆነ፣ እኛን ለመፍጠር ለምን ወሰኑ?** 8

2) **የተለያዩ ብሔሮች መኖራቸዉ፣ በረከት ነዉ ወይስ መርገም?** 10

**የተለያዩ ነገር ግን እኩል ዋጋ የሚሰጣቸዉ** 10

3) **የተፈጠረዉ ስህተት ምን ነበር?** 11

**ትምህርት ሁለት** 13

የቅድመ ፍረጃ አስከፊው ኃይል፡ መራራ ሥሮች 13

**ሰዎች የቅድመ ፍረጃን አደገኝነት እንዲረዱ እና  እንዲተውት መርዳት።** 13

1) **ቅድመ ፍረጃ ምን ማለት ነዉ?** 13

2) **ቅድመ ፍረጃን መለየትና ይህ አመለካከት በእኛ ዉስጥ እንዳለ ማመን** 14

3) **መንሰኤ፡ መጥፎ ወደሆነ ግንኙነት የመሩን እነዚህ ቅድመ ፍረጃዎቻችን እና እምነቶቻችንን ከየት ተማርናቸዉ?** 15

**የዛፍ ምስል ህይወታችንን ይወክላል ብለን ብናስብ** 16

4) **ኢየሱስ – ምንም ቅድመ ፍረጃ የሌለበት ነው።** 17

5) **በኢየሱስ በመኖር ለለውጥ ያለ ተስፋ** 18

የታደሰዉ ማንነት 22

**በተቀደሰዉ ህዝብ ዉስጥ የዳነ ማንነትን መፈለግ** 22

1) **በቤተክርስቲያን ዉስጥ ያለ መገለል** 22

2) **ለእግዚአብሔር የተመረጠ ቅዱስ ህዝብ** 23

**በብሉይ ኪዳን** 23

***በአዲስ ኪዳን*** 24

**የሁሉም ቡድን ህዝብ ይጠቃለላል** 25

**ሁሉም እኩል ዋጋ ያለዉ ይሆናል** 26

3) **በቅዱሱ ህዝብ የሚዋጀዉ ምንድነዉ?** 26

**የተዋጀ ማንነት** 27

**የተዋጀ ብሔር** 27

**የተዋጀ ባህል** 28

4) **የእግዚአብሔርን ቅዱስ ህዝብ እውነታ ያለመረዳት አስከፊነት** 29

5) **የቅዱሱ ህዝብ አካል መሆን አዲስ ነጻነትን ይሰጠናል** 31

**ትምህርት አራት** **32**

ቤተክርስቲያን እንደ የለውጥ ማዕከል /ወኪል/ 32

**ትምህርት አምስት** **38**

የእግዚአብሔር ፍቅር እና መከራ 38

እግዚአብሔርን እንደ አፍቃሪ አባት ማወቅ 47

**ክፍል ሁለት** **57**

**ግድግዳዎችን መገንባት** **57**

**ሌባው** **59**

የቆሰለ ልብ 66

**ትምህርት ዘጠኝ** **77**

ለሰው ልጆች መከራ የእግዚአብሔር መልስ 77

የመስቀሉ ሥራ 88

**ክፍል ሶስት** **92**

**ጣሪያውን መክደን** **92**

የጎዱንን ይቅር ስለማለት /ይቅርታ ማድረግ/ 94

ንስሀ የመግባት የለውጥ ሀይል እና ይቅርታ እንዴት መጠየቅ አለብን 104

የቡድናችንን ( የእኛ ወገን የሆኑትን) ሀጢያት በመናዘዝ ሰላምን ለማስፈን የራሳችንን ድርሻ መወጣት(ማቴ 5፡9) 114

**ክፍል 4** **123**

**ቆርቆሮውን ማልበስ** **123**

በረከትን ማወጅ 126

ከዚህ ወደየት እንሄዳለን? 130

**አባሪ** **137**

**ሀ/ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር እና መከራን በተመለከተ ተጨማሪ ሀሳቦች** **137**

**ለ/ አስደናቂውን ሰማያዊውን አባትህን ማወቅ** **144**

**ሐ) አሰቃቂ (አጋጣሚ) እና አሳዛኝ ሁኔታን መረዳት** **145**

**መ) የውስጥ ስብራትን /ቁስልን/ መፈወስ (*ካለብን የውስጥ ቁስል መዳን*)** **152**

**ሠ) ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ሰዎች ማገልገል** **166**

**ረ/ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ስብስብ** **172**

# መግቢያ

ዛሬ የምንኖርባትን ዓለም ስንመለከት፣ በሁሉም ሥፍራዎች ግጭቶች እንዳሉ ማየት እንችላለን። በቡድኖች መካከል ያለዉ የኃይል ፉክክር ተባብሶ፤ አንዳንዴ ዉጤቱ ወደ ዘር ማጥፋት ሲያመራ እናያለን። የተረጋጋች ሀገር ትሆናለች ተብላ ታስባ በነበረችው ሀገር ኬንያ እንኳን በድንገት የሚባባስ አስከፊ የሆነ የብሔር ጥቃቶች ይከሰቱባታል።

ለነዚህ ሁሉ ጉዳቶች መልስ ይኖር ይሆን? በኃጢአት ለተሞላችው እና ለተጎዳችው አለማችን ተስፋ ይኖር ይሆን? ተስፋ እንዳለ እናምናለን! ምክንያቱም እግዚአብሔር የተስፋ አምላክ ነዉ! ይህ ደግሞ የእርሱ ባህሪ ነዉ፤ እርሱ ከባህሪይዉ ዉጪ ሌላ ሊሆን አይችልም። እግዝአብሔር የራሱን ቤተክርስቲያን በተለያዩ ህዝቦች መካከል የፈዉስ እና የእርቅ ወኪል እንድትሆንና ሊጠቀምባትም እቅድ አለዉ። ይሁን እንጂ በመጀመሪያ እራሷ ቤተክርስቲያን መፈወስ አለባት።

ይህ የማስተማሪያ መመሪያ በመጀመሪያ የተዘጋጀዉ እ.አ.አ በ1994 በሩዋንዳ በተፈጠረዉ አስከፊዉ የዘር ማጥፋት በነበረበት ጊዜ ነበር። በመጀመሪያ በተደረገዉ ጉብኝት ጊዜም ከተለያዩ ቤተ እምነቶችና ቡድኖች የተዉጣጡ ክርስቲያን የሆኑ መሪዎች ስለቤተክርስቲያን ዉድቀት እና ስለሚያስፈልገው ውጤት ለመነጋገር ስብሰባ አደረጉ። በዚህም ወቅት የተጠየቀ ወሳኝ የሆነ ጥያቄ ነበር፤ ይህም ጥያቄ 85 በመቶ የሚሆነዉ የሀገሪቱ ህዝብ ወደ ቤተክርስቲያን በሚሄድበት ሀገር ቤተክርስቲያን ሀገሪቷን ለመፈወስ ያላት ሚና ምን እንደ ሆነ የሚጠይቅ ነበር። በዚህ ጊዜ ነበር የእግዚአብሔርን ፈዋሽ የሆነዉን ፍቅር፣ የፈዉስ ተአምራትን ማግኘት የጀመሩት፤ እርቅም የወረደዉ። በዚህ የቤተክርስቲያን መሪዎችም በነበራቸዉ በጎ ምላሽ በሁሉም የሩዋንዳ ከተሞች፣ ለቤተክርስቲያን መሪዎች ለሶስት ቀናት የቆየ ሴሚናር ተዘጋጅቶ ነበር።

ይህ የስልጠና መመሪያ በደቡብ አፍሪካ ለሚገኙ ለተለያዩ የብሔር ቡድኖች እንዲያገለግል የበለጠ ተሻሽሎ ነበር። በደቡብ አፍሪካ ስለ ዘር ውይይት ሲደረግ ዘር አካራካሪ

ሀሳብ መሆን እንደሌለበት መደምደሚያ ተሰጥቷል ምክኒያቱም አንድ የሰው ዘር ብቻ ነው ያለው። ሁኖም ግን በአንዳንድ የአለም ክፍሎች ዘረኝነት የግጭቶች እና የመከፋፈል ስር እንደሆነ ይታመናል። እናም በዚህ የስልጠና መመሪያ ለማካተት ችለናል።

ይህ አገልግሎት በአሁኑ ጊዜ በዲሞክራቲክ ኮንጎ፣ በቡሩንዲ፣ በኬንያ፣ በዩጋንዳ፣ በአይቮሪኮስት፣ በናይጄሪያ፣ በሲሪላንካ፣ በህንድ እና በዩክሬን ተመሥርቶ ዎርክሾፖች እየተሰጡ ይገኛሉ። በእነዚህ ሀገራት ተመሳሳይ የሆነ የፈዉስና የእርቅ ተአምራት እየተከናወኑ ይገኛሉ። መሠረታዊ በሆነዉ በብሔር ግጭት ምክንያት የተጎዱትን ሰዎች መፈወስ በሚል ርዕስ ላይ የተዘጋጁ ዎርክሾፖች በሌሎችም በርካታ ሀገራት እየተሰጡ ይገኛሉ፣ ይህንም ስራ ለማስፋፋት ስራው ቀጥሏል።

ይህ የስልጠና መመሪያ በብሔሮች መካከል ወይም በሌሎች ምክንያቶች ለሚፈጠሩ ግጭቶች ጥቅም ላይ እንዲዉል ፀሎታችን ነዉ። ፈዉስንና እርቅን ለማምጣት እንድትጠቀሙበትም በትህትና እናቀርብላችኋለን።

## የቤት ቅርጽ የያዘዉን ምስል መግለጽ

ህዝቦችን ወደ ዳኑ ልቦች ማሸጋገር ስልጠና ቅደም ተከተላቸዉን ጠብቀዉ የሚሰጡ ከሆነ በጣም ዉጤታማ እንደሚሆኑ ለበርካታ ዓመታት ግንዛቤ አግኝተንበታል። ይሁን እንጂ መሰናክል ሊሆኑ የሚችሉትን ነገሮች ሳናስወግድና አስፈላጊዉን መሠረት ሳንጥል ከባድ የሆኑ ጉዳዮችን አንሰቶ ጉዳት ያደረሰዉን ሰዉ ይቅር ለማለት ፣ ንስሃ ለማስገባትና እርቅን ለማዉረድ መቸኮል አይገባም። የቤት ቅርጽ የያዘዉ ምስልን መጠቀም የፈዉስና የእርቅ ሂደት ላይ ለመድረስ እንደሚረዳ ግንዛቤ አግኝተናል።




**መሠረትን መጣል**

ጥልቅ ስለሆነዉ የእግዚአብሔር የልብ ሀሳብ ማወቅ ወደ መጨረሻዉ የፈዉስ መፍትሄ የሚመራን ብቸኛዉ መሠረት እንደሆነ እናምናለን። እርሱ  በመጀመሪያ ሲፈጥረን ለእኛ የነበረዉ ዋና ሀሳብ ምን እንደነበር እና ይህ እቅዱ እንዴት እንደተባላሸ እና እንደጠፋ ማወቅ ይኖርብናል። መከራ በገጠመን ጊዜ የእርሱን ፍቅርና ርህራሄ እንደገና ማወቅ እንዲሁም አፍቃሪ አባት መሆኑን ልንለማመድ ይገባናል።

**ግድግዳዉን መገንባት**

እግዚአብሔር አምላካችንን እና መገለጫ ባህሪዎቹን ማወቅ የሚገጥሙንን ህመሞች እንድንጋፈጣቸዉና ወደ እርሱ ለፈዉስ እንድናመጣቸዉ ልባችንን ያዘጋጃል። ዋናዉ የፈዉሳችንም ምንጭ የክርስቶስ መስቀል ነዉ።

**ኮርኒሱን ማስገባት**

ልባችን በህመም ተሞልቶ ባለበት ሰዓት ይቅርታን ማድረግ እጅግ ከባድ ይሆናል። ኢየሱስ የእኛን ህመም እንደሚሸከም ገብቶን፤ ህመማችንን ወደ እርሱ ልብ ስናፈስ፣ ይቅርታ ማድረግ የሚያስችለንን አዲስ ነጻነት እናገኛለን። በተመሳሳይ መንገድ የእኛን ጥፋተኝነት ስሜት በእምነት ወደ እርሱ ስናስተላለፍ፣ ንስሃ ለመግባት የሚያስችለን አዲስ ነጻነት እናገኛለን።

**ጣሪያውን መስራት**

ንስሃ መግባትና ይቅርታ ማድረግ ባለበት በታ ሁሉ፣ እርቅ ማምጣት ይቻላል።

# ክፍል አንድ: መሠረትን መጣል

## የእግዚአብሔርን የልብ ሀሳብ መረዳት እና መለማመድ

ማንኛዉም የህንፃ ግንባታ ሥራ የሚጀመረዉ መሠረትን ከመጣል ነዉ። መሰረቱን በትክክል ካልጣልን፣ ጠንካራና ረጅም ጊዜ የሚቆይ ግንባታን መገንባት አንችልም። የእግዚአብሔርን ልብ ማግኘት ለሁሉም ፈዉስ መሠረት ነዉ። እርሱ ከፍጥረት ጀምሮ እሰካሁን ድረስ ለሰው ልጆች እርስ በእርስ ስላላቸዉ ግንኙነት ምን እቅድ እንዳለዉ ልንረዳ ይገባል። ሁሉም ነገር ወደ ተሳሳተ መንገድ ሲሄድብን፣ የእርሱን የልብ ሀሳብ መረዳት ያስፈልጋል። ከሁሉ በፊት አስቀድመን እርቅን መፍጠር ያለብን ከእርሱ ጋር ነዉ። እኛ ክርስቲያኖችም ብንሆንም ይህን ማድረግ ያስፈልገናል፣ ምክንያቱም ፍትሃዊ ያልሆነ መከራ በሚገጥመን ሰዓት እግዚአብሔር ጣልቃ ስላልገባ ልንኮንነዉ እንችላለን። እርሱን የሁሉም መከራ ምክንያት

ካደረግን፣ ፈዉስን ፍለጋ ወደ እርሱ አንሄድም። ስለዚህ በመከራችንና ኢፍትሃዊነት መካከል ሆነን እግዚአብሔር የት አለ በሚል ከባድ የሆነ ጥያቄ እርሱን የሚከሱ፣ በልባችን የሚሞሉ ሀሳቦችን ልንታገል ይገባል። ክርስቲያኖች ብዙ ጊዜ ጥርጣሬ፣ ጥያቄዎች፣ በእግዚአብሔር ላይ ቁጣ በዉስጣቸዉ ሲፈጠር ልብ ሊሉ ይገባል፣ ይህ ደግሞ የፈዉሳቸዉ ጅማሬ ይሆናል።

የእግዚአብሔርን አባትነት ምስል ከአዕምሮአችን ያጠፉብን፣ በልጅነት ጊዜ የደረሱብን ጉዳቶች መፍትሔ ልንፈልግላቸዉ ይገባል፣ እነዚህ በመተማመን እና በነጻነት በእርሱ ፊት እንዳንቀርብ እንቅፋት የሚሆኑ ናቸዉ። በመገለል ግጭት ምክኒያት የደረሱብን ቁስል፤ በልጅነት ጊዜ ከደረሱብን ቁስሎች ለይተን ብቻውን መፈወስ ከባድ ነዉ፤ ምክንያቱም በልጅነት ጊዜ የደረሱብን ጉዳቶች በኋላ የሚደርሱብንን ጉዳቶች ሁሉ የከፋ ያደርጉታልና። በተጨማሪም፣ ማንም ቤተሰቡን መጀመሪያ ሳያድን ሀገሩን ከተጨማሪ ግጭት ማዳን የሚችል የለም።

የተበላሸ አስተዳደግ ካለ እርቅ እንዴት መሆን እንዳለበት እንኳ አናዉቅም። የወላጅን ፍቅር የማያዉቁ አጠገባቸዉ ባለዉ ሰዉ ላይ መሰሪያ ለማንሳት ከባድ አይሆንባቸዉም፣ ምክንያቱም ባህሪያችን የሚቀረጸዉ በቤተሰባችን ዉስጥ ነዉ።

Revelation of God's Heart

# ትምህርት አንድ

# ስለ እርስ በእርስ ግንኙነቶች የእግዚአብሔር የመጀመሪያው ዓላማ


## እግዚአብሔር እኛን ሲፈጥረን የነበረዉን ሃሳብ መረዳት

በማንኛዉም የግጭት ሁኔታዎች ሁሉ የሻከሩ ግንኙነቶች ይኖራሉ። ሰዎችም ይቆስላሉ፣ ይበሳጫሉ፣ ክርክርና ሙግት ይኖራል፣ ይከሳሉ ወይም ፍትህ ይፈልጋሉ። እነዚህ የተበላሹትን ግንኙነቶች ለመፈወስ ከመሞከራችን በፊት፣ የእግዚአብሔርን ፍቃድ ማወቅ ይኖርብናል። እርቅ ምንድነዉ? መሳካቱንስ እንዴት ማወቅ እንችላለን? ሁላችንም ሳንፈጠር ወደ ነበረዉ ሁኔታ እስኪ እንመለስ።

### 1) ሥላሴ -ለግንኙነት ፍጹም የሆነዉ ምሳሌ

ዓለም ሳይፈጠር በፊት፣ አባት፣ ልጅና መንፈስ ቅዱስ ዘላለማዊ በሆነ አስደናቂ ህብረት ዉስጥ ይኖሩ ነበር። አንዱን ከአንደኛዉ ጋር ያስተሳሰራቸዉን ባህሪያት ስንመለከት፡

- ፍቅር
- እምነት
- የእርስ በእርስ መከባበር
- የእርስ በእርስ ፍቅር
- አንዱ በሌላዉ መደሰት
- ፍጹም የሆነ አንድነት
- እርስ በርስ መደጋገፍ
- ለተመሳሳይ ግብ አብሮ መሥራት
- አንዱ በአንዱ ላይ መተማመን
- እርስ ለእርሰ ያላቸዉ ፍላጎት




- በጋራ አብሮ መሥራት - አጋርነት
- ግልጽ የሆነ የእርስ በርስ ተግባቦት
- አንዱ ሌላዉን የራሱ ማድረግ እና እርስ በእርስ ዋጋ መሰጣጥ
- ሁልጊዜ አንዱ ለአንዱ መገኘት
- የሚና ልዩነት ኖሮ ነገርግን ፍጹም የሆነ መደጋገፍ ያለበት


በዚህ ሥፈራ የምንመለከተዉ አንዱ ሌላዉን ሙሉ የሚያደርግበትን ፍጹም የሆነዉን ፍቅር ነዉ። በአካል አንድ መሆናቸዉን ብናይም ተመሳሳይ አይደሉም። ይሁን እንጂ በአባት፣ ልጅና መንፈስቅዱስ ማንነት መለያየታቸዉ ምንም ችግረ ሲፈጥር አናይም፤ ይልቁንም በልዩነታቸዉ ዉስጥ ፍጹም የሆነዉን አንድነታቸዉን ነዉ የምናየዉ። የፉክክር፣ የስልጣን ሹክቻ፣ አንዱ በአንዱ ላይ ሲዝት፣ አንዱ አንዱ ላይ የበላይነቱን ሲያሳይ አናይም፤ አንዱ በአንዱ ላይ ሲቀናና የፍላጎትን ግጭት አናይም። ይህ ፍጹም ለሆነዉ ህብረት ምሳሌ ሊሆን የሚችልና አንዱ በሌላዉ ሁል ጊዜ ደስ የሚሰኝበት ነዉ።

## በስላሴዎች መካከል የነበረዉ ህብረት አስደናቂ ከሆነ፣ እኛን ለመፍጠር ለምን ወሰኑ?

ፍቅርን በተመለከተ ያለው አንድ ነገር ቢኖር ሁልጊዜ መትረፍረፍ የሚፈልግ መሆኑን ነው። በግንኙነት ውስጥ ያለውን አስደናቂ የሆነ የላቀ ባህርይ ከሌላው ጋር መልካም ነገርን የመከፋፈል ፍላጎት ነበረ። ይህን አስቀድመው ይለማመዱት የነበረ ነዉ። ይህ በራሳቸው አድርገው አቆይተውት ቢሆን እጅግ መልካም ነበር እግዚአብሔር ግን በሶስቱ መካከል የነበረዉን

የግንኙነት ክብ ክፍት ማድረግ ፈለገ። እግዚአብሔር እንዲህ አለ "አሁን ሰውን በመልካችን በመፍጠር እነርሱ ከእኛ ጋርና ከእርስበርሳቸው ጋር ጭምር ይህንን አስደናቂ የሆነ ግንኙነትን ለመካፈል እንዲችሉ እንድናድርግ እኛ ያለን ዓይነት ህብረት ውስጥ እነርሱንም እናካትት››። ኢየሱስም በኋላ ዮሐንስ 17፡21-22 የጸለየዉ ጸሎት ዓይነት ነበር።

አሁን ይህን አስደናቂ ነገር ለማሰብ ጊዜ ዉሰዱ። የተወለድነዉ ለከበረ ህብረት ነዉ!




ስለዚህ የዕርቅ ግቡ ታዲያ ምንድነዉ? ወደ ቀደመዉ የእግዚአብሔር ዓላማ ከመመለስ የተሻለ ነገር ምን አለ። ሶስቱም የስለሴ አካላት እኛን በመፍጠር ሥራ ዉስጥ ተሳትፎ እንደነበራቸዉ እናዉቃለን። እኛን ሲፈጥሩ የነበራቸዉ ስሜት እንዴት ነበር? ከመጀመሪያው የዘፍጥረት መጽሐፍ ጀምሮ የስላሴ አካላት ደስተኝነት ሲሰማቸው እንደነበር በተጨማሪም በጣም ደስተኛ እንደነበሩና ከተፈጠረው ሰው ጋር ህብረት ለማድረግ ይጓጉ እንደነበር እናውቃለን። ምክንያቱም በእግዚአብሔር አካላት መካከል ህብረት ነበር፣ በእኛ የጠበቀ ህብረት ውስጥ የእግዚአብሔር መልክ በግልጥነት ይታይ (ላይታይም ይችላል) እንደነበር መደምደም እንችላለን። ይህ በሰዎችና ሰዎች መካከል ያለዉንም ህብረት የሚያካትት ነው።

## 2) የተለያዩ ብሔሮች መኖራቸዉ፣ በረከት ነዉ ወይስ መርገም?

የተለያዩ ብሔሮች መኖራቸዉን በተመለከተ ይህ በእግዚአብሔር እቅድ ዉስጥ የነበረ ነበር? በተለያዩ ብሔሮች መካከል ባለዉ ግጭቶች ከምንፈተነው ፈተና የተነሳ፣ የተለያዩ ብሔሮች መኖራቸዉ የእግዚአብሔር እቅድ እንዳልሆነ ልናስብ እንችላለን። የሐዋርያት 17፡26 እግዚአብሔር ሁሉንም ብሔሮች ከአንድ ሰዉ ወይም ደም እንደፈጠረ ይናገራል[1]። የተለያዩ ብሔሮች መኖራቸዉ የእግዚአብሔር ሀሳብ ነበር። በኤፌሶን 3፡15፣ 'ቤተሰብ' የሚለዉ ቃል የህዝብ ወገኖች፣ ዜጎች ወይም ዘሮች የሚለዉን ይወክላል። ይህ ሊገርመን አይገባም፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር ልዩነትን ይወደዋል[2]። ይህን ለመረዳት ፍጥረቱን ማየት ብቻ በቂ ነዉ። (ሮሜ 1፡20)። የእግዚአብሔር ክብር በጣም ትልቅ የሆነና በአንድ የተወሰነ ህዝብ ብቻ ሊገለጥ የሚችል አይደለም። በዘፍጥረት 1፡28፣ እግዚአብሔር ለሰዉ ልጆች 'ፍሬያማ ሁኑ ተባዙ፤ የምድርንም ፊት ሙሉአት።' ከዚህም የተነሳ የተለያየን ወደ መሆንና የራሳችንን ባህል ወደ ማዳበር መጥተናል። የሰዉነት አቋማችንም እራሱ ይለያያል። ከእርሱ ጥብብ የተነሳ፣ የተለያዩ የሰዉነት አቋሞቻችን፤ (ለምሳሌ፣ የቆዳችን ቀለም፣ ጸጉራችን ውፍረት) እንድንኖርባቸዉ ከመረጠልን አካባቢዎች ጋር ተስማሚ እንዲሆኑ አድርጎ ነዉ።

## የተለያዩ ነገር ግን እኩል ዋጋ የሚሰጣቸዉ

እኛ የተለያየን ነን፣ በእግዚአብሔር ፊት ግን እኩል የሆነ ዋጋ ያለን ነን። እርሱ የሰዉን ልጆች ሲፈጥር ለይቶ የሚመለከተዉ ሰዉ አልነበረም (ሐዋርያት 10፡34-35)። ልዩነታቸዉ ጎልቶ እንዲወጣ፣ በእያንዳንዱ ብሔር ዉስጥ ልዩ የሆነዉን መዝገቡን አኑሯል፣ የእግዚአብሔርም እቅድ የነበረዉ ሁላችንም እርስ በእርሳችን እንድንዋደድ፣ እንድንደናነቅ፣ እንድንቀባበል እና አንዳችን በአንዳችን ደስ እንድንሰኝ፣ ሌሎች ከእኛ የተሻሉ ናቸዉ ብለን እንድናስብ ነበር። ፊሊጵሲዩስ ምራፍ 2 መጀመሪያ አካባቢ ያለዉ እኛን የሚፈትን ሃሳብ ነዉ። እርሱ እርስ

[1]2 ህዝብ የሚለዉ ቃል በአዲስ ኪዳን ብሄሮች የሚለዉን የሚወክል ነዉ፣ ይህም ዛሬ ሀገር ብለን እንደምንረዳዉ ሳይሆን የሰዎችን ቡድን የሚወክል ነዉ።

[2] በሩዋንዳና ቡሩንዲ ሁቱ፣ ቱትሲ እና ትዋ የሚባሉት ብሄሮች የሚናገሩት ቋንቋ፣ ባህላቸዉ እና ምድር አንድ ነዉ ይሁን እንጂ አንድ ብሄር አይደሉም። ይህ መከፋፈል ኢፍትሃዊ ነበር ስለዚህ በእነዚህ ዜጎች መካከል ይህን ጉዳይ በጥንቃቄ ልንይዘዉ ይገባል።

በርሳችን አንዳችን ለአንዳችን ለብልጽግና ምንጭና በረከቶች እንደሆንን እንድናስብ ይፈልጋል። ባለፈዉ ገጽ ላይ የዘረዘርናቸዉን ተመልሳችሁ እዩ። የተለያዩ ሰዎች ስበስስብ እርስበርሱ እንደዚህ ዓይነት ግንኙነት እንዲኖረዉ ይፈልጋል!

አልማዝ የተለያየ ገጽታ (ፊት) ያለው ሲሆን አንድ ወጥ ከሆነ፣ ልሙጥና አንድ ገጽ (ፊት) ካለው መስታወት እጅግ የበለጠ ዋጋ አለው። አልማዝ ትልቅነቱ ብዙ የተለያዩ ገጽታዎች ያለው መሆኑ፣ ውበት የሚጨምር መሆኑ፣ እያንዳንዱ ገጽታ የየራሳቸው ብርሃንን የሚያንጸባርቁበት መንገድ ሲሆን በተጨማሪም ደግሞ በጣም ጠንካራ ነዉ። በተመሳሳይ መንገድ እግዚአብሔር እያንዳንዱ ብሔር ከትልቁ ገጽታ አንዱ ሆኖ፣ እያንዳንዱም የእርሱን ክብር ልዩ በሆነ መንገድ የሚያንጸባርቁ አስደናቂ አልማዝ እንዲሆኑ ይፈልጋል። በራዕይ 21፡ 24-26 እግዚአብሔር ክብሩንና ሞገሱን በሁሉም ብሔሮች ላይ እንዳስቀመጠና ወደ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም እንዲገቡ ይፈልጋል።

### 3) **የተፈጠረዉ ስህተት ምን ነበር?**

በሚያሳዝን መልኩ፣ ሀጢያት ዉብ ወደ ሆነዉ የእግዚአብሔር ፍጥረት ገባ። የሰዉ ልጅ ከእግዚአብሔር፣ ከእርስ በእርሱ እና ከፍጥረቱ ተለያየ። በዘፍጥረት 11 እንደምናየዉ የሰዉ ልጅ እግዚአብሔር ምድርን እንዲሞሉና እንዲገዙ ያዘዘዉን ትእዛዝ ተቃወሙ። ከዚህ ይልቅ አንድ ቦታ ለአመጽ ተሰብስበዉ ሰማይ የሚደርስ ግንብ ለመሥራት ተስማሙ (ቁጥር 4) እግዚአብሔርም በሀይል በተናቸዉ። ከዚህም የእግዚአብሔርን የመጀመሪያ ሀሳብ ምን እንደነበር መረዳት እንችላለን።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፣ የተለያየን ብሔሮች መሆናችንን አዉቀን ከመቀባበልና ከመከባበር ይልቅ እርስ በርሳችን አንዳችን በሌላችን ላይ እንነሳለን፤ እንፎካከራለን። እግዚአብሔር የሰጠንን ያንን እኩል የሆነ ዋጋ ትተን ለ ስልጣን እርስ በርሳችን እንገፋፋለን። አንዱ ባህል የበላይ እንደሆነ አስቦ ሌላዉን ለመጫን ይፈልጋል። አንዳችን ለአንዳችን የብልጽግናና የበረከት ምንጭ ከመሆን ይልቅ፣ ብሔርተኝነት የጉዳት መሳሪያ ሲሆን እንመለከታለን። ይህ ፈጽሞ የእግዚአብሔር ሃሳብ

አልነበረም። ይህም በፍጥረቱ ላይ የነበረዉን የእግዚአብሔርን መንፈስም አሳዝኗል። እግዚአብሔር ወገንተኝነትንና ፍረጃን ይጠላል።

ስለዚህ እግዚአብሔር ለሰዉ ልጅ የነበረዉ የመጀመሪያዉ እቅዱ ልክ እንደ ስላሴ የሚያስተሳሥር ህብረት እንዲኖረን ነበር፣ ነገር ግን የሰዉ ልጅ በራሱ ዓላማ (ሃሳብ) ፈጽሞ ሲወድቅ እናያለን። ለዚህ ነዉ እግዚአብሔር እራሱ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ወደ ዓለም መጥቶ እኛን ከራሱ ጋርና ከእርስ በርሳችን ጋር እንድንታረቅ ያደረገው።

## ከራስ ጋር ማዛመድ

- እንደ ሸክላ የሰራህን አንትን በመሥራቱ ደግሞ የተደሰተዉን፣ እንዳታምነዉ የሚያግድህ ነገር ምንድነዉ?
- ካንተ የተለዩትን ሰዎች ላንተ የፍርሃት ምንጭ ከመሆናቸዉ ይልቅ ላንተ የበረከት ምክንያቶች እንደሆኑ እንድታስብ የሚያደርጉህ ነገሮች ምንድናቸዉ?

## ቁልፍ ነጥቦች

- ስላሴ ፍጹም ለሆነዉ ለሰዎች የእርስ በእርስ ግንኙነት ምሳሌ የሆነ ነዉ።
- ሰዎች የተለያዩ ብሄሮች ሆነዉ የመፈጠራቸዉ ምክንያት የእግዚአብሔርን ክብር በተለያየ መንገድ እንዲገልጡ ነዉ።
- የእርሱ እቅድ የነበረዉ በልዩነታቸዉ እንዳሉ፣ አንዱ የሌላዉን የተለየ ባህል እንዲያከብር፣ አንድነታቸዉን እንዲጠብቁ ነበር፤ ይሁን እንጂ ኃጢአት ይህን የእግዚአብሔር መልካም የሆነ እቅድ ለማበላሸት ወደ ሰዉ ልብ ገባ።

# ትምህርት ሁለት

## የቅድመ ፍረጃ አስከፊው ኃይል፡ መራራ ሥሮች

### ሰዎች የቅድመ ፍረጃን አደገኝነት እንዲረዱ እና እንዲተውት መርዳት።

ሰዎች በአለም ላይ ለምን ብዙ ግጭቶች እንደሚከሰቱ ሲጠየቁ፣ አብዛኞቹ የመሬት፣ የኢኮኖሚ ወይም ማህበራዊ ኢፍትሀዊነት፣ ዉጫዊ የሆኑ ምክንያቶች፣ እና የመሳሰሉት እንደሆነ ይናገራሉ። ነገር ግን አብዛኛዎቹ ሰዎች መርዛማ የሆነው ቅድመፍረጃ እንደሆነ አያስቡም። በሩዋንዳ ሀገር የነበረዉን ስንመለከት፣ ጭፍን የሆነዉ የብሔር ጥላቻ ልክ ከመሬት ዉስጥ እንደተቀበረና እንደሚወጣ ማዕድን ይመሰል ነበር። ፖለቲከኞች በብልሃት የፍርሃት ሀሳቦችን በማመንጨት ‹‹የቆየ ሰይጣናዊ›› የሆነ ጥላቻ እንዲነሳሳ በማድረግና በሺህ የሚቆጠሩ ወጣቶችን ለክፉ ዓላማቸው አንቀሳቅሰዉ ነበር።

በብሔሮች መካከል ለሚፈጠሩ ግጭቶች እንደ ምክንያት ሊጠቀሱ የሚችሉ ብዙ ስሮች አሉ። እነሱም መጥፎ አስተዳደር፣ ድህነት፣ ከዚህ በፊት ያልተፈታ ያለፈ ግጭት፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰዎችን በስነ ስርዓት አለማብቃት፣ መዝሙርነት የማብቃት ችግር፣ የቅኝ ገዢዎች ከፋፍሎ የመግዛት ፖሊሲ፣ በተጨማሪም የጣዖት አምልኮ ተጽዕኖዎች ናቸዉ። ሆኖም ግን ቅድመ ፍረጃ ዋናዉ መንስኤ ነዉ።

### 1) ቅድመ ፍረጃ ምን ማለት ነዉ?

ፍረጃ ስንገልጸዉ አንድ ሌላን ሰዉ የሚጎዳና መብቱን የሚጋፋ በዉስጣችን የሚፈጠር ቅድመ ድምዳሜ የሆነ አመለካከት ነዉ። ሁሉም የብሔር ግጭቶች የሚጀምሩት በአዕምሮችን ውስጥ ነው ስለዚህ ቅድመ ፍረጃ ምን ያክል የሚረብሽ ነገር መሆኑን ይበልጥ መረዳት ያስፈልጋል። የሚያስከትላቸው መጥፎ ጉዳቶችም ይኖሩታል።

የቅድመ ፍረጃ አስከፊው ነገር በአንድ ሁኔታ ምክንያት ሁሉንም የሚያጠቃልል መሆኑ ነዉ። አንድ ሰዉ ላይ መጥፎ የሆነ ባህሪ ልናስተውል እንችላለን፤ ከዚህም ሰው ባህሪ ተነስተን

እሱን የሚወክሉ ሁሉንም ሰዎች ልክ እንደሱ ናቸው ብለን ልናስብ እንችላለን። ከዚያም በኋላ ሁሉንም የቡድኑን አባላት እንኮንናቸዋለን፤ እንዲሁም እንፈርድባቸዋለን። ቅድመ ፍረጃዎች ይበልጥ መጥፎ የሚሆኑት አንድ ጥቃት ሲከሰትና ሰዎች በቅድመ ፈራጁ እምነት እና በጠላት ቡድኑ መካከል ያለው እውነታ ምን እንደሆነ ለመለየት ከባድ ይሆንባቸዋል።

ቅድመ ፍረጃ ኃጢአት ነው፤ ምክኒያቱም እንድንፈርድ ያደርገናል። ጉዳዩ በጣም ከባድ ነዉ ምክኒያቱም በሰው ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔር አምሳል ስለሚክድ፣ የእግዚአብሔር እቅድ የሆነዉን በልዩነት ዉስጥ ያለዉን አንድነት አለመቀበል፣ እውቅና አለመስጠት፣ ሰዉን ዝቅ ማድረግ ወይም ማሳነስ፣ እንዲሁም ሌሎች ከእኛ የተሻሉ እንደሆኑ ማሰብ እንዳለብን የሚያስተምረውን የእግዚአብሔርን ቃል የሚቃወም ነዉ (ፊሊጵስዮስ 2፡3) ። እግዚአብሔር የወደዳቸዉን እና ኢየሱስ ክርስቶስ የሞተላቸዉን የሁሉንም ቡድን ሰዎች መኮነን፤ እርስ በእርሳችን እንድንዋደድ እንዲሁም ለእኛ እንዲደረግልን የምንፈልገዉን ለሌሎች እንድናደርግ የሚነግረንን የኢየሱስን ትዕዛዝ አለማክበር ነዉ። (ማቴዎስ 7፡12)

## 2) **ቅድመ ፍረጃን መለየትና ይህ አመለካከት በእኛ ዉስጥ እንዳለ ማመን**

ታማኞች ከሆንን፣ ሁላችንም ለቅድመ ፍረጃ የተጋለጥን መሆናችንን ማመን አለብን። በእያንዳንዱ ሀገር ዉስጥ ሰዎች የሌሎች ቡድን ሰዎችን ከራሳቸው ቡድን ሰዎች ያነሰ ዋጋ እንዳላቸው የማሰብ ዝንባሌ ያለ ይመስላል። እናንተ በምትኖሩበት አካባቢ በዚህ ሰአት ወደ አዕምሮአችሁ ውስጥ የመጣው ምንድነው?

ብዙ ጊዜ ስለ ሌሎች ቡድን ሰዎች የምንናገራቸዉ ቀልዶች የቅድመ ፍረጃ እንዳለን ማስረጃዎች ናቸዉ። ይህም የሚያመለክተው በመላዉ ዓለም መኖሩን ነዉ! ለተወሰኑ ቡድን ሰዎች የምንሰጣቸዉ ስሞችም ይህንን የሚያሳዩ ናቸዉ። (ለምሳሌ፣ በ1994 እኤአ በሩዋንዳ ዘር ማጥፋት ጊዜ ሁቱዎች ቱሲዎችን በረሮ እና እባብ ብለዉ ይጠሩአቸው እንደነበር ይነገራል) ።

በሠራንባቸዉ በእያንዳንዱ ሀገራቶችም ብዙ ቅድመ ፍረጃዎች እንዳሉ ተመልክተናል። ሁሉም ቡድኖች ስለሌላኛው ቡድን የሚናገሩት መልካም ያልሆነ ንግግር አለ። ለምሳሌ፣

በደቡብ አፍሪካ፣ ሁሉም ነጮች የዘር ጨቋኞች ናቸዉ፣ ሁሉም ጥቁሮች ኋላ ቀሮችና አመጸኞች ናቸዉ፣ ሁሉም ህንዳዉያን ታማኞች አይደሉም፣ ሁሉም የተቀላቀለ ዘር (ውህድ ማንነት) ያላቸዉ ሰዎች ጠጪዎች ናቸዉ። እና ሌላም ሌላም....


በሩዋንዳ፣ ሁቱ፣ ቱትሲ እና ትዋ የሚባሉት እውነተኛ የብሔር ቡድኖች አይደሉም። ነገር ግን እርስ በእርሳቸው ጠንካራ የሆነ ቅድመ ፍረጃ አላቸው። ሁቱዎችን እንደ ደደብ ፣ ለእርሻ ስራ ብቻ ጎበዞች እንደሆኑ እና ብዙ የሚመገቡ/ሆዳሞች/፣ የሚያስጠሉ፣ ገዳዮችም ናቸዉ ይሏቸዋል። ቱትሲ እብሪተኛ፣ ተንኮለኛ፣ ግብዞች፣ ሰነፎችና ሁቱዎችን ሁሉንም ሥራ የሚያሰሩ ናቸዉ ይሏቸዋል። ቱዋዎች ቆሻሾች፣ አዕምሮ አልባ የሆኑ ለማኞች፣ ለማኞች፣ ሙሉ ሰዉም ያልሆኑ ናቸዉ ይሏቸው ነበር።

ቅድመ ፍረጃ ልክ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ረጅም እድሜ ያስቆጠረ ነዉ። ኢየሱስ ራሱ በቅድመ ፍረጃ ተጠቂ ነበር። ናትናኤል ኢየሱስ ከናዝሬት እንደሆነ ሲሰማ፣ ከናዝሬት መልካም ነገር ይወጣልን? (ዮሐንስ 1፡46)፣ በአይሁዶችና ሳምራዉያንም መካከል ይህ ነዉ የማይባል ቅድመ ፍረጃ ነበር (ዮሐንስ 4፡9) ።

### 3) **መንሰኤ፡ መጥፎ ወደሆነ ግንኙነት የመሩን እነዚህ ቅድመ ፍረጃዎቻችን እና እምነቶቻችንን ከየት ተማርናቸዉ?**

አሁን ላይ ያላችሁን ሰዋዊነት፣ ስለ ሕይወት ያላችሁ እምነት፣ የግል ሀሳባችሁ እና በተለይም ቅድመ ፍረጃዎቻችሁ እንዴት እንደተሰራ ለማዎቅ ፈልጋችሁ ታውቃላችሁ?

## የዛፍ ምስል ህይወታችንን ይወክላል ብለን ብናስብ




መጽሐፍ ቅዱስ አብዛኛዉን ጊዜ ህይወታችን ለመግለፅ የዛፍ ምስልን ይጠቀማል (መዝሙር 1፡ 3፣ 92፡12፣ ኢይሳያስ 61፡3፣ ኤርምያስ 11፡16፣ 17፡8) ። ይህን ምስል የቅድመ ፍረጃዎቻችንን ምንጭ ይበልጥ ለመረዳት እና ምን ዓይነት ፍሬን በህይወታችን ሊያፈራ እንደሚችል ለማወቅ እንጠቀምበት።

ሁላችንም የመጣነዉ ከአንድ ሰዉ እና ከአንድ ደም (ከአዳም) ነዉ። በእግዚአብሔርም አምሳል የተፈጠርን ነን፤ ሁላችንም ህሊና ፣ የገዛ ፈቃድ ያለን ፣ የራሳችን የሆነን ነገር መምረጥ፣ መውደድ ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት መፍጠር የምንችል ነን። ይህን ሁሉ መልካም ነገር ከአዳም ወርሰናል። እግዚአብሔር ልክ እንደዛፍ መልካም ፍሬን እንድናፈራ ይፈልጋል። ባለፈው ምዕራፍ ላይ እንዳየነዉ፣ እኛ እንድንደሰት፣ የተለያየን ሆነን መፈጠራችንን እንድናከብርና እንድናደንቅ እግዚአብሔር ይፈልጋል። ነገር ግን አዳም በኃጢአት ወደቀ፣ የእግዚአብሔርም የነበረው መልካም እቅድም ተበላሸ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መልካም የሆነ ፍሬን ከማፍራት ይልቅ፣ የምናፈራዉ ፍሬ መራራና ኮምጣጣ እንደ ሆነ ማየት እንችላለን። ለቅድመ ፍረጃ፣ ተጠራጣሪነትና ጥላቻም እንደተጋለጥን እንመለከታለን።

ሁሉም ዛፍ የራሱ ሥር አለዉ፣ ለምን መራራ ፍሬን እንደምናፈራ ለመረዳት ተመልሰን ወደ ሥሮቹ መሄድ ይኖርብናል። እግዚአብሔር ሁሉም ሥሮች መልካም እንዲሆኑና ጤናማ የሆነ ምግብ ከአፈር እንዲያገኙ ይፈልጋል። ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ በ (ሮሜ 5፡12-21) እንደሚነግረን ከአዳም ኃጢአተኛነትን መዉረስ ችለናል። በዚህም ምክኒያት ሰይጣን በህይወታችን ላይ እድል ፈንታን ስላገኘ በሁሉም አቅጣጫ ያለዉ ሥር ሁሉ በኃጢአት የተመረዘ ነዉ።.

ቅድመ ፍረጃ በሁሉም አህጉራት፣ ሀገራት፣ ብሔሮች፣ ዘሮች፣ ፖለቲካ፣ ሀይማኖት፣ ፆታ መካከል ምን እንደፈጠረው አስቡ። ከራሳችሁ የግል ልምድ መጥቀስ የምትችሉት ነገር አለ? ከቅድመ አያቶቻችንስ እንዴት ተላልፎ መጣ? ምን ዓይነት ቅድመ ፍረጃዎችን ከቤታችሁ ተማራችሁ? ይህ አብዛኛውን ቅድመ ጃዎችችንን የተማርንበት ቦታ ሊሆን ይችላል። የህይወት ልምዶችስ ስለቅድመ ፍረጃ ለእናንተ እንዴት ያረጋግጡአችኋል? በቤተክርስቲያን ያላችሁ ልምድስ፣ ከቅድመ ፍረጃ የፀዱ ናቸዉ?

ቅድመ ፍረጃ፡ ጥላቻ፣ አለመግባባት፣ ራስ ወዳድ የመሆን ፍላጎት፣ ስግብግብነትና የመሳሰሉትን ዓይነት የራሱን ፍሬ ያፈራል። እነዚህም ከመንፈስ ፍሬዎች ፍፁም ተቃራኒ ናቸዉ።

ዘዳግም 29፡18 መራራ ሥሮቻችን መርዛማ የሆኑ ፍሬዎችን እንደሚያፈሩ ይናገራል። በዕብራዉያን 12፡14-15 መራርነት ተላላፊ እንደሆነና ብዙ ሰዎችን እንደሚያረክስ ተመሳሳይ ሀሳብ እናገኛለን።

### 4) **ኢየሱስ – ምንም ቅድመ ፍረጃ የሌለበት ነው።**

ምንም ቅድመ ፍረጃ የሌለበት እና በህይወቱ መልካም የሆነውን የፍቅር፣ የደስታ፣ የሰላም፣ ትእግስትና ሌላዉን የመንፈስ ፍሬ ሁሉ የሚያፈራዉን ሌላኛውን ዛፍ እንመልከት።




ምንም ቅድመ ፍረጃ ወይም መራራነት በኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ የለም፤ ምክንያቱም ሥሩ እኛን በእኩል ዋጋ ከፈጠረን፣ ለሁሉም ምርጡን ከሚመኝ ከእግዚአብሔር ላይ ስለሆነ ነው። በዮሐንስ ምእራፍ 4፣ ኢየሱስ ከሰማርያ ከሆነችዉ ሳምራዊቷ ሴት ጋር ሲነጋገርና ጥልቅ የሆነዉን እዉነት ሲያካፍላት፣ ለሳምራዉያን ሆነ ለሴቶች እንዲሁም የእርሱ ከሆኑት ለአይሁዶች ምንም ቅድመ ፍረጃ እንደሌለዉ ማየት እንችላለን። በሉቃስ 7 ሮማዉያን ለአይሁዶች ምንም እንኳን ጠላቶች የነበሩ ቢሆኑም እርሱ ግን የሮማዊዉን መቶ አለቃ ባሪያ በፈቃዱ ሲፈዉስ እናያለን። በማርቆስ 7 ታሪኩ መጀመሪያ ላይ እንደተጠቀሰው እየሱስ ከሲሮፊኒቃዊት ሴት ጋር ያለዉን ንግግር ቅድመ ፍረጃ የሚያሳይ ይመስላል፣ ኢየሱስ ሲያደርግ የነበረዉ ግን እምነቷን እያጠነከረ ነበር። ከእርሱ እምነትን እንደምትቀበል ሲያዉቅ፣ በደስታ ልጇን ሲፈዉስ እናያለን።


## 5) በኢየሱስ በመኖር ለለውጥ ያለ ተስፋ

ምንም እንኳን መርዛማ ፍሬን የሚያፈራ በሥሮቻችን ዉስጥ መራርነት ቢኖርም፣ በዚህ መልኩ መቀጠል ግን አስፈላጊ አይደለም። ሮሜ 12፡2 በአዕምሮ መታደስ መለወጥ እንዳለብን

ይነግረናል። እኛ ለምንኖርበት ማህበረሰብ ማረጋገጫዎች መሆን የለብንም፤ ነገር ግን የክርስቶስ ልብ ሊኖረን ይገባል (ፊሊጵስዮስ 2፡5፣ 1ኛ ቆሮ 2፡16) ።

ተስፋ አለ! ኢየሱስ ወደ እርሱ መጥተን በእርሱ ዉስጥ እንድንኖር እና እኛም በእርሱ ዉስጥ በመኖር መንፈስ ቅዱስ በሂደት ወደ ክርስቶስ መልክ እንዲለዉጠን እንፍቀድለት ይጋብዘናል። በሰስተኛዉ ምስል ዉስጥ (በሚቀጥለዉ ገጽ) በኢየሱስ ዉስጥ ያለዉን ህይወታችንን የሚወክለዉን በትልቁ የኢየሱስ ዛፍ ዉስጥ የእኛን ትንሽ ዛፍ ማየት እንችላለን። የዚህ ዛፍ አካል መሆናችንን በእዉነት ከተረዳን ጤናማ የሆነዉን ፍሬ ማፍራት እንጀምራለን (ዮሐንስ 15፡4-5) ። በነገራችን ላይ እዚህ ሁሉም ሥሮቻችን መዋጀት እና አዲስ የሆነ እምነትና አመለካከትም ልናዳብር እንችላለን።

አብዛኛዉን ጊዜ በአመለካከታችን ፍጹም የሆነ ለዉጥ ማድረግ እንደሚያስፈልገን እንኳ አናስብም። በኃጢአተኛነት የተሞላዉን ለሌሎች ያሉንን አመለካከቶቻችንን መመርመርና መንፈስ ቅዱስ እንዲያነጻን፣ እንዲያድሰንና የክርስቶስ ልብ እንዲኖረን እንዲለውጠን መፍቀድ አለብን (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡16) ። በፍቅር ላይ መሠረትን መጣልና ሥር መስደድ፣ የእግዚአብሔርን ፍቅር ታላቅነት ይገልጥልናል (ኤፌሶን 3፡14-20፣ ቆላስይስ 2፡7) ። ይህ ደግሞ ቅዱስ የሆነ አመለካከትን በእኛ ዉስጥ ያፈራል፣ ከዚህም የተነሳ የተቀደሰ አመለካከትና የተፈወሰ ፍሬ እናፈራለን መልካም ግንኙነትም ይኖረናል። በቅድመ ፍረጃ ከመሞላት ይልቅ ሌሎች ብሔሮችን ማክበርና ማድነቅ እንጀምራለን።




በክርስቶስ መሆን ማለት ምን ማለት እንደሆነ አብዛኛዉን ጊዜ በትክክል አንረዳም። ኢየሱስ እንደሚናገረዉ እርሱ የወይን ግንድ እኛ ደግሞ ቅርንጫፍ ነን። ወደ ኢየሱስ መምጣት ማለት የእግዚአብሔር ቤተሰብ መሆንና ብዙ ወንድሞችንና እህቶችን ከሌሎች ቡድኖች ጭምር ማግኘት ነዉ።

ይህ ለዉጥ በአንድ ጊዜ የሚመጣ አይደለም። ጳዉሎስ በ2ኛ ቆሮንቶስ 5፡17 በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት እንደሆንን ቢናገርም የዚህን እውነት ሙሉ ሃሳብ አልተገዘብነውም፤ ምክንያቱም ከአሮጌዉ ማንነታችን አሁንም እኛነታችንን የምንመግበው ነገር ይኖራል (ሮሜ 7፡22-25) ። እውነታው ግን ይህ ነው፤ በእዉነተኛ ንስሃና በእምነት እዉነተኛ ክርስቲያኖች ከሆንን፣ የሰማይ

ቅዱስ ህዝብ ዜጎች እንሆናለን (1ኛ ጴጥሮስ 2፡9) ። የሚያሳዝነዉ ግን ወንጌል ሲሰበክ አብዛኛዉን ጊዜ ይህ ጉዳይ አይነሳም! ይህንን በሚቀጥለዉ ምዕራፍ ዉስጥ በስፋት እናያለን።

## ከግል ህይወት ጋር ማዛመድ

ጊዜ በመዉሰድ የራስህን የተለያዩ ሥሮች እንዳሉ አስቡና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

- ያሉኝ ሥሮች በእምነቴና በአመለካከቴ ላይ ተጽዕኖ እንዴት ሊያመጡ ይችላሉ?
- በሥሮቼ ዉስጥ መራራ ነገር አለ? ካለ ምን ዓይነት ፍሬን እያፈራ ነዉ?

## ቁልፍ የሆኑ ነገሮች

- ፍረጃ የቡድን አባል የሆኑትን በሙሉ የሚኮንን ፍርድ ነዉ።
- ፍረጃዎቻችንን የምንማረዉ ከተለያዩ ምንጮቻችን ነዉ።
- ፍረጃ በጣም አፍራሽና የጠብና የክፍፍል መንስኤ ነዉ።

# ትምህርት ሶስት

## የታደሰዉ ማንነት

### በተቀደሰዉ ህዝብ ዉስጥ የዳነ ማንነትን መፈለግ

ይህ የትምህርት ክፍል በዋናነት የሚያደርገው የዘር ማንነት ከተቀደሰው ህዝብ አንፃር ላይ ትኩረት የሚያደርግ ሲሆን ነገር ግን ከሁሉም አንፃር ያለንን ማንነትም በተመሳሳይ መልኩ ሀሳቦችን ያነሳል። እናም የአፍሪካ ቤተክርስቲያን በቁጥር እየጨመረችና እያደገች በመሄዷ ብትመሰገንም፤ በአብዛኛው ግን ጎሰኝነትን በመዋጋት ላይ የዉጤታማነት እጥረት ስላለ ትፈተናለች። 'ክርስቲያን' ተብለው በሚጠሩ ሀገራት እንኳ ያለው ስህተት ምንድነው? ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔርን ተጨማሪ ራዕይ/መገለጥ/ መቀበል የሚያስፈልጋት ጊዜ አሁን ነዉ። ቤተክርስቲያን ብሔርን በተመለከተ ምን ማድረግ እንዳለባት አታዉቅም። ክርስቲያን ስንሆን የእኛ የሆኑ ተፈጥሮአዊ ማንነቶችን እንረሳለን እንዴ? ይህ ርዕስ ትክክለኛ በሆነ መንገድ በተፈጥሮ ባለን ማንነት እና በክርስቶስ ባለን ማንነት መካከል ሚዛናዊ እንድንሆን ይረዳናል ።

### 1) በቤተክርስቲያን ዉስጥ ያለ መገለል

እግዚአብሔር በልዩነት ዉስጥ አንድነትን እንድንለማመድ በእርሱ አምሳል ቢፈጥረንም፣ ይህንን ለእኛ ያለውን የእርሱን ሃሳብ፣ አንዳችን ሌላዉን እንድናከብርና አንዱ የአንዱን ክፍተት እንዲሞላ እንደተፈጠረ የምንረዳው በቤተ ክርስቲያን እንኳን ሳይቀር ጥቂቶች ነን። የአንድ ብሔር ብቻ የሆኑና፣ ሌሎች ብሔሮች በነጻነት እንዲያመልኩ እንዳልተጋበዙ እንዲሰማቸው የሚያደርጉ ብዙ አብያተክርስትያናት አሉ። የተለያዩ ብሔሮች ያሉባቸዉ አብያተክርስትያናት ቢኖሩም እንኳ በቤተክርስቲያን መሪነትና ቢሮ ዉስጥ እንዲያገለግሉ የሚመረጡት በብሔር ማንነታቸዉ እንጂ ባላቸዉ የፀጋ ስጦታና ችሎታ መሠረት አይደለም። ከተለያዩ ብሔሮች ጋር

መጋባት አብዛኛዉን ጊዜ ተቀባይነት የሌላቸዉ እና በግልፅ የሚቃዎሙዋቸው ጉዳዮች ናቸዉ። በሀገር ዉስጥ በሚኖረዉ ግጭት ቤተክርስቲያን የችግሩ መፍትሄ መሆን ሲገባት የችግሩ ፈጣሪ አካል ስትሆንም እንመለከታለን፤ በዉጪው ማህበረሰብ ላይ ያለዉ መከፋፈል እና ጥላቻ በተመሳሳይ መልኩ በቤተክርስቲያን ዉስጥ ሲከሰት እናያለን። አብዛኛዉ ሰዉም በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም ስህተት እንዳለ አይመለከትም። ሁኖም በምዕራፍ አንድ ዉስጥ እንዳየነዉ ይህ የእግዚአብሔርን እቅድ በአጠቃላይ የሚቃወም ነዉ።

የእግዚአብሔር ምላሽ ለዚህም ለእርሱ ከተለዩትና ከተመረጡት ሰዎች አዲስና ልዩ የሆነ ህዝብን መፍጠር ነዉ።

## 2) ለእግዚአብሔር የተመረጠ ቅዱስ ህዝብ

## በብሉይ ኪዳን

የእግዚአብሔር እቅድ በአብርሃም ተጀመረ፣ በእርሱ በኩል አዲስ ህዝብን ለመፍጠር ከሀገሩ፣ ከወገኑና ከአባቱ ቤት ውጭ ተጠራ። ይህም ህዝብ የራሱ የግሉ የሆኑና እርሱን የሚወዱ፣ የሚታዘዙና ዉብ የሆነዉን የተቀደሰ ህይወት በዙሪያዉ ላሉት አህዛብ የሚኖሩበት መንገድና ከሌሎች ጋር ያላቸውን ህብረት እንዲያሳዩ ነዉ (ዘፍጥረት 12፡1-3) ። ይህንንም በዘጸአት 19፡5-6፣ የእሥራኤል ልጆች ከግብጽ በሚወጡበት ጊዜ የተረጋገጠ ነበር።

የእግዚአብሔር ቃል ብዙ ቦታ ላይ የእግዚአብሔር አላማ እሥራኤላዉያን ህዝብ ለዓለም በረከት እንዲሆኑ ይገልፃል። ለምሳሌ፡ ኢሳ 51፡ 1-4 መጨረሻ ላይ እንደዚህ ይላል፤ *'ኣዳምጠኝ፣ ህዝቤ፣ ስማኝ፣ ህዝቤ፡ ህግ ከእኔ ይወጣልና፣ ፍርዴም ለአህዛብ ብርሃን ይሆናልና።'* ኢሳ. 42፡6 እና 49፡6 እሥራኤልንና መሲሁን ሁለቱንም በተመለከተ የሚናገረዉ ትንቢት ይህንኑ ያረጋግጣል።

***በአዲስ ኪዳን***

በ1ኛ ጴጥሮስ 2፡9 ጴጥሮስ ተመልሶ ከዘጸአት 19፡5-6 ያለዉን ሀሳብ በመጥቀስ በሌላ መንገድ ሲገልፀዉም ማየት እንችላለን። በተለያየ ህዝብ ዉስጥ ያሉትን አማኞች ጠቅሶ እንደዚህ ብሎ ሲናገር እናያለን *‘«እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራቻሁን የእርሱን በጎነት እንድትናገሩ የተመረጠ ትዉልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ፤»’* (1ኛ ጴጥሮስ 2፡9)። ከየትኛዉም ዘር የመጡት አማኞች ሁሉ 'የክርስቶስ አካል ናቸዉ፣ ቤተክርስቲያን፣ የተቀደሰ ህዝብ፣ የእግዚአብሔር የራሱ ቤተሰብ ናቸዉ። አሁን በእምነት ሁላችንም የአብርሃም ልጆች ነን (ገላትያ 3፡28-29፤ ሮሜ 4፡16)፣ በመንፈስም፣ የእግዚአብሔር የተቀደሰ ህዝብ እንድንሆን ‘ሀገራችንን፣ ህዝባችንንና የአባታችንን ቤት ትተን እንድንወጣ’ ታዘናል።

ኢየሱስ በሞቱ የጥል ግርግዳ አፍርሷል፤ በኤፌሶን 2፡14-22 ሲናገር፣ *‘«ይህም ከሁለታቸዉ አንድን አዲስን ሰዉ በራሱ ይፈጥር ዘንድ፣’»* እና *«‘ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁለታቸዉን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነዉ።»’* እግዚአብሔር ሁለቱንም አይሁድንና አህዛብን፣ ልዩ የሆነ አዲስ ህዝብ፣ የራሱ ቅዱስ ህዝብ፣ በዚህ መንገድ ልዩነት ካላቸዉ ሰዎች አንድነትን ከአማኞች ሲፈጥር እናያለን።

የጳዉሎስ ማንነት (ከብንያም ዘር) ፣ እንደ ፈሪሳዊያን ትምህርትና ህግ የተከበረ፣ በኃይማኖተኛነትም ቅዱስ የሆነ ነዉ። ይሁን እንጂ በፊሊጲስዮስ 3፡4-11 በክርስቶስ ያለዉን የመዳንን በረከት በእምነት ለመቀበል ተፈጥሯዊ ማንነቱን መተዉ እንዳለበት ይናገራል። ጳዉሎስ በእዉቀት ማደጉን አላቆመም፣ ዘሩንም አልቀየረም፣ ነገር ግን የተፈጥሯዊ ማንነቱን እሴቶችን በመተዉ ክርስቶስን ያወቀባቸዉን እሴቶች ሲይዝ እንመለከታለን።

ታድያ ቤተክርስቲያን ይህን ወሳኝ የሆነ እዉነታ እንዴት ሳተች?! በባለፈው ምእራፍ በእምነት ወደ ኢየሱስ መምጣት ማለት ሁሉም እርስ በርስ የሚዋደድበትንና የሚከባበርበትን ዓለምአቀፍ የሆነዉን፣ ከልዩ ልዩ ብሔር ማንነት የመጣዉን ቤተሰብ መቀላቀል ነዉ የሚለውን ተመልክተናል። እግዚአብሔርን መዉደዳችንን የምናሳይበት ብቸኛዉ መንገድ ከየትኛዉም ዘር

ይምጣ ወንድማችንን በመዉደድ ነዉ (1ኛ ዮሐ. 4፡19-21) ። ከዚህ በኋላ ሰዎችን ከሰዉኛ አስተሳሰብ አንፃር ማየት አይኖርብንም (2ኛ ቆሮ. 5፡16-19)፣ እኛ በኑሯችን ሁሉ ሰላም አብሳሪ፣ አምባሳደር፣ በሁሉም ረገድ መንግስቱን የምናሳይ ቅዱስ ህዝብ ነን። የአብርሃም ዘሮች የእርሱን ብርሃን ለህዝቡ እንዳሳዩ፣ እንደተቀደሰ ህዝብ እኛም እንደዚሁ ልናደርግ ይገባል።

ይህም አንዱ የማዳን ስራ ሲሆን፤ ሰይጣን ይህንን ወሳኝ የቤተክርስቲያን ተልዕኮ ይሰርቃል።

## የሁሉም ቡድን ህዝብ ይጠቃለላል

የተቀደሰዉ ህዝብ በጣም ልዩ የሆነ ህዝብ ነዉ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔርን ከሚወዱ ከተለያዩ ብሔሮች የተገነባ አንድነት ነዉ (ራዕይ 5፡ 9-10) ። ዓለም አቀፍ የሆነ የተለያዩ ብሔሮች የተገናኙበት ህዝብ ነዉ። ሁሉም የተለያዩ ባህሎች የተወከሉበት ሁሉም የብሔር ቡድኖች የራሳቸዉን ሞገስ ይዘዉ የሚመጡበት ነዉ (ራዕይ 21፡ 24-27) ። ከተቀደሰዉ ህዝብ ጋር ስንቀላቀል ተፈጥሯዊ የሆነ ማንነታችንን አናጣም፤ ነገር ግን የብሔር ማንነታችን፣ በቅዱሱ ህዝብ ዜጋ የበለጠ በመድመቅ፣ ክብር በማግኘት የትልቁ ማንነታችን አንዱ አካል ይሆናል። የብሔር ማንነታችን አይጠፋም ነገር ግን በቀደመው ማንነታችን እንደ ቅዱስ ህዝቦች ትክክለኛውን ቦታ ያገኛል። አሁን እኛ ከራሳችን ቡድን ብሔር ይልቅ ከክርስቲያኖች ጋር ህብረት የምናደርግበት የተሻለ እምነት አለን

### ድራማ

አብዛኛዉን ጊዜ ይህን ለመግለፅ እጅጌ የሌላቸዉን አነስ ያሉ ጃኬቶችን በመልበስ የብሔር ማንነታችንን ለመወከል እንጠቀማለን። እጅጌ የሌላቸውን ትንንሽ ጃኬቶች ስንለብስ የወከልናቸዉን ቡድን ጉዳት ወይም ኩራት ለማሳየት እንሞክራለን። ከዚህ በኋላ አንድ ሰዉ ቅዱሱን ህዝብ የሚወክለዉን ዉብ የሆነ ‘የንጉስ’ ካባ፣ ብዙ ከሆኑ ተስፋ ከሚታዩባቸዉ የተለያዩ ብሔሮች/ሀገሮች ሰንደቆች ወይም ምልክቶች ጋር ያቀርብልናል። ከዛም ምርጫ ይኖረናል፤ የመጣንበትን ብሔር የሚወክለዉን የራሳችንን እጅጌአልባ የሆነዉን ትንሽ

ጃኬታችንን መወከል እና መጀመሪያ የብሔር ማንነታችንን መያዝ ወይም የእኛ ብሔር የተዋጀበትን የቅዱስ ህዝብ የሆነውን የንጉሱን ካባ መተካት።

**ሁሉም እኩል ዋጋ ያለዉ ይሆናል**

በመጀመሪያው ምዕራፍ ላይ እግዚአብሔር ሁላችንም እኩል የሆነ ዋጋ ሰጥቶ እንደፈጠረን አይተናል። ቅዱስ ህዝብ ቀድሞ በእግዚአብሔር ሀሳብ በነበረዉ በተለያዩ ብሔሮች መካከል መኖር ስለሚገባዉ ግንኙነት በተግባር የተፈፀመበት ነዉ። በተቀደሰዉ ህዝብ መካከል ማንም ለማንም የበላይ የሚሆንበት፣ ማንም ለማንም በመቃወም የሚወዳደርበት፣ ማንም ለማንም የሚያስፈራራበት አይደለም። እዚህ ለሁላችንም የሚሆን ቦታ አለ። በዚህም ሥፍራ ልዩነቶች እውቅና የሚያገኙበት መከፋፈል ግን የሚጠፋበት ነው። እርስ በርሳችንም በመቀባበል ልዩነታችንን እናከብራለን። ልክ እንደ ቀደመዉ ቅዱስ ህዝብ (እሥራኤል) ለዓለም ሁሉ ትንቢታዊ መልዕክት እንደነበረዉ ('አምላካችን ይህ ነዉ እኛም እንደ የእርሱ ህዝብ እንዴት መኖር እንዳለብን የሚያሳይ ነው)፣ ስለዚህ እኛም አዲሱ የቅዱስ ህዝብ የሆነዉ ተመሳሳይ የሆነ ትንቢታዊ መልዕክት በተለይም በግጭት ዉስጥ ላሉት ሀገራት አለን። ለዚህም ነዉ ቤተክርስቲያን በተለያዩ ቡድኖች መካከል ያለውን አስደናቂ የሆነውን አንድነት በመግለጥ ቀዳሚ መሆን ያለባት። እኛም ለዓለም ሁሉ ፍቅር ምን እንደሆነ ማሳየት እንችላለን!

እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ከእሥራኤላዉያን ጋር ያደረገዉ፣ ከዛም ልጆቹ ለሆኑት (ለሁለቱም አይሁዶች እና አህዛቦች) በአዲስ ኪዳን ሊያደርግ ላሰበዉ ጥላ ነዉ። እንደዚሁም ደግሞ አዲሱ ቅዱስ ህዝብ ለአዲሲቷ እየሩሳሌም ጥላ ነዉ።

3) **በቅዱሱ ህዝብ የሚዋጀዉ ምንድነዉ?**

ስለመዋጀት ብዙ ነገሮችን ማለት ይቻላል፣ አሁን ግን ቅዱሱን ህዝብ በሚመለከተዉ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ እናተኩራለን።

## የተዋጀ ማንነት

ጤናማ የሆነ ማንነት መያዝ አንዱ የሰዉ ልጅ መሰረታዊ ፍላጎት ነዉ። ሁላችንም ከሌላዉ ዓለም ጋር ባለን ግንኙነት ዉስጥ ምን ዓይነት ሰዎች እንደ ሆንን እና ምን ዓይነት ተቀባይነት እንዳለን ማወቅ ያስፈልገናል። ማንነታችን የሚታነጸዉ ብዙ የተለያዩ መንገዶች ሲሆን፤ ከቤተሰብ፣ ከማህበረሰባችን፣ ከሃይማኖታችን እና ከመሳሰሉት በምንማራቸዉ ነገሮች ነዉ። በህይወታችን የሆነ የተገደብ ነገር አይደለም፤ ነገር ግን እንደ ህይወት ልምዶቻችን ወይም ማድረግ በቻልናቸው እና በጥሩ መንገድ ማድረግ ባልቻልናቸው ነገሮች ምክኒያት ሊቀየር ይችላል። በምዕራባዉያን ዓለም ማንነት ፍፁም ግላዊነትን ሲታይበት፣ በአፍሪካ ውስጥ ደግሞ የአንድ ሰው ማንነት እርሱን በሚወክል ቡድን ላይ የተመሰረተ ነዉ። አብዛኞቻችን ከማንነታችን ጋር እየታገልን እንኖራለን፣ በተለይም በሀፍረት የምንሸማቀቅባቸው ጉዳዮች ካሉና የተገኘንበት ማንነት በስኬት አልባነት የምንታወቅ ከሆነ ተቀባይነት አይኖረውን ብለን እናምናለን።

በክርስቶስ እነዚህ ሁሉ ነገሮች መለወጥ ይችላሉ። አዲሱን ማንነታችንን በእግዚአብሔር የተወደድን ወንድና ሴት ልጆች እንዲሁም በእርሱ ቤተሰብ ውስጥ ያደግን መሆናችንን አቅፎ ይይዛል (ሮሜ 8፡14-17፣ 29፤ ገላትያ 4፡6-7፤ ዕብራዉያን 2፡11-12)። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሁሉንም ሀፍረታችንንና ኃጢአታችንን የተሸከመዉ እኛ ሀሴት እንድናደርግ ነዉ። ሀፍረት በተሞላበትና ተቀባይነት በሌለዉ ማንነት ዉስጥ ከመኖር ይልቅ፣ ክብርና ተቀባይነት ባለበት ቦታ መኖር እንችላለን፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር ፈፅሞ በኢየሱስ ክርስቶስ ለኃጢአታችን ሥርየት በከፈለልን መስዋእት በኩል ተቀብሎናልና። በእርሱ በኩል ባገኘነዉ ማንነት በሁሉም መንገድ ተቀባይነትን እንድናገኝ አድርጎናል ስለዚህም በእርሱ ባለን ማንነት መተማመን እንችላለን።

## የተዋጀ ብሔር

የመጣንበት ብሔር አስፈላጊ የሆነ የማንነታችን አንዱ ክፍል ነው። የብሔር ግጭት ባለበት ሀገር ለሚኖሩት አብዛኛዉ ህዝብ፣ የብሔር ማንነት በጣም ህመም የሚፈጥር ሀሳብ

ነው። ከጨቋኝ ወይም ከተጨቋኝ/ተጠቂ ወገን ልንሆን ስለምንችል፤ ሁለቱም ማንነቶች በሀፍረት የተሞሉ  ሲሆኑ፤ እግዚአብሔር እንድንሆን ፈልጎ በፈጠረን ላይ ደስተኞች መሆን አንችልም፤ የሚሰማንም ስሜት የበላይነት ወይም የበታችነት ነዉ። የተቀላቀለ/ከሁለት/ አይነት ዘር የሆነ ማንነት ያላቸው ሰዎች ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ የትኛውንም ወገን እንደማይወክሉ በሚሰማቸው ስሜት የበለጠ መከራ ውስጥ ይገባሉ።

እግዚአብሔር አማኞችን የቅዱስ ህዝብ ዜጋ እንደመሆናቸው አዲሱን ማንነታቸዉ እንዲያከብሩት እና  ደስተኞች ሆነዉ እንዲኖሩ ይፈልጋል። የቅዱስ ህዝብ አካል መሆናችን፣ ከመጣንበት የብሔር ማንነት የሚያለያየን አይደለም። ይህ *ሥፍራ* የብሔር ማንነታችን የተዋጀበትና የታደሰበት ነዉ። ራሳችንን ባለን ማንነት መቀበል እንችላለን፤ እግዚአብሔርም ለብሔራችን ወዳዘጋጀን መድረሻ ፍጻሜም እንደርሳለን። ይህም አንዳችን ሌላኛዉን ሙሉ የምናደርግበትና በረከት የምንሆንበት *ሥፍራ* ነዉ። በራዕይ 22፡2 ‘«*በወንዙም ወዲያና ወዲህ በየወሩ እያፈራ አሥራ ሁለት ፍሬ የሚሰጥ የሕይወት ዛፍ ነበረ፥ የዛፉም ቅጠሎች ለሕዝብ መፈወሻ ነበሩ*[3]’» ብሎ ይናገራል። የእግዚአብሔር አላማ ሁሉንም ብሔሮች መፈወስ እንጂ፣ ማጥፋት አይደልም። የእያንዳንዱ ብሔር መኖር አላማ አለው፤ በዓለም በረከት ለማድረግ እና በምድር ላይ ያለዉን ህይወት ለመለወጥ የተጠቀመበትም ልዩ መንገድ ነዉ። አብዛኛዉን ጊዜ ሰይጣን እግዚአብሔር ለመልካም ያሰበዉን ነገር ማበላሸትና መረዳታችንን ማዛበት ይፈልጋል። ሁላችንም እግዚአብሔር እንዲያነፃንና ከእርሱ ይቅርታን መቀበል ያስፈልገናል፤ እግዚአብሔር ለብሔሮቻችን የሰጠዉን ስጦታና ጥሪ በማወቅ፣ በዚህ ህይወትም ለእርሱ ክብር በሚሆን መልኩ በመተማመን መመላለስ ይኖርብናል።

## የተዋጀ ባህል

የእግዚአብሔር እቅድ የነበረዉ ቅዱስ የሆነዉ ህዝብ የባህል መገለጫዎችን ጨምሮ በብዙ ነገሮች የበለጸገ፣ ብዙ ቀለማት ያለዉ እንዲሆን ነበር። የተቀላቀሉት ብሔሮችም ከሚወክሏቸዉ ብሔሮች የሚያመጧቸዉ መልካም ባህሎች ይኖራሉ። ላለፉት ጊዜያት የነበረን

[3] የቃል በቃል ትርጉሙ ኤትኖስ ነዉ

መረዳት ክርስትናን በተቀበልንበት ጊዜ፣ (የምዕራባዉያን ባህሎች ካልሆኑ!)፣የተሳሳተና የእኛ ባህሎች መጥፎ/ሰይጣናዊ/ እንደሆኑ ነበር። አብያተክርስትያናት የተለያዩ ባህሎችን ለመግለፅ ቦታ አልነበራቸዉም፤ በሮቻቸዉም ዝግ ነበር። በአሁኑ ጊዜ፣ እግዚአብሔር ይመስገን፣ በእያንዳንዱ ባህል ዉስጥ ውብ የሆነ እና እግዚአብሔር ሊገልጠዉ የፈለገዉ የራሱን ክብር በዉስጣቸዉ የያዙ እንዳሉ እየተገነዘብን ነዉ።

ይሁን እንጂ፣ በወደቀዉ ዓለም ዉስጥ ስንኖር፣ ሰይጣን አብዛኛዉን ጊዜ እግዚአብሔር በባህላችን ዉስጥ ሊገልጥ የፈለገዉን መልካም ነገር ሲከላከልና ሲያጣምም እናያለን። የራሳችን ትክክለኛ መጨረሻ ወደሆነው

የራሳችን ውደሆነው ትክክለኛ መጨረሻ የተቀደሰዉ ህዝብ ውስጥ እስከመጣን ድረስ፣ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያሰበዉን እቅድ ባህላችንን እንዲዋጅና በረከት እንዲሆን መጠየቅ እንችላለን። በኤርምያስ 12፡15 እግዚአብሔር፣ *‹‹ከነቀልኋቸዉም በኋላ መልሼ እምራቸዋለሁ፥ እያንዳንዱንም ወደ ዕርስቱ እያንዳንዱንም ወደ ምድሩ እመልሳለሁ።››* ይሁን እንጂ አስተዋዮችና ስንዴዉን ከገለባ የምንለይ መሆን አለብን። በባህላችን ዉስጥ ያሉት ሁሉም ነገሮች ከእግዚአብሔር ቃል ጋር አብረዉ የሚሄዱ አይደሉም። በቅዱሱ ህዝብ መካከል ብሔራችን የተጣራና ንጹህ የሆነ፣ እግዚአብሔር በዉስጡ ያስቀመጠዉ ልዩ የሆነ መዝገብ በዉስጡ የያዘ ነዉ። ከጠንቋይ ወይም ጣኦት ጋር የተያያዘና መጽሐፍ ቅዱስ የያዛቸዉን እሴቶች የሚጻረር ማንኛዉም ባህላዊና ሥነምግባራዊ እሴቶች በመስቀሉ ሥር መጣል አለብን (ራዕይ 21፡26-27)። በቅደሱ ህዝብ ያለን ዜግነትና በመንግስቱ ዉስጥ ያለን ባህል ቅድሚያ ሊሰጠዉ የሚገባ ነዉ።

## 4) የእግዚአብሔርን ቅዱስ ህዝብ እውነታ ያለመረዳት አስከፊነት

እግዚአብሔር ለቅዱሱ ህዝብ ያለዉን የትልቁን እቅድ ምስል ካልተረዳን፣ አርቀን ማየት የተሳነን ሰዎች እንሆናለን። በብሔራችን/ቡድናችን ላይ ብቻ የምናተኩር እንሆናለን መጨረሻችንም ይኸዉ ይሆናል። የሚከተሉትም ነገሮችም ይከሰታሉ፡

- ከተፈጥሯዊ ማንነታችን ወጥተን በአዲሱ የንጉሳዊያን ዜጋና ሁሉም በእኩልነት በሚኖርበት በእግዚአበሔር ቅዱስ ህዝብ ማንነት ከመኖር ይልቅ በተፈጥሯዊዉ ማንነታችን ቁስል ፣ ኩራትና የመሰሰሉት በሞላት መኖራችንን እንቀጥላለን። ኢሳ. 54፡2 ላይ ሲናገር ሰፊ የሆነ ሥፍራ እንጂ ዉስንነት ያለበት ቦታ መኖር እንደሌለብን ይናገራል።
- በብሔራችን የምንመካ እንሆናለን፣ የእኛ ማንነት የተሻለ ነዉ ብለን ማሰብ እንጀምራለን፣ በሌሎች ላይ የበላይነታችንን መጫን እንፈልጋለን። የሌሎችን ብሔሮች ባህል በጎ ነገሮችንም ማየት ያዳግተናል።
- የራሳችንን ብሔር/ህዝብ ድካምና ጉድለቶች፣ መልካም ወይም ክፉ ባህርያትን ማየትና መለየት ያዳግተናል። የሌሎች ሰዎች/ህዝቦች፣ ባህሎች/ብሔሮች ከእኛ ጋር እኩል ዋጋ እንዳላቸዉ አስበን ማድነቅ ያስቸግረናል።
- አመለካከቶቻችንን እንዲደግፍልን የእግዚአብሔርን ቃል በተሳሳተ መንገድ እንጠቀማለን፣ መናፍቅም ወደ መሆን እንሄዳለን (ልክ በአፓርታይድ ጊዜ በደቡብ አፍሪካ እንደተፈጠረዉ ዓይነት ማለት ነው)።
- ተጨቁኖ ከኖረ ጉዳት ከደረሰበትና ተቀባይነት በሌለዉ ብሔር ዉስጥ ካደግን፣ የሚከተሉት ነገሮች ሊደርሱብን ይችላሉ፤
  - የበታችነት ስሜት በዉስጣችን ይፈጠራል። ይህ ደግሞ በራስ እንዳንተማመንና መነሳሳት እንዳይኖረን ሲያደርግ፤ ይህ ደግሞ በህይወት እጣ ፋንታችን ላይ መወሰን እንዳንችል ያደርገናል።
  - ይህ ደግሞ የራሳችንን ብሔር/ህዝብ/ባህል ወደ ጣኦትነት ይቀይርብናል። ያለንን ጊዜና ጉልበትም ለብሔራችን እኩልነትን ለማምጣት እናጠፋለን።
  - በመጨረሻም ራሳችን ጨቋኞች ሆነን እናገኘዋለን። ራሳችን የእግዚአብሔርን ፈዉስና ምህረት ካልፈለግን ይህ ሊከሰት ይችላል።

### 5) **የቅዱሱ ህዝብ አካል መሆን አዲስ ነጻነትን ይሰጠናል**

በአሁኑ ጊዜ በሺህ የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች የቅዱሱን ህዝብ ዜግነት ተቀብለዉ አዲስ የሆነ ነጻነት አግኝተዋል። በአንድነት ለሃገራቸዉ ጠንካራ ትንቢታዊ ድምጽ ሆነዋል፣ የከፍታን ህይወት ኖረዉ ማሳየት ችለዋል። በፍረጃ፣ ጥርጣሬ፣ አለመተማመን፣ ክፍፍል፣ ኢፍትሃዊነትና እኩልነት የሌለበት፣ ህይወት ከመኖር ፈንታ በእግዚአብሔር እቅድ በመጀመሪያም እንደነበረዉ ልዩነት የሚከበርበት እና አንዱ ሌላውን ወደ ሚያከብርበት አዲስ ህብረት ዉስጥ መኖር ጀምረዋል።

### **ከራስ ጋር ማዛመድ**

- ከአንተ ባህል ዉስጥ ተዋጅተዉ በተቀደሰዉ ህዝብ መካከል እግዚአብሔርን ሊያስከብሩ የሚችሉት እሴቶች የትኞቹ ናቸዉ?
- ከአንተ ብሔር/ባህል ዉስጥ የሚታዩ ጥሩ ያልሆኑ ባህርያት ምን ምንድናቸዉ? (ለምሳሌ፡ ኩራት፣ የበታችነት፣ ብሔርን እንደ ጣኦት ማየት እና... ወዘተ)
- በሀገርህ ዉስጥ ያሉት ሁሉም አማኞች እንደ ቅዱስ ህዝብ መኖር ሲጀምር ምን ዓይነት ልዩነቶችን ማየት ትችላለህ?
- ባንተ በኩል ይህ እዉን እንዲሆን ለመርዳት ምን ዓይነት አስተዋጽኦ ማድረግ ትችላለህ?

### **ቁልፍ የሆኑ ነገሮች**

- የብሔር ማንነታችን አብዛኛዉን ጊዜ የተበላሸ ሲሆን፣ መዋጀትና መታደስ ያለበት ነዉ።
- እንደ ቅዱስ ህዝብ ዜጋ፣ እዉነተኛ የሆነዉን ማንነታችንን ማወቅ እንችላለን።
- ከተለያየ ብሄር የመጣን ብንሆንም እንኳ ሁላችንም በክርስቶስ እኩል የሆነ እሴት ያለን፣ ሌላዉን መቀበል፣ ማቀፍ የምንችልና አንዱ የሌላዉን ጉድለት መሙላት የምንችል ነን።

# ትምህርት አራት

## ቤተክርስቲያን እንደ የለውጥ ማዕከል /ወኪል/

### ቤተክርስቲያን ውድቀቶቹዋን በማሸነፍ እና ሀላፊነቶችዋን በመቀበል የእግዚአብሔር የለውጥ ማዕከል እንድትሆን መርዳት

የእግዚአብሔር ዓላማ ቤተክርስቲያን ላለችበት ሀገር «ጠባቂ» እንድትሆን ነው (1ኛጢሞ.3፥15)። የተለያዩ ነገሮች በተሳሳተ መንገድ በሚሄዱበት ጊዜ አብዛኛውን ጊዜ የጥፋተኝነት ወቀሳው የሚወድቀው ቤተክርስቲያን ላይ ነው። አንዳንድ ጊዜ ቤተክርስቲያን ይህንን የጥፋተኝነት ወቀሳ ወደ መንግስት የማዞር ተግባር ትሰራለች። በማንኛውም ሀገር ውስጥ ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር የፈውስ ወኪል እንደሆነች እናምናለን፤ ይህችም ቤተክርስቲያን የተፈወሰችና የታረቀች እንዲሁም ተልዕኮዋን እንደገና የተረዳችና ያወቀች መሆን አለባት። ምንም እንኳን በብዙ ሀገራት ያሉት ቤተክርስቲያናት እየወደቁ ቢሆንም፤ እግዚአብሔር ለማንኛውም ሀገር ያለው ተስፋ ግን አሁንም ድረስ ያው ነው።

1) **እግዝአብሔር ለቤተክርስቲያን ያለው ዕቅድ**

እግዚአብሔር ለቀደመው ትውልድ ተሰውሮ የነበረ ዕቅድ አለው (ቆላ.1፥26-27) እቅዱም ለመሪዎች እና ለባለስልጣናት እንዲሁም በመንፈሳዊው ዓለም ላይ በቤተክርስቲያን በኩል (በየትኛውም ቤተ እምነት ሊሆን ይችላል፤ እግዚአብሔርን በእውነተኛ ፍቅር በሚወዱና ራሳቸውን ለእርሱ በሰጡ ሰዎች) ላይ የእርሱን ጥበብ ለዓለም ማሳወቅ ነው። እርሱ ለራሱ ቤተክርስቲያን ያለው ፍላጎት ሰዎች፣ በተለያዩ የብሔር ቡድኖች፣ በተለያዩ ፆታዎች እና በተለያዩ ማህበረሰቦች መካከል ሁነው እርስ በእርሳቸው መልካም የሆነ ግንኙነት እንዲኖራቸው እንደሚፈልግ ለአለም እንድትገልጥለት ነው። እርሱ አስቀድሞ ኢየሱስን ወደ ዓለም የላከው የመዋጀታችንን ዋጋ ከፍሎ እንዲገዛንና የእርሱን ሀሳብ /ልብ/ የታወቀ እንዲሆን ነው። ነገር ግን ይህ ጅማሪ ብቻ ነበር፤ ኢየሱስ በምድር ላይ የቆየው ለጥቂት ጊዜያት ብቻ ነበር፤ እርሱ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ የእግዚአብሔር እቅድ ቤተክርስቲያንን በመጠቀም የእርሱን ጥበብ መግለጥ ነበር (ኤፌ.3፥8-11)።

የእግዚአብሔር ዓላማ ሁሉም አማኞች እርሱ የሚኖርበት የእርሱ ማደሪያ በመሆን እንዲገነቡ ነው (ኤፌ.2፡21-22) ። ኢየሱስ በምድር ላይ ብዙም ባይቆይም፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር መንፈስ የድህነትንና የፈውስ ሥራን ለመሥራት ኃላፊነትን በሚወጡ በራሱ ሰዎች ውስጥ ይኖራል። እኛ አማኞች የእግዚአብሔርን ክብር ለዓለም የምንገልጥ ሰዎች ነን።

## የእግዚአብሔር ልጆች በማህበረሰቡ ውስጥ ጨውና ብርሃን እንዲሆኑ ነው

ኢየሱስ፡- «እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ» አለ (ዮሐ.8፡12)፣ እንዲሁም በማቴ 5፡14–16 ደግሞ እንዲህ ብሏል «እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ» ኢየሱስ በሰዎች ህይወት ሲያድር በማህበረሰባቸው ውስጥ የሚያበሩ ብርሃናት ይሆናሉ (ፊሊ. 2፡14–16)። ብርሃን ከጨለማ ባህሪያት ፈፅሞ የተለየ ነው። ከጨለማ ጋር አብረው መኖር አይችሉም፤ ምክንያቱም ብርሃን ጨለማውን ያስወግደዋል።

እኛ ከጨለማው የተለየን ለመሆን የግድ አስቀድመን አዕምሮአችንን በማደስ መለወጥ ይኖርብናል (ሮሜ12፡2)። በምንኖርበት ማህበረሰብ ውስጥ በተመሳሳይ ቅድመ ፍረጃ፣ አለመታመን፣ ጥላቻ፣ በኢፍትሐዊነት ላይ ቸልተኛ መሆንና በመሳሰሉት ላይ እነሱን በመምሰል ከመስማማት ይልቅ እኛ የክርስቶስ ልብ ሊኖረን ያስፈልጋል። እኛ የእግዚአብሔርን ሀሳብ ልናስብና ሁሉንም ነገሮች ከእርሱ እይታ አንጻር ልንመለከት ያስፈልገናል። ሀሳባችን ከተለወጠ ባህሪያችንም ይለወጣል። የዚህ መጽሐፍ ቀሪ ክፍሎች እግዚአብሔር እንዴት አድርጎ ሀሳባችንንና አመለካከታችንን እንደሚያነፃ፣ እንደሚፈውስና እንደሚለውጥ የሚናገር ነው። የተለወጠውም ህይወታችን በምንኖርበት ማህበረሰብ ውስጥ የክርስቶስን ብርሃን እንድናበራ እና በአጭሩ ለወደቀው ማህበረሰባችን የእግዚአብሔርን ሀሳብ ይገልጣል።(ኢሳያስ 60፡1-3)


## ኢየሱስም እኛ የምድር ጨው እንደሆንን ተናግሯል (ማቴ. 5፡13)፡

- እኛ የእግዚአብሔርን እሴቶችና መስፈርቶች በመጠበቅ፣ በማህበረሰባችን ውስጥ ማቆየት አለብን።
- እኛ እግዚአብሔር እንድንኖር በሚፈልገው ዓይነት ኑሮ እየኖርን፣ በማህበረሰባችን ውስጥ የነፃ ሚና እንዲኖረን ነው።

- እኛ የፅድቅን ጥማት እንዲኖረን ነው።
- እኛ ለህይወት ጣዕምና ትርጉም በመስጠት ልዩነት እንድንፈጥር ነው
- ኢየሱስ ለእኛ እንደማለደልን እኛ ለማህበረሰባችን ማላጆች እንድንሆን ነው።
- ቤተክርስቲያን ማንኛውም ዓይነት ያልተገቡ ፖሊሲዎች ሲወጡ ነብያታዊ ድምጿን እንድታሰማና ሁሉንም ክፋቶች/መጥፎ ድርጊቶች/ በመቃወም መቆም አለባት።

**ቤተክርስቲያን እንደ ነብያታዊ ድምጽ**

በብሉይ ኪዳን ላይ፣ እግዚአብሔር በነብያት በኩል ለነገስታትና ለህዝቡ መልዕክት ይልካል (ዕብ.1፡1)። ከዛም ንጉስ ወይም ህዝቡ ለእግዚአብሔር መስዋዕት ማቅረብ ሲፈልጉ ወደ ካህኑ ይሄዱና ካህኑ ደግሞ በእነርሱ ፈንታ በእግዚአብሔር ፊት ይቀርባል።




ይሁን እንጂ በዕብ.1፡2 መሠረት «... *ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን፤*» እንዲሁም በኤፌሶን 3፡10-12 «... *ብዙ ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጥበብ አሁን በቤተ ክርስቲያን በኩል በሰማያዊ ሥፍራ ውስጥ ላሉት አለቆችና ሥልጣናት ትታወቅ ዘንድ፤ ይህም በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የፈጸመው የዘላለም አሳብ ነበረ፤ በእርሱም ዘንድ ባለ እምነታችን በኩል በመታመን ድፍረትና መግባት በእርሱ አለን።*»።

ስለዚህ በአዲሱ ኪዳን የእግዚአብሔር ዕቅድ በቤተክርስቲያን በኩል ለህዝቡ መናገር ነው። ነብያት፣ ካህናት፣ አማኖች፣ አንዳንድ ጊዜ ንጉስ፣ አሁን የቤተክርስቲያን የአካል ክፍሎች ሲሆኑ ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ የቤተክርሰቲያን ራስ ነው (ኤፌ.5፡23»። የእግዚአብሔር ፍላጎት ቤተክርስቲያንን በመጠቀም እንዴት መኖር እንደሚገባን ለሀገር እንድታሳይ ነው። ስለዚህ ቤተክርስቲያን በሁሉም ሀገራት ውስጥ ነብያታዊ ድምጽ መሆን አለባት።

2) **የሰይጣን ዕቅድ**

የብሔረሰብ ግጭት ባሉባቸው አብዛኛው ሀገራት፣ ቤተክርስቲያን የኢፍትሐዊነት እና መከፋፈል መንሳኤዎችን በማድረስ ላይ ያላት ድምጽ ደካማ ሆኖ ቆይቷል። ከዚህም ይልቅ ትኩረቷ ሆኖ የነበረው ስለ መንግስተ ሰማያት ወይም የሀይማኖት ጉዳዮች ላይ ነበር።

ሰይጣን የቤተክርስቲያንን ብርሃን ለማጥፋት ይፈልጋል። የእርሱ ዓላማ ቤተክርስቲያን እና በዙሪያዋ ባሉ ማህበረሰቦች መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት እንዳይኖር እና ቤተክርስቲያንም በማህበረሰቡ ላይ በጎ ተጽዕኖ እያደረገች እንዳልሆነ ማረጋገጥ ነው። ይህንንም የሚያደርገው ደግሞ ተመሳሳይ የሆኑ ሀጢያቶችን፣ ቅድመ ፍረጃን፣ ስግብግብነት፣ ሀይል፣ ፈተናዎች፣ ከሰዋዊነት የወጡ ድርጊቶችን እናም ሌሎች የመሳሰሉትን በዙሪያው ባሉት ማህበረሰብ እና በቤተክርስቲያን ውስጥ እንዳሉ በማሳየት ነው። የሚታይ ልዩነት ከሌለ ቤተክርስቲያን ምንም ልትናገር አትችልም።

እርሱ በተለያዩ ሀገራት ውስጥ የተለያዩ ስልቶች አሉት፤ ነገር ግን መርሆዎቹ ተመሳሳይ ናቸው። በአንዳንድ ከባድ የሆነ ግጭቶች በነበሩባቸው ሀገራት ቤተክርስቲያን ብዙውን ጊዜ ስለ ኢፍትሃዊነት ምንም ነገር አትናገርም ነበር፤ እንዲያውም አንዳንድ ቦታዎች በግጭቶች ውስጥም ተሳታፊ ነበረች። በምዕራባውያን ዘንድ ዓለማዊነት /መንፈሳዊ ያልሆነ/ በአብዛኛው ወደ ቤተክርስቲያን በሙላት ስለገባ በእግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ኃይል ማመን በጣም ደካማ ሆኗል። ቤተክርስቲያን ከዓለም /ከአካባቢው ማህበረሰብ/ የምትለይበት ብቸኛው መንገድ የእግዚአብሔር ህልውና በቤተክርስቲያን ውስጥ መመላለስ /መፍሰስ/ ነው።

የአምፖል ብርሃን ለዚህ መልካም ምሳሌ ነው። የአምፖል ዋናው ተግባር ከዋናው የኤሌክትሪክ ምንጭ ጋር ማገናኘትና ብርሃንን ማመንጨት ነው። ከራሱ ምንም ብርሃን ማመንጨት አይቻለውም። እኛ ምናልባትም ብዙ የተለያዩ መጠን፣ ቅርጽና ቀለም ያላቸው እንዲሁም የራሳቸውን የሚያብረቀርቁበት ጊዜ የሚወስድ የኤሌክትሪክ አምፑሎች ሊኖሩን ይችላሉ፤ ነገር ግን ሁላቸውም ከዋናው የኤሌክትሪክ ምንጭ ጋር  ካልተገናኙ /ካልተሰኩ/ ምንም ጥቅም መስጠት አይችሉም። ቤተክርስቲያን እንደ ብርሃን አምፑል ናት። ሰይጣን እኛን ከእግዚአብሔር  ህይወት ጋር ያለን ግንኙነት በማቋረጥ በጨለማው ዓለም ላይ ምንም ዓይነት ልዩነት እንዳንፈጥር ሊያደርገን ይፈልጋል።

### 3) እግዚአብሔር አሁንም ድረስ ለራሱ ቤተክርስቲያን ተስፋ አለው።

ኢየሱስ ከትንሳኤ /ከሞት ከተነሳ/ በኋላ ለምን ዓይነት ሰዎች ነበር የተገለጠው? እነዚህ ሰዎች ብርቱዎች /አሸናፊዎች/ ነበሩን? አይደሉም፣ እነዚህ ሰዎች ተስፋ የቆረጡ፣ በፍርሃት የተሞሉ፣ ስለውድቀታቸው በጣም ሀዘን የገባቸው ሰዎች ነበሩና ስለወደፊት ያላቸው ተስፋና ራዕይ የጠፋባቸው ሰዎች ነበሩ። ኢየሱስ በተዘጉ በሮች ውስጥ በመካከላቸው በተገለጠ ጊዜ በአንድ ላይ ተሰብስበው የነበሩትን ሰዎች እንዲህ በማለት « *አው፣ እኔ በእናንተ ተስፋ ቆርጫለሁ፣ እኛንተ ምን ዓይነት ደካማ ናችሁ፣ እኔ ሶስት ዓመታት በሙሉ በእናንተ ህይወት ላይ ይህን ያህል መላውን ህይወቴን ሰጥቼ ሠርቼ እናንተ ግን ያው ምንም አልተለወጣችሁም*» ብሎ አልገሰጻቸውም፣ ነገር ግን «*... ሰላም ለእኛንተ ይሁን፣ አባቴ እንደላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ*» (ዮሐ.20፡21) ነበር ያላቸው። በዚህም እግዚአብሔር የራሱን ዕቅድ እንዳልተለወጠ እየተናገረ ነበር። እርሱ አሁንም ቤተክርስቲያኑን ያምናል፤ ከዚያም መንፈስ ቅዱስን በላያቸው ላይ እፍ አለባቸው። በኋላም ሁላቸውንም በመንፈስ ቅዱስ አጠመቃቸው። እነዚህ ለዚህ ብቁ ያልሆኑ ሰዎች ዓለምን ለመለወጥ ጉዞአቸውን ቀጠሉ።

- እግዚአብሔር በማንኛውም ሁኔታዎች ውስጥ የተስፋ አምላክ ነው። ስለዚህ እኛም ተስፋ ማድርገ እንችላለን (ሮሜ 15፡13)።
- ክርስቶስ በአናንተ ውስጥ ነውና ከእርሱ ጋር ያላችሁ ግንኙነት በማህበረሰቡ መካከል የእግዚአብሔር ክብር ተስፋ የሚገልጥ ይሆናል። (ቆላ. 1፡27)።

- እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን እንደዚህ ዓይነት ተስፋ ለምን ኖረው? የእግዚአብሔር ተስፋ ምንጩ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በፈጸመው ሥራ ነው። ክርስቶስ በመስቀል ላይ የፈጸመው ሥራ ሰዎችን ወደ እርሱ የክብር ዓላማዎች ለመመለስ በቂ እንደሆነ እግዚአብሔር ያውቃል (ዕብ. 2፡10)።
- እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን የመጨረሻውን ድል /አሸናፊነት/ ለመስጠት ቃል ገብቷል (ማቴ.16፡18)።

እግዚአብሔር ሁልጊዜ ቅሬታዎች አሉት (እንደ ኖህ፡ ወይም እንደ ኤልያስ ዘመን የነበሩ 7000 ምርጦች) እርሱ እንደገና ካስቀመጠላቸው መስፈርቶችና ጽድቅ የሚመጥኑ ሰዎች ማለት ነው። እኛ ብዙውን ጊዜ በማንኛውም የጦርነት ሁኔታዎችና የብሔርሰብ ግጭት ጥቃቶች ውስጥ ያሉትን የእምነት ጀግኖችን እናከብራለን፤ እንዲሁም እውቅና እንሰጣቸዋለን።

እግዚአብሔር የመጽናናት አምላክ ነው፤ እርሱ በቤተክርስቲያኑ ተስፋ አይቆርጥም። እርሱ በእኛ ሊሠራ የጀመረውን ሊፈጽመው እንደሚችል እምነት /ድፍረት/ አለው(ፊሊ. 1፡6)። እርሱ በቤተ ክርስቲያኑ ይደሰታል (ሶፎ. 3፡17)። ይህ እርሱ ለእኛ የሚናገረው ነገር ምንድን ነው፡

- «እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ»።
- «እናንተ የዚህ ሀገር ተስፋ ናችሁ»።
- «በእናንተ እተማመንባችኋለው»።

ምዕራፍ 15 ቤተክርስቲያን በማህበረሰቡ ላይ እንዴት ተጽዕኖ ማምጣት እንደምትችል የሚገልጥ ተግባራዊ ምክሮችን ሊሰጠን ይችላል፣ ነገር ግን በመጀመሪያ እግዚአብሔር ቤተክርስቲያንን ሊፈውስ እንደሚፈልግ መረዳት አለብን።

### ከራስ ጋር ማዛመድ

- ላላችሁበት ሁኔታዎች አዲስ የሆነ የእግዚአብሔርን ተስፋ ለመቀበል ጊዜ ውሰዱ።
- እርሱ እንዲያበረታህ በመፍቀድና እርሱ በራሱ ህዝብ በኩል ፈውስንና ለውጥን እንደሚያመጣ ማመን።

- ቤተክርስቲያን በአካባቢያችሁ ላሉት ማህበረሰብ የፈውስ ማዕከል /ወኪል/ መሆን ከመቻሏ በፊት ለራሷ ፈወስ የሚያስፈልጋት የሆነበት ምልክቶች ምን ምን ናቸው?

**ቁልፍ ነጥቦች**

- ቤተክርስቲያን በማንኛውም ሀገር ውስጥ ለእርሱ ዓላማ የእርሱን ፈውስና ተሃድሶ ለማምጣት የእርሱ ወኪል እንድትሆን የእግዚአብሔር እቅድ ነው።
- ሰይጣን የእግዚአብሔር እቅድ ተቃዋሚ ነው ነገር ግን እግዚአብሔር አሁንም ለቤተክርስቲያን ተስፋ አለው።
- ቤተክርስቲያን የፈውስ ወኪል መሆን ከመቻልዋ በፊት፣ አስቀድማ በራሷ ካሉ መከፋፈሎች እና ውስጣዊ ጉዳት መፈወስ አለባት።

# ትምህርት አምስት
## የእግዚአብሔር ፍቅር እና መከራ

በአስቸጋሪ አሳዛኝ ሁኔታዎቻችን ውስጥ የፍቅር፣ የፍትህ አምላክን፣ መታመንና መፈለግ እናም እግዚአብሔር የኃጢአት፣ የኢፍትሃዊነትና ከእነዚህ የሚመነጨው መከራ ምንጭ አለመሆኑን ማወቅ።

ሰዎች ለፈውስ ወደ እግዚአብሔር ለመምጣት ከመቻላቸው በፊት፣ እግዚአብሔር ለገጠማቸው ለራሳቸው መከራ እርሱ ተጠያቂ እንዳልሆነ ማወቅ ያስፈልጋል። በአብዛኛውም የአፍሪካ ሀገራት በእጣ ፈንታ ማመን መሠረታዊ እምነት በሆነባቸው ሥፍራዎች ብዙዎች እግዚአብሔር በቸልተኝነት ወይም በግድየለሽነት ይከሱታል። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔርን ስለ ሁሉም

ክፋቶች ይተቹታል፤ ሌሎችም መከራ መቀበል መስቀል የመሸከም አንዱ ክፍል እንደሆነ ይናገራሉ።

ይህ ትምህርት ብዙዎች ለጥርጣሬያቸውና ለቁጣቸው ድምጻቸውን እንዲያሰሙ የሚረዳ ሲሆን ነገር ግን እግዚአብሔር በመከራችን ወቅት ከእኛ ጋር እንደሚሆን እርግጠኛ እንዲሆኑ የሚረዳ ነው። የዚህ እውነት መገለጥ ለብዙዎቹ ወደ እርሱ እንዲመጡና ህመማቸውን ለእርሱ እንዲሰጡ ያደርጋል።

## መከራ በእግዚአብሔር ላይ ለመታመን ያለን አቅም ላይ የሚያመጣው ተፅዕኖ

ሰዎች በአንዳንድ መከራዎች ውስጥ በሚያልፉበት ጊዜ አንዳንድ ጥያቄዎች በልባቸው ሊነሱ ይችላሉ። *«እግዚአብሔር በእውነት እኔን ይወደኛል? እርሱ ክፉ ነገሮች በእኔ ላይ ሲሆኑ ለምን ፈቀደ? እርሱ የእኛን ዘር /ብሔር/ የሚቃወም ነውን?* እንላለን፤ እግዚአብሔር አፍቃሪ፣ መልካምና ቸር አምላክ እንደሆነ መዝሙር መዘመር እንችላለን። ነገር ግን በአንዳንድ ነገሮች ሌላ ልምምድ ያለን ይመስላል። ከንፈራችን መዝሙር ቢዘምርም፣ ልባችን ግን ምናልባት ዝም ሊል ይችላል ወይም ሊቆጣም ጭምር ይችላል። ይሁንም እንጂ ልባችን ስለሚፈረድብን፣ ስለሚገስፁንና ንስሀ ግባ ብለው ስለሚናገሩን እኛ ጥርጣሬዎቻችንን ለመግለጥ እንፈራለን።

ያልተነገሩ በልባችን ውስጥ ያሉ ጥርጣሬዎቻችን ብዙውን ጊዜ «ጭምብል የምናጠልቅ» አስመሳዮችና ሁሉም ነገር መልካም ነው ብለን እንድንገልጥ ሲያደርጉን፤ እኛ ግን ምንም መግለጫ ያልሰጠናቸው በውስጣችን ግን ብዙ ህመሞችና ትግሎች አሉብን። ይህ ደግሞ በጣም ብቸኝነት የሚሰማን እንድንሆን ሊያደርገን ይችላል። ምክንያቱም እነዚህ ስሜቶቻችን ምቾትን የማይሰጡን ምናልባትም በእውነት የሚሰሙን ስሜቶች እንዳሉ ጭምር እንክድ ይሆናል። ነገር ግን ብዙ የእግዚአብሔር ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደዚህ ዓይነት ተመሳሳይ ስሜቶች ጋር ሲታገሉ ነበሩ (መዝ. 22፡1፣ 74፡1፣10-11፣ እንባ.1፡2 አንብብ)።

የሰው ልጆች በተለይም እግዚአብሔር ጻድቅና ፍቅር መሆኑን ሲያስቡ ሁልጊዜ በሚገጥማቸው መከራዎች ጋር ይህንን እውነት ካሉበት ነባራዊ ሁኔታ ጋር ለማጣጣም ሲቸገሩ

ይታያል። ለዚህ እኛ የተለያዩ ምላሾች ሊኖሩን ይችላሉ። ምናልባት እኛ በእጣ ፈንታ የምናምን እንሆንና *«አው መልካም! ነገሮችን ሁሉ እንዳሉበት ሁኔታ መቀበል አለብህ፣ ሌላ ምን ማድረግ ትችላለህ? እኛ በጣም መንፈሳዊ ማድረግና በሁሉም ነገሮች ውስጥ ያለውን ዓላማ እንደገና ለመፈለግ እንሞክራን፣ ወይም እንዲሁ ዝም ብለን ተስፋ ቆርጠን ለወደፊት ያለንን ሁሉንም ተስፋ እናጣለን። ነገር ግን ብዙውን ጊዜ በመከራና በኢፍትሃዊት ውስጥ በማለፋችን ምክንያት ልባችን እንደገና እግዚአብሔርን መክሰስ ይጀምራል፣ ይህንን ሁሉ እርሱ ያቀደው ነውን? ይህንን እርሱ ያቀደው ካልሆነ ለምን ጣልቃ የመግባት እርምጃ አይወስድም? በእርግጠኝነት፣ እርሱ የሚወደን ከሆነ ችግሮች እንዳይሆኑ ሊያስቆማቸው ማድረግ አለበት፣ ስለዚህ እኛ ግራ በመጋባትና በህመም /ስቃይ/ውስጥ እንገኛለን። በተወሰነ ደረጃም ቢሆን እርሱ ለህይወት ደስታና አስተማማኝ ማድረግ የእግዚአብሔር የሥራ ድርሻ እንደሆነና አሁን ግን እንደተካድንና እንደተተውን ይሰማናል። በልባችን ጥልቀት ውስጥ  እውነት እርሱ በመከራችን የማያስብልን ነው? በሚል ልባችን ወደ ክስ ሊቀየር ይችላል።*

ብዙውን ጊዜ ስለዚህ ጉዳይ ምንም አንናገርም፤ በጣም ጠንካራ ክርስቲያኖች ለመሆን እንጥራለን፤ ነገር ግን በልባችን ጥልቅ ውስጥ ብዙ ክሶችና ስቃዮች ሊኖሩ ይችላሉ። እግዚአብሔር በኤር.31፡3 መሠረት ለእኛ ፍቅር እንዳለው እንደሚወድደን ይናገረናል። እኛም *«እንደዚህ ዓይነት ነገር እንዳምን ምንም አትጠይቀኝ፣ አንዳንድ ነገሮች በጣም የተለዩ ነገሮች እንደሆኑ እንዳስብ የሚያደርጉኝ ብዙ ማስረጃዎች አሉኝ»* ብለን ብዙውን ጊዜ በልባችን ውስጥ የምንመልሰው ነገር አለን። ከዚህ ይልቅ እግዚአብሔር ራሱ የችግራችንና የስቃያችን ምንጭ ሊሆን ይችላል ብለን እናስባለን። ምንም እንኳን ለሁሉም ጥያቄዎቻችን መልስ የማናገኝ ቢሆንም ቤተክርስቲያን ለህይወት ትግላችንና ለህመማችን ድምጽን የምናሰማበት አስተማማኝ ሥፍራ ልትሆንልን ይገባል። ነገር ግን እኛ ሁላችንም ልናስታውሰው የሚገባ ነገር ቢኖር የህይወትን የዚህኛውን ገፅ ሁሉንም ነገሮች ለማወቅ እንዳልተፈቀደልን ነው።

## 1. አንዳንድ በልባችን ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉ ድብቅ ክሶች/ ቅሬታዎች/

*1.1. እግዚአብሔር ፍትሃዊ አይደለም፣ ከሌሎች ይልቅ ለአንዳንድ ቡድኖች ያደላል።*

*1.2. እግዚአብሔር ጨካኝ ነው። እርሱ የመከራ ሁሉ ምንጭ ነው። ይህ የእርሱ ፍጹማዊ ፍቃድ ነው። እርሱ እኛን ይቃወመናል፣ በምናልፍበት መከራ እየተመለከተ ይደሰታል።*

*1.3. እግዚአብሔር አቅም የሌለውና ሩቅ የሆነ አምላክ ነው። እርሱ ኃጢአተኞች ክፉት እንዳያደርጉ ሊያስቆማቸው አይችልም፣ ስለዚህ ሰይጣን ከእርሱ ይልቅ በጣም ጠንካራ ነው።*

*1.4. እግዚአብሔር ንጹሃን በመከራ ውስጥ ሲያልፉ አያስተብላቸውም፣ አይገደውም።*

አንተ/ቺም በእንደነዚህ ዓይነት ቅሬታዎች እየታገሉ ይሆን? እነዚህ ቅሬታዎች አብዛኛውን ጊዜ የሚመነጩት ከህመም /ስቃይ/ና ከተሰበሩ ልቦች ውስጥ ነው። ስለዚህ ለእነዚህ ከሥነ መለኮታዊ መልሶች የበለጡ መልሶች ያስፈልጉናል። ከመንፈስ ቅዱስ ስለእግዚአብሔር ባህርይ መገለጥን ያስፈልገናል። ያሉንን አስቸጋሪ ጥያቄዎቻችንና ጥርጣሬዎቻችንን ልናወጣ፣ ልናሰማ፣ የልባችንን ህመሞች በእግዚአብሔር ፊት ልናፈስስ ያስፈልገናል። በዚህ መጽሐፍ ስለእነዚህ ጉዳዮች ወደ ኋላ ላይ ብዙ እንማራለን። ነገር ግን ከመጽሐፍ ቅዱስ ሊረዱን የሚችሉ እውነቶችን ፈልገን ማውጣት እንችላለን።

## 2. እነዚህ ሊረዱን የሚችሉ አንዳንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆዎች ናቸው።

### 2.1. እግዚአብሔር ጻድቅና ፍትህን የሚወድድ አምላክ ነው።

በዚህ ርዕስ ላይ ቅዱሳት መጽሐፍት በጣም በግልፅ «... *እርሱ አምላክ ነው፤ ሥራውም ፍጹም ነው፤ መንገዱም ሁሉ የቀና ነው፤የታመነ አምላክ፥ ክፋትም የሌለበት፥ እርሱ እውነተኛና ቅን ነው» (ዘዳ.32፡4)* ይናገራል።

*«... የምትሠሩት ነገር ይህ ነው፤ እያንዳንዳችሁ ከባልንጀራችሁ ጋር እውነትን ተነጋገሩ፤ በበር አደባባያችሁም የእውነትንና የሰላምን ፍርድ ፍረዱ፤ ሁላችሁም በባልንጀራችሁ ላይ ክፉን ነገር በልባችሁ አታስቡ፤ የሐሰትንም መሐላ አትውደዱ፤ ይህን ነገር ሁሉ እጠላለሁና፥ ይላል እግዚአብሔር»* (ዘካ. 8፡16 -17) ።

ስለዚህ እርሱ የምንም ዓይነት ኢ-ፍትሃዊነት ምንጭ ሊሆን አይችልም። ሰዎች በሀገር ውስጥ ላለው ለኢፍትሃዊነት ችግር የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ብለው ለሚናገሩት ነገር ይህ ከእግዚአብሔር ባህርይ ጋር የሚጣጣም አይደለም። ነገር ግን ለምን ህይወት ኢፍትሃዊነት አጋጠማት? ይህንን ለመረዳት እንዴት ይቻላል ለሚለው ህይወት ኢፍትሃዊ በሆነችበት ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔር ግን ፍትሐዊና ጻድቅ ነው፣ ስለዚህ አስቀድመን ስለእግዚአብሔር ፈቃድ የበለጠ ማወቅ ያስፈልገናል።

**2.2.እግዚአብሔር መልካምና ቸር አምላክ ነው። ማንኛውም የሚሆኑ ነገሮች የእርሱ ፈቃድ አይደሉም። ምክንያቱም**

2.2.1. ***እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ከሰጣቸው ስጦታዎችዎ መካከል አንዱ ነጻ ፈቃድ ነው።*** እኛ በነጻ ፈቃድን በኩል ክቡርና ዋጋ ያለን ሰዎች ነን። እኛ ሮቦቶች አይደለንም። እግዚአብሔር በራሳችን ነጻ ፈቃድ ህይወትን እንድንመርጥ ይፈልጋል (ዘዳ. 30፡15 -19) ። እግዚአብሔር ለእኛ በሰጠው ነጻ ፈቃድ ተጠያቂ የሚሆነው ለምንድን ነው? ያለመምረጥ ነጻነት ፍቅር የሚባል ነገር የለም። ሮቦት ምንም ማፍቀር አይችልም። ነጻ ፈቃድ ከነጻነት ጋር እኩል ነው። እግዚአብሔር ለእኛ በሰጠው የመምረጥ ነጻነት ኃላፊነቱን ይወስዳል፤ ይህም ማለት እኛ ባደረግነው የተሳሳተ ምርጫ ጭምር ማለት ነው። እኛ ሮቦቶች ብንሆን ኖሮ የፍቅር ግንኙነት ማድረግ የማንችልና ለራሳችን ህይወት ምንም ክብር የሌለን እንሆናለን።

2.2.2. ***እግዚአብሔር ኃጢአትን ይጠላል*** (ምሳ.6፡16–19) ።ኃጢአት የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም። ሁሉም ነገር የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ እግዚአብሔርን ለኃጢአትም ተጠያቂ ያደርገዋል ማለት ነው? ያዕ. 1፡13 -17 ግን ግልጽ እንደሚያደርግልን ሰው ለራሱ የኃጢአት ምርጫ ተጠያቂ እንደሆነና እግዚአብሔር ሁልጊዜ ለሰው የሚሰጠው መልካም ስጦታን እንደሆነ በግልጥ ይናገራል። እግዚአብሔርን አለመታዘዝ መምረጥ አደገኛ የሆነ መዘዝ ይዞብን ይመጣል። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን ለመስማት አለመፈለግ ስለሚያመጣው መከራ

ማስጠንቀቂያ የተሞላ ነው። መጽሐፍ በያዕቆብ መልዕክት ውስጥ ኃጢአት ወደ ሞት እንደሚያመራ ይናገራል።

**ማሳሰቢያ፡** መከራችን ሁልጊዜ የእኛ የተሳሳተ ምርጫ ውጤት ነው እያልን አይደለም። መከራን ከእኛ የተሳሳተ ምርጫ ብቻ የተነሳ የምንቀበል ባይሆንም ነገር ግን ከሌሎች የተሳሳተ ምርጫ የተነሳም ጭምር መከራን ልንቀበል እንችላለን። መሪዎች የተሳሳተ ምርጫን የሚያደርጉ ከሆነ ብዙ ንጹሃን አስጨናቂ መከራን ሊቀበሉ ይችላሉ።

2.2.3. ***እግዚአብሔር በእኛ የተሳሳተ ምርጫ ይጎዳል*** (ዘፍ.6፡5-6)፡ የእርሱ ልብ በሀዘን ሊሞላ ይችላል። ሁሉም የቅዱሳን መጽሐፍት ክፍሎች የእግዚአብሔርን የልብ ጩኸት ያሰሙናል።

- መዝ.81፡10-14 ቢሰሙ ኖሮ፣ የበረከት ህይወት ይኖራቸው ነበር።
- ኢሳ 48፡17-18 ልብ ብለህ ቢሆን ኖሮ ሰላምህ እንደ ወንዝ በፈሰሰ ነበር።

2.2.4. ***እግዚአብሔር አንዳንድ ነገሮች እንደሚሆኑ ያውቃልና አንዳንዴ እንዲሆኑ ፈቀደ ማለት ዘላለማዊ ፈቃዱ ነው ማለት አይደለም።*** ኢየሱስ ይህንን በሉቃስ 13፡34 እና ሉቃስ 19፡41-44 ባለው ክፍሎች ግልጽ ሲያደርግ የእርሱ ዘላለማዊ ፈቃድ ህዝቡን መውደድና መጠበቅ ነበር፤ ነገር ግን እነርሱ ወደ እርሱ ለመምጣት ፈቃደኞች አልሆኑም። እርሱ ራሱ የእነርሱ ምርጫ መዘዝ ምን እንደሆነ አስቀድሞ ተናግሯቸዋል፣ ነገር ግን ስለዚህ ጉዳይ እናለቅሳለን። ይህ እርሱ እንዲሆን የሚፈልገው ጉዳይ አይደለም።

2.2.5. ***በጌታ ጸሎት ውስጥ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ስለ ጸሎት አስተማራቸው።*** «... *ስምህ ይቀደስ፤ መንግሥትህ ትምጣ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን*» (ማቴ.6፡10)። በሰማይ በእግዚአብሔር ዘንድ ምንም ዓይነት ኢፍትሃዊነት፡ ህመም፣ መከራ የለም። በግልፅነት፣ የእርሱ ፈቃድ ብዙውን ጊዜ በምድር ላይ ሲሆን አይታይም።

### 2.3.እግዚአብሔር ሁሉንም የሚችል አምላክ ነው ነገር ግን፡

2.3.1. ***እርሱ ለሰው ልጆች የሰጠውን የመምረጥ ነጻነትን /አይወስደውም/ አያስወግድም ።*** እርሱ በማስገደድ ኃጢአትን እንዳንሠራ ቢያደርግ (ለምሳሌ፡ በመግደል ወይም ገዳዮችን በማዳከም ወይም እነርሱ በተለየ ሁኔታ እንዲያስቡ ማስገደድ) በእርሱ አምሳያ የተፈጠርን ነጻ የእርሱ ወኪሎች መሆን አንችልም።

2.3.2. ***እርሱ ኃጢአተኞችን ሁሉ ባጠፋት በዛች ቅስፈት (አሁኑኑ፤እዚሁ) ወደ ፍጻሜ ፍርድ ላያመጣቸው ይችላል።*** 2ኛጴጥ. 3፡7– 13 እንደሚያስተምረን እግዚአብሔር ለፍርድ አይቸኩልም /ይዘገያል/። ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ብሉይም ሆነ አዲስ ኪዳን እንደሚነግሩን እግዚአብሔር ይፈርዳል፤ ነገር ግን እንዲሁም በተመሳሳይ ጊዜ እርሱ ኃጢአተኞችን በተመለከተ ለቁጣ የዘገየና ታጋሽና ትዕግስተኛ እንደሆነ ይናገራል። አምላካችን እግዚአብሔር በኃጢአተኞች ላይ በሚደርሰው ፍርድ ደስተኛ አይደለም፣ነገር ግን ከዛ ይልቅ ወደ ንስሀ እንዲመጡ ይናፍቃል (ህዝ. 18፡23)። እርሱ ንስሃ በሚገቡት ሰዎች ምህረትን በማድረጉ ደስተኛ ነው (ሚክ. 7፡18)።

ነገር ግን የፍርድ ቀን ግን ወደፊት ይመጣል። *«…መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳደረገ፥ እያንዳንዱ በሥጋው የሠራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናልና»* (2ኛ ቆሮ.5፡10) ። ንስሃ ለሚገቡ ምህረትን ይቀበላሉ፤ እንዲሁም ንስሃ በማይገቡ ላይ ፍርድን ያመጣል። እስከዚያው ድረስ እኛ የምንኖረው በጸጋ ጊዜ /ቀን/ በእግዚአብሔር ምህረት ንስሃ ለሚገቡ ሁሉ የሚሰጥ እድል አለ።

በእርግጥ፣ ኃጢአት ሁልጊዜ የራሱ የሆነ መዘዞች አሉት። «… *አትሳቱ፤ እግዚአብሔር አይዘበትበትም። ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና፤ በገዛ ሥጋው የሚዘራ ከሥጋ መበስበስን ያጭዳልና፥ በመንፈስ ግን የሚዘራው ከመንፈስ የዘላለምን ሕይወት ያጭዳል»* (ገላ.6፡7– 8)። በተጨማሪ ንስሃ ብንገባ ከእግዚአብሔር ዘንድ ዘላለማዊ ይቅርታን እንቀበላለን፣ እኛ በዚህ ህይወት ስለሠራነው ብድራትን ለመቀበል አሁንም እንገደዳለን።

***የማይለወጠው የፍትህ፣ የቸርነት፣ የጸጋና የምህረት አምላክ እግዚአብሔረር ለቤተክርስቲያን በዓለም ላይ እርሱን ለመወከል ኃላፊነትን ሰጥቷታል።***

ምንም እንኳን እግዚአብሔር ለጸሎታችን መልስ ለመስጠት አንዳንድ ጊዜ በተዓምራት ጣልቃ ቢገባም (ማብራርያ ላይ ያለውን ይመልከቱ)፣ እርሱ ግን በቤተክርስቲያን በኩል ለመሥራት ቅድሚያ ይሰጣል። ይህ መንገድ ቤተክርስቲያንንም ሆነ ማህበረሰብን ሊለውጥ ይችላል። እርሱን ለሚወዱት ሰዎች ኃላፊነትን ይሰጣል፡-

- እርሱ እንዴት እንድንኖር እንደሚፈልግ ሊያሳየን፤
- ለሀገራችን እንድንማልድ፤
- በህይወታችን አደጋ ላይ ያለን ብንሆንም እንኳን ኢፍትሃዊነትን ተቃውመን እንድንናገር፣
- የመጣበት ብሔር ምንም ይሁን፣ ባልንጀራችንን /ጎረቤቶቻችንን/ እንደ ራሳችን አድርገን እንድንወድ ነው።
- ጨቋኞችን (የሚያስጨንቁትን) እንድንታገል፤
- በሁሉም ሁኔታ ውስጥ ፍቅር የሚፈልገውን ማንኛውንም ነገር እንድናደርግ፤
- የእርሱ የፈውስና የእርቅ ወኪል ለመሆን፤

## መ. እግዚአብሔር ፍቅርና በርህራሄ የተሞላ ነው። እርሱ ንፁሃን መከራን ሲቀበሉ በጥልቀት ያስባል።

***እግዚአብሔር ይገደዋል፡*** እርሱ የልጆቹን መከራ ሲመለከትና (ዘጸ. 3፡7) በእርሱ ፈንታ ሆነው እንዲረዱአቸው አገልጋዮቻቸውን ለመላክ ይፈልጋል (ኢሳ.6፡8)። በወንጌላት ውስጥ ብዙ ጊዜያት መከራን እየተቀበሉ ላሉት «ኢየሱስ በርህራሄ ያዝን ነበር» ብለን አስቀድመን ተነጋግረናል። እግዚአብሔር «… *የርኅራኄ አባት የመጽናናትም ሁሉ አምላክ የሆነ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት*» (2ኛቆሮ. 1፡3-4) ተብሎ ይጠራል።

***እግዚአብሔር ያዝናል፡*** እግዚአብሔር በመከራ ውስጥ እየተሰቃዩ ለሚገኙት ሰዎች ማንም ሰው ጣልቃ በማይገባበት ጊዜ ያዝናል (ኢሳ. 59፡15-16፣ ህዝ. 22፡30) ።

***እርሱ ህመማችንን ይጋራል፡*** ከልበ ጨካኝነት /ግድየለሽነት/ የራቀ ነው፣ እርሱ ከእኛ ጋር መከራን ይቀበላል (ኢሳ 63፡9፣ ኢሳ 43፡2፣ መዝ. 139፡7-8) ። እኛ በምንፈልገው መንገድ በመከራችን ጊዜ ጣልቃ ባይገባም እንኳን፣ እርሱ ስለ እኛ አይገደውም ማለት አይደለም።

***እርሱ ጉድለታችንን /ማጣታችንን/ ወደ ሙላት ሊለውጠው ይፈልጋል።*** እርሱ መርገምን ወደ በረከት መለወጥ የሚችል አምላክ ነው (ዘዳ.23፡5) ። ስለዚህ ጉዳይ ወደ ኋላ ላይ በሰፊው እንመለከታለን።

## ከራስህ ጋር አዛምድ

- እግዚአብሔር ላንተ ያለውን ፍቅር የምትጠራጠርበት ምን ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ነህ ?
- በልብህ ውስጥ ያለ ስለእግዚአብሔር ያሉህ ቅሬታዎች ምንድን ናቸው?
- ከምን ዓይነት አስቸጋሪ ጥያቄዎች ጋር እየታገልክ ትገኛለህ? ለአንተ ሰላምን የሚሰጡህን ሀሳቦች በማስታወሻ መዝግብ።

## ቁልፍ ሀሳቦች

- እግዚአብሔር መልካምና ጻድቅ አምላክ ነው፤ እርሱ የኢፍትሃዊነት ምንጭ አይደለም።
- እግዚአብሔር በፍቅርና በርህራሄ የተሞላና መከራዎቻችን ከእኛ ጋር ሚካፍል ነው።

# ትምህርት ስድስት

## እግዚአብሔርን እንደ አፍቃሪ አባት ማወቅ

### እግዚአብሔር ምድራዊ ወላጆቻችን ያጎደሉብንን በመሙላት የደረሱብን ህመም/ቁስሎች/ እንዴት እንደሚፈውስ/እንደሚያድን/ መረዳት

እግዚአብሔር ሁሉም ሰው የእርሱን ፍቅር ምሳሌ ባደረጉ አፍቃሪ በሆኑ ወላጆች እንድናድግ ሀሳቡ ነው፤በርግጥ የተወሰኑ ሰዎች ብቻ ይህንን ለማግኘት ችለዋል። ብዙዎች ግን ከቀደመው ልምምዳቸው የተነሳ የእግዚአብሔርን አባታዊነት ልብ ማየት አቅቷቸዋል። ይህም ደግሞ ካሉባቸው ሌሎች ህመሞች/ቁስሎች ለመፈወስ ወደ እግዚአብሔር መምጣት እንዳይችሉ እንቅፋት ይሆንባቸዋል።

የዚህ ተፅዕኖ እጅግ ብዙ ነው፣ የግለሰቦች ህይወት ላይ ብቻ ሳይሆን ቤተሰቦቻቸውንም፣ ሀገርንም ጨምሮ ይጎዳል። ሀገር ከመዳንዋ/ከመፈወሷ/ በፊት ግዴታ ቤተሰብ መፈወስ/መዳን/ ይኖርበታል፤ እርቅ የሚጀምረውም ከቤት ነው።

### 1. ኢየሱስ አብ አባቱን ለእኛ አሳየን

ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እግዚአብሔርን እንደ አባት ይ

ግልፁታል። አንዳንዶች በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሲሆኑ (መዝ. 68፡5፣ ኢሳ 63፡16፣ 64፡8፣ ኤር 3፡19) ነገር ግን አብዛኞቹ ደግሞ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይገኛሉ፤ ምክኒያቱም ከማንም በበለጠ አብን ያስተዋወቀን እየሱስ ስለሆነ። ዮሐ.1፡18 እንደሚናገረው ኢየሱስ የመጣው ከአባቱ እቅፍ ነበር። እርሱ በቋሚነት በአባቱ እቅፍ ነበር፤ በአባቱ ታቅፎ ነበር የሚኖረው። በዮሐ.17፡24 ኢየሱስ እርሱ ባለበት ሥፍራ ሁሉ ከእርሱ ጋር እንድንሆን እንደሚፈልግ ተናገረ። ይህም ማለት እኛንም ወደ አባቱ እቅፍ ሊወስደን ይፈልጋል ማለት ነው። ይህም እርሱ ወደ

ምድር የመጣበት ዓላማ ነው። በእርሱ በኩል ካልሆነ በስተቀር ማንም ወደ አባቱ ሊመጣ አይችልም። ኢየሱስ መንገድ ነው፤ የአባቱ እቅፍ ደግሞ የእኛ መዳረሻ ነው። ኢየሱስ የመጣው ለኃጢአታችን ዋጋ ሊከፍልና ወደ አባቱ የምንሄድበት መንገድ ሊከፍትልን ነው። እንዲሁም እርሱ ደግሞ ያረጋገጠልን ጉዳይ እርሱ እራሱ አባቱን እንደሚመስል ነው።

## 2. ወደ እግዚአብሔር እቅፍ እንዳንሮጥ የሚከለክለን ምንድን ነው?

ኢየሱስ ከእኛ የሚፈልገው እንደ አፍቃሪ አባት ከእግዚአብሔር ጋር ባለን የጠበቀ ህብረት ሙሉ በሙሉ ፍቅርን እንድንለማመድ ነው። ነገርግን ብዙዎቻችን ከእርሱ ርቀን የሆነ ቦታ ተደብቀን ወደ እርሱ ለመቅረብ እንፈራለን። አሁን ለብቻችን እርሱ እቅፍ ውስጥ ለመግባት መገስገስ አለብን። ለዚህ ደግሞ ብዙ ምክንያቶች አሉ፤ እነርሱም፡-

2.1. እግዚአብሔርን እንደ ጨካኝ፣ አምባገነን አድርጎ የሚያቀርብልን የተዛባ የሥነመለኮት ትምህርት።

2.2. በሕይወታችን ውስጥ ለሚያጋጥሙን ኢፍትሐዊነት እና ጉዳቶች (እግዚአብሔር) እርሱ ምንጬ እንደሆነ አድርጎ የሚያሳየን።

2.3. ከምድራዊ አባቶቻችን ጋር የነበረን አሉታዊ የሕይወት ግንኙነት እና ልምምዶች።

ይህም በመላው ዓለም ባሉት ሁሉም ባህሎች የሚከሰት ነው። በዚህ ምዕራፍ ትኩረታችን አድረገን የምንመለከተው በሶስተኛ ደረጃ ላይ የተጠቀሰው እንቅፋት እርሱም ከምድራዊ አባቶቻችን ጋር የነበረን አሉታዊ ግንኙነት ነው። ከዚህ በፊት ግን ሁሉም የሰው ልጆች የሚፈልጉት ምንድነው የሚለውን እናስብ።

## 3. የሰው ልጆች መሠረታዊ ፍላጎቶች

ሁሉም የሰው ልጆች ከብዙ አይነት ፍላጎቶቻቸው ጋር ተወልደው ወደዚህ ምድር /ዓለም/ መጥተዋል፡ አካላዊ (ምግብ፣ ልብስ፣ መጠለያና የመሳሰሉት)፤ አዕምሮአዊ (ትምህርት) እና መንፈሳዊ ፍላጎቶች ናቸው። እግዚአብሔር እነዚህን ፍላጎቶች በትኩረት ይመለከታቸዋል፣ እኛም

እንደዛው መመልከት ይኖርብናል። ሁሉም ሰው የልብ የሚለው ፍላጎት አለው፤ እነዚህም ፍላጎቶች ልክ እንደሌሎችም ፍላጎቶች አስፈላጊ ናቸው። ነገር ግን አብዛኛውን ጊዜ በትክክል አልተረዳናቸውም ወይም ችላ ብለናቸዋል። እነዚህ ፍላጎቶች ምንድን ናቸው?

**ጥበቃ፡** ሁሉም ልጆች የተወለዱባት ዓለም ለመኖሪያ የተመቸች ሰላማዊ ሥፍራ እንድትሆን ማወቅ ይፈልጋሉ። ብዙውን ጊዜ ልጆች ዋስትና የማጣት ስሜት ሊሰማቸው ይችላል፤ ምክንያቱም

1. በወላጆቻቸው መካከል ፍቅር የሌለ እንደሆነ፤
2. በአንዳንድ ጉዳዩች /መንገዶች/ በወላጆቻቸው ጥቃት ደርሶባቸው ከሆነ፣ ወይም ወላጆች ከልጆቻቸው አቅም በላይ የሚፈልጉት/የሚጠብቁት ነገር ሲኖር፤
3. በቤተሰባቸው መካከል በሽታ ወይም በሞት መለየት አጋጥሟቸው ከሆነ፤
4. በቤተሰባቸው ወይም በማህበረሰባቸው መካከል ግጭቶች ተፈጥረው ከሆነ፤

ያህዌህ ሻሎም የሆነው የሰላም አምላክ በእያንዳንዱ የህይወታችን ቀናት ሰላምን ያውጅልናል (መዝ. 91፣ ኢሳ. 41፡10)።

## ተፈላጊነት ያለው፣ ዋጋ ያለውና ዓላማ ያለው መሆን

ተፈላጊነት ያለው፣ ዋጋ ያለው /የከበረ መሆን/ ና ዓላማ ያለው መሆን የሁሉም የሰው ልጆች የልብ ጩኸት ነው። ሁሉም ሰው ህይወቱ ዓላማ ያለው መሆኑን ማወቅ ይፈልጋል። ሁሉም ልጆች በዚህ ዓለም ላይ አንድ ነገር ማድረግ /አስተዋጽኦ ማበርከት/ እንዳለበትና እርሱም እዚህ ምድር ላይ ከመኖሩ የተነሳ ይህቺ ዓለም የበለጸገች እንደሆነች ማወቅ ይፈልጋሉ፤ እነርሱ በዚህ ምድር ላይ ከሌሉ አንድ ነገር ሊጎድል ይችላል። ይህ በተለይ ደግሞ ልጆች በተወሰነ የአካል ክፍሎች የአካል ጉዳተኛ ከሆኑ የሚታይ ሐቅ ነው። የእኛ ዋጋ አሰጣጥ በምናደርገውና ባላደረግነው ነገር ላይ በመመርኮዝ ሳይሆን በእግዚአብሔር ውስጥ እኛ ባለን ማንነት መሆን አለበት። እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ የሰው ልጆች ዓላማ ያለው ነው።

***ሀ. ልጆች ዋጋ እንዳላቸው እንዴት ሊቀበሉ ይችላሉ?*** ከሰዎች አድናቆትን የሚሰሙ ከሆነ፣ እውቅና ከተሰጣቸው፣ በስማቸው የምንጠራቸው ከሆነ፣ ለመምረጥ እንዲችሉ እድል ከሰጠናቸው፣ ከእነርሱ አስተያየት የምንጠይቅ ከሆነ…

***ለ. እንዴት ዋጋ እንደሌላቸው /እንደማይጠቅሙ እንዲሰማቸው/ እናደርጋቸዋለን?*** በመስደብ፣ በአደባባይ በህዝብ ፊት በመቅጣት፣ እንዳይጫወቱ መብታቸውን በመከልከል፣ በእኛ ፊት ወንድማቸው/እህታቸው ከእነርሱ ይልቅ ተቀባይነትን ሲያገኙ፣ ከእንግዳ ጋር እንዲቀመጡ ስናስገድዳቸው፣ በጠረጴዛ ላይ ከእኛ ጋር እንዳይበሉ ስንከለክላቸው …

***ሐ. እግዚአብሔር እንዴት ዋጋ ሰጠን /አከበረን/?*** ፡ በእርሱ አምሳያ እኛን በመፍጠር፣ የራሳችንን ነጻ ምርጫ እንድንጠቀም በማድረግ፣ ከእኛ ጋር አብሮ በመሥራት ( 2ኛ ቆሮ. 6፡1)፣ እኛ ለመዋጀት ትልቅ ዋጋ በመክፈል (1ኛጴጥ.1፡18-19)፣ እንደ ወዳጅ እኛን በመጥራት (ዮሐ.15፡ 15)።

***ፍቅር፡-*** እያንዳንዱ ሰው በሰው እንደሚወደድ ሊሰማው ይፈልጋል። እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ፍቅር በምንም ነገር ላይ ያልተመሠረተ ፍቅር ነው፣ አንዳንድ ነገሮች በማድረግ ወይም አንድ ነገር በመሆን ላይ የተመሠረተ አይደለም። እግዚአብሔር በፍቅር ይናግረናል (ኢሳ 49፡15፣ ኤር.31፡3)። እኛ እንኳን ንስሃ ሳንገባ በፊት እርሱ ልጁን ለእኛ በመላክ ፍቅሩን ገለጠልን (ሮሜ 5፡ 8፣ ኤፌ. 2፡4)። የእግዚአብሔር ፍላጎት እኛ ለወላጆቻችን በምንም ነገር ላይ ያልተመሠረተ ፍቅር እንድናገኝ ነው።

አብዛኛውን ጊዜ ወላጆች ለራሳቸው ፍቅርን በማያገኙበት ጊዜ እነርሱም በአጸፋው መልሰው መስጠት አይችሉም፣ እንዲያውም ለልጆቻቸው መሠረታዊ ፍላጎቶችን አያሟሉም። ብዙውን ጊዜ የምድራዊ ቁሳቁስ ፍላጎቶችን ለማሟላት ጥረት ሲያደርጉ ይታያል፤ ይህ ደግሞ እግዚአብሔር እንድናውቀው ከሚፈልገው የፍቅር ግንኙነት ጋር ሲነጻጸር  በቂ አይደለም። ተዓማኒነት ያለው ለመሆን ፍቅር በንግግርና በስሜታዊ መንገዶች የሚገለጥ ሲሆን በአካላዊ ፍላጎቶችና በአዕምሮዊ ፍላጎቶች መሟላት የጠነከረ ይሆናል።

**ፍቅርን በትክክል ለመተግበር የተለያዩ መንገዶች አሉ።**

***ሀ. በቃላት፡-*** ልጆች የተወደዱ መሆናቸውን በሚሰሙት የፍቅር /ቸርነት/፣ ሙገሳና አድናቆት ቃላት ማወቅ ይችላሉ። ይሁንም እንጂ በብዙ ባህሎች ውስጥ ለወላጆች «እወድሃለሁ» «እኮራብሃለሁ» ማለት እጅግ አስቸጋሪ ነው። እነርሱ ማቀፍን ወይም እንደሚወዷቸው መናገር (በእንዲህ ዓይነት መንገድ ፍቅርን መግለጥ) የሚያበላሽባቸው ይመስላቸዋል። የጣፋጭ የፍቅር ቃላት መጉደል እንደ ክፉ ቃላት ዓይነት የሚጎዱ አሉታዊ ነገሮች ናቸው (ምሳ.12፡18፤ 15፡4፣ 18፡21)። እግዚአብሔር ግን «እወድሃለሁ» ብሎ ለመናገር ምንም ቸልተኛ /ሰነፍ/ አይደለም። እኛ የእርሱ አድል ፈንታ /የከበረ ሀብቱ/ ነንና (ዘዳ.7፡6)።

***ለ. በፍቅር በማቀፍ /ወዳጅነት/፡-*** አግዚአብሔር አካላዊ ፍቅርን እንድንቀበል አድርጎ ፈጥሮናል። ይህ በአንዳንድ ባህሎች ግን ትንንሽ ልጆች ካልሆነ በስተቀር በማሽማቀቅ ወይም የፆታዊ ግንኙነት ትርጉም እንዳለው ይታሰባል ። ይህ በጣም ያሳዝናል ምክንያቱም ሁላችንም መታቀፍ ያስፈልገናል።

***ሐ. በጋራ ትርጉም ያለውን ጊዜ በማሳለፍ፡-*** አንድ አባት ወይም እናት ከልጃቸው ጋር ጊዜ ሰጥተው ግንኙነት ሲያደርጉና ጊዜ ሰጥተው ልጆቻቸውን ሲሰሙ፣ አብረው ሲጫወቱ፡ *«አንተ ለእኔ አስፈላጊ ነህ» «ለአንተ ጊዜዬንና ትኩረቴን የምሰጥህ አንተ የሚገባህ ነህ»* ማለት ነው። አንድ ልጅ ከወላጆቹ አንድ ነገር ሲፈልግ ወላጆች አንተ ታስፈልገኛለህ እንዲሁም አንተ የተገባህ ነህ ብሎ መልዕክት በማስተላለፍ ህብረት ማድረግ አለባቸው። በተለይ የቤተክርስቲያን መሪዎች ለልጆቻቸው ፍቅር ማሳየት እጅግ አስፈላጊ ነው። በቤተክርስቲያን ያሉ ሰዎች ለአገልግሎት ብቻ ትኩረት ስለሚያደርጉ ብዙውን ጊዜ ልጆች የተዘነጉ ይሆናሉ።

አንድ ልጅ *«አባቴ ለሁሉም ሰው ጊዜውን ይሰጣል ነገር ግን ለእኔ ጊዜ የለውም»* የሚል ሰሜት ሲሰማው ለዚህ ልጅ እኔ ተፈላጊ ነኝ ግን የሚል ስሜት ይሰማዋል ከባድም ይሆንበታል።

**4. ያልተሟላ ፍላጎት**

የእግዚአብሔር እቅድ ሁሉም ወደዚህ ዓለም ተወልደው የመጡ ልጆች መሠረታዊ ፍላጎታቸው በወላጆቻቸው በኩል እንዲሟላ ነው። የሚያሳዝነው ግን አንዳንዶቻችን ለቤተሰባችን ካለው ከእግዚአብሔር የከበረ ዓላማ ጎድለን ርቀን መኖርን እንለማመዳለን፤ እንዲሁም አንዳንዶቻችን ከዚህ በጣም ተቃራኒ የሆነውን እንለማመዳለን።

ለምሳሌ፡

- አንዳንዶች ወላጆቻቸውን አጥተዋል፤
- አንዳንዶች በማይንከባከቧቸው ቤተሰብ ውስጥ አድገዋል፤
- አንዳንድ ወላጆች ለልጆች ፍላጎት እንዴት ምላሽ እንደሚሰጡ አያውቁም፤
- አንዳንድ ወላጆች ምንም የርህራሄ ልብ የላቸውም (ለራሳቸው ፍቅርን ተቀብለው አያውቁም)።

ብዙውን ጊዜ ማንኛውም ነገሮች በተሳሳሳ መንገድ ቢሄዱ ምንም ነገር አናደርግም፤ በራሳችን ባህሎች እና ከምንናውቀው ነገር በመነሳት፣ ያደግንበትን አስተዳዳግ ትክክል ነው ብለን እናስባለን። ነገር ግን እግዚአብሔር እንደዚህ ዓይነቱን ነገር የተለመደ እና ትክክል ነው ብሎ አይጠራውም።

**እያደግን ስንሄድ የተቀበልናቸው ጉዳቶች**

ክፉና ጨቋኝ ወላጆች ጉዳቶችን ሊያደርሱብን እንደሚችሉ መረዳት እጅግ ቀላል ነው። ነገር ግን እኛ ምናልባት በአንድ ሰው እድገት ላይ የሚመጣን ጉድለት ወይም እጥረት እንደ አይምዕሮ ችግር/ ጉዳት ሊያድግ ይችላል፤ ይህ ዓይነት ችግር ለረጅም ጊዜያት የሚቆይ ሊሆን

ይችላል። በማንኛውም ምክንያት ሊሆን ይችላል፣ ከወላጆቻችን ፍቅርን የማንቀበል ከሆነ በህይወታችን ላይ ጥልቅ ተጽዕኖ አለው። ይህ ለራስ ባለን አመለካከት ላይና በድፍረታችን ላይ አደገኛ የሆነ ተጽዕኖ የሚያመጣ ይሆናል። እኛ በህይወታችን ገጽታዎች ተጎጂ በምንሆንበት ጊዜ «አንተ ተወዳጅ አይደለህም /አንተን ማንም አይወድህም/፣ አንተ የምትረባ አይደለህም፣ አንተ አይሳካልህም፣ እና የመሳሰሉት» ብሎ ጠላት እስከ ውሸቱ ወደ ህይወታችን እንዲገባ በር የሚከፍት ይሆናል። ከዚያም ብዙውን ጊዜ ይህ በቀጣይነት በባህሪያችን ላይ ተጽዕኖ በመፍጠር ሌሎችን ሰዎች እንድንጎዳ ያደርገናል። በተጨማሪም እንደ አዋቂ ሰዎች ለቤተሰቦቻችን ፍቅር መስጠት የምንችል እንዳንሆን ስንኩል ያደርገናል።

### *ብዙውን ጊዜ ጉዳቶች ወደ ልጆቻችንና ወደ ቤተሰቦቻችን የሚሻገር ይሆናል።*

የእግዚአብሔርን ፈውስ ካልተቀበልን በስተቀር፤ አብዛኛውን ጊዜ እኛ ያጣነውን መሠረታዊ ፍላጎቶች እንዴት ለልጆቻችን ማሟላት እንደሚገባን አናውቅም። እኛም በቤተሰቦቻችን ውስጥ እንዲሁ ተመሳሳይ የሆነ ጉዳቶችን እናደርጋለን፤ ይህ ዓይነት የጉዳት አዙሪት /ክበብ/ ከትውልድ ወደ ትውልድ ተደጋግሞ የሚከሰት ችግር ይሆናል።

### *በሀገራችን ላይ የሚያመጣው ተጽዕኖ*

ቤተሰብን መውደድ እና መወደድን ፤ ማክበርንና እርስ በእርስ መከባበርን ምን ማለት እንደሆነ የምንማርበት ሥፍራ መሆን ይገባል። ቤተሰብ በትክክል ማንነቱ የማይገለጥ /የማይኖር/ ከሆነ በማህበረሰቦቻችን ላይ ተጽዕኖ የሚፈጥር ይሆናል። ልጆች ትክክለኛውን ፍቅር ማጣትን የሚለማመዱ ከሆነና በየቤታቸው ውስጥ በትክክል ጉዳትን የሚያስተናግዱ ከሆነ መሳሪያ አንስተው በአመጽ /በወንጀል/ ውስጥ ተሳታፊ ለመሆን በብዙ የተጋለጡ ይሆናሉ። በሀገራችን ውስጥ ግጭቶችና ኢፍትሐዊነት ካሉብን፤ ከልጅነታችን ጀምሮ ያሉት ያልተፈወሱ ጉዳቶቻችን ከአዕምሮ መቃወስ ችግር ለመፈወስና ይቅርታን ለማድረግ ከምንችልበት አቅም በከፍተኛ ሁኔታ ሊያስተጓጉለን የሚችል እንቅፋት ሊሆንብን ይችላል።

### *በእግዚአብሔር ላይ ባለን እምነት ተጽእኖ ይፈጥርብናል።*

ይህ ምናልባትም እጅግ በጣም አደገኛ ችግር ሊሆን ይችላል። በትክክል የማንረዳው ካልሆነ በስተቀር ከእግዚአብሔር ጋር ያለን የግንኙነት ልምምድ ከምድራዊ አባታችን ጋር የነበረን ዓይነት ይሆንብናል። አባታችን ጨካኝና አምባገነን ከሆነ፣ እግዚአብሔርም እንደዚሁ ጨካኝ አምባገነን እንደሆነ እናስባለን። ምድራዊ አባታችን ምንም ምቾት የማይሰጠን ከሆነ «የማጽናናችሁ እኔ ነኝ» (ኢሳ.51፡12) ብሎ እግዚአብሔር ሲናገረን ይህንን ለማመን እጅግ ከባድ ይሆንብናል። ለመጽናናት ወደ እርሱ መሄድ ፈጽሞ ምንም የማይጠቅመንና እንዲሁ ያለእርሱ መጽናናት የምንችል ወይም በሌላ ተገቢ ባለሆኑ መንገዶች መጽናናትን የምንፈልግ እንሆናለን። ፈጽሞ ምንም ዓይነት የፍቅር ስሜት ከሌለን በተጨማሪ በእውነት በሚወደን በእግዚአብሔር ላይ ጥርጣሬ ይኖረናል።

ብዙውን ጊዜ በልጅነታችን የእንደዚህ ዓይነት ልምምድ ችግሮች ካሉብን ማግኘት የምንፈልገውን ነገር ወደ ሰማዩ አባታችን ቀርበን ለማግኘት እንዳንችል የሚያግደን ይሆንብናል። ይህ ፈጽሞ ለመናገር የማንችለው ያልተማርነው ቋንቋ ዓይነት ነው። እምነታችን የተመሠረተበት አስተምርሆ /ዶክትሪን/ ምናልባት ትክክል ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን በጥልቀት በውስጣችን የእግዚአብሔርን አስደናቂ ፍቅር በትክክል ለማመንና ለመለማመድ ትግል ሊሆንብን ይችላል።

## 5. እግዚአብሔር ፍጹም የሆነ የአባትነትን ፍቅር ሊሰጠን ይፈልጋል /ይናፍቃል/።

**«… ለእናንተም አባት እሆናለሁ … » (2ኛቆሮ.6፡18) ።**

እግዚአብሔር በሰዋዊው ህይወታችን የጎደለንን /ያጣነውን/ ማንኛውም ነገር ሊያሟላልን ይፈልጋል። እግዚአብሔር «እኔ አባት ልሆናችሁ እፈልጋለሁ፣ ማንኛውንም የጎደለንን ነገር እኔ ላሟላላችሁ እወዳለሁ» ይላል። ማንም ሰው ወደ አንተ መጥቶ «እወድሃለሁ፣ እኮራብሃለሁ» ባይልህም እንኳን እኔ እነዚህን ነገሮች ልነግርህ እወዳለሁ። «ፍጹሙን የሰማዩን አባታችንን አስደናቂ ልብ ማወቅ ስብራታችንን ይፈውሰዋል። ከምናስበው በላይ እርሱ እጅግ የተለየ አባት ነው። (በአባሪ ላይ አንዳንድ የእርሱን አስደናቂ ባህርያት ዝርዝር ልናገኝ እንችላለን)።

***በተጨማሪም እርሱ የእናትነት ፍቅር ይሰጠናል።***

(መዝ. 27፡10፣ ኢሳ.49፡15-16፡ 66፡13)

ትክክለኛ ካልሆኑ ወላጅነቶች የተነሳ ማንም የማልረባ ነኝ የሚል ስሜት ሊሰማው አይገባም። ፍላጎቶቻችንን ሊያሟሉልን ያልቻሉትን ወላጆቻችንን በሁሉም መንገዶች ይቅር ልንላቸው ይገባልና፤ ከዚያም በውስጣችን ያለውን ክፍተት ሊሞላልን ወደሚችለው ብቸኛ ወደ ሆነው ወደ ሰማዩ አባታችን  መምጣት አለብን። እኛ የጎደለን ነገር ሁሉ ሊሞላልን የሚችለው እርሱ ነው።

***የእግዚአብሔር ፍቅር ዘላለማዊና በሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ አይደለም።***

እግዚአብሔር ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ የሚወደን አምላክ ነው ይህ እውነት ደግሞ  በጣም መልካም ነው፤ ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ግልጽ መልዕክት ነው፤ እግዚአብሔር ራሱ በዘላለማዊው ፍቅር እንደወደደን ይናገራል (ኤር. 31፡3)።  እርሱ ለእኛ ያለውን ፍቅር ለመለወጥ ምንም ማድረግም ሆነ አለማድረግ አንችልም። ይህ የጸጋ መልዕክት ነው። ስለ እግዚአብሔር የፍቅር  ባህርያት  ቸላ ብለን  እንደገናም የፍቅር አምላክ መሆኑን ዘንግተን በቅድስናው ላይ ብቻ  በማተኮር፣ በኃጢአጥያን  ላይ ስላለው ቁጣ ብቻ አተኩረን እንደገናም ፣እርሱ ስለሚያደርጋቸው  ፍርድ ላይ ብቻ በማተኮር ስለ እግዚአብሔር ያለንን አመለካከት በ አንድ ጎን ብቻ አተኩረን ትክክለኛ ያልሆነ የተዛባ ትምህርት ተቀብለን (ተምረን) ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ ያለውን ቁጣውን ሁሉ በመስቀል ላይ በኢየሱስ ላይ አፍስሶታል።



በደመናማ፣ ጭልም ባለ ቀን፣ አየሩ ብዙ ጊዜ ክብድ የሚል፣ ዝናባማና ቀኑ ከደመናው በታች ደስ የማያሰኝ ይሆናል። ይህ ሁልጊዜ ከቀን ወደ ቀን እንዲሁ የሚቀጥል ከሆነ፣ አንድ ሰው ጸሐይ የጠፉች ቀን ቀኑን ሊጀምር ሊከብደው ይችላል፣ ነገር ግን ወደ አይሮፕላን ውስጥ ገብተህና ከደመናት በላይ ስትበር፣ ጸሐይ ማግኘት ብትፈልግ እርሷ አሁንም እዚያው ናት። ደመናት የጸሐይን መውጣትና ማብራት ማስቆም አትችልም፣ ነገር ግን በምድር ላይ ያሉ ሰዎች ብርሃኗንና ሙቀቷን እንዳያገኙ ሊከለክሉ አይችሉም። ደመናት በአንድ ሰው ህይወት ላይ እንደ ኃጢአትና አለማመን ናቸው። ጸሐይ እንደ እግዚአብሔር ፍቅር ናት ማብራቷን ማቆም ፈጽሞ አይቻልም፣ ነገር ግን በህይወታችን ያለው ያልተናዘዝነው ኃጢአትና አለማመን ልክ እንደ ደመና ወደ እኛ እንዳይደርስ ይጋርዳሉ።

### ***የእግዚአብሔርን ፍቅር ለሌሎች ማሳየት***

የእግዚአብሔር ፍቅር ለእኛ ከሚገለጥባቸው መንገዶች መካከል አንዱ እርስ በርሳችን የእርሱን ፍቅር በማሳየት ነው። እንደ ቤተ ክርስቲያን ወላጅ አልባ ለሆኑ ልጆች አባት ወይም እናት ለመሆን ወይም በማንኛውም ምክንያት የወላጅ ፍቅር ላላገኙ ሰዎች የሚሆን ግሩም አጋጣሚ አለን። ነገር ግን መጀመሪያ የራሳችን ልብ በእግዚአብሔር ፍቅር መሞላት አለበት አለበለዚያ የምንሰጠው ትንሽ ወይም ምንም አይኖረንም።

### **ከራስ ጋር ማዛመድ**

ፈውስን እንዴት እናገኛለን፡

- በቤተሰብህ ውስጥ ስለነበረህ ልምድ ጊዜ ወስደህ አስብ።
- ወላጆችህ ያልሰጡህ ከእነርሱ ግን የምትሻው (መቀበል) የምትፈልገው ነገር ምንድነው
- ስለ እግዚአብሔር ማንነት ያለህ እይታ ላይ እና እንዲሁም ከሌሎች ሰዎች ባለህ ግንኙነት ምን ያህል በልብህ ላይ ተጽዕኖ አሳድሯል ?
- 2ኛ ቆሮ 6፡18፣ መዝ. 103፡1-6፣13 አሰላስል።
- እግዚአብሔር አባትህ እንዲሆን ጋብዘው ከእርሱም ፍቅርን፣ ሰላምንና ዋጋን ተቀበል።

- በህይወትህ ውስጥ የጎዱህን ወላጆቻህን ይቅር በላቸው።
- በጎደልህ ነገር ምክንያት ለሌሎች መጎዳት ምክንያት የሆንክበትን ጉዳይ ካለ ንስሃ ግባ።
- የእግዚአብሔርን ፍቅር እንደ አባትና እንደ እናት የምታሳየው አንድ ሰው ካለ ያ ሰው ማን እንደሆነ አስብ።

**ቁልፍ ሀሳቦች**

- በችግር ውስጥ ያለች ሀገር ተሀድሶ የምትጀምረው ከቤተሰብ ነው።
- እኛ የተፈጠርነው ከወላጃዊ ፍቅር ፍላጎት ጋር ነው፣ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር በሚመሰል፣ ነገር ግን በወደቀ አለም ውስጥ ስለምንኖር፣ ወላጆቻችን ብዙውን ጊዜ የምንፈልገውን ፍቅር ሊሰጡን አይችሉም።
- ይህ ራሳችንን አባታችንን ከሆነው ከእግዚአብሔር ጋር እንድንርቅ ሊያደርገን ይችላል፡፤ ነገር ግን እግዚአብሔር የልብን ፍላጎት ሁሉ የሚያሟላ ፍጹም አባት ነው።

# ክፍል ሁለት

# ግድግዳዎችን መገንባት

በዮሐ.10፡10 ክፍል መሠረት ጊዜ ወስደን የተዘረፍነው ነገር ምን እንደሆነ ስንመለከት ምን ያህል የተጎዳን እንደሆንን ለማወቅ እንችላለን፤ እንዲሁም ከጉድለታችን በስተጀርባ ያለውንና በዓለም ሁሉ የሚሠራውን ጠላት ማን እንደሆነ ማወቅ እንችላለን። በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ስብራት /ጉዳት/ በጣም ከባድነት የሚናገረውን ማወቅ ያስፈልገናል። ይህ እግዚአብሔር በጥልቀት የሚመለከተው ጉዳይ ነው። ኢየሱስ ወደ ምድር የመጣው ስለኃጢአት

ብቻ መፍትሔ ለማምጣት ነው ብለው ያምናሉ፤ ነገር ግን እርሱ ግን በተጨማሪ ከስብራታችን ሊፈውሰን ነው የመጣው። መስቀሉ ለሁሉም የሚሆን መፍትሔ አለው።

ወደ ፈውስ ከመምጣታችን በፊት አስቀድመን ህመማችን መጋፈጥና መግለጥ አለብን፣ ይህንን ለማድረግ ተግዳሮታችንን ማሸነፍ ይኖርብናል። አንዳችን የሌላውን የእርስ በእርስ ህመም የመስማትና ከብሔራችን ውጪ ላሉ ሰዎች መጸለይ ለፈውስ ትልቅ እገዛ ያደርጋል። ነገር ግን ከሁሉም በጣም ውጤታማው ነገር ህመማችንን ወደሚሸከምልን ወደ ኢየሱስ ጉዳታችንን ማስተላላፍና /ወደ ኢየሱስ ማምጣትና/ እርሱ ከህይወት ጉዳቶታችን ሊታደገን እንደሚችል በእርሱ መታመን ነው




# ትምህርት ሰባት

# ሌባው

## ሰዎች ያጡትን /ጉድለታቸው ምን እንደሆነ እንዲረዱ፣ እውቅና እንዲሰጡና የተሀድሶ ተስፋ እንዲያገኙ መርዳት

በዮሐ.10፡10 የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ በብሔሮች መካከል ስላለው ግጭት ያመጣውን ስብራት ለመፈወስ ይሄ ክፍል ለእኛ የሚሰጠው ትርጉም ብዙ ነው። «… *ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም፤ እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ።*» ሌባው እንደ ግለሰብና እንደ ብሔር ቡድን ዘርፎናል /ሰርቆናል/። በዚህ ምዕራፍ የምናተኩርበት እንዱ በብሔር ቡድን በጋራ ያጣናቸው ጉድለቶች ላይ ነው። በብሔር ግጭት ውስጥ የተሳተፉ ሰዎች ብዙውን ጊዜ የእነርሱ ወገን ብዙ ጉዳት እንደደረሰበትና የእነርሱ ወገን ብቻ በጣም እንደ ተጎዳ አድርገው ያምናሉ። «ከእርስ በርሳችን ታሪኮች የተሻለ ግንዛቤ እንድናገኝ የእርስ በርሳችንን ታሪኮች መስማት፤ እንዲሁም ለእርስ በርሳችን ይበልጥ እንድንራራ ለእኛ እጅግ አስፈላጊያችን ነው። ይህ ምዕራፍ የሚያሳየን በአንዳንድ መንገዶች የሆኑ ሁሉም ኪሳራዎች የመጡት እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያቀደውን ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ለመስረቅ ከሚፈልገው ከሌባው የተነሳ የመጣ መሆኑን ነው።

### 1. ሌባው ሰብአዊነትን ይሰርቃል።

በዙሪያችን ያለውን ኃጢአተኛና የተጎዳውን ዓለም ስንመለከት ሰይጣን፣ በእርግጠኝነት ከጀርባችን እንቅስቃሴ /በሥራ/ ላይ እንዳለ እንመለከታለን። ሰይጣን በትዕቢትና በዓመጻ ያጣውን የራሱን እድል አሁን እግዚአብሔር ያዘጋጀልንን የእኛን የሆነውን ሁሉ ነገር ለመስረቅና ለራሱ ለመድረግ እየፈለገ ይገኛል። ሁሉም የሰው ዘር ሁሉ የተዘረፈ ነው፣ ሁሉም የሰው ወገን የተዘረፈ ነው፣ እንዲሁም ሁሉም ብሔረሰብ፣ ሁሉም ሀገር፣ ሁሉም አህጉር የተዘረፈ ነው። በግል ህይወታችን ላይ፣ በህዝብ ወገኖች ደረጃና በሀገር ደረጃ ያመጣው ችግር ብዙ ነው። አሁንም ብዙዎቻችን፣ በክህደት ውስጥ አለን፣ ሆኖም ብዙዎቻችን ምንም ችግር እንደሌለ በማስመሰል ራሳችንን ለማሳመን ጥረት እያደረግን እንገኛለን። እኛም የሌሎችን ኪሳራ አናውቅም። ለከሰርናቸው ነገሮች እውቅና መስጠትና ለእምነታችን ምክንያት እንዲሆን ማድረግ

ለመፈወሳችን እጅግ ጠቃሚና አስፈላጊ እርምጃ ነው። በተጨማሪም የሌሎችን ኪሳራ መረዳት መጀመራችንም አስፈላጊ ነው።

በችግር በተሞላ ባህል ውስጥ ሌላውን ከሚያስቆጣ ነገር ባሻገር ያለውን መመልከት መቻልና ከሁሉም ነገሮች በስተጀርባ አንድ አካል እንዳለ ማየት መልካም ነው፣ ይህም አካል የሰውን ዘር በሙሉ ለማጥፋት የሚፈልግና የእግዚአብሔር ዓላማ እንዳይፈጸም የሚከለክል ነው። በእርግጥ የወንድም ወይም የእህትን ኃላፊነት ከራስ ላይ አንስቶ በሰይጣን ላይ በማድረግ ራስን ነጻ ለማድረግ መሞከር አይገባም። አዳምና ሄዋን ጭምር እንዲህ እንዲያደርጉ እግዚአብሔር አልፈቀደም።

## 2. ማጣቶቻችንን መቀበል እና መጋፈጥ

አንድ የህዝብ ወገን የማጣትን /ኪሳራን/ ህይወት ሊለማመድ የሚችልበትን የተለያዩ ተግባራዊ መንገዶች ምን እንደሆኑ የተለያዩ ግንዛቤዎች ለመስጠት እንፈልጋለን።

### *2.1. በተለያዩ ደረጃዎች ያሉ ማጣቶች ላይ ማተኮር*

ከአህጉር ደረጃ መጀመር እንችላለን የተለያዩ የኪሳራ ልምምድ ደረጃዎችን ለይተን ለማውጣት እንሞክራለን፡ ከዚያም ወደ ሀገር፡ ወደ ብሔር /ዘር/ና ወደ ቤተክርስቲያን ደረጃ እንመጣለን። በቤተሰብ ደረጃ ያለው ላይ ትኩረት እኛደርጋለን።

### *2.2. ማጣቶቻችንን እና ያመጡትን መዘዞች በሰንጠረዥ ዘርዝሮ ማስቀመጥ*

2.2.1. በግጭቶች ጊዜ የሚሆን የቁሳቁስ ኪሳራ፣ እነዚህን ለይቶ ለማወቅ በጣም ቀላል ነው።

2.2.2. ውስጣዊ ማጣት፣ ለምሳሌ ፍቅር፣ እምነት/መተማመን/፣ ሰላምና የመሳሰሉት ናቸው።

2.2.3. ያመጡት ኪሳራ /መመዞች/፤ በተለይም የውስጣዊ ህይወት ኪሳራዎች መዘዞች

**2.3.** ***የወገኖቻችንን ማጣቶች መቀበልና መጋፈጥ***፡- እያንዳንዱ የብሔር ወገን የተዘረፈባቸው /ኪሳራዎቻቸውን/ ማወቅ በጣም ውጤታማ ሊሆን ይችላልና

ዝርዝራቸው። በተጨማሪም በታሪካዊ ክፍላቸው ዝርዝር ከፋፍሎ ማስቀመጥ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ፡- በቅኝ ግዛት ዘመን፣ በአፓርታይድ ዘመን በፊት፣ በዚያን ጊዜ፣ ከዚያም በኋላ፤ በዋና የዘር /ብሔር /ግጭቶች ጊዜና በማሳሰሉት ጊዜያት ያለውን መዘርዘር። ከዝርዝሩ በስተ ግርጌ የብሄር ወገኑ ስለእግዚአብሔር፣ ስለ ራሳቸው ያላቸውን የተሳሳተ እምነት ለይቶ ማወቅ መልካም ነው። (ለምሳሌ፡- በደቡብ አፍሪካ ሌላው ብሔር አንዱን የብሔር ወገን የተረገመ ነው ብሎ ሲረግም፣ እግዚአብሔር ኢፍትሃዊ ነው፣ ለነጮች ያደላል የሚል የተሳሳተ እምነት አላቸው)። በመጨረሻም በሁሉም ወገኖች በጋራ ያጡትን ኪሳራዎች ምንነት በመዘርዘር ማስቀመጥ እጅግ ጠቃሚ ነገር ነው (ለምሳሌ፡ እውነት፣ ዋስትና፣ በመካከላቸው ያለ ምቹ የሆነ ግንኙነትና የመሳሰሉት)። ይህ በእግዚአብሔር እይታ ማንም አሸናፊ እንደሌለ የሚያሳይ ነው።

## 3. በግጭት ወቅት የሚከሰቱ የተለመዱ የጋራ ማጣቶች እና መዘዞቻቸው

### *እውነት*

ሰይጣን ዋናው የሚዘርፈን ነገር ቢኖር እውነትን ነው፣ ለዚህ ነው ኢየሱስ ሲጠራው የውሸት አባት ያለው (ዮሐ. 8፡44) ። እኛ አሁን በብሔር ግጭት ወቅት የሚሆነውን አስፈሪና ፍረጃዎችን ለይተን እናውቃለን። በመጨረሻም ብዙ ውሸቶች በእያንዳንዱ የህይወታችን ክፍሎች ላይ የሚያመጣውን ተጽእኖ እንዳለ እናምናለን። ሰይጣን የእግዚአብሔርን ቃል ጭምር ከሰው ልብ ላይ ይነጥቃል (ማቴ. 13፡19) ። እርሱ ሰዎች በአዕምሮቸው በእሥራትና በተጽዕኖ ሥር እንዲወድቁ ለማድረግ ይፈልጋል፣ ነገር ግን ከኢየሱስ የተነሳ አይሳካላትም (ዮሐ. 14፡30) ።

### *እምነት/መታመን*

መተማመን በሌለበት ትርጉም ያለው ግንኙነት አይኖርም። በዚህም የምንጠራጠር፣ የምንሰጋ ወይም ሁልጊዜ ራሳችንን ከሰዎች የምንከላከል እንሆናለን። እንደ እግዚአብሔር ልጆች

በመካከላችን ያለው ህብረት ችግር ውስጥ ይገባል። እንዲሁም ግንኙነቶቻችን የበለጠ ይሆናል። ምንም እንኳን ግልጽ የሆኑ ሰዎች በዙሪያችን ያሉ ቢሆንም እጅግ በፍርሃት ውስጥ በምንሆንበት ጊዜ በልባችን ውስጥ ያለውን ለሌሎች ማካፍል የምንፈራ ብቸኞችና የተገለልን እንሆናለን።

***ፍቅር***

ፍቅር በሌለበት ሰዎች ራስ ወዳድ ይሆናሉ። እኛ ራሳችን በገዛ ራሳችን ፍላጎት የተዋጥንና ለሌሎች ፍላጎት ምንም ግድ የማይለን እንሆናልን። ስለሌሎች ያለን ስሜቶች አሉታዊ ሆነው ወደ ጥላቻ የሚያድጉ ይሆናሉ። ይህ ደግሞ ለሁሉም ዓይነት ኃጢአቶችና ክፋቶች ሁሉ በር የሚከፍት ይሆናል።

***ሰላምና ዋስትና /ደህንነት/***

የውስጣዊና የውጪያዊ ህይወታችን ሰላም የደፈረሰ ከሆነ መረጋጋት የሌለን፣ የምንፈራ፡ የምንጨነቅና ዘና ብሎ ለመኖር፣ የደህንነት ስሜት የማይሰማን ወይም በሰላም ለመተኛት አለመቻል ውስጥ እንገባለን።

**ተስፋ**

ተስፋ ማጣት በሕይወታችን ውስጥ ስላለው የእግዚአብሔር እቅድ እና አላማ ያለንን እይታ ይወስድብናል። ቀጣይ ሂወታችን ተስፋ የሌለው እንዲመስለን ያደርጋል።ለምንም ነገር ምንም ፍላጎት የሌለን, ምንም ተነሳሽነት የሌለን, ለለውጥ ለመስራት ምንም ጉልበት የሌለን, ለመቀጠል ፍላጎት የሌለን.፣ በውስጣችን እንደ ወጣ ብርሃን አይነት ያደርጋል።

**ክብር**

እግዚአብሔር ለሰዎች ካዘጋጀላቸው እውነተኛ ሰብዓዊ ማንነት ውጪ ሆነው ሲጨቆኑና ሲጨቁኑ የራሳቸውን ክብር የሚያጡ ይሆናሉ። ሰይጣን ሁልጊዜ የሰውን ልጆች ክብር ማሳጣት

/ማዋረድ/ ይፈልጋል። እርሱ እግዚአብሔር ወዳዘጋጀልን መዳረሻ እንዳደርስ ይጠላል፤ በዚህ ፈንታ እርሱ አሁን ወዳለበት የውድቀት ደረጃ እንድወርድ ሊያደርግ ወደታች ይስበናል።

### ፅድቅነት

በማህበራሰቡ ውስጥ እግዚአብሔር ያስቀመጠውን የሞራል መስፈርቶች ውድቀት ውስጥ ስንገባ ለሁሉም ዓይነት የክፍት አሠራሮች በር የምንከፍት እንሆናልን። ህሊናችን «በጋለ ካውያ እንደተጠበሰ» የደነዘዝን ይሆናል ። (1ኛጢሞ. 4፡2) መልካምና ክፉውን ለይተን ለማወቅ የማንችል እንሆናለን። ሌሎች ደግሞ ክፋትን የመቋቋም ብርታት ያጣሉ። እኛ በፍርሃት፣ በጥላቻና በትዕቢት ውስጥ እንገባለን።

### ፍትሃዊነት

ኢፍትሃዊነት በልባችን ውስጥ ቁጣና የንዴት ስሜት ይፈጠራል። እግዚአብሔር ማንኛውንም ዓይነት ኢፍትሃዊነትን ይጠላል። እጅግ የበዛ ኢፍትሃዊነት በማንኛውም ሀገር ላይ፣ በግለሰብ ላይ የሚገለጥ አደገኛ ኃጢአትና ሰብዓዊነትን የሚሸረሽር ነው። ብዙውን ጊዜ ወደ ከፍታ የወጣ ንዴት ለጥቃት የሚያጋልጥ ሆኖ ይፈነዳል።

### እምነት

እምነት እኛ ካሉን እጅግ የከበሩ ነገሮች መካከል አንዱ ነው። እምነት ከወርቅ ይልቅ የከበረ ነው (1ኛጴጥ.1፡7)። ለክርስቲያኖች እምነት ማለት ለሁሉም ነገር ቁልፍ ነው፣ ለድነታችን፣ ለእግዚአብሔር ፍቅር፣ ለወደፊቱ ተስፋ ቁልፍ ነገር ነው። እምነት ሰይጣን ከእያንዳንዳችን ሊያስወግደው የሚፈልገው ነገር ነው። በእግዚአብሔር ፍቅር ውስጥ እምነታችን ከጠፋ ሁሉንም ነገራችን ይጠፋብናል። ከላይ ያሉት ሁሉም በልባችን ውስጥ ያሉት ጉዳዮች ማለትም እንደ ግለሰብም ሆነ እንደ ሀገር የዚህ ውጤት ናቸው። ነገር ግን እምነት የፈውሶች ሁሉ መሠረት ስለሆነ በእግዚአብሔር ፍቅር ውስጥ የእምነት መጥፋት ወደ ከፋ መዘዝ ይወስዳል። ሰይጣን ተስፋችንና በሚወደን መልካም አምላክ እግዚአብሔር ላይ ያለንን እምነት የሚሰርቅ ከሆነ እኛ ከፈውስና ከተሀድሶ ምንጭ የተቆረጥን እንሆናለን።

## 4. የተሀድሶ ተስፋ

ስለዮሐ.10፡10 ሁለተኛው ክፍል እግዚአብሔር ልናመሰግን እንችላለን፤ « *… እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ*»። ሌባው የሚናገረው የመጨረሻ የስንብት ቃል የለውም! ኢየሱስ « *… እኔ ሌባው ከእናተ የሰረቀባችሁን ላድስላችሁ እችላለሁ፣ እንዲሁም ከመጀመሪያው ከነበራችሁ ይልቅ የሚበልጥ ነገር እሰጣችኋለሁ! እኔ ህይወትን እስከ ሙላቱ ልሰጣችሁ እችላለሁ*።

ሁሉንም ነገር ወደነበረበት መመለስ እንደማንችል ግልጽ ማድረግ አለብን። የሞቱት የምንወዳቸው ወገኖቻችን በዚህ ሕይወት ወደ እኛ ሊመለሱ አይችሉም፣ ነገር ግን እግዚአብሔር አሁንም ትርጉም ያለው፣ የፍቅር ግንኙነትን ሊመልስልን ይችላል። በተጨማሪም የቁሳዊ ነገሮቻችን ተመልሰው ታድሰው ላናገኛቸው እንችላለን ። ነገር ግን ሁላችንም የተዘረፍንበትን (እውነት፣ ዝምድና እና የመሳሰሉት ናቸው) እነዚህን ሁሉ ነገሮች እግዚአብሔር ወደ ሁላችን ሊመልስ የሚናፍቃቸው ነገሮች መሆናቸውን እናያለን። እነዚህ የልባችን በትክክል የሚሆኑ ነገሮች ናቸው እናም በጣም አስፈላጊ ናቸው፡፡

ማቴ. 12፡29 እንደሚናገረው «ኃይለኛውን ሰው» ማሰርና ወደ ቤቱ በመግባት በቤቱ ውስጥ ያለውን ዕቃዎች ሁሉ መበዝበዝ /መቀማት/ ነው። በመስቀሉ ላይ ኢየሱስ «ኃይለኛውን ሰው» አሰረው። አሁን ቤተክርስቲያኑ ሌባው ከእኛ የዘረፈውን ነገር እንዲያድስልን ይሰራል።

በማቴ.16፡18 እንደሚለው ኢየሱስ ቤተክርስቲያኑን እንደሚሠራና የገሀነም ደጆች ሊቋቋሙት እንደማይችል ይናገራል። ብዙዎች ይህን የገሀነም ደጆች ቤተክርስቲያንን ሲያጠቃ አይሳካለትም ብለው ያምናሉ። ነገር ግን የገሃነም ደጅ አንድን ሰዉ መቼ ያጠቃል? ቤተክርስቲያን የገሃነም ደጆችን ስትቃወም በኃይለኛው ቤት ውስጥ ያሉትን ዕቃዎች እንደገና በዝብዛ የራስዋ ታደርጋለች፣ የገሃነም ደጆችም ደግሞ እንደተዘጉ ይቀራሉ ማለት አይደለም። ይህ እንደ እግዚአብሔር ልጆች የእኛ ተግዳሮታችን ነው። ቁጭ ብለን ስላጣናቸው ነገሮች ለዘላለም ማዘን እንችላለን። ወይም በመስቀሉ የድል ብርሃን መነሳት እንችላለን፣ የተሰረቁብንን ነገሮች እንደገና የራሳችን ለማድረግ ቁርጠኛ መሆን እጅግ ጠቃሚ ነገር ነው።

በ1ኛ ሳሙኤል 30 ላይ፣ ዳዊትና ሰዎቹ ከጦርነት ወደ አገራቸው ሲመለሱ፣ በእሳት መውደሙን እናያለን። ሚስቶቻቸውንና ልጆቻቸውን ተማርከው ንብረታቸውንም ተዘርፈዋል። ማልቀስ እስኪያቅታቸው ድረስ ጮክ ብለው አለቀሱ። ከዚያም ዳዊትን በመፍራት ሰዎቹ ወደ እሱ ዘወር ብለው ሊወግሩት ፈለጉ! ከዚያም 'ዳዊት ግን በእግዚአብሔር ኃይልን አገኘ' የሚሉትን አስደናቂ ቃላት እናነባለን። ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፣ እናም ሄደው ከእነርሱ የተወሰዱትን ሁሉ እንዲያነሱ ጥያቄን አቀረበ። በዚህ ምዕራፉ ውስጥ ቀጥሎ ሁሉም ነገር እንደተመለሰ እናያለን. ከዚህ ታሪክ ብዙ መማር እንችላለን። ሁሌም ተቀምጠን በደረሰብን እና በስለቀሰን ጉዳይ ማዘን እንችላለን፣ መሪዎቻችንን መውቀስ እንችላለን፣ ወይም ተነስተን በመስቀሉ ድል ሌባው የሰረቃቸውን ጠቃሚ ነገሮች ለማስለቀቅ ቁርጥ ውሳኔ ማድረግ እንችላለን።

## ከራስ ጋር ማዛመድ

- በሀገርህ ታሪክ ውስጥ ከብሔር /ዘርህ/ ወገንህ እየተዘረፈብህ የነበረው ምንድን ነው?
- ሌባው በግል ህይወትህ የሰረቀብህ ነገር ምንድን ነው?
- ያጣኸው ነገር በእግዚአብሔር ፣በራስህና በሌሎች ላይ ባለህ እምነት ላይ ያመጣብህ ችግር ምንድን ነው?
- ኢየሱስ ለአንተና ለህዝብህ መልሶ ሊያድሳቸው ስለሚፈልጋቸው ነገሮች ምን ታስባለህ?

## ቁልፍ ነገሮች

- ትልቁ ነገር ሰይጣን የሰረቀብን ነገር ስለእግዚአብሔር፣ ስለሌሎችና ስለራስህ ያለህን አመለካከት ነው፡፡
- በተጨማሪም ሰይጣን እርስ በርሳችን ያለንን ህብረት እና ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን የጠበቀ ህብረት ዘርፎብናል።
- ኢየሱስ የመጣው ሌባው የወሰደብንን ነገር ሊመልስልንና አትረፍርፎ ሊያድስልን ነው።

# ትምህርት ስምንት

# የቆሰለ ልብ

## ቁስለትን ፤ መንሴውን እና መዘዞችን መረዳት

ከዚህ በፊት በነበረው ምዕራፍ ሌባው ምን ያህል እጅግ የከፋ ሥራ እየሰራ እንዳለ ተመልክተናል። በዚህም ምክንያት እኛ ሁላችንም እግዚአብሔር ካዘጋጀልን የክብር ኑሮ ጎድለናል ። ኃጢአተኛነት የሰው ልጆች ብቸኛው ችግራችን እንዳለሆነ፣ ሃጢአት ባለበት በየትኛውም ሥፍራ ሰዎች ልባቸው እንደሚሰብር ፤እኛ በገዛ ኃጢአታችን የተጎዳን ሰዎች መሆናችን እና ሃጢአትን ስናደርግ በተጨማሪም በህይወታችን ውስጥ የምናጣው ነገር አለ። በዚህም ምክንያት እኛ እጅግ የተጎዳን ሰዎች እንሆናለን፣ እንዲሁም ብዙውን ጊዜ በስብራታችን እኛም ሌሎችንም እንጎዳለን።

1. **ስብራትን/ቁስልን/ መረዳት**

ስለስብራታችን በትክክል ለማወቅ አስቀድመን እግዚአብሔር ለዓለም ሁሉ ያለውን እውነተኛውን መልካም ዕቅድ ማስተዋል አለብን።

## የእግዚአብሔር የመጀመሪያው ( መልካም የሆነው ሀሳብ) እቅድ

1. ***ስለ አደግንበት ቤተሰብ***

ስለሰዉ ልጆች አጠቃላይ ዕድገት የእግዚአብሔር የልብ ዕቅድ ምን ነበር፡

- ወላጅነት በትክክል የእግዚአብሔርን ባህርይ የሚገልጡ ተወካዮች እንዲሆኑ።
- ልጆች በሁሉም መንገድ ተወዳጆች፣ እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸውና ሁሉም ነገር ሊዘጋጅላቸው የሚገባቸው እንደሆነ ማወቅ የሚገባቸው። ስለዚህም በስሜታቸው ሙሉ በሙሉ ደህንነት ሊሰማቸው እንደሚገባ፡
    - ስለማንነታቸው (እኔ ማን ነኝ)
    - ፍጻሜአቸው ምን እንደሆነ (ወደየት እንደሚሄዱ/የት እንደሚደርሱ)
    - አለኝታነት (ግንኙነታቸው)

2. **ስለምንኖርበት ማህበረሰብ**

- ግንኙነት የሚገለጥባቸው መንገዶች በፍቅር፣ ራስወዳድ ባለመሆን፣ የጋራ /የወል/ መከባበርና አንዱ ለአንዱ ያለው አድናቆት ናቸው። ስግብግብ አለመሆን፣ ማንም ሌላውን ሰው ማጥቃት /ማዋረድ/ የለበትም።
- ጠንካራ የሆነ የማህበረሰቡ ውስጥ ያለው መስተጋብር አንዱ ለሌላው እንክብካቤ /ጥንቃቄ/ ሲያደርግና አንዱ የሌላውን ጥቅም ሲጠብቅ ነው።
- መንግስት ለሰዎች በእውነተኛነት ጥበቃ ሲያደርግና በጽድቅ ሊመራቸው የሚያስችል ፍላጎት ለማሳየት መነሳሳት ሲኖረው፤ በስልጣን ላይ ካለው አካል ጋር ትግል ሲቆም፣ የራስ የግል ጥቅም /ፍላጎት/ ብቻ ማራመድ ሲያቆም፣ ኢፍትሃዊነትን ሲያቆም፣ ሙስና ሲቀር፤

3. **ፍጥረት በአጠቃላይ**

- ሁሉም ነገር ከእግዚአብሔር አገዛዝ/ጌትነት/ ሥር በመስማማት በአንድነት ተያይዞ ሲሠራ፣
- ምንም ዓይነት ተፈጥሮአዊ አደጋዎች ሲጠፉ፣ በሽታ ሲጠፋ፤

**ነገር ግን ሰው ሲያምጽ የእግዚአብሔር መልካም የነበረው ዕቅድ ሁሉ ተበላሸ /ጠፋ/።**

ኃጢአት ቤተሰብን፣ ማህበረሰብንና ፍጥረትን በሞላው በከፍተኛ ደረጃ ይረብሻል፤ ከዚህም የተነሳ የሰው ልጆች በሶስት አቅጣጫዎች በሞላው የልብ ስብራትን በህይወታቸው ውስጥ መከሰት ይጀምራል። በተጨማሪም ግለሰቦች ብቻ ሳይሆኑ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ሊጎዱ ይችላሉ። እንዲያውም ፍጥረት በችግር ውስጥ ይወድቃል (ሆሴዕ 4፡1-3)። እኛ በኃጢአተኛው ዓለም ውስጥ ከመኖራችን የተነሳ እኛ ሁላችንም እንደየደረጃችን በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ጉዳት ይደርስብናል። የተለዩ ዓይነት ጉዳቶች አሉ፤ እነርሱም መተው /መገለል/፣ የመተማመን መጥፋት፣ ተስፋ መቁረጥና የተለያዩ ዓይነት ማጣቶች /ጉድለቶች/ ናቸው።

**የዘር መድሎ /በብሔር መገለል/**

በዚህ ምዕራፍ የምናተኩረው በዘር /ብሔር/ ግጭቶች ምክንያት በሚፈጠረው ጉዳት /የልብ ስብራት/ ላይ ነው። ማንኛውም የሰው ልጅ የሚቀበለው እጅግ ትልቁ ስብራት /ጉዳት/

መገለል ነው። ማንኛውም የዘር /የብሔር ግጭት በአንድም ሆነ በሌላ መገለል ይባላል። መገለል እጅግ የሚያሳምም ነው ምክንያቱም የሚያስተላልፈው መልዕክት «እኛ ዋጋ የሌለን፣ የማንወደድና በዚህ ቦታ ሥፍራ የሌለን ነን የሚል ነው…

ብሔር ማንነትን በመቅረጽ ውስጥ እጅግ ወሳኝ ሚና የሚጫወት ነው፣ ስለዚህ ማንኛውም ብሔራችን ላይ አተኩሮ የሚመጣ ጥቃት በእኛ ዋና ማንነት ላይ ያነጣጠረ ጥቃት ነው። አንድ ሰው በባህርይው ምክንያት የሚገፋ ወይም የሚገለል ከሆነ፣ እርሱን ለመለወጥ ይሞክራል፣ ነገር ግን በብሔሩ ምክንያት የሚሰደድ ከሆነ ግን ምን ማድረግ ይችላል? ይህ ደግሞ ወደ ተስፋ መቁረጥ /ወደ መጨቆን/ ስሜት ሊያመራው ይችላል። ከብሔር ማንነታችን የተነሳ የሚመጣ መገለል በመንፈሳችን ላይ ጥልቅ የሆነ ስብራት ያመጣል። ማንኛውም ኢፍትሃዊነት፣ ማንኛውም መዋረድ /ዝቅ ማድረግ/ የመገለል አንዱ ገጽታ ነው።

## 2. የልብ ስብራት /ጉዳት/ በመጽሐፍ ቅዱስ ምልከታ።

ምሳሌ 18፡14 ላይ *«… የሰው ነፍስ ሕመሙን ይታገሣል፤ የተቀጠቀጠን መንፈስ ግን ማን ያጠንክረዋል? »* ይላል የተሰበረ ልብ የሕይወትን ችግር ተቋቁሞ ለማለፍ ባለው ችሎታ ላይ የሚያመጣው አደገኛ መዘዝ አለ። «… *ደስ ያላት ልብ መልካም መድኃኒት ናት፤ ያዘነች ነፍስ ግን አጥንትን ታደርቃለች።»* (ምሳ.17፡22) ። የደረቀ አጥንት /መገጣጠሚያ/ ግትር ያለና የማይተጣጠፍ ስለሆነ እጅግ የሚያም ነው፤ በቀላሉም ይሰበራል።የቆሰለ ልብ ካለን ሕይወታችን እንዴት ሊሆን እንደሚችል የሚያሳይ ሥዕላዊ (ምሳሌያዊ) ገለፃ ነው። እግዚአብሔር ይህን የሚረዳ በተለይ ልባቸው ለቆሰለ ሰዎች ቅርብ መሆኑን በቃሉ አሳውቆናል። መንፈሳቸው የተሰበረውንም *ያድናቸዋል።»* (መዝሙረ ዳዊት 34፡18) ።

የኢየሱስ አገልግሎትም ሲገልጥም « … *የተቀጠቀጠን ሸምበቆ አይሰብርም፥ የሚጤስንም ክር አያጠፋም፤ በእውነት ፍርድን ያወጣል።»* (ኢሳ. 42፡3)። እነዚህ ሁሉ ምሳሌዎች የተሰበረ ልብ ስብራት ምን እንደሚመስል ግልጽ ስዕል የሚሰጠን ነው። የተቀጠቀጠ ሸንበቆ ቀጥ ብሎ ለመቆም ምንም አይችልም ነገር ግን ይታጠፋል። ይህ እኛ በውስጣችን ልንሆን የምንችለው ነው - ከጭንቅላታችን ቀና ብለን ለመቆም ምንም አንችልም ነገር ግን ይልቁንም ወደታች ማዘንበልና ማጎንበስ ነው። በተጨማሪም የሰውን መንፈስ በውስጣችን እንደሚነድ ፍም መሳል እንችላለን። «… *የሰው መንፈስ የእግዚአብሔር መብራት ነው የሆዱን ጕርጆች ሁሉ የሚመረምር።»* (ምሳ.20፡27)። በህይወት መጎዳት በውስጣችን በጣም እየጨመረ የሚሄድ የነበልባል ግለት ሲሆን በውስጣችን እየነደደ ወደ መደብዘዝ የሚሄድ ነበልባል ይሆናል። ይህ እየጠፋ የሚሄድ ነበልባል የሚጤስ ጧፍ ሊሆን ይችላል። ኢየሱስ ፈጽሞ የተቀጠቀጠን ሸንበቆ አይሰብርም። ይልቅስ «… *እግዚአብሔር በቃሉ የታመነ ነው፥ በሥራውም ሁሉ ጻድቅ ነው፤ እግዚአብሔር ለመቆም ያቃታቸውን ሁሉ ይደግፋቸዋል፥ የወደቁትንም ያነሣቸዋል።»* (መዝ. 145፡14፣ 146፡8)። «… *አንተ ግን አቤቱ፥ መጠጊያዬ ነህ፥ ክብሬንና ራሴንም ከፍ ከፍ የምታደርገው አንተ ነህ።»* (መዝ.3፡3)። «… *ባሪያዎች እንዳትሆኑአቸው ከግብፅ ምድር ያወጣኋችሁ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ፤ የባርነታችሁን ቀንበር ሰብሬአለሁ፤ ቀና ብላችሁ እንድትሄዱ አድርጌአችኋለሁ።»* (ዘሌ.26፡13)።

እርሱ የሚጤስን ጧፍ አያጠፋም፤ ነገር ግን በተቀጠቀጠው መንፈሳችን /በዛለው/ መንፈሳችን ላይ እንደገና መንፈሱን ይተነፍስበትና «… *ለዘላለም የሚኖር ስሙም ቅዱስ የሆነ፥ ከፍ ያለው ልዑል እንዲህ ይላል፦ የተዋረዱትን ሰዎች መንፈስ ሕያው አደርግ ዘንድ፥ የተቀጠቀጠውንም ልብ ሕያው አደርግ ዘንድ፥ የተቀጠቀጠና የተዋረደ መንፈስ ካለው ጋር በከፍታና በተቀደሰ ሥፍራ እቀመጣለሁ።»* (ኢሳ. 57፡15) ። (የኢሳ. 42፡3 አውድ በሙሉ ስለፍትሃዊነት የሚያወራ ተገቢ ምልከታ ያለው ነው። ኢየሱስ የእግዚአብሔር አገልጋይ «… *የተቀጠቀጠን ሸምበቆ አይሰብርም፥ የሚጤስንም ክር አያጠፋም፤ በእውነት ፍርድን ያወጣል። በምድርም ፍርድን እስኪያደርግ ድረስ ይበራል እንጂ አይጠፋም፤ አሕዛብም በስሙ ይታመናሉ።»* (ኢሳ 42፡3-4) ።

## 3. የልብ ስብራትእንዴት እኛን ይጎዳል።

### *አሰቃቂ አጋጣሚ ( አደጋ)*

እኛ ምናልባት በአሰቃቂ (አደጋ) አጋጣሚ የተጎዳን ልንሆን እንችላለን። አሰቃቂ አደጋ የሚለው ቃል የሚገልጠው አንድ ሰው በጣም አሳዛኝ በሆኑ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ሲያልፍ የሚመጣ የአካል፡ የአዕምሮና የስሜት ችግርን ነው። የአሰቃቂ አጋጣሚ (አደጋ) ችግሮች በየእለቱ ህይወታችን የሚያጋጥመንን ችግር ለመቋቋም አስቸጋሪ ሊሆን ሲችል ማለት ነው። በዚህ ሁኔታ ያሉ ሰዎች በተመለከተ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተለይተው የሚታውቁ ምልክቶች አሉ። እነዚህም በቀጣይ ውስጥ ተዘርዝረው /ተገልጠው/ ይገኛሉ።

### *እምነታችን*

የልብ ስብራታችንን የምንለካበት አንዱ መንገድ ጥልቅ የሆነውን እምነታችንን ምን ያህል እንደጎዳው ስንመለከት ነው። በጣም ብዙውን ጊዜ በጉዳታችን ቦታ በመገለል ውስጥ ስንሆን ስለራሳችን፡፣ ስለሌሎች፣ ስለህይወትና በተለይም ስለእግዚአብሔር በውስጣችን ያለን የምንወስነው ጉዳይ ላይ መልዕክት እንቀበላለን/ እናገኛለን/። ሰይጣን የሀሰት አባት ተብሎ ይጠራልና፤ የእርሱ ዋናው መሳሪያ በውስጥ ማንነታችን ውስጥ ውሸትን ማመን እንድንጀምር ማድረግ ነው።

ሰዎች እጅግ አስቸጋሪ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ እንደሚያልፉ እናውቃለን፤ ነገር ግን ከእነርሱ የሚወጣው ነገር በመሠረታዊ እምነታቸው ምንም ጉዳት አያመጣም። እነርሱ በጽድቅ በሚወዳቸውና በሚያከብራቸው እንዲሁም ከመከራቸው ሊታደጋቸው በሚችል አምላክ እንደሚወደዱ ያውቃሉ። በእርግጥ እነርሱ የማጣት ጉዳት እንደሚደርስባቸው ነገር ግን ከእግዚአብሔር፣ ከሌሎችና ከራሳቸው ጋር ጤናማ ግንኙነት እያደረጉ ሊኖሩ ይችላሉ። እነርሱም በጣም በከፋ ጉዳት ውስጥ እንደማይሆኑ ሊያጠቃልሉ ይችላሉ። እንደዚህ ዓይነት ተመሳሳይ የሆነ ችግር ውስጥ የሚያልፉ ሰዎች ሊኖሩ የሚችሉ ሰዎች ይኖራሉ። ነገር ግን እነርሱ ከዋጋ ቢስነት ስሜት ይወጣሉ። እነርሱ የዋስትና ስሜት ወደሚሰማቸው ሥፍራ አይኖርምና

በሚወዳቸው አምላክ ላይ ያላቸው እምነታቸው ይጠፋል። በአጠቃላይ እነርሱ በጣም በጥልቀት የተጎዱ ሰዎች ናቸው።

**በሀጢያት መንገድ ምላሽ እንሰጣለን።**

ምንም እንኳን እኛ በከፋ ኃጢአት ውስጥ ያለን ቢሆንም ኢየሱስ ክርስቶስ ግን በኃጢአት መንገድ ፈጽሞ ምንም ምላሽ አይሰጥም (አልሰጠም) (1ኛ ጴጥ. 2፡22-23) ። ይሁን እንጂ ከስብራታችን /ጉዳታችን/ የተነሳ ኢየሱስ እንዳደረገው ራሳችንን በእግዚአብሔር ከመታመን ይልቅ ብዙውን ጊዜ እኛ የምንሰጠው ምላሽ በሃጢአታዊ መንገድ ነው።

***ሀ. እኛ ፍርዶችን እናስተላልፋለን***

እኛ በልባችን አንድ ሰው ቢቃወመን የፍርድ ውሳኔ እናስተላልፋለን ማለት ነው፣ እንኮንናቸዋለን፣ ስለወደፊት ህይወታቸው ምንም ተስፋ እንደሌላቸው እናስባለን ። መጽሐፍ ቅዱስ ፍርድን በጣም አደገኛ እንደሆና ይጠቅስና ስንፈርድ ተመልሰን እኛም የምናስተላልፈው ዓይነት ፍርድን እንደምንቀበል ይናገራል(ማቴ.7፡1-5)።

***ለ. ምንም እንኳን ልናረጋግጥ ባንችልም በጣም ጠንካራ ውስጣዊ ውሳኔ እንወስናለን።***

እነዚህ የውስጥ ውሳኔዎቻችን ስለህይወት ባለን አመለካከት ላይ ተጽዕኖ የሚፈጥሩ ናቸው።

ለምሳሌ፡-

- ሁለተኛ ፈጽሞ ማንንም አልታመንም /አላምንም/።
- እኔ ፈጽሞ መጎዳት ወይም ደካማ መሆን አልፈልግም /አልፈቅድም/።
- ፈጽሞ መልካም ነገር ይሆናል ብዬ አልጠብቅም፤ እናም ተስፋ አልቆርጥም።

**ሐ. ብዙውን ጊዜ በምናስተላልፋቸው ፍርዶች ምክንያት የሚዛባውን ውስጣዊ እምነቶቻችን እንጠብቃለን።**

እምነት በጣም ኃይለኛ ነው። ይህም ስሜቶቻችንና ባህርያቶቻችንን የሚያነሳሳ ነው። እኛ ያሉብን የተዛቡ የውስጥ አምነቶቻችን ምናልባት

- እኔ/ የእኔ ህዝብ /ወገን/ ሁልጊዜ የተጠቃ ይሆናል።
- ስለእኔ ማንም ግድ የሚለው የለም።
- ምንም የሚታመን ሰው የለም።
- እኔ በራሴ ጉዳይ ብቻ እኖራለሁ።

በተጨማሪም ፍረጃዎች የተዛቡ እምነቶች ምሳሌዎች ናቸው።

## *መ. ከራሳችን ወገን መራቅ*

ከደረሰብን ጉዳት /ስብራት/ የተነሳ ራሳችንን ከሌሎች ወገኖች እናገላለን፣ ሰዎችን ላለማመን እንመርጣለን ወይም ከገዛ ራሳችን ወገኖች ወጪ ከማንም ጋር ግንኙነት ላለማድረግ እንመርጣለን ገላ.6፡7፣ እኛ የዘራነውን እንደምናጭድ ይናገራል። በተጨማሪም ይህ በእኛ የውስጥ እምነት እና እውነት ላይም ነው። ኢየሱስ እንዲህ አለ «... እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ ብሎ ዓይኖቻቸውን ዳሰሰ።» (ማቴ.9፡29)። በእግዚአብሔር ስናምን እግዚአብሔር እንዲሰራ በር የሚከፍት ሲሆን አሉታዊ እምነቶች ወደ እውነታ እንዲመጣ የሚያስችል ኃይል አለውና (ኢዮብ 3፡25) የእኛን ሁለንተናዊ ህይወት የሚጎዳ ነው።

## 4. **ያልተፈወሱ ቁስሎች (ጉዳቶች) አደገኛነት**

እኛ ሁላችንም ያልተፈወሱ ቁስሎች ምን እንደሚሆኑ እናውቃለን - እነዚህ ቁስሎች በጣም እንደሚበከሉ እናውቃለን። እነዚህ እንክብካቤ /ህክምና/ ካልተደረገላቸው ከተጎዳው አካል ወደ መላው የሰውነታችን ክፍል የተመረዘ ነገር ይዛመታልና አንዳንድ ጊዜ ፈጽሞ ወደ አለመዳን ሊለወጥ ይችላል። በተጨማሪም ያልተፈወሱ የአካል ክፍሎች ዝንቦችን ሊስብ ይችላል። የሰይጣን አንዱ ስም ብኤልዘቡል ይባላል፤ ትርጉሙም *«የዝንብ ጌታ /አለቃ/»* ማለት ነው (ማቴ 10፡25፣ 12፡24 -27)። የተጎዳ አካላዊ *ሥፍራ* ዝንብን የሚስብ እንደሆነ ሁሉ ለብዙ

ጊዜያት ያልተፈወሰ የውስጥ ቁስል ለአጋንንታዊ እንቅስቃሴ በግለሰብ ደረጃም ሆነ በሀገር ደረጃም በር የሚከፍት ይሆናል።

በምንሠራበት ሁሉም ሀገራት፣ ያልተፈወሱ ቁስለቶችና መፍትሔ ያልተገኘላቸው ተመሳሳይ ዓይነት ምሳሌዎች እንደሆኑ ለይታን ማወቅ እንችላለን፣ ብዙውን ጊዜ ትውልድን ወደ ኋላ ያስቀረ ነው። እግዚአብሔር እንደሚያዝን የሚያስገርም አይደለም በኤር. 6፡14ና 8፡11 ላይ *«... የሕዝቤንም ስብራት በጥቂቱ ይፈውሳሉ፤ ሰላም ሳይሆን፡- ሰላም ይላሉ።»* እግዚአብሔር የልብ ስብራቶቻችንን እንደ ኃጢአተኛነታችን እንደ ዋና ሁኔታ የሚወስደው መሆኑን ማወቅ መጽናናትን የሚሰጠን ነው። እርሱ የተጎዱትን ልቦች የሚረዳና የሚያጽናና ነው፣ የልብ ስብራታችን ሁለንተናችንን እንደሚያጠቃ ያውቃልና እርሱ ሊፈውሰን የሚፈልግ ነው። በኤር. 31፡12-13 እንደምናነብበው እንደሰው ንግግር ካየን የጠለቀው የሰው ልብ ስብራት መፈወስ የማይቻል ነው። ነገር ግን ደስ የሚያሰኘው ነገር ቢኖር ከጥቂት ጥቅስ በኋላ (ኤር. 30፡17) እግዚአብሔር ቁስለታችንን /ስብራታችንን/ ሊፈውስና ጤናችንን ሊያድስልን ተስፋ ሠጥቶናል። ይህንን በምዕራፍ 9 ላይ በዝርዝር እንመለከታለን።

## 5. ፈውስ የሚጀምረው ጉዳታችንን ከማወቅና ከመቀበል ነው።

በስፋት ተቀባይነት ያለውና ሰዎችን በፈውስ ሂደት ለመርዳት ሰዎች የራሳቸውን ህመም፣ ቁጣና ሀዘን መግለጥ መቻል ያስፈልጋቸዋል። ነገር ግን ብዙዎቻችን ይህ ማድረግ ከባድ ይሆንብናል።

የተጎዱ /ልባቸው የተሰበረ/ ሰዎች ለፈወስ ከመምጣታቸው በፊት አስቀድመው ህመማቸውን ማወቅ መጋፈጥ እና መግለጥ አለባቸው።

**ህመም**

***ህመማችንን /ጉዳታችንን/ መግለጥ እንዳንችል ከባድ የሚሆንበት ለምንድነው?***

- ትዕቢት፡ በዚህ ጊዜ እኛ ህመም እንዳለብን መካድ፣ መሰወርና ጠንካራ መስሎ መታየትን እንመርጣለን።

- ሰዎችን ለማመን አለመቻል፤
- ልጎዳ እችላለሁ ብሎ መፍራት፤ ከሰዎች የተነሳ
  - ሰዎች አያስቡልኝም፣ እንዲያውም ሊስቁብኝ ይችላሉ፤
  - የእኔን መጎዳት ሰዎች ሊጠቀሙበት ይችላሉ፤
  - ሰዎች ሊተቹኝ ወይም ሊፈርዱብኝ ይችላሉ፤
- ፍርሃት ሞኝ /ሰነፍ/ ያደርጋል፤ «ጩኸት ከጀመርኩ ፈጽሞ ላላቆም እችላለሁ!»
- ባህላዊ /ልማዳዊ/ እምነት (ለምሳሌ፡ የብሪታንያ እምነቶች፣ የላይኛውን ከንፈር ማጣመም ልብህን በራስህ መሸፈኛ ማልበስ፣ ወንድ ልጅ አያለቅስም)፤
- በአንዳንድ ጉዳዮች ፖለቲካዊ አለመረጋጋት /አደጋዎች/ ካሉ ችግሮቻችንን መግለጥ በተለይም የእኛ አመለካከት «ፖለቲካዊ ማስተካካያ» እንደሆነ ካላስተዋልንና ስህተቶች ፈጽሞ በግልጥ ተቀባይነት የላቸውም።
- መንፈሳዊነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ የተሳሳተ መረዳቶች። አንዳንድ ቤተክርስቲያናት እኛ ሁልጊዜ አሸናፊዎች መሆን እንደሚጠበቅብን ያስተምራሉ፤ የሚያሳዝነው ግን ይህ ሰዎች «የግብዝነት መሸፈኛ» እንዲለብሱ ወደ ማድረግ ስሜትና የራሳቸውን እውነተኛ ማንነት እንዲደብቁ የሚያደርግ ነው።

አሁንም በጣም አደገኛ የሆነው ነገር ህመምን ጥርስ ነክሶ ሸፍኖ (አደባብሶ) መኖር ነው። ህመማቸውን፣ ቁጣቸውን ወይም መራርነታቸውን በልባቸው ውስጥ የሚሰውሩ ሰዎች ከሁሉ በላይ ለአካላዊና ለአዕምሮአዊ በሽታ የተጋለጡ ይሆናሉ። እነዚህ ሰዎች በህይወታቸው ወደ ፊት መራመድ የማይችሉና ወደፈውስ የሚደረገው ጉዞ መጓዝ የማይችሉ ይሆናሉ። በተጨማሪም ግጭቶች ሁሉ በቶሎ መፍትሔ ካልተሰጣቸው በስተቀር፣ በሀገራችን ታሪክ ውስጥ የከፋ መዘዝ ሊያመጣ ይችላል።

## ተግዳሮቶቻችንን እንዴት እኛሸንፋቸዋለን?

የተለያዩ ባህሎች የተለያዩ ነገሮችን ያስተምሩናል። የትኛው ትክክል ባህል እንደሆነ እንዴት ልንመዝን እንችላለን? ስለዚህ ወደ ቅዱሳት መጽሐፍ መመለስ ያስፈልገናል። ሁሉም ባህሎች

ከመጽሐፍ ቅዱስ ሊማሩ ይችላሉ፡ መጽሐፍ ቅዱስ ከሁሉም ባህሎች የበላይ ነውና። መጽሐፍ ቅዱስ ስሜትን ስለመግለጥ ምን የሚያስተምረው ነገር አለ? በቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ ብዙ ስሜትን ስለመግለጥ ምሳሌ የሚሆኑን ሰዎች ተጠቅሰዋል።

- ሐና ልጅ በማጣቷ ህመሟን ገልጣለችና ስሜቷን የገለጠችበት መንገድ ካለችበት ሁኔታ የተነሳ እንደተቀለደባት /እንደተነቀፈች/ ገለጠች። (1ኛሳሙ. 1፡10፣15-16)።
- ዳዊት በተለያዩ ብዙ መዝሙራት ውስጥ ህመሙን ገልጧል። ምክንያቱም በኢፍትሃዊነት ስለተጠቃ ነበር (መዝ. 5፣7፣10፣12፣13፣22፣31፣69ና የመሳሰሉት)።
- ኤርምያስ ስለህዝቡ ሁኔታ በእግዚአብሔር ፊት አለቀሰ /አጉረመረመ/ (ኤር. 8፡18 – 9፡1)።

ኢየሱስ ፍጹም ሰው ነበረና እርሱም በትክክለኛው መንገድ ስሜቱን ሁሉ ሲገልጥ ነበር (ዮሐ.11፡35፣ ሉቃ.19፡41፣ ዕብ.5፡7)። እርሱ የሸንገላ መሸፈኛ አልለበሰም፤ የእርሱ ልብ ግልጥነትን የተሞላ ነበር። እርሱ ትዕቢት ወይም ኩራት አልነበረበትም  የሌሎች ሰዎች አስተያየት ፍርሃት አልነበረበትም። ኢየሱስ ስሜቱን ለመግለጥ ነጻ ከነበረ እኛም እንደእርሱ ነጻ መሆን እንችላለን። እርሱ በትክክል እኛን ይረዳናል። አድካሚና ከባድ ሸክም የሆነውን ወደ ኢየሱስ ወደ መስቀሉ ማምጣትና የህመማችንን ሸክም በእርሱ ላይ ልንጥለው እንችላለን። እኛ ልናውቀው የሚገባ ነገር ቢኖር እግዚአብሔር ሊያጽናናን እየጠበቀን እንደሚገኝ ነው። ቤተክርስቲያን ሰዎች ህመማቸውን በመቀበልና በመጋፈጥ ፈውሳቸውን የሚያገኙበት የተመቸች ሥፍራ መሆን ያስፈልጋታል።

አሁንም ምንም ዓይነት ፍትሃዊነት በሌለበት ጉዳይ ላይ ክርስቲያን የሆኑ ሰዎች እግዚአብሔርን እንደ ጻድቅ ፈራጅ /ዳኛ/ ፈልገው ኢየሱስ በመስቀል ላይ እንዳደረገው (1ኛጴጥ.2፡23) በሁሉም ነገር እርሱን በመታመን በእርሱ እጅ አደራ እንዲሰጡት መርዳት ይችላሉ። ክርስቲያኖች በተጨማሪም በተቃዋሚዎች ፊንታ «በጎደለው ለመሙላት» (ክፍተትን መሙላት) የክህነት ሚናቸውን ለመወጣት ይችላሉ። በጎደለው ሥፍራ መቆም ሌሎች ፈውሳቸውን እንዲያገኙ ለመርዳት በጣም እጅግ አስፈላጊ መንገድ ነው። እንዲያውም ለብዙ

ዓመታት ተሰውሮ ለነበረው የልብ ስብራት አስፈላጊ ነው። ይህንን በምዕራፍ 13 ላይ በዝርዝር እንመለከተዋለን።

ከታች ባለው የግራ በኩል ስዕል በአንድ ሰው ላይ በሁሉም ዓይነት በአሰቃቂ አጋጣሚ (ችግር) ውስጥ ሲያልፍ እንመለከታለን፤ ነገር ግን አሁን ደህና የሆኑ ዓይነት ስሜት ያሳያሉ (የፊት መሸፈኛ ጭንብል እንደለበሱ ዓይነት) በስተቀኝ ባለው ምስል ለሚቀበሉት መከራ እውነተኛነት ሆነው የራሳቸውን ጭምብል የሚያስወግዱ ሰዎችን የሚያሳይ ነው። ነገር ግን በተጨማሪ የምንመለከተው ነገር የእግዚአብሔር እጅ ደግፎ ሲይዛቸው እንመለከታለን፤ ይህም የዋስትና ስሜት እንዲሰማቸው ያደርጋል።



**ከራስ ጋር ማዛመድ**

- በህይወትህ ምን ዓይነት የልብ ስብራት ምልክቶች ይታያሉ?
- ምን ዓይነት የተሳሳተ እምነት የተሰበረውን ልብህን ይዞታል?
- ስሜትህን ስለመግለጥ በተመለከተ ምን ዓይነት እምነቶች ባህል ሆነውልሃል?
- እነዚህ እምነቶች ምን ያህል ተጽዕኖ አሳድረውብሃል?

**ቁልፍ ሀሳቦች**

- የልብ ስብራት ኃጢአት ወደ ዓለም መግባት ያመጣው መዘዝ ሲሆን የዘር /የብሔር/ መድሎ ማለት ጥልቅ ጉዳት ነው።
- እኛ ስንጎዳ ሰይጣን ስለራሳችን፣ ስለሌሎችና ስለእግዚአብሔር የሚዋሸን ውሸት ማመን ስንጀምር በባህርያችን ላይ የሚያመጣው ተጽዕኖ አለው።
- እግዚአብሔር የልብ ስብራታችንን እንደ ሃጢአታአችን በትኩረት ይመለከተዋል፣ እናም እንድንፈውስ ቁስላችንን እንድንጋፈጠው እና እንድንቀበለው ይፈልጋል።

# ትምህርት ዘጠኝ

## ለሰው ልጅ መከራ የእግዚአብሔር መልስ

### ኢየሱስ ኃጢአታችንም ሆነ ህመማችን እንደሚሸከምልን መረዳት

በዓለም በምድር ላይ ለሚሆኑት ለሁሉም ክፉ ነገሮች፣ ለሁሉም ኢፍትሓዊነት፣ ለሁሉም መከራዎች የእግዚአብሔር መልስ /ምላሽ/ ምን ነበር? እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዓለም የመጣበት ትልቁ ምክንያት መከራ ተቀባይ ለመሆን፣ በሁሉም ነገር ኃላፊነትን በመቀበል እንዲሁም ምንም እንኳን እርሱ በደል የሌለበት ቢሆንም ሁሉንም ኢፍትሃዊነትን ተቀበለ። (ይህ በእርግጥ ጥፋታችንን አምነን ጥፋታችንን ለመቀበል እና ንስሐ የመግባት ኃላፊነታችንን አይወስድም) እርሱ ሁሉንም በመስቀል ላይ በራሱ ላይ አደረገ፣ የእኛን በደልና ቅጣት ተሸከመና ሥርየትን አዘጋጀልን። ይህን በሚያደርግበት ጊዜ እርሱ ኃጢአታችንንና ህመማችንን ሁሉ ተሸከሚ ሆነ ።

### 1) ኢየሱስ ኃጢአታችንን እንደተሸከመ ሁሉ ህመማችንንም ተሸከሚል

ዮሐንስ መጥመቁ በአገልግሎቱ መጀመሪያ ላይ ስለ ኢየሱስ በአደባባይ አወጀ። *«እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ»* (ዮሐ 1፡29 በአደባባይ አገልግሎቱ መጀመሪያ ላይ ኢየሱስ በናዝሬት በምኩራብ ውስጥ የተጠቀለለ መጽሐፍ ተቀብሎ (ሉቃ 4፡14-

21) ከኢሳ 61 ላይ አንብቦ ይህን ቃል አወጀ፤ እንዲህም አለ *«ልባቸው ለተሰበረ እፈውስ ዘንድ ልኮኛል››*። ኢየሱስ ወደ ዓለም የእኛን ኃጢአት ለማስወገድ መጥቷል የሚለውን ብቻ የምናስተምር ከሆነ ትምህርታችን ግማሽ ወንጌል ብቻ ይሆናል። እርሱ ኃጢአተኛነት ብቻ አይደለም፤ የእኛ ጉዳት የመጣው በእኛ ኃጢአት ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን በሌሎችም ኃጢአትም ጭምር ነው የተጎዳነው። ኢየሱስ ለኃጢአታችን ብቻ የመጣ ቢሆን ኖሮ ስለ ህመማችን ምን እናደርግ ነበር?

የወንጌል የከበረ ዜና የሆነው ኢየሱስ ኃጢአታችንና ህመማችንን ጭምር በመስቀል ላይ ስለተሸከመልን ነው። ኢሳ. 53፡4 እንዲህ ይላል *«በእውነት እርሱ ደዌያችንን ተቀበለ ህመማችንንም ተሸክሞአል»*። የዕብራዊያን ቃል በዚህ ሥፍራ የተጠቀመው ህመምና ሐዘን ብሎ ነውና። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ኃጢአቻችንን ብቻ ሳይሆን የተሸከመው እርሱ በዓለም ላይ የሆነውን የኃጢአታችን መዘዞችን ሁሉ ጭምር ነበር የተሸከመው። በመስቀል ላይ ኢየሱስ እንዲህ አለ *«እኔን በደለኛ አድርገህ ቁጠረኝ። ሁሉንም የዓለም ኃጢአትና ህመም /ሀዘን/ ስጠኝ፡ ፡ እኔ በአንተ/ቺ/ በእናንተ ቦታ መከራውን እቀበላለሁ።*

### ***ኢየሱስ መከራን ይረዳል።***

ኢየሱስ በምድራዊ ህይወቱ ወቅት ብዙ መከራን ተቀብሏል። *«እርሱ የህማም ሰው መከራን የሚያውቅ»* ተብሎ ተተንብዮለት ነበር። *«... እርሱ የተናቀና ከሰውም የተጠላ»* (ኢሳ 53፡3)። እርሱ ወደዚህ ዓለም በመጣ ጊዜ የሚወለድበት ሥፍራ አልነበረውም። እንዲሁም የእርሱ ወላጆች እርሱ የተቀበሉበት ሥፍራ የቆሸሸ፣ የሚያስጠላ ደስ የማያሰኝ ሥፍራ ነበር። ገና ልጅ /ህፃን/ በነበረበት ጊዜ እርሱና ቤተሰቡ ወደ ግብፅ ተሰድደው በዚያ ጥገኛ ሆነው ነበር። በትውልድ ከተማው በናዝሬት ሰዎች እርሱን ከህግ ውጪ የተወለደና በድህነት ያደገ፣ ዝቅተኛ ክፍያ ያለው ሥራ የሚሠራ /የተዋረደ ሥራ/ ነው ብለው ያስቡ ነበር። በምድራዊ አገልግሎቱ ጊዜ በራሱ ቤተሰብ ጭምር ተቀባይነት /ያልተረዱት/ ያላገኘ ነበር። በመንግስትና በኃይማኖት መሪዎች ዘንድ የተዋረደና ተቀባይነት ያልነበረው ነበር።

ስለዚህ እርሱ /ኢየሱስ/ መከራን የሚያውቅ /የሚረዳ/ ነው ማለት ግልፅ ነው፡፡ ለልጁ ያለው ፍቅር ከፍተኛ ቢሆንም እግዚአብሔር ከመከራ ሊያድነው መጠለያ አልሆነውም፡፡ ዕብ. 2፡ 10 እንዲህ ይላል፡፡ ‹‹... *ብዙ ልጆችን ወደ ክብር ሲያመጣ የመዳናቸውን ራስ በመከራ ይፈፅም ዘንድ››*

### ***ኢየሱስ ያለፈባቸው አንዳንድ መከራዎች፡-***

- እርሱ በጓደኞቹ የተካደ ነበር፡፡
- በገዛ ወገኖቹ ተቀባይነት ያጣ (የተገለለ) ነበር፡፡
- የተገረፈ፣ የተቀለደበትና የተተፋበት ነበር፡፡
- እራቁቱን የተገረፈ ነበር፡፡
- እጅግ ከባድ መስቀል የተሸከመ ነበር፡፡
- የተሰቀለ ነበር፡፡
- በሰማዩ አባቱ የተተወ ነበር፡፡

አንዳንዶች አሁንም *«ኢየሱስ እንዴት የእኔን መከራ ሊረዳ /ሊያውቅ/ ይችላል?»* ብለው ይጠይቃሉ፡፡ የእርሱ ቤተሰቦች በመላው በዘር ማጥፋት ፈፅሞ አልጠፋበትም፡፡ የተደፈረች ሴት የሚሰማትን አይነት ስሜት አያውቅም፡፡ ምንም እንኳን በዚህ ሁሉ መከራ ውስጥ ማለፉ እውነት ቢሆንም በምድራዊ ህይወቱ ወቅት ሁሉንም ዓይነት የሰው ልጆች መከራ ቃል በቃል አልተቀበለም፡፡ ወደ መስቀል ሲያደርግ በነበረው ጉዞ ወቅትም ቢሆን ሁሉንም ዓይነት መከራ አልተቀበለም ነበር፡፡ ነገር ግን ኢየሱስ በመስቀል ላይ የሰው ልጅ ያልፍበታል ተብለው ከሚጠቀሰው በላይ እጅግ ታላቅ የሆነ ነገር አድርጓል፡፡

### 2. ለኢየሱስ የመስቀሉ ስራ የልውውጥ ሥፍራ እንጂ የእርሱ መገለጫ አይደለም፡፡

በመስቀል ላይ የሆነው ነገር እኛ ከምንገምተው በላይ እጅግ አስገራሚ ነገር ነው፡፡ በ2ኛ ቆሮ 5፡21 ኢየሱስን እንዲህ እንለዋለን፡፡ ምንም እንኳን አንድም ኃጢአትን ያላደረገ ፍፁም ቢሆንም *«እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው»*፡፡ እኛ ፈፅሞ ልንረዳው በማንችለው መንገድ

ሁሉንም የዓለም ኃጢአት በመስቀል ላይ ወደ እርሱ ተላለፈ፤ እርሱ ሁሉንም የሰዎች አስፈሪ ኃጢአተኛነት በራሱ ተቀበለ። በተመሳሳይ መንገድ ሁሉንም የእኛን ህመም ጭምር ወደ እርሱ ተላለፈ። ሁሉም አሳዛኝ የሰው ልጆች ሁኔታ በዚያው ነበር። ኢየሱስ በመስቀል ላይ እንደተሰቀለ እርሱ የአስገድዶ ደፋሪዎችንም ኃጢአት ተሸከመ። በተጨማሪም በተመሳሳይ ሰዓት እርሱ የተደፋሪዎችን ጥቃት ህመም ተሸክሟል። እርሱ ገዳይና ተጠቂ ጭምር ሆነ። እርሱ ሌባና የተዘረፈ ሆነ እርሱ አስገድዶ ደፋሪና የመደፈር ተጠቂ ሆነ። እርሱ ሁሉም የሚሰማው ሆነ፤ እንዲያውም እርሱ መጥፎ ስሜት እንዳይሰማው የሚያደርገውን የህመም ማደንዘዣ መቀበልን አልፈቀደም።

## 3. ህመማችንን እንዴት እናስወግደዋለን

ሰዎች በኃጢአታቸው ካሉ እንዴት አድርገን እንደምንረዳቸው እናወቃለን። ኃጢአታቸውን እንዲናዘዙና ወደ ኢየሱስ መስቀል እንዲወስዱ እንነግራቸዋለን። *«ስለዚህ ጉዳይ እርሳውና ስለሌላ ነገር አስብ›*› አንለውም። ምክንያቱም እንዲናዘዙና ከዚያም እንዲርቁ እንደሚያስፈልጋቸው እናውቃለን። በህመምም እንዲሁ ተመሳሳይ እውነት አለ። ነገር ግን ስለዚህ ህመምን በቃ እርሳው ወደ ማለት እናዘነብላለን። ነገር ግን በዚህ መንገድ ፈፅሞ እንዲፈወሱ አናደርግም። ሀዘናችንንና ህመማችንን በመሸከም ኢየሱስ እንዲህ ይላል *«እኔ ስለ አንተ ልጎዳ»* ህመማችንንና የልብ ቁስለታችንን የምንሰውር ከሆነ እንዲፈወሰው ወደ ኢየሱስ ልንወስደው አንችልም።

የአልዓዛርን የማርታና የማሪያም ወንድም የሆነውን፣ የሞተውንና በመቃብር የተቀበረውን ታሪክ እናስብ (ዮሐ 11፡1-44)። ኢየሱስ በሥፍራው እንደደረሰ ኢየሱስ ከመቃብሩ ላይ ያለውን ድንጋይ ያነሱ ዘንድ ጠየቃቸው። ማርታ በተቃውሞ መልስ ሰጠች። ‹‹ነገር ግን አልዓዛር እዚያ ከሆነ አራት ቀናት ሆኖታል። ድንጋዩን ብናነሳው ይገማል ‹ይሸታል!›› ይሁንም እንጂ ኢየሱስ ድንጋዩ እንዲነሳ አዘዛቸው። ከዚያም አልዓዛር ከመቃብሩ እንዲወጣ ጠራው። ኢየሱስ ከመቃብሩ በስተጀርባ ግማት/መጥፎ ሽታ እንዳለ ያውቃል። ነገር ግን ድንጋዩ እስኪወገድ ድረስ አልዓዛርን ወደ ውጪ ሊጠራው አልቻለም። በተመሳሳይ ኢየሱስ እኛ በልባችን

ውስጥ የቀበርነውን እና ‹‹ይሸታል›› ብለን የያዝነውና ወደ መመርቀዝ እየሄደ ያለው ያልተፈወሰ ቁስላችንን ያውቃል። እርሱ ልባችንን ሊፈውስ ይፈልጋል። ነገር ግን ወደ ቁስላችን እንዲመጣ በር ካልከፈትን ወደ ህመማችን ኢየሱስ እንዲመጣ ካልጋበዝነው በስተቀር እርሱ እኛን ሊፈውስ አይችልም።

በመስቀል ላይ ኢየሱስ በደሙ ለኃጢአታችንና ለህመማችን ሙሉ ዋጋ ከፍሏል። እርሱ እኛ ከሁሉም ነጻ እንድንወጣ ህይወቱን ሰጥቶናል። ኢሳ. 53፡3 እንዲህ ይላል። እኛ ኢየሱስን ናቅነው እንዲሁም አላከበርነውም። እኔ ህመሜን ተሸክሜ ወደ ኢየሱስ ለመምጣት ፈቃደኛ ካልሆንኩ አሁንም እኔ እርሱን እያከበርኩት አይደለም ማለት ነው። በዚህ ላይ ትኩረት የምናደርግ ከሆነ እርሱ በከንቱ ሞተ ማለት ነው። ይህም ኢየሱስን እንዲህ እንደማለት ነው ‹‹እኔ ያንተን መስዋዕትነት አልፈልግም እኔ በራሴ የራሴን ህመም መሸከም እችላለሁ›› እኔ እርሱን ላከበር የምችልበት መንገድ በትክክል በህጋዊነት የእርሱ የሆነውን ኃጢአቴንና ህመሜን ለእርሱ እየሰጠሁት ከሆነ ነው።

## *ልባችንን ለእግዚአብሔር ፊት ማፍሰስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው።*

ከህይወታች ቁስለቶች /ጉዳቶች/ ለመፈወስ የምንችልበት ብቸኛው መንገድ ሁሉንም የእኛን ህመም ወደ እግዚአብሔር በግ ማምጣትና እርሱ በእኛ ሥፍራ ሆኖ እንዲሸከመው መፍቀድ ነው። ዘማሪው ልባችንን በእግዚአብሔር ፊት እንድናፈስ ያበረታታናል።

- መዝ 142፡ 1-2 - ዳዊት በጣም ታማኝ ነበር። እርሱ ነገሮችን በልቡ ውስጥ አይሰውርም ነበር።
- መዝ 62፡8 - ሁሉም ሰዎች የገዛ ልባቸውን በእግዚአብሔር ፊት ያፈሳሉ።

- መዝ 56፡8 - ህመማችንን በእርሱ ፊት ብናፈስስ ጌታ እምባችንን ይቀበለዋል። የእኛ መከራ ለእርሱ ዋጋ ያለው ነው።
- (መዝ. 72፡ 14፣ 116፡ 15) እርሱ ሁሉንም እምባችንንና ህመማችንን ይመዘግበዋል።
- ሰቆቃ 2፡19 - እንዲህ ይላል ‹‹በእግዚአብሔር ፊት ልባችሁን እንደ ውሃ አፍስሱ››

እንደ ክርስቲያን፣ እኛ ለዘለዓለም መጽናናትን ማግኘት የምንችለው ህመማችንን ሊወስድልን የሚችል እግዚአብሔር ባዘጋጀው ሥፍራ አለን። አማኝ ላልሆኑት ማድረግ የሚችሉት ብቸኛው ነገር ቢኖር ስለ እርሱ መናገር ብቻ ነው። አሁንም ይህ የሚረዳ ሲሆን ስለ ህመማቸው በብዙ በተናገሩ ቁጥር በብዙ የራሳቸው የሆነ የጠለቀ ሀዘን ውስጥ ለመግባት ጉድጓድ ይቆፍራሉ። አንድ ክርስቲያን መሪ ይህን ጉዳይ በዚህ መልኩ አስቀመጠው። የህመማችንን ጣኦት መሥራት የምንችለው መከራችንን በመሠዊው ላይ አድርገን በማምለክ ነው። ለአንዳንዶች የተጠቁ መሆን የሚቻለው የማንነታቸው አንዱ አካል በመሆን ጭምር ነው፡ ፡


እንደ አማኞች ኢየሱስ ህመማችንን የተሸከመልን መሆኑን ማወቅ ለእኛ እድል ነው። እኛ ከብዶን ስንሸከም የነበረውን የህመማችን ከባድ ሸክም ለመገላገል እንችላለን። ይህም እኛም ኃጢአትን ወደ መስቀሉ በምናመጣበት ጊዜ ንስሀ መግባት ያስፈልገናል። ። በውስጣችን ላለው መራርነት ወይም በቀልን በመፈለጋችን ንስሀ መግባት ያስፈልገናል። ነገር ግን የልብ ስብራታችንን ወደ እርሱ ስናመጣ ንስሀ መግባት አያስፈልገንም የእግዚአብሔር ልብ በህመም ያዝናል (ዘፍ 6፡6)፣ እንዲሁም በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ ለሀገራችን ህመም (መከራ) በቂ ሥፍራ አለ። በመስቀል ላይ ህመማችንን መተው አለብን። እንደ ጉዳታችን ውጤት እኛ ያመነውን ውሸት ለይተን ማወቅና ይህን ሀሰት /ውሸት/ ማጋለጥ እንችላለን። ከዚም ወደፊት በነጻነት ለመሄድና ህይወትን እንደገና ለመኖር መጀመር እንችላለን። ነገር ግን የሚበልጥ የተሻለ መልካም ዜና አለ (ይኖራል)።

**የተጎዱ ሰዎች ከመፈወሳቸው**

**በፊት መጀመሪያ**

**ህመማቸውን መግለጽ እና መጋፈጥ አለባቸው**

**ህመም**



**ኢሳ 53፤4**

4) **መከራ በማጣት ፈንታ ማግኘት ሆኖ የሚያበቃው እንዴት ነው?**

***የእግዚአብሔርን ርህራሄ ማግኘት እንችላለን።***

በሌላ መልኩ ፈጽሞ የማናውቀውን ፣ በመከራ ውስጥ ልንለማመደው የምንችለው የእግዚአብሔር የልብ ርኅራኄ በረከት አለ። ስለዚህ መከራ እንደ ክርስቲያን በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚሠቃዩ ሰዎችን እንድናገለግል ያስታጥቀናል። አግዚአብሔር ክርስቲያኖች መከራ እንዳይደርስባቸው የሚጠብቃቸው ከሆነ መከራ በሚደርስባቸው ሰዎች ላይ እምነት የሚኖረን እንዴት ነው? እንዳልገባን ይሰማቸዋል። ነገር ግን፣ በመከራችን መካከል የእግዚአብሔርን ርኅራኄ ስንገናኝ እና የእርሱን ማጽናኛ ስንቀበል፣ ይህ በእጃችን ለሌሎች ልናቀርበው የምንችለው ሀብት ይሆናል።

***እምነታችን ይፈተናል፤ ይጠነክርማል***

መከራ የእምነታችንን እውነተኝነት የሚፈትን ሲሆን ምንም ይሁን ምን እግዚአብሔርን ለመከተል ያለንን ቁርጠኝነት ያጠናክራል ስለዚህ ማንም ሰው የምቹ አየር አማኞች ናችሁ ብሎ አይወቅሰንም ይህም እንድንጸና እና እንድንታገስ ያስተምረናል። ክርስቲያኖች ፈጽሞ እንደማይሠቃዩ ዋስትና ቢሰጣቸው ኖሮ ሰዎች በተሳሳቱ ምክንያቶች ወደ ክርስትና ለመመለስ ይጥሩ ነበር። እራሳችንን ስለምንወድ እና ቀላል ህይወት ስለምንፈልግ እንጂ እግዚአብሔርን ስለምንወድ አይደለም።

በመከራ ውስጥ ስናልፍ በእግዚአብሔር ላይ የመደገፍና በእርሱ የመታመን መልካም አጋጣሚን እናገኛለን። እምነታችን እንዲያድግ ይረዳናል። በባህሪያችን ውስጥ ያለውን ድካማችንን እንድንሠራበት ሊረዳን ይችላል። በሚያሳዝን ሁኔታ ግን ፣ እኛን በእግዚአብሔር እጅ ለመጣል ፣ እሱን እንድንፈልግ፣ እሱን ለማስደሰት በቁም ነገር እንድንሰራ ለማድረግ ብዙ ጊዜ ተስፋ እንቆርጣለን።


ይህ ማለት ግን መከራን ጣዖት እናድርገው ወይም ራሳችንን ለሥቃዩ መተው አለብን ማለት አይደለም። እግዚአብሔር መከራን ለማስታገስና ግፍን ለመዋጋት የምንችለውን ሁሉ እንድናደርግ ይፈልጋል። ነገር ግን መከራ የማይቀር ከሆነ ሊቤዠን ይችላል ኢየሱስም በዮሐንስ 16፡3 ተስፋ እንደሰጠው በእርሱ ድልን ሊሰጠን ይችላል።

### *እግዚአብሔር ከመከራችን ሊታደገን ይችላል።*

'መቤዠት' የሚለው ቃል 'መልሰን መግዛት' ማለት ነው። ኢየሱስ በሞቱና በትንሳኤው ሰይጣን የዘረፈውን መልሶ ለመግዛት ሙሉ ዋጋ ከፍሏል። ቅዱሳት መጻሕፍትን ስንመለከት፣ እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ጋር ባለው ግንኙነት ውስጥ አስደናቂ ማሳያዎችን እናገኛለን። ምንም እንኳን ሰይጣን የሰውን ልጅ እግዚአብሔር ካሰበው ብዙ ነገር ቢዘርፍም እግዚአብሔር ግን የመጨረሻው ሁኔታ ከመጀመሪያው የበለጠ እንዲሆን የኋለኛውን እኛነታችን ሊያድስልን ይችላል። የተፈጠረው ዓለም መልካም ነበር፤ ነገር ግን ሞት ገባ።መንፈሳዊ የሆነው አዲሱ ፍጥረት ከመጀመሪው ፍጥረት እጅግ የተሻለ ነው። በኢፍትሀዊነት መከራን መቀበልን በተመለከተ ዮሴፍ ትልቅ በደል የደረሰበት ነገር ግን ለራሱ ብቻ ሳይሆን ለቤተሰቡ እና ለሀገሩ

ሰዎች ጥቅም ላይ ለዋለ ሰው ጥሩ ምሳሌ ነው፤ፍፃሜው ግን በመልካም /በታደሰ/ ሁኔታ የተጠናቀቀ ነበር፡፡ በሩት መጽሐፍ ውስጥም ኑኃሚን ወደ ሞዓብ ሄዳ ባሏንና ሁለት ልጆቿን አጥታለች። በኋላም ምራቷን ይዛ ወደ ቤተልሔም ተመለሰች እና ቦዔዝን አገኘች፣ ከዚያም የኢየሱስ ክርስቶስ ከቀደሙ አባቶች መካከል የሆነውን የልጅ ልጅ አገኘች። ።ብዙ ምሳሌና ማሳያ የሚሆኑ እግዚአብሔር ከመከራቸው የታደጋቸው የብዙ ሰዎችን ምሳሌዎች እናገኛለን።

**<u>ማስታወሻ ፡</u>** ይህን የህይወት መርህ በትክክል ማወቅ እጅግ አስፈላጊ ነው። በዚህ ህይወት የተሰናበቱትን ወገኖቻችንን ወደ እኛ መመለስ አንችልም እናም ቁሳዊ ነገሮችንም ወደ ነበሩበት ቦታ መመለስ አንችል ይሆናል ፣ ልባችን ግን የሚያገኘው ነገር ይኖራል ፣ ። ትኩረታችን በሰማያዊው ሀብት ማንም ሊሰርቀው በማይችለው ላይ ነው ይህ ‹‹የብልፅግና ወንጌል›› ተብሎ የሚጠራው ዓይነት እንደሚያስተምረው እግዚአብሔር ሁሉም ሰው ከመከራ ነጻ መሆንና ሀብታም ብሎ በምድራዊ ቁሳቁስ ላይ ትኩረት ከሚያደርገው ትምህርት ተቃራኒ የሆነና ይህን የማንለማመድ ከሆነ የእኛ ውድቀት ነው ብሎ ከሚናገረው ትምህርት የተለየ ነው።



ነገሮች ከአሁን በኋላ እንደነበሩት
ጥሩ እንደማይሆኑ እናስባለን እና
ያለ ክርስቶስ፣ ይህ ነው የሚሆነው።
ከዚያም ቀሪ ሕይወታችንን
ባጣነው ነገር በማዘን እናሳልፋለን።

እኛ በኪሳራ ህይወት
ድምዳሜ ላይ

ነገሮች ወደ
መልካም እየተለወጡ ሲመጡ

እግዚአብሔር ሁሉንም የህይወትን አሳዛኝ ሁኔታዎች ማዳን ይችላል። የዮሐንስ ወንጌልን 10፡10 ስንመለከት፣ “ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም፤ እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ።” ቀጣይነት ባለው ኪሳራ ከመሰቃየት፣ በጣም ውድ የሆነ እና ዘላለማዊ ትርጉም ያለው ነገር አግኝተን ከህይወት ስቃይ መውጣት እንችላለን! እግዚአብሔር ለበለጠ ጥቅም ሊጠቀምበት የማይችለው ምንም መጥፎ ነገር የለም። ይህ ድንቅ ዜና ነው! “በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን” (ሮሜ 8፡37) ለእኛ ከሆነው በላይ አስደናቂ ነገር የለም ።

የእኛ ደካማ ጎን ወይም የእኛ የመጎዳት ነገር ምን የሚጠቅም ነገር አለው? እግዚአብሔር ነገሮችን ቀይሮ ወደ ጠንካራ ጎን መለወጥ ይችላል። ይህም የእግዚአብሔር የጦር ዕቃ የሆነው ምስክርነታችን ነው። ይህ እርሱ ወደ መከራችን እንዲመጣ ከጋበዝነው ጊዜ ጀምሮ ይህ ነገር መሆን ይጀምራል። እርሱ በህይወታችን እንዲሠራ ያደርጋል (ሮሜ 8፡28) ።

## 5) **መስቀሉ የልውውጥ ሥፍራ ነው።**

እኛ በመስቀሉ ላይ በቀላሉ ህመማችንን ቁጣችንን ሀጢያታችንን እና ሌሎችንም በቀላሉ በመስቀሉ ላይ መተው አንችልም። ኢየሱስ አንድን ነገር በልውውጥ ለእኛ ሊሰጠን እንዲችል ዕዳችንን በሙሉ ከፍሎልናል። በኃጢአታችን ፈንታ የራሱን ፅድቅ ሰጠን፤ በህመማችን ፈንታ የራሱን ደስታ ሰጠን፣ በመገፋታችን ፈንታ የራሱን ተቀባይነትን ሰጠን፤ በፍርሃታችን ፈንታ

ሰላምን ሰጠን፣ በተስፋ መቁረጥ ፈንታ ተስፋን ሰጠን በቁጣችን ፈንታ የይቅርታን ኃይል እና ሌሎች ነገርንም ሰጠን።

## ከግል ህይወት ጋር ማዛመድ

- ከበደለኝነት ስሜትና ከህመም ጋር ትግል ያደረግህበት የመጨረሻ ጊዜ መቼ ነው? ኢየሱስ ኃጢአትህን የሚሸክምና ህመምህን ጭምር የተሸከመ መሆኑን በትክክል የገባህ መቼ ነው?
- ለኢየሱስ ልትሰጠው የምትፈልገው በልብህ ውስጥ የተሸከምከው ነገር አለን?
- ህመምህን በእግዚአብሔር ልብ ማፍሰስ (መጣል) ምን ሊረዳህ ይችላል? ይህን እንዳታደርግ ምን ሊያግድህ ይችላል?
- እርሱን ወደ መከራህ ጋብዘው እርሱ ሊታደግህ ይችላል?
- ኢየሱስ የኃጢአታችን ሸክም እንደተሸከመ ሁሉ የህመማችን ሸክም ተሸክሟል።
- ህመማችንን ወደ ኢየሱስ በእምነት ማስተላለፍ ልባችንን የሚያሳርፍና ነፃ የሚያወጣ ነው።
- ኢየሱስ ከመከራችን ሊታደገን የሚችለውን ሁሉ አድርጓል።

## ቁልፍ ሀሳቦች

- ኢየሱስ በልውውጥ ሊሰጥህ ስለሚፈልገው ነገር ምን ታስባለህ?

# ትምህርት አሥር

## የመስቀሉ ሥራ

**ሰዎች ተጨባጭ በሆነ መንገድ ህመማቸውን ወደ መስቀሉ እንዲወሰዱ እድሉን መፍጠር፡፡**

ኢየሱስ የኃጢአታችንና የህመማችን ሸክም እንደተሸከመልን የሚናገር ትምህርት መቀበል አንዱ ነገር ነው፡፡ ሌላው ጉዳይ ደግሞ ይህንን እውነት ወደ ተግባር በመለወጥ ለኢየሱስ ኃጢአታችንንና ህመማችንን በእውነት መስጠት አለብን፡፡ እኛ በዚህ የህይወት መርሆዎች የምንመላለስ ከሆነ ሁልጊዜ የሚረዳን መንፈሳዊ መርሆ በህይወታችን መሥራት ይጀምራል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ኢየሱስ ሰዎች አንድን እውነት መጨበጥ ይችሉ እንደሆነ ጥያቄዎችን ይጠይቃቸው ነበር፡፡ በዓይነ ስውር ሰው ዓይን ላይ ጭቃ በመቀባትና ወደ ሰሊሆም መጠመቂያ ሄዶ ዓይኑን እንዲታጠብ ነገረው (ዩሐ 9፡1-7)፡፡ በጭቃው ወይም በመጠመቂያ ውስጥ ምን ዓይነት የተለየ ነገር የለም፡፡ ነገር ግን ለዚህ ሰው አንድ ነገር በማድረግ ፈውሱን ለመቀበል የሚችልበት ሥፍራ ሲሄድ እምነቱ እንዲያድግ እንደሚረዳው ያውቃል፡፡ ንዕማን በዮርዳኖስ ወንዝ ሰባት ጊዜ እንዲታጠብ ተነገረው (2ኛ ነገስ 5፡10)፡፡ የልብ ስብራታችንን ፈውስ ለመቀበል ሊረዳን የሚችል ተግባራዊ እንቅስቃሴ እንመለከታለን፡፡

የራሳችንን የልብ ስብራት አውቀን ለማስተናገድ ሊረዳን እንዲችል የከፋውን መከራችንንና ጉድለቶቻችንን ዘርዝረን መጻፍ አለብን፡፡ ይህንን መከራንና ጉድለቶቻችንን ለአንድ ሰው ማካፈል አለብን (በተለይ የምንነግራቸው መከራ ካመጣብን ብሔር የመጣብን ከሆነ) ለፈውስ እጅግ በጣም መልካም ሊሆን ይችላል፡፡ ከሌላኛው ወገን የርህራሄ ህይወት

ከመጣልን ማለት ነው፤ ከዚህ ቀደም በነበረው ምዕራፍ እንደተገለጠው ህመማችንን በኢየሱስ ፊት ማፍሰስ ወደ ፈውስ ለመምጣት ሌላኛው ወሳኝ እርምጃ ነው። ኢየሱስ በእኛ ላይ ያለውን ሸክማችንን በእኛ ፈንታ ከእኛ ላይ አንስቶ ሊሸከምልን የሚጠብቀን እንደሆነ የምናምን ከሆነ ማለት ነው። በወረቀት ላይ የፃፍናቸውን መከራዎቻችንንና ጉድለቶቻችንን በመስቀል ላይ በሚስማር ጠርቀን ኢየሱስ በመስቀል ላይ በእውነት ያደረገልን እውነት የበለጠ እውን ይሆንልናል። በተጨማሪም ሁሉንም ነገራችንን ለእርሱ የርህራሄ እጅ ላይ አደራ በመስጠት ይህን ከእኛ ላይ እንዲሄድ ሊረዳን ይችላል (ቆላ. 2፡14 ተመልከት)። ይህን ወረቀቶቹን ከመስቀል ላይ በማስወገድ በእሳት ማቃጠል በተጨማሪም በልባችን ውስጥ ማተም አለብን።

ይህን በምናደርግበት ጊዜ የሚቀረው የአመድ ክምር ነው። አሁን እንግዲህ እግዚአብሔር እንዴት ከመከራ እንደሚታደገን አይተናልና በተጨማሪ ኢሳ 61 የምንናገረው እውነት ማጣቀሻ ነው። በቁጥር 3 ላይ ያለው ትንቢታዊ አዋጅ /መልዕክት/ ኢየሱስ በአመድ ፈንታ ውበት ሊሰጠን ይፈልጋል። በአንዳንድ የዓለም ክፍሎች መሬቱ በእለት ከተቃጠሉ በኋላ እኛ አበባዎች መብቀል ይጀምራሉ። የአበባ ዘር ለብዙ ዓመታት ከምድር በታች ተቀብረው ሊቀሩ ይችላሉ። ነገር ግን ቁጥቋጦዎች በእሳት ሲቃጠሉ የእለቱ ሙቀት የአበባዎች የዘር ቅንጣቶች ከቅርፊታቸው ተሰንጥቀው ሊከፈቱ ምክንያት ያገኛሉ። ከዚያም ቀይ አበባዎች ማበብ ይጀምራሉ። ከዚያም *«የእሳት አበባዎች»* ተብለው ይጠራሉ። ይህ እግዚአብሔር በህይወታችን ሊሠራ ለሚችለው ውብ ምሳሌ ይሆናሉ። ሁሉን መከራዎቻችን በእርሱ እጅ ላይ የምንሰጠው ከሆነ እርሱ ካለንበት አሳዛኝ የህይወታችን ገጽታዎች አመድ ውስጥ ውበት ያለውን ነገር አውጥቶ ሊሰጠን ይችላል።

ከላይ ያለው ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች በብዙ ሀገራት እና ሀጉሮች ውስጥ ባሉ የህዝብ ወገኖች የመስቀሉ ሥራ ድራማ/ተብሎ ይታወቃል። ይህም ኢየሱስ ህመማችንን በመስቀል ላይ ተሸክሞ የሠራው ሥራ ከሚለው እምነታችን የሚነሳ ተግባራዊ ሥራ ነው። ብዙውን ጊዜ ይህ ኢየሱስ ህመማችንን እንደተሸከመ በትክክል በእርሱ ለመታመን የምንወስደው የእምነት እርምጃ ነው፣ በውጤቱም የፈውስን ሂደት ለመጀመር የሚረዳን ነው። ይህ ደግሞ የሌሎችን ሰዎች ልብና መከራ ለመስማት መልካም አጋጣሚን የሚፈጥር ነው። ይህም አስቀድሞ

በጠላትነት በሚተያዩ ሰዎች መካከል የርህራሄ ልብ እንዲፈስስ የሚያስችል ነው። በመጨረሻም እግዚአብሔር እኛ ካለንበት መከራ ውስጥ አንድን ውብ ነገር እንዲያወጣ የሚያስችል አዲስ ተስፋን የሚሰጥ ነው።

በመስቀሉ በኩል ነጻ መውጣትና ነጻነትን መቀናጀት አስደናቂ ሁኔታ ነው። ይህም ለብዙዎች ለመጀመሪያ ጊዜ የጎዱአቸውን ሰዎች ይቅር ለማለት እንዲችሉ የሚያስችል ነው። በሚቀጥለው ምዕራፍ ስለዚህ ጉዳይ የበለጠ እንመለከታለን።

ምንም እንኳን ኢየሱስ የህመማችን ተሸካሚ እንደሆነ በመስቀሉ ሥራ ን ላይ ዋና ትኩረት ብናደርግም፤ ብዙዎች ለኃጢአታቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ይቅርታ የሚያገኙበት ነው፤ ይህም አስቀድመን የምናውቅ ከሆነ ማለት ነው። ይህ ደግሞ የመዳናችው መንገድ ይሆንላቸዋል። ብዙዎች የአካላዊ ፈውስ ልምምድ እንዲኖራቸው የልባቸውን ሸክም በእግዚአብሔር ልብ ላይ ማፍሰስ አለባቸው።

## ከራስ ህይወት ጋር ማዛመድ

- ከላይ ያለውን አንብበህ በራስህ ወደ ተግባራዊ ልምምድ የማታስገባው ከሆነ የዚህን መጽሐፍ እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆነውን ዓላማ ።ከላይ ያለውን አንብበህ እና ራስህ በተግባር ላይ ካላዋልከው, የዚህን መጽሐፍ በጣም አስፈላጊ የሆነውን አንዱን ዓላማ ታጣዋለህ።
- በመጀመሪያ በራስዎ፣ ከቤተሰብዎ ጋር፣ ወይም ከአንድ ወይም ከሁለት የቅርብ ጓደኞችዎ ጋር ማድረግን ይለማመዱ።
- እና ልንመክርህ የምንወደው ነገር ቢኖር ሌላውን ሰው ለመረዳት ከመፈለግህ በፊት በመጀመሪያ በራስህ ህይወት ላይ ሥራ ሥራበት፤ ለዚህ ደግሞ ወረቀት ብዕር /እስክሪፕቶ/ አነሰ ያለ የመስቀል (2 አነስተኛ ቅርንጫፍ ይበቃሉ) መዶሻ ወይም ትልቅ ድንጋይ አንድ ወይም ሁለት ሚስማሮችና ክብሪት ያስፈልጋል።
- አስቀድመህ መንፈስ ቅዱስ በዚህ ጉዳይ ላይ እንዲነካልህ የሚገባውን ሁሉንም ነገሮች ወደ አዕምሮህ እንዲያመጣ ለምነው። በእርሱ ምሪት ውስጥ በልብህ ውስጥ ያሉትን

ህመሞችንና ጉዳቶችህን ሁሉ በወረቀት ላይ ፃፋቸው ወይም በግልህ ሌባው በማንኛውም መንገድ የሰረቀብህን ነገሮች ሁሉ ፃፍ። ርዕሶችን ብቻ መጻፍ በቂ ነው። ሁሉን ዝርዝር ታሪክ መፃፍ አያስፈልግህም።

- ይህን አንተ /አንቺ/ ለብቻ/ሽ/ ለራስህ አድርጊው። ስለሁሉም ነገር ለኢየሱስ ንገረውና በገጽታህ ላይ የሚገለጠውን ማንኛውንም ስሜት አታግደው /አትሸፍነው/። ከሌላ ሰው ጋር የምታደርገው ከሆነ እርስ በርስ ያላችሁበትን ለማካፈል ጊዜ መውሰድና እርስ በርሳችሁ ፀልዩ።
- የልብህን ህመም በእግዚአብሔር ልብ ላይ አፍስሰው ከዚያመ ወረቀት ላይ የፃፍከውን በመስቀል ላይ ቸንክረው መስቀሉን ተሸክመህ ወደ ውጪ ውጣና ከመስቀሉ ላይ አንስተህ ወረቀቶቹን አቃጥላቸው።
- ለአንተ መስዋዕት ስለሆነልህ እግዚአብሔርን ጊዜ ወስደህ አመስግነው።
- በመጨረሻም በህመምህ ፈንታ በልውውጥ ለአንተ ሊሰጥህ ስለሚፈልገው ነገር እግዚአብሔርን በፀሎት ጠይቀው። ከዚያም የተወሰነ ጊዜ ወስደህ እግዚአብሔር በመከራዎች መካከል እያደረገ ስላለው መልካም ነገሮች ሁሉ መዝግብ ወይም እርሱ ስላሰማህ ድሎች ሁሉ አመስግነው።
- ስለፃፍካቸው ነገሮች ሁሉ እግዚአብሔር ታድጎህ ስለሚሰጥህ ኃይል ተስፋ ምሳሌ እንዲሆን በአመድ ላይ የመልካም ምኞት መግለጫ አበባ ማኖር ትችላለህ። ከዚያም አንድ ውበት ያለው ነገር ሊወጣ እንደሚችል ምኞትህን ግለጥ።

## ቁልፍ ሀሳቦች

- የራሳችንን ህመም የተሞላ ችግሮቻችንን ለሌሎች ማካፈልና ይህ ህመም እንዲመጣብን ምክንያት የሆነብንን ወገኖች በርህራሄ ልብ ማየት መቻል ለመፈወስ ዋና ምንጭ ነው።
- ህመማችን ወደ ኢየሱስ ማስተላለፍ የመስቀሉ ሥራ ንድፍ ሙከራ ዋናው አስፈላጊ ክፍል ሲሆን ይህ ምሳሌያዊ ልምምድ ለመፈወሳችን ሊረዳን የሚችል ተግባር ነው።

- እግዚአብሔር ከመከራችን ውስጥ መልካም ነገር ሊያወጣ እንደሚችል መመልከት ለወደፊቱ ተስፋችን የሚሰጠን ነው።

# ክፍል ሶስት

# ጣሪያውን መክደን

## ሌሎችን ይቅር ማለት ምን ማለት እንደሆነ መረዳት

ለብዙዎች የበደሉአቸውን ይቅር ማለት ትልቅ /ከባድ/ እንቅፋት ነው። በተለይም በእነርሱ ላይ በደል የሠራውን ሰው ይቅርታ መጠየቅ እጅግ ከባድ ነው። ይህ ምንም አይደለም ይላሉ። በዚህም ምክንያት ይቅርታ ማድረግ ምን ማለት እንደሆነና ምን ማለት እንዳልሆነ በትክክል ሊገባን ይገባል። ይቅርታ ስለማድረግ በተመለከተ ያለው የተለያዩ ትክክል ያልሆኑ አስተሳሰቦችን ማስወገድ በጣም ጠቃሚ ጉዳይ ነው።

## ሰዎች በቀላሉ ይቅርታ በማድረግ ፈውሳቸውን ማግኘት እንዲችሉ መርዳት

በህይወታችን በጥናት የደረስንበት ነገር ቢኖር ህመማችንን ወደ መስቀሉ መውሰድ እጅግ ወሳኝ ጉዳይ እንደሆነ አሰቀድመን አይተናል። ይህም ልባችን ይቅርታን ለማድረግ እንዲችል ነጻ የሚያወጣን ነገር ነው፤ምክንያቱም ልባችን እስካሁን ድረስ በህመም የተሞላ ከሆነ ሌሎችን ይቅር ለማለት በጣም አስቸጋሪ ነው። ሰዎች እንዲፈውሱ ከመርዳት በፊት ሰዎች የራሳቸው የውስጥ ጉዳት መፈወስ እንዳለበት እናምናለን። መስቀሉ ይቅርታ ማድረግ እጅግ

ዋጋ የሚያስከፍል መሆኑን ያሳየናል። ነገር ግን ይቅርታ አለማድረግ የሚያስከፍለው ዋጋ እጅግ የበለጠ ዋጋ እንደሚያስከፍል ማወቅ ጠቃሚ ነው።

**ንስሀ መግባት**

መስቀሉ በተጨማሪ ወደ ንስሀ ህይወት የሚመራን ነው። ይህም የእግዚአብሔር የከበረው ስጦታ ወደ ነፃነትና ወደ ደስታ ህይወት የሚያመጣን ነው። ንስሀ መግባት ማለት የአስተሳሰብና የልብ ለውጥ ሲሆን ይህም ወደ ተለወጠ ባህርያት የሚመራን ነው። የግልና የጋራ ንስሀ መግባት ሁለቱም በጣም አስፈላጊ የሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆዎች ናቸው። በፈረሰው በኩል የሚቆም /ክፍተቱን የሚዘጋ/ ነው።

**በመካከል መቆም**

ክፍተትን የሚዘጋ ማለት የራሳችንን ብሔር/ወገን ኃጢአት የሚናዘዝና ይቅርታን መጠየቅ ማለት እጅግ ወሳኝ ከሆኑ ነገሮች አንዱ ሆኖ የተጎዱ ሰዎች ፈውስን እነዲያገኙ መርዳትና እርቀ ሰላምን ማስኬድ ማለት ይህ ከህይወት ዘይቤ ለውጥ ጋር አብሮ መቀናጀት የሚገባውና በፈረሰው በኩል መቆምን የሚያሳይ ነው።




# ትምህርት አስራ አንድ

## የጎዱንን ይቅር ስለማለት /ይቅርታ ማድረግ/

**እውነተኛውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይቅርታ ማድረግና ይቅርታ አለማድረግ የሚያስከትሉትን መዘዞች ማወቅ።**

በቤተክርስቲያን ውስጥ ሌሎችን ይቅር ስለማለት ትምህርት በሚሰጥበት ጊዜ ምናልባትም በቤተክርስቲያን ውስጥ ባሉ ሰዎችና በውጪ ባሉ ሰዎች ዘንድ አንዱ አጨቃጫቂና ሰዎች በተሳሳተ መንገድ የሚረዱት ርዕሰ ጉዳይ ሊሆን ይችላል፡፡ የሰው ልብ ሌሎችን በቀላሉ ይቅር ለማለት አይፈልግም፡፡ ይቅርታ ለማድረግ እንሞክርና ነገር ግን እንደገና ተመልሶ ተመሳሰይ ህመም የምናተርፍበት ጊዜ አለ፡፡

ምንም እንኳን ከዚህ ትምህርት ጋር በውጪያዊ /በአንደበት/ የምንስማማ ቢሆንም ብዙውን ጊዜ በልባችን ውስጥ ከተደበቀ ያልተፈወሰ ስሜት እንታገላለን፡፡ ይህም አመፀኛና እግዚአብሔር ይቅርታ እንዲያደርግለት ለመለመን እንኳን ክፉ ይሆናል፡፡ የተጎዳን መሆናችን ምንም ክፋት የለውምን? ይቅርታን መጠየቅ የበለጠ የተጎዳን ይመስለናል፡፡ ብዙውን ጊዜ የጎዳንን ሰው ይቅር ማለት ከእኛ አንድ ነገር ወስዶ መልሶ እኛን የማጥቃት ያህል ነው ብለን እናስባለን፡፡ አሁንም እውነተኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይቅርታዎች ለእኛ ጥቅም የሚሠሩ ናቸው፡፡

እግዚአብሔር እጅግ የሚራራና ምህረትን የተሞላ አምላክ መሆኑን፣ ትክክለኛ መሆኑን ማወቅ የግድ ነው፡፡ ይቅርታ እንድናደርግ ስንጠየቅ በእግዚአብሔር በኩል አመጸኛ መሆን ማለት አይደለም፡፡ ይቅርታ እንድናደርግ እግዚአብሔር በሚጠይቀን ጊዜ ማድረግ ትክክለኛ ዕውቀት መሆኑ ወሳኝነት ያለው ነው፡፡

### 1. ሌሎችን ይቅር ለማለት አስቀድመን ይቅርታ ማድረግ ምን ማለት እንዳልሆነ ማየት አለብን፡፡

ይቅርታ ማድረግ ማለት ምንም ችግር የለውም ማለት አይደለም ወይም ከኃጢአት ጋር መስማማት ማለት አይደለም፡፡ ይቅርታ እንድናደርግ ስንጠየቅ እኛ በቀላሉ ሊሰማን ይችላል፤ እግዚአብሔር ህመማችንን ወይም ኪሳራችንን እንደትልቅ ነገር ይወስደዋል ማለት አይደለም፡፡ እርሱ በእኛ ላይ በደረሰው ነገር እንደተስማማ የሚመስል ስሜት ጭምር ሊሰማን ይችላል፤ ነገር ግን ይህ እውነት አይደለም፡፡ ኃጢአት በጣም አደገኛ ነገር ነው፤ ይህ የእግዚአብሔርን ፍጥረት ሙሉ በሙሉ የሚቃወም ነው፡፡ ይህ የተፈጥሮን የርስ በርስ መስተጋብር የሚያጠፋና የሚያፈርስ ነው፡፡ ለእግዚአብሔር ሁሉም የኃጢአት ጉዳይ ላይ ትኩረት ያደርጋል፤ ምክንያቱም

ኃጢአት አጥፊ ስለሆነ ነው። እግዚአብሔር ስህተትን ትክክል ነው ለማለት ምንም ነገር አይናገርም። አንድ ነገር ሲደረግ ስህተት ከሆነ ያ ነገር አሁንም ድረስ ስህተት ነውና ወደፊትም ከአንድ ሺህ ዓመታትም በኋላ ስህተት ነው። ኃጢአት መቼም ቢሆን ኃጢአት ከመሆን ቀርቶ አያውቅም። ስለዚህ እግዚአብሔር እኛ ያደረግነውን ስህተት ችግር የለውም ያለበት አንድም ጊዜ የለም። ይቅርታ ማድረግ ኃጢአትን ይለውጠዋል ማለት አይደለም።

ይቅርታ ማድረግ ምን ማለት እንደሆነ ልንማርበት የምንችልበት ሥፍራ አንድ ብቸኛ ሥፍራ ነው ያለው፤ ይህ ብቸኛው አስተማማኝ ምሳሌ እግዚአብሔር እንዴት ይቅር እንዳለን ነው። እግዚአብሔር ኃጢአታችን ይቅር ሲለን ምን ዓይነት ቅሬታ የለውም እርሱ ኃጢአተኛውን ዓለም በንቀት ዓይን አይመለከተውም እናም እኛ በቀላሉ ሁሉን ይቅር ብለን ሁሉንም እናሸንፈዋለን። ይህም በእውነት ምንም ችግር የማያመጣ ነገር ነውና አሁን ወዳጅነታችንን እንቀጥል›› አይልም።

አንዳንድ ሰው የይቅርታን ዋጋ ይከፍላል። አንዳንድ ሰው ለኃጢአትና ለሚያመጣቸው መዘዞቹ ኃላፊነቱን ይወስዳል። ይህ ኢየሱስ በመስቀል ላይ በትክክል ያደረገው ነገር ነው። እርሱ ለዓለም ሁሉ ኃጢአት ሥርየት አድርጓል። ካለመስቀሉ እግዚአብሔርን እኛን ይቅር ሊለን አይችልም። ይህም የሚነግረን ነገር በዓለም ላይ በጣም ዋጋ የሚያስከፍል ነገር ቢኖር ይቅር ማለት ነው። በተጨማሪም እግዚአብሔር ኃጢአትን ማንኛውም የግል ኃጢአትንም ይሁን ወይም እኛን የሚጎዳ ወንጀልም ቢሆን እንዴት በትኩረት እንደሚመለከተው ይነግረናል። እግዚአብሔር ሁሉንም ኃጢአቶች ልጁ ለእነዚህ ኃጢአቶች ስለሞተ በትኩረት ይመለከተዋል። እርሱ በቀላሉ ይህን ጉዳይ እንድንተወው አይጠይቀንም። ይህን በትኩረት ከአዕምሮአችን እንድናወጣውና ምንም እንዳልተከናወነ እርምጃ እንድንወስድበት አይጠይቀንም። ይልቅስ ወደ መስቀሉ እንድንወስደውና በጣም በተለየ ሁኔታ እንድንወስደው ይጠይቀናል።

- **ይቅርታ ማድረግ ማለት የተሰማንን የቁጣ የሀዘንና ተመሳሳይ የሆኑትን ስሜቶቻችንን መካድ አይደለም።**

ይቅርታ ስናደርግ ህመማችንን እንዳለ መቀበል አለብን፡፡ ለጎዱን ይቅርታ ማድረግ ያደረጉትን ነገር በደልንና በደሉ ያመጣቸውን መዘዞች ሁሉ በትክክል ተለይቶ መታወቅ ይገባል፡፡

- **ይቅርታ ማድረግ ማለት መርሳት ማለት አይደለም ወይም ለማስታወስ አለመቻል/አለማስተዋል/ ማለት አይደለም፡፡** ሰዎች እኛን በመጉዳት በጣም ኢ-ፍትሓዊ ጉዳት ባደረሱብን ጊዜ እንዴት አድርገን ይቅር ልንላቸው እንችላለን፤ በተለይም ዘመዶቻችን ተገድለውብን ከሆነስ? ምንም እንኳን ይቅር ብንላቸውም አሁንም እናስበዋለን። ሁሉንም ነገር ለኢየሱስ መስጠትና እርሱ በእኛ ፈንታ ሁሉንም ይሸከምልናል፡፡
- **ይቅርታ ማድረግ ከሀገሪቱ የፍትህ ሥርዓት ጋር አለመተባበርና መቃወም ማለት አይደለም፡፡**

  አንዳንድ ሰዎች ይቅርታ ማድረግና ፍትህ አብሮ ሊሄድ አይችሉም ብለው ያስባሉ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ሁለቱንም ያስተምራል (ሮሜ 12፡17-13፡5፣ ጳውሎስ እንደጻፈው በመጀመሪያው ደብዳቤ ላይ ምንም የምዕራፍ ክፍፍል አልነበረም)።ማህበረሰብን ለመጠበቅ ሲባል በሁሉም ሀገራት የፍርድ ቤት ሥርዓት (የፍትህ ሥርዓት) መኖር የእግዚአብሔር ሀሳብ /ዕቅድ/ ነበር ፡ ነገር ግን የፍትህ ሥርዓቶች ትክክለኛ /ፍትሀዊ/ ይሆኑ ዘንድ ልንፀልይላቸው ይገባል፡፡ በእግዚአብሔር ፊት ንስሀ መግባት ፣ወንጀለኛው በህግ አግባብ መቀጣት የለበትም ማለት አይደለም፡፡ እግዚአብሔር የሚለን ‹‹አስተውል በራስህ እጅ በቀልን በመበቀል ፍትህን ለማምጣት አትሞክር ይልቅ ልትባርካቸው ፈልግ እንጂ ነው (ሮሜ 12፡19-21)፡፡

- **ይቅርታ ማድረግ ማለት ነገሮች እንዳይሠሩ ማድረግ ማለት አይደለም፡፡**

በቤተክርስቲያን አሠራር መሠረት አንድ የጎዳንን ሰው እንድንፈልግና ከእነርሱ ጋር ያለን የተበላሸ ግንኙነት ካልታደሰ በዚህ ላይ መሥራት እንዳለብን እንመክራለን። በማቴ 18፡ 15-17 ኢየሱስ እንዲህ አለ *«ወንድምህ ሲበድልህ ወደ እርሱ ሄደህ ስህተቱን አሳየው /ንገረው/፡፡ ኢየሱስም «በቀላሉ ይቅር በለው»* አላለም፡፡ ምክንያቱም እርሱ ወንድማችንን ገንዘባችንን

ለማድረግ እንድንጥር ይፈልጋል። ኢየሱስ በቤተክርስቲያን ውስጥ ለሰው ግንኙነት በከፍተኛ ደረጃ ዋጋ ያለው እንዲሆን አድርጓል። እርሱ ወደ ወንድማችን ሄደን በምህረት መንፈስ ግንኙነታችንን እንድናድስ ይፈልጋል።

እርቀ ሰላም ለኢየሱስ እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። ይቅርታ ማድረግ በአንድ አቅጣጫ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን እርቅ በሁለት አቅጣጫ የሚሆን ግንኙነት ነው። የበደለን ሰው ንስሀ ካልገባ በቤተክርስቲያን አሠራር የበለጠ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል። የቤተክርስቲያንን ንፅህና ለመጠበቅ ሲባል ንስሀ ያልተገባበት ኃጢአት ምን ዓይነት ሥፍራ መስጠት አይገባም። ምክንያቱም *«ጥቂት እርሾ ሊጡን ሁሉ እንዲያቦካ አታውቁምን›* (1ኛ ቆሮ 5፡6) በከፋ ኃጢአት በዝምታ የሚያልፉትን (ኃጢአት የሚሠሩትን) ከቤተክርስቲያን ማስወገድ ያስፈልጋል (1ኛ ቆሮ 5፡ 12-13) ንስሀ ሊገቡ ለሚችሉ ከዚያ ህይወታቸው ይታደሳል (2ኛ ቆሮ 2፡6-8፣ ገላ 6፡1)። የቤተክርስቲያን ተግባር በጣም አስፈላጊ ነው።

## 2. እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ይቅርታ ምን ይላል?

- ***ለበደሉን ሰዎች የማይገባቸውን የልግስና ስጦታ መስጠት***

  እውነተኛ የሆነ ይቅርታ ማድረግ ለማይገባው ለበደለን ሰው ስጦታ በልግስና መስጠት ይገባል። እግዚአብሔር ለሁሉም ኃጢአታችን በይቅርታ የሰጠውንና ከሁሉም ዓመፃችን ያነፃንን አስደናቂ ስጦታ አስብ።
- ***በቀልን ለማድረግ ያለንን መብት መጣል***

  ከብሉይ ኪዳን ሥርዓት ሥር እያለን የተወሰነ በቀል የተፈቀደ ነበር። ነገር ግን ኢየሱስ የተሻለውን መንገድ አሳይቶናል። (ማቴ 5፡ 38፣ 48) ።
- ***ከፍርድ ይልቅ ምህረትን መምረጥ***

  ራሳችንን ከሳሽ ከሆነውና ሁልጊዜ በቀልን ከሚፈልገው ሰይጣን ጋር ከመወዳጀት ፈንታ እኛን ለማዳን እንጂ ለመፍረድ ወደ ዓለም ካልመጣው ከኢየሱስ ጋር ለመወዳጀት መምረጥ አለብን።

- ***አንዳንድ ነገሮች ዋጋ ያስከፍላሉ ነገር ግን ይቅርታ አለማድረግ ግን የበለጠ ዋጋ ያስከፍላል።***

  የበደለንን ሰው ይቅር ማለት በእርግጥ እጅግ ዋጋ ያስከፍለናል፤ ነገር ግን ይቅር የማንል ከሆነ ግን እኛን የሚጎዳ ነገር በህይወታችን ይሆንብናል። ይህ የመጨረሻውን ትልቅ ዋጋ የሚያስከፍለን ይሆናል።

(3) **ይቅርታ ያለማድረግ አደገኝነት**

***እግዚአብሔር የበደሉንን ይቅር እንድንል የሚጠይቀን ለምንድን ነው? ይቅር ያለማለት ያለው ችግር ምንድን ነው?***

***ሀ) ይቅር አለማለት ምህረትን ለመቀበል የምንችልበትን ጸጋ እንዳናገኝ ይከለክለናል ።***

የእኛ የልብ መራርነትና ጥላቻ የእግዚአብሔርን ምህረት ለመቀበል እንዳንችል የሚያስረን ይሆናል። በማቴ. 6፡15 ላይ እግዚአብሔር የበቀል አምላክ እንደሆነ ያሳያልን? ፈፅሞ አይደለም! ኢየሱስ ለኃጢአታችን ዋጋ በመክፈል በመስቀል ላይ ደሙን ስላፈሰሰ ለዚህ ኃጢአተኛው ዓለም ነጻ የኃጢአት ይቅርታ ስጦታ ሰጥቶናል። ችግሩ ያለው ከኢየሱስ አቅጣጫ አይደለም። የእኛ የእርሱን ይቅርታ ለማግኘት አቅም የምናገኘው በንስሀ ህይወታችን ላይ በመመሥረት ነው። ይህም ከጥላቻ ኃጢአትና ይቅርታ ካለማድረግ ኃጢአት ንስሀ መግባትን የሚያካትት ነው።

***ለ) ይቅርታ አለማድረግ ፈውስንና የነጻነት ህይወት ለመቀበል ያለን ብቃታችን ላይ እንቅፋት ይሆናል።***

እኛ ከምንጠላው ሰው ጋር ለዘላለም እንተሳሰራለን። ይህም ትልቅ ክብደት ያለውን ሸክም ከኋላው እንደሚጎትት ያህል ነው ። ወደ ሙሉ ብቃታችንና ወደ ፍፃሜአችን ለመድረስ ፈጽሞ የማንችል እንሆናለን።

‹‹ይቅርታ እስግናደርግ ድረስ፣ ከበደለን ሰው ጋር ያለን ግንኙነት ህመም ያለበት ህይወት ይሆናል፡፡ በህይወት የጠላነውና ቅር የተሰኘንበት ሰው ባየነው ጊዜ ሁሉ ሊረበሸን ይችላል፤ ምናልባትም ዓመታት ጭምር የሚወሰድ ችግር ሊሆን ይችላል፡፡ ከእኛ ጋር ያለው ቁርኝት ሙሉ በሙሉ ተቋርጦ ራሱ በጥላቻ ገመድ ከታሰርን ሕይወታችንን እያበላሸ ይቀጥላል፡፡ እኛ ደግሞ የምንጠላቸው ሰዎች ባሪያዎች እየሆንን እንቀጥላለን፣ ይቅር ስንል ግ ከዚህ ከሚያጠፋ እስራት ነፃ እንወጣለን፡፡

***ሐ) ይቅርታ አለማድረግ መስቀሉን ሙሉ በሙሉ ከማወቅ እንቅፋት ይሆንብናል፡፡***

ኢየሱስ የሞተው ከኃጢአታችን ሊያነጻን ነው፤ እንዲያውም በአዕምሮአችን ከምንገምተው በላይ ከሆነ ከከፋ ኃጢአት ሁሉ ያነፃናል፡፡ ከእርሱ ሞት የተነሳ ሁሉም የሰው ልጆች በትክክል በደለኞች ናቸው፡፡ ምክንያቱም እርሱ ለሁሉም ኃጢአታችን ቅጣት ለመቀበል በመከራ ሞተ፤ ኢየሱስ ይቅር ሊለን ምን ያህል ዋጋ እንደከፈለ ብንመለከት እኛ እርስ በርሳችን /እያንዳንዳችን/ ይቅር ለመባባል ወደ ኃላ አንልም ነበር፤ አለበለዚያ ወንጌል ፈጽሞ በትክክል አልገባንም ማለት ነው፡፡

***መ) ይቅር አለማለት በህይወታችን ለሰይጣን የእግር ማስገቢያ እድል መስጠት ነው፡፡***

/ኤፌ. 4፡ 26-27፣ 2ኛ ቆሮ 2፡7-11) ሌላው ላይ የምንፈርድ ከሆንን እኛ ተወቃሽ እንሆናለን ስለዚህ የሚፈረድብን ይሆናል፡፡ (ማቴ 7፡1-2) ፡፡

**4) የበደሉንን ሰዎች ይቅር የምንልበትን ጸጋ እንዴት እናገኛለን?**


***ህመማችንን በመቀበል መጋፈጥና መግለጥ፤ በእግዚአብሔር ልብ ላይ እንጣለውና ኢየሱስ ሁሉንም ኃላፊነት እንዲወስድ እንፍቀድለት፡፡***

ኢየሱስ ኃጢአታችንን እንደተሸከመልን ሁሉ ህመማችንንም ተሸክሞልናል የሚለውን በምዕራፍ 9 ተመልክተናል፡፡ ልባችን እስካሁን ድረስ በህመምና በቁጣ ተሞልቶ ከሆነ ይቅርታ ለማድረግ እጅግ ከባድ ይሆንብናል፡፡ እኛ ምናልባት ከልባችን ይቅርታ ለማድረግ እንሞክር ይሆናል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ከእኛ ምን እንደሚፈልግ ስለምናውቅ ፤ እንዲሁም እኛ

ምናልባት አንዳንድ ለውጦችን እናደርግ ይሆናል፤ ነገር ግን ማንኛውም ነገር ወደ ኋላ ተመልሰን ህመምንና ቁጣን መልሶ እንድናስታውስ የሚያደርግን ሁኔታ /ክስተት/ ፈጽሞ ይቅርታ እንዳላደረግን እንዲሰማን ያደርጋል ፡፡

አሁን ወደ ምስላችን ሶስተኛው ክፍል /ዙር/ መጥተናል፡፡ ይህም እኛ በነፃነት ይቅር ስንል ምን ሊሆን እንዳለበት ያሳየናል፡፡ ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም የመጣው እንዲህ ለማለት ነው ‹‹በበደለህ ሰው ፈንታ እኔ በደለኛ እንደሆንኩ ይቆጠርብኝ፣ እኔ የመጣሁት የሁሉም ነገር ነውርን በመስቀል ላይ ለመቀበል ነው»፡፡ ስለዚህ ኃጢአትችንን እና "በእኛ ላይ የተፈፀመውን በደል ለእርሱ ልንሰጠው ይገባል እና በደረስብን በደል እርሱ ሀላፊነቱን እንዲውሰድ መስጠትነው ፡፡

**የተጎዱ ሰዎች ከመፈወሳቸው**
**በፊት መጀመሪያ ህመማቸውን መግለፅ**
**አለባቸው፡፡**




ኢየሱስ በማቴ 18፡35 ከልባችን ይቅር እንድንል ነግሮናል፡፡ ነገር ግን ልባችን አሁንም ድረስ በህመም ተሞልቶ ካለ ይቅርታ ለማድረግ አንችልም፤ ይሁንም እንጂ ኢየሱስ በእውነት የህመማችንን ሸክም በመስቀል ላይ ተሸከመልንና ከጉዳታችን /ከቁስለታችን/ ለመፈወስ ቻልን፡ ፡ ከዚያም ህመማችንን ለእርሱ መስጠት እንችላለን ከዚያም ይቅርታ ለማድረግ ነፃ እንሆናለን፡፡ ይቅርታ ለማድረግ የምንፈልግ ከሆነ እንኳን ይህ በልባችን የተካሄደ አስገራሚ የተዓምራት ውጤት ነው፡፡

> **ራሳችንን እና የበደሉንን ሰዎች በፃድቅ ፈራጅ እጅ አደራ እንሰጣለን፡፡**

እውነተኛ ንስሀ መግባት እንደተከናወነ የምንመለከት ከሆነ የአንድን ሰው ይቅርታ መስማት ይቅርታ ለማድረግ ቀላል ነገር ይሆናል። ነገር ግን አንድ ሰው ምን ዓይነት ይቅርታ ካላለ ምን ይሆናል? አንድ በወንጀል ውስጥ የተሳተፈ ሰው ንስሀ ካልገባ በዚያ ሰው ላይ ምን ሊሆን ይችላል? እንዲሁም ከተኩራራስ ምን ሊያደርግበት ይችላል? በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ ይቅርታ ለማድረግ የምንችልባት ብቸኛው መንገድ ሁሉንም ነገር በሰማይ ወዳለው ፃድቅ ፈራጅ እጅ ራስን አደራ መስጠት ነው (1ጴጥ 2፡23)። ይህ ሁኔታ ኢየሱስ እንደ ሰው ያስቻለው ነገር *«አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው››* (ሉቃ 23፡34)፤ ይህን የተናገረው በመስቀል ላይ በሚስማር እየቸነከሩት እያለ ነው። እርሱ መራርነት ወደ ልቡ እንዲገባ አልፈቀደም፤ በዚህም ፈንታ በእግዚአብሔር ለመታመን ወሰነ። ይህም ኢየሱስ ከመበቀል ፈንታ ያደረገው ነገር ነው። እውነተኛውን ዳኛ መታመን እንችላለን። የበደለን ሰው ንስሀ ከገባ እርሱ ይቅርታን ያገኛል፤ ነገር ግን እርሱ ንስሀ ካልገባ ወደ ፍርድ ይሄዳል (ይፈረድበታል)፤ ይህ በዚህም ህይወት ሳለ ባይሆንም እንኳን በእርግጠኝነት በሚቀጥለው አለም ይፈረድበታል።

ሌላው ሰዎችን የምንረዳበት ጠቃሚ መንገድ ንስሐ ገብተው የማያውቁትን የሚረዳበት መንገድ ‹‹ክፍተትን መሙላት›› ወይም «የአደባባይ ንስሃ›› ይባላል። ይህንን በምዕራፍ 13 ላይ እንመለከታለን።

> **እኛ ራሳችን የእግዚአብሔር ይቅርታ ምን ያህል እንደሚያስፈልገን ማወቅ**

ምን ያህል ኃጢአተኞች እንደሆንን እና እግዚአብሔር እኛን ይቅር ለማለት ያስከፈለውን ዋጋ ማወቅ ይቅር ለማለት ቀላል ያደርገናል። ማቴዎስ 18፡21-35ን ማንበባችን ነገሮችን በእግዚአብሔር እይታ እንድናይ ይረዳናል።

ማጠቃለያ፣ ይቅርታ ማድረግ የሚሠራውም /የሚጠቅመውም/ ለእኛው ነው እንጂ እኛን የሚጎዳ ሆኖ አይደለም። እግዚአብሔር ይቅርታ እንድናደርግ ሲጠይቀን ክፉ ሆኖ አይደለም፤ ይልቅስ ምን ያህል እንደሚወደን ለማሳየት ነው።

## ከራስ ጋር ማዛመድ

- ይቅርታ ያላደረግህለት አንድ ሰው አለን?
- ይቅርታ እንዳታደርግ የሚከለክሉህ እንቅፋቶች ምንድን ናቸው?
- ንስሀ ልትገባበት የሚያስፈልግህ ቁጣና መራርነት ምንድነው?

## ቁልፍ ሀሳቦች

- እግዚአብሔር በመስቀሉ ላይ ለእኛ ያደረገው ይቅርታ የይቅርታ ማድረግ ምሳሌ ነው፡ ፡
- ይቅርታ ማድረግ ህመማችንን መጋፈጥና መግለጥን እንዲሁም ህመምን ወደ ኢየሱስ ማስተላለፍን ይጠይቃል።
- ከኢየሱስ ምሳሌ የምንማረው ነገር ጉዳያችንን ለፃድቅ ፈራጅ አደራ መስጠትን ነው።
- ይቅርታ ማድረግ ዋጋ ያስከፍላል። ይቅርታ አለማድረግ ግን የበለጠ ዋጋ ያስከፍላል።

# ትምህርት አስራ ሁለት

## ንስሀ የመግባት የለውጥ ሀይል እና ይቅርታስ ስንጠይቅ እንዴት መጠየቅ አለብን

### ንስሀ መግባት በእርቅ ውስጥ ያለው ሚና

ከዚህ ቀደም እንደተናገርነው ያለ ንስሀ መግባት እርቅ ሊመጣ አይችልም። ኃጢአትን በመናዘዝ እና ንስሀ በመግባት ወደ መስቀሉ በወሰድን ጊዜ አዲስ ጅማሬ ሊመጣ ይችላል። ንስሀ ባለበት የእግዚአብሔር ፀጋ ወዲያው ይገኛል። ንስሀ መግባት ሰፊ ርዕሰ ጉዳይ ነው፣ ነገር ግን በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ትኩረት የምንሰጠው በብሔር ግጭት እና በ ኢ-ፍትሀዊነት ማጣት ውስጥ ይቅርታ እንዴት መጠየቅ እንዳለብን ነው።

### 1. ንስሀ መግባት የሚያስፈልገው ማነው?

የሌላን ሰው ህይወት መጥፎ ወይም አላግባብ በሆነ መንገድ ካበላሸንበት ወይም በሕይወቱ ያሳጣነው ነገር ካለ ንስሀ መግባት እንደሚጠበቅብን ግልፅ ነው። ነገር ግን ቀላል የሚባሉ የተሳሳቱ አመለካከቶች፣ ሀሳቦች ወይም ድርጊቶችም ካሉን ንስሀ መግባት ያስፈልገናል። በምዕራፍ 2 ላይ እንደተመለከትነው እነዚህ የብሔር ግጭት መፈጠር መነሻ ሥሮች ናቸው። ለሌላ ሀይማኖት ተከታዮች፣ ዘር፣ ብሔር ያላቸውን ቡድኖች የገዘፈ ጥላቻ፣ ቅሬታ፣ ቅድመ ፍረጃ ወይም መፍረድ ካለን ንስሀ መግባት ያስፈልገናል። ኢየሱስ ‹ሀሳቦቻችንና አመለካከቶቻችን እንደ ድርጊቶቻን አደገኛዎች ናቸው ብሏል (ማቴ 5፡21-22)።

## 2. እውነተኛ ንስሀ መግባት ምን ማለት ነው?

### ሀ. እውነተኛ ንስሀ መግባት አስተሳሰብና ልብ መቀየር ነው።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ ንስሀ የጠለቀና በጣም አስደናቂ ነው። በሁለቱም ብሉይ እና አዲስ ኪዳን ውስጥ የዚህ ቃል ትርጉም ጥልቅ መፀፀት፣ የአምዕሮ መለወጥ ከልብና ከባህርይ መለወጥ ጋር የተያያዘ ነው። ይህም ማለት ሙሉ በሙሉ መቀየር ማለት ነው። ሀጢያት በመጀመሪያ ደረጃ በአምሳያው የፈጠረንንና ለከበረ ህይወት የሠራንን እግዝአብሔርን መቃወም መሆኑን ማወቅ አለብን። በዚህ ብርሃን ስንመለከት ሁሉም ኃጢአት ምን ያህል አደገኛ እንደሆነና ከዚህ የከበረ ህይወት ምን ያህል ወድቀንና ጎድለን እንደተገኘን እንመለከታለን።

አስቀድመን እምነቶቻችን ድርጊቶቻችንን ለመወሰን ዋና ሚና እንዳላቸው ተመልክተናል። ንስሀ መግባት ማለት እምነታችንን በመለወጥ አኗኗራችንንም በቀየረ መንገድ ነው። ይህም የእግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሰጠው የከበረ ስጦታ ሲሆን ይህም አዲስን ህይወት ለመጀመር የሚያስችል ነው። ይህ ደግሞ ከሚሰማን መጥፎ ስሜት የበለጠ የጠለቀ ሲሆን በመፀፀት ላይ የተመሠረተ ነው። ይህ ደግሞ በ2ኛ ቆሮ 7፡9-10 ላይ በግልፅ የታየ ነው።

### ለ) እውነተኛ ንስሀ መግባት ግንኙነት ማደስ መፈለግ ነው።

አንድ ሰው በግሉ ብቻ ንሰሀ መግባት በቂ አይደለም። እውነተኛ ንስሀ በእግዚአብሔርና በሰውም ፊት ዘንድ መሆን ያስፈልጋል፤ ይቅርታን መጠየቅንም የሚያካትት ነው (ማቴ 5፡ 23-24) ። እርቅ ምናልባት ሁልጊዜ ላይሣካ ይችላል። ሰዎች መጥተው ይቅርታ እንዲያደርጉልን ፈፅሞ ማስገደድም ሆነ መጫን የለብንም። ይቅርታ ፈጽሞ የማይገባን ሊሆን ስለሚችል በትህትና መጠየቅ ብቻ እንችላለን። እኛ የራሳችንን ድርሻ መወጣትና የሚመጣውን ውጤት ግን በእግዚአብሔር እጅ ላይ መተው አለብን።

**ሐ) እውነተኛ ንስሀ ሙሉ ኃላፊነትን ይወስዳል።**

አብዛኛውን ጊዜ ለራሳችን ሁኔታ፣ ድርጊት እና ጥፋተኝነት ሌሎች ሰዎችን ተጠያቂ እናደርጋለን። ብዙ ሰዎች ላደረጉት ስህተት ኃላፊነት ላለመውሰድ ራሳቸውን ያሸሻሉ። ነገር ግን እውነተኛ ንስህ መግባት ይህን አያደርግም፤ በጠፋው ልጅ ታሪክ ላይ እንደምንመለከተው እርሱ ያደረገውን ስህተት ሁሉ ተቀብሎ ተጋፈጠውና ራሱን ከምንም ዓይነት ኃላፊነት አላሸሸም (ሉቃ. 15፡ 18-19) ።

**መ) እውነተኛ ንሰሀ መግባት የሚመጡትን መዘዞች መጋፈጥ ነው፡**

በእግዚአብሔር፣ በተጠቂው እንዲሁም በቤተክርስቲያን ፊት ንስሃ መግባት በተጎዳው ሰው ፊት ወይንም በቤተክርስቲያን ፊት ጭምር ንሰሀ መግባት አንድን ሰው ካደረጉት የተሳሳቱ ድርጊቶች መዘዞች ሊያስቆመው አይችልም፤ በተለይም ህግን ጥለን ከተገኘን ማለት ነው። የቤተክርስቲያን መጋቢ አንድን ንሰሀ የሚገባውን ሰው ወንጀል ሰርቶ መጥቶ ከሆነ ለህግ አካል ራሱን ሪፖርት እንዲያደርግ ማበረታታት አለበት፣ ምናልባት ብዙ ዓመት እስረኛ ሊያደርገው የሚችል ድርጊት ፈፅሞ ሊሆን ይችላል።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ንሰሀ መግባት ሙሉዕ የሆነ ነው፣ የጠፋውን ጥፋት እውቅና በመስጠት ሀጥያትን የማራቅ ሀይል አለው።(ዘፀ. 34፡7) የአባቶች ኃጢአት በሚቀጥለው ትውልድ ላይ ጭምር ተፅዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል ይናገራል። በመጀመሪያው የዕብራውያን መጽሀፍ ቅዱስ ትርጉም የአባቶች ኃጢአት ልጆችን ይጎበኛል ይላል። እግዚአብሔር ይህን ተፅዕኖ

በትልቅ ትኩረት ይመለከተዋል። ኃጢአታችን ለብዙ ጊዜያት ሊቆይ የሚችል ብዙ መዘዞች አሉት፤ ሆኖም ግን ንስሀ መግባት የኃጢአት የአዙሪት ድግግሞሻዊ ሂደት የሚሰብር ነው። የእኛ ብቸኛ ተሰፋ ግን በተስፋ በመቁረጥ የተጸጸትንበትን ነገር እና ምንም መለወጥ የማንችለው ነገር ጭምር እግዚአብሔር መለውጥ የሚችል መሆኑን ማመን ነው ። በሉቃ 3፡8 ላይ መጥምቁ ዮሐንስ እንዲህ ይላል እኛ ንስሀ በመግባታችን በህይወታችን ፍሬ ልናፈራ እንደሚያስፈልገን ነው።

**ሠ) እውነተኛ ንስሀ መግባት ካሳ የሚያስፈልግበት ሥፍራ ሊኖር ይችላል።**

ንሰሀ መግባት ላደረግነው ነገር የተሰማንን ጥልቅ ሀዘን መግለጥ ብቻ ሳይሆን፣ በየትኛውም አይነት መንገድ ሙሉ በሙሉ መተካት ማንችለው ነገር ቢሆንም እንኳን ለመተካት መፈለግን ይጨምራል። በዘኬዎስ ህይወት እንደምንመለከተው (ሉቃ 19) ከኢየሱስ ጋር ከተገናኘ በኋላ ወዲያውኑ በተሳሳተ¨መንገድ ለበደላቸው ሰዎች ካሳ መልሶ ለመስጠት አቀረበ። ይህን ያደረገው ኢየሱስ እንዲያደርግ ስላስገደደው ሳይሆን ከልቡ ከተከናወነው ንስሀ መግባት የመጣው ፍሬ ነው። የተዘረፈ ዕቃ ሁልጊዜ መመለስ ይጠበቅበታል። ህይወት በጠፋ ጊዜ ግን ተመልሶ የሚከፈል ምንም ነገር የለም፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ጥልቅ የሆነ መፀፀታችንን ተግባራዊ በሆነ መንገድ የምንገልጥበትን መንገድ ሊያሳየን ይችላል።

## 3. ለንሰሃ መግባት የእግዚአብሔር ምላሽ

የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ለንስሀ ሲጠራቻው እናያለን። በኢሳ 1፡ 18 እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን እንዲህ ብሎ ይጋብዛል *«ኑና እንዋቀስ»* ይላል ጌታ። « *ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነፃለች እንደ ደምም ብትቀላ እንደባዘቶ ትጠራለች›*›። ምንም እንኳን እኛ በግልጽ በአደባባይ የተገለጠ ኃጢአት ባይኖረንም እኛ ሁላችን

ኃጢአተኞችና እግዚአብሔር ካዘጋጀልን የክብር ህይወት ጎድለን የተገኘን ሆነናል። ኃጢአት ሁላችንንም የሚያጠፋ አደገኛ ነገር ነው፤ ሁሉንም ፍጥረት የሚጎዳ ነው (ሆሴዕ 4፡1-3) ።

እግዚአብሔር ለእኛ ካለው ታላቅ ፍቅር የተነሳ ከዓለም ፍጥረት አስቀድሞ ልጁን ለመላክ አቅዶ ነበር። ኢየሱስ የመጣው የዓለምን ኃጢአት እና ሀዘንን ሁሉ በመስቀል ላይ በመሸከም እንዲሁም ለሁሉም የሚበቃ የኃጢአት ሥርየትን ለማዘጋጀት ነበር። እኛ ንሰሀ በመግባት በኢየሱስ ስናምን አዲስን ልብ መቀበል እንችላለን። ይህ እግዚአብሔር የሚፈልገው ነገር ነው። እርሱ ማንም ሰው እንዲጠፋ አይፈልግም። ገሀነም ማለት እጅግ አስፈሪ የሆነ ሥፍራ ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር ገሀነምን ያዘጋጀው በራሱ አምሳያ ለፈጠራቸው` ወንዶችና ሴቶች ሳይሆን ለሰይጣንና ለአጋንንቶች ነው። እኛ ወደዚያ እንድንሄድ አይፈልግም፣ ለዚህ ነው ኢየሱስ ይህን ያህል ርቀት ሄዶ ለእኛ እንዲሞት ያደረገው።

እርሱ ምህረትን ማሳየት የሚወድ አምላክ ነው፣ ነገር ግን እኛ ንስሀ ለመግባት እምቢታን ካሳየን ከምህረት ራሳችንን አራቅን ወይም አጎደልን ማለት ነው። እኛ ልንገምተው ከምንችለው በላይ እንደሚወደንና ትልቅ ክብር ለእኛ እንዳለው እግዚአብሔር ሊያሳየን የሚፈልግ አምላክ ነው። እርሱ እኛ ንሰሀ ገብተን ከእርሱ ጋር እርቅ ማድረግ እንድንችል ይፈልጋል። በአንድ ኃጢአተኛ ንሰሀ መግባት የሰማይ መላእክት ሁሉ ደስ ይላቸዋል (ሉቃ 15፡10) ።

ልባችን የሚለወጠው ፀጋው እንጂ ህግ አይደለም። በዚህ ሥፍራ ከግንዛቤ ውስጥ መግባት ያለበት ጉዳይ ***በኃጢአት መወቀስና በኃጢአት መኮነን*** ሁለቱ በጣም የተለያዩ ነገሮች ናቸው። **ኩነኔ** ለምህረት ምንም ተስፋ እንድሌለን እንዲሰማን የሚያደርግ ሲሆን ሰይጣን ከእግዚአብሔር እንድንርቅ ከሚጠቀምባቸው መሣሪያዎቹ መካከል ዋናው ነው። እሱም እኛ የተፈረደብን እንደሆንን እና ከዚያም መውጣት የምንችልበት ምንም አይነት መንገድ እንድሌለን ይነግረናል። በሌላኛው መንገድ ድግሞ የመንፈስ ቅዱስ **ፀጋ** ወደ ንስሀ ያቀርበናል፤ በዚህም ከእግዚአብሔር ሰላምና ተሀድሶ እናገኝበታለን። ይህም አዲስ ህይወትን የምናገኝበት መንገድ ነው።

**ንስሀ የመግባት ጥቅሞች፡-**

ሀ) ከእግዚአብሔር ጋር ሠላምንና እርቅን ያስገኛል።

ለ) የሀጢአትን (የበደልን) ክብደት ከእኛ ላይ ያነሳል (ምሳ 28፡13።

ሐ) በኃጢአት ላይ ድልን ይሰጠናል።

መ) ነጻነትን ይሰጠናል ፍርሀትን ያስወግዳል።

ሠ) ጤናችንን ያበዛል፤ ይህም መንፈሳዊ አዕምሮአዊና አካላዊ ጤንነትን ጭምር ያበዛል (መዝ 32፡1-5)

ረ) በራስ መተማመናችንን ይገነባል።

ሰ) ከተጠቂው ሰው ጋር እርቅን እንድናደርግ ይመራናል ያለ ንሰሀ መግባት ምንም ዓይነት እርቅ ሊኖር አይችልም።

ሸ) የተጎዳው/ተጠቂው ሰው ይቅር እንዲል ይረዳዋል።

ቀ) ለፍትህ አስተዋፅዖ ያደርጋል።

በ) በፍርድ ሥርዓት ውስጥ ምናልባትም ቅጣትን ሊያቃልል ይችላል።

ተ) ማህበረሰቡ እርስ በእርስ ያላቸውን ግንኙነት እንዲገነቡ ይረዳል።

ቸ) ለተጎዳው/ለተጠቃው ሰው ይበልጥ ዋስትና ይሠጣል።

ኀ) በሕይወታችን ካጋጠሙን አሰቃቂ አጋጣሚዎች እንድንፈወስ ይረዳል።

ነ) የሰዎችን እምነት መልሰን እናገኛለን።

ኘ) ስለ እግዚአብሔር ምህረት መልካም ምስክሮች እንሆናለን።

አ) በሰማይ ወዳለው ዘላለማዊ ህይወት ይመራል።

ንስሀ በመግባት ግለሰቦች ብቻ አይደሉም የሚጠቀሙት፤ ነገር ግን ሁሉም ማህበረሰቦች ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡ ከእኛ አመለካከት መለወጥ የተነሳ ፍጥረት ጭምር ይጠቀማል (ሮሜ 8፡ 19-21) ፡፡

## 4. ንስሀ መግባት ከሌለ ምን ይከሰታል?

የንስሀ ህይወት ማጣት ወደ ሞት ማዝገምን ያመጣል፡፡ አንዳንድ ሰዎች በአልኮል፣ በተለያዩ ሱሶች እና የሕይወት መስመራቸውን የሚረብሹ መንገዶችን በመፈለግ ራሳቸውን ማስመለጥ ይፈልጋሉ፡፡ አንዳንዶች ወደ ከፋ ራስን የመኮንን/የመፍረድ ደረጃ በመድረስ የራሳቸውን ሕይወት እስከማጥፋት ድረስ ይወስናሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ከባድ ወደሆነ የልብ ድንዳኔ ይገቡና ራሳቸውን ተጨማሪ ወንጀል ውስጥ ያስገባሉ፡፡

**ንስሀ እንዳንገባ እንቅፋት የሚሆኑ**

ብዙ በደለኞች ለሠሩት በደል (ስህተት) ንስሀ እንደማይገቡ የሚከለክላቸውን ነገር ምን እንደሆነ አይረዱም፡፡ ነገር ግን ብዙ ምክንያቶች ለእነርሱ አስቸጋሪ እንዲሆንባቸው ያደርጋል፡፡

- የሰው የኃጢአተኛነት አዳማዊ ተፈጥሮ መንፈስ ቅዱስን ይቃወማል፡፡
- ስለሀጢአት ምንም ወቀሳ ሳይኖር ሲቀር - እንዲያውም ባደረጉት ነገር ይበልጥ ይኩራራሉ፡፡
- የሚመጣባቸውን መዘዞች በመፍራት - ቅጣት፣ ከሌሎች ሰዎች የሚመጣውን ምላሽ፣ በሰው ዘንድ ያላቸውን ተቀባይነት ወይም ስራ አጣለሁ የሚል ፍርሃት፡፡
- በሰሩት በደል የአዕምሮ ህመም ተጠቂዎች መሆን
- እናም የመሳሰሉት፤

## 5) ንስሀ መግባትና ይቅርታ መጠየቅ

**ይቅርታ መጠየቅ የሚያስፈልገው እነ ማንን ነው?**

- የመጀመሪያውና ከሁሉም በላይ የሆነው እግዚአብሔርን ነው። እኛ ኃጢአትን በመሥራት በዋናነት የበደልነው እርሱን ነው። ኃጢአታችን በሀሳባችን ብቻ ከሆነ እና ሌላው ሰው ስለዚህ ጉዳይ የማያውቅ ከሆነ እኛ ወደ እግዚአብሔር ብቻ በመናዘዝ ይቅርታ ልንጠይቀው ይገባል፡፡
- እኛ በግልጥ አንድን ሰው በድለን ከሆነ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ብቻ መጠየቅ በቂ አይደለም (ማቴ 5፡23-24)፡፡
- ኃጢአታችን በአደባባይ ተደርጎ ሁሉም ሰው የሚያውቀው ከሆነ ቤተክርስቲያንንና ማህበረሰቡን በአደባባይ ይቅርታ መጠየቅ፤
- እንደ መግደልና አስገድዶ መድፈር ዓይነት ኃጢአቶች ከሆኑ የተቀቡ የእግዚአብሔር ሰዎችን በመፈለግ ለፈውስና ለአርነት (ነፃ) ለመውጣት እንዲፀልዩ በማድረግ ንስሀ ስለመግባትህ ምስክር እንዲሆኑና ከአንተ ጋር በመፀለይ ማንኛውንም እርግማን ያመጣውን ድርጊት እንዲሰበር ማድረግ አስተዋይነት ነው፡፡

## ለሌሎች ሰዎች ይቅርታን እንዴት እንደምንጠይቅ ተግባራዊ ሀሳቦች (መንገዶች)

- የሠራነውን ሀጢአት በግልፅ በመናገር ለድርጊታቸው ሙሉ የሆነ ኃላፊነትን መቀበል ያስፈልገናል፡፡
- አንድ ድርጊት ፈፅመን በቀላሉ አዝናለው ብሎ ከማለፍ ይልቅ ወደ በደልነው ሰው ቀርበን ይቅርታ መጠየቅ ከሁሉም ይልቅ ውጤታማ ነው፡፡
- ‹‹ጎድቼህ ከሆነ /ከጎዳሁህ/›› የሚለውን ቃል ፈፅሞ መናገር የለብንም። ይህ የሚያስተላልፈው መልዕክት ምንም አይነት ስህተት አለመስራታችንን ማመናችንን ነው፡፡
- የበደልነውን ሰው ፈፅሞ የተናደድንበትን ስህተቶቻቸውን እያነሳን መክሰስ ወይም መወቃቀስ የለብንም፡፡
- አንድ ጉዳይ አቅልለን ወይም አግዝፈን ማንሳትና መነጋገር የለብንም፡፡
- በዚያው ጊዜ ምንም ዓይነት ስብከት መስበክ የለብንም፡፡

- በምንም ዓይነት ሁኔታ ስህተታችን መሸፈን ወይም ማሳበብ የለብንም፡፡ አንዳንድ ጊዜ ግን ማብራሪያ መስጠት ስለተሰራው ኃጢአት ግልፅ ማድረግ ሊረዳ ይችላል።
- በተቻለ መጠን ወዲያውኑ ሰዎችን ይቅርታ መጠየቅ አለብን (የተደረገው ኃጢአት ወሲባዊ ባህርይ ያለው ካልሆነ በስተቀር ፊት ለፊት በመገናኘት ይቅርታ መጠየቅ ከሁሉም የተሻለ ነው፣ ከሆነ ግን በጥንቃቄ በተመረጡ ቃላት፣ በተጻፈ ደብዳቤ መጠቀም ተገቢ ነው)።
- በአስፈላጊው ሥፍራ ካሳ ለመክፈል መፈለግ ይገባናል። በዘፀ 22፡3፣ ዘሌ 6፡4፣ ዘሁ 5፡ 6-7፣ ምሳ 6፡31፣ ህዝ 33፡15 መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ካሳ መርሆዎችን ያስተምረናል።
- ሉቃ 3፡8 እና የሐዋ 26፡20 ተግባራዊ ፍሬ ስለሚያስፈልገው ስለ ንስሀ ሀሳብ ይሰጠናል፡፡

**ማጠቃለያ** (**ለማጠቃለል**) ፡- እውነተኛ ንስሀ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚሰጥ ስጦታ ነው፡፡ እግዚአብሔር ኃጢአትን በትኩረት ይመለከተዋልና ንስሀ ካልገባን በስተቀር በህይወታችንና በቀጣይ ዘመናችን ላይ አደገኛ የሆነ መዘዝን ይዞ ይመጣል፡፡ እግዚአብሔር በሙላት ንስሀ እንድንገባ ይፈልጋል፡፡ ምክንያቱም እርሱ ምህረትን ማሳየት የሚወድ አምላክ ስለሆነ ነው (ሚክ 7፡18) ። እርሱ ማንንም ሰው በመቅጣት ደስታን አያገኝም (ሰቆ. 3፡33) ፡፡እውነተኛ ንስሀ ከንግግር በላይ ነው፡፡ ህይወታችንን በሙላት የሚለውጥ ነው፡፡

**ከራስ ጋር ማዛመድ**

- ንስሀ መግባት ለምን ያስፈልጋል?
- የበደልካቸውን ሰዎች ዘርዝረህ ፃፍ ሳታስብ የጎዳኋቸውን ጭምር ማለት ነው፡፡

- ስለዚህ ማድረግ የሚጠበቅብህ ምንድን ነው ብለህ ታስባለህ?
- መንፈስ ቅዱስ ከራስ እይታ አቅጣጫ ሁሉንም ነገር እንድትመለከት ይረዳህ ዘንድ ፀልይ።

## ቁልፍ ሀሳቦች

- ንስሀ መግባት ከህሊና ነቀፌታ (በደለኝነት ስሜት) እሥራት ለመላቀቅ ብቸኛው መንገድ ነው።
- ንስሀ መግባት በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያስፈልጋል። ይህን ስናደርግ ለሚመጣው መዘዝ ሁሉ ለመቀበል ፈቃደኛ መሆን ያስፈልጋል።
- ንስሀ መግባት ለጎዳን ሰው ለወደፊቱ አብሮ ለመኖር ተስፋ መስጠት መቻል ሲሆን የተጎዳውም ሰው እንዲፈወስ መርዳት ነው፤ በመካከላቸው እርቅ እንዲኖር የሚያስችል ነው።

# ትምህርት አስራ ሶስት

## የቡድናችንን ( የእኛ ወገን የሆኑትን) ሀጢያት በመናዘዝ ሰላምን ለማስፈን የራሳችንን ድርሻ መወጣት(ማቴ 5፥9)

ሰዎች ጉዳት ሲደርስባቸው/ሲጎዱ/ ቅሬታቸው በጎዳቸው ሰው ላይ ብቻ አይሆንም፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ዘመዶቻ ቸውን፣ ብሔራቸውን ወይም ዘራቸውን፣ ፆታቸውን፣ ሀገራቸውን እና ሌሎችን አምርረው ይጠላሉ፤ ለምሳሌ በሩዋንዳ የዘር ጭፍጨፋ አብዛኛውን ጊዜ የቱሲ ተጠቂዎች ቤተሰቦቻቸውን የገደሉ የሁቱ ግለሰቦችን ብቻ ለይተው ሳይሆን የሚጠሉት ሙሉ ቡድናቸውን ነው፡፡ በሩዋንዳ ለእርቅ መካከል በመቆም በተግባር የቡድናቸውን ሀጢያት በመናዘዝ ጥላቻን በማሸነፍ ጥልቅ የሆነ እርቅ እና ፈውስ ማምጣት ችለዋል፡፡ እነዚህ ቁስሎች ካልዳኑ ከትውልድ ወደ ትውልድ መተላለፋቸው አይቀርም፡፡ በዚህም ምክንያት እኛ እንደ አማኞች የክህነት ሚናችንን ማወቅና በግጭት ወቅት የተከሰተን ቁስል እንዴት መርዳት እና ማዳን እንደምንችል ማወቅ አለብን፡፡

### 1) **የእኛ ተግባርና ሥልጣን**

በቀደመው ምዕራፍ ላይ ስለግል ጥፋተኝነት እና ንስሀ መግባት ተመልክተናል፡፡ በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሁሉን አቀፍ ጥፋተኝነት እና ንስሀ መግባት እንደሚያስፈልግ ይናገራል፡፡ በብሉይ ኪዳን ነብያት በተለይም በዕዝራ፣ በነህሚያና በዳንኤል ይህን ሀሳብ በሰፊው እናያለን፡፡ እነዚህ ሰዎች በራሳቸው ቅዱሳን (ፃድቃን) ሰዎች ሆነው ሳለ ራሳቸውን ከህዝቡ ኃጢአት ጋር በደለኛ አድርገው ቆጥረው ራሳቸውን ለንስሀ አቀረቡ፡፡ እነዚህም በአዲስ ኪዳን ላለን አማኞች እንደ ንጉስ ካህናት የራሳችንን የኃላፊነት ድርሻ ለመወጣት እንድንችል ምሳሌ የሚሆኑን ናቸው፡ ፡ በአዲስ ኪዳን ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን *«… በደላችንን ይቅር በለን›* ብለው እንዲፀልዩ አስተምሯል (**ማቴ 6፥12**) ፡፡

**አናንተ የተመረጠ ህዝብ፣ የንጉስ ካህናት፣ ቅዱስ ህዝብ ናችሁ 1ኛ ጴጥሮስ 2፡9**

እነዚህ ቃላት የተነገሩት ለተለየ አገልግሎት ለተመረጡ ጥቂት ሰዎች ሳይሆን ለሁሉም አማኞች ነው። በብሉይ ኪዳን ያለውን የካህናት ሥራ ጥናት ስናደርግ እግዚአብሔር ዛሬ በአዲስ ኪዳን ካለን ከእኛ ምን እንደሚጠብቅ እንድንረዳ ያደርገናል።

የካህን ዋናው ጠቃሚ ሚና በመካከል መግባት (መማለድ) ነው። ካህን በእግዚአብሔር ፊት የህዝቡን ኃጢአት ተሸክሞ መገኘት ነው፤ እንደ ኃጢያተኛ ሰው ወኪል መሆን ማለት ነው። በህዝቅኤል 22፡30 መሠረት እግዚአብሔር በፈረሰው ቅጥር በኩል የምድሪቱን ህዝብ ወክሎ የሚቆምን አንድ ሰው እፈልጋለሁ ይላል። በዚህም የተሰጠው የእግዚአብሔርን ፍርድ ዞር የሚያደረግ ነው። ከሁሉም የሚበልጠው ዋናው ካህን ኢየሱስ ከኃጢአተኞች ጋር ለመቆጠር መረጠ (ኢሳ 53፡12)። እርሱ ራሱን ከሰው ልጆች ኃጢአት ጋር እንደ አንዱ ራሱን መቁጠር ብቻ ሳይሆን እርሱ ራሱ ስለእኛ ኃጢአት ሆነ (2ኛ ቆሮ 5.21) ስለዚህ እርሱ አንዱና ብቸኛው የኃጢአት የሥርዓት መስዋዕት ለመሆን ቻለ።

ኢየሱስ መስቀላችንን ተሸክመን እንድንከተለው ነግሮናል። መስቀላችንን የመሸከም የአንድ ክፍል ትርጉም ፈቃደኛ መሆን፣ እንደ እርሱ መሆን፣ «ከዓመጸኞች ጋር መቆጠር» ከህዝቡ ኃጢአት ጋር አንድ መሆን እንደሆነ እናምናለን። አንድ ሰው ‹‹በእኛ ፈንታ ሆነህ እንድትናገር ማን ስልጣን ሰጠህ?›› ብሎ ቢጠይቅህ በድፍረት የእግዚአብሔር ቃል ይህንን ስልጣን እንደሰጠን ለመናገር እንችላለንና እግዚአብሔር ይህን ሚና እንድንወጣ (ኃላፊነት እንድንቀበል) ከእኛ ይጠብቃል።

በ2ኛ ቆሮ 10፡3-5 እንደ አማኞች እኛ ምድራዊ የጦር መሣሪያ እንደማንጠቀም ተነግሮናል። እንደ ንጉስ ካህናት አባልነት እኛ ‹‹የአደባባይ ኑዛዜ›› የሚል የጦር መሣሪያ በመጠቀም ወይም ክፍተትን በመሙላት የበደሉንን ልብ የሚያሸንፍ አቅም ያለው በጣም ኃይለኛ መሣሪያ ለመጠቀም እድል ተሰጥቶናል። ይህ መሣሪያ አቢጊያ የባልዋን ስንፍና ያመጣውን ክፍተት ለመሙላት በተንቀሳቀሰች ጊዜ በተግባር ላይ የዋለ የጦር ዕቃ ነው (1ኛ

ሳሙ 25፡14-35) ። የእርሷ ጣልቃ መግባት የዳዊትን ልብ በመለወጥ ለመላው ቤተሰቧ ሞገስን ያመጣ (ያስገኘ) ነበር።

እኛ በተፈጠረው ክፍተት በኩል በሰማይዊ ዓለም ውስጥ አንድ ጉልህ ነገር ይከናወናል። ። በኤፌ. 6፡12 ላይ መጋደላችን ከሥጋና ደም ጋር እንዳይደለ ተነግሮናል። ከምድራዊ ሳይሆን ከሰማያዊው ፍርድ ቤት ጋር ነው። እናም ራሳችንን በእግዚአብሔር ምህረት ላይ እየጣልን፣ ለውጥ እንዲመጣ በማመን ነው (ሕዝ 22፡30) ። ጸጋና ምህረት እንዲፈስ እና በፍርድ ላይ ድል እንዲነሳ እድል የሚሰጥ መለኮታዊ ነው እንጂ ሕጋዊ ነገር አይደለም (ያዕቆብ 2፡13)

## 2) የአደባባይ ኑዛዜ ወይም በክፍተት መካከል መቆም ስንል ምን ማለታችን ነው?

በክፍተት መካከል ስንቆም ምን እያደረግን እንደሆነ የተሳሳተ ግንዛቤ ሊኖር ስለሚችል እና ለአንዳንድ ሰዎች ሥነ-መለኮታዊ ጥርጣሬ ሊያስነሳም ይችላል። ስለዚህ የበለጠ ማብራሪያ ያስፈልጋል።

**በክፍተት መካከል መቆም ማለት፡-**

- እኛ ያደረግነው ስህተት እንደሆነ ተቀብያለው
- የሌላኛው ብሔር/ቡድን/ መጎዳቱን ተቀብያለው
- በሆነው ነገር በጥልቅ ተፀፅቻለው፤ ከእግዚአብሔር ዘንድ ምህረት ለማግኘት በለቅሶ ቀርባለው
- እኛ ሁላችንም አንድ ዓይነት መንፈስ የለንምና በተደረገው ነገር እኔ ፈፅሞ አልስማማም። ነገር ግን እኔ በተደረገው ነገር በኩራት አልቀርብም (አልታበይም) ምክንያቱም እኔ ራሴ በተመሳሳይ ኃጢአት ውስጥ ልገኝ እንደምችል በማሰብ ይህን ስህተት እቀበላለሁ።
- እኔ ራሴ በተለየ መንፈስ ውስጥ ለመኖር ራሴን እሰጣለሁ።

**በክፍተት መካከል መቆም ማለት ምን ማለት አይደለም።**

- የበደለኝነት ኃላፊነትን ላለመቀበል ራስን ማሸሽ አይድለም፤

- በደለኛው ላጠፋው ጥፋት ከ ተጠያቂነት ያመልጣል ማለት አይድለም ወይም በዛ ምክንያት ፍትህ ይጣመማል ማለት አይድለም፤
- እኛ ቡድናችንን የምንወክለው በተወሰነ ባለን ሀላፊነት ደረጃ ሲሆን፣ ነገር ግን ከቡድናችን ጋር ስንገለፅ እንደ ካህን እና አማላጅነት ከእግዚአብሔር ቀድመን ሀላፊነት እንወስዳለን ማለት አይደለም።



### 3) የአደባባይ ኑዛዜ (ንስሀ) ለምን አስፈለገ?

ሀጢያት የሰራ ሰው ወይም እኛን የበደለን ሰው ቢናዘዝ/ንሰሀ ቢገባ እኛ በቀላሉ ይቅርታ ለማድረግ ይቀለናል፡፡ ሁኖም ግን ኑዛዜአቸውን ለመስማት ምናልባት ሁሌም ማንችልበት አጋጣሚ ይኖራል። ምናልባት እኛን የበደለን ሰው ወይም ሀጢያት የሰራው ሰው ሞቶ ወይም በራሳቸው ንስሀ ለመግባት ብቁ ሁነው ካልተዘጋጁ፤ ይህ የሀጢያት ሁኔታ ሳይወገድ ይቆያልን? (ሰቆቃ 5፡7 ተመልከት)

መጽሐፍ ቅዱስ ሳንናዘዝበት የቀረውን ኃጢአት እንዴት አድርገን ማስተናገድ እንዳለብን ያሳየናል፡፡ አንድ ሰው በክህነታዊ የአገልግሎት ሚናው በምልጃ ፀሎት በፈረሰው ቅጥር በኩል በእግዚአብሔር ፊትና እንዲሁም በተበደሉት ሰዎች ፊት በመቆም መማለድ አለበት (ዘፀ 32፡32፣ ህዝ 22፡30)። በዘሌ 26፡40 እንደተነገርነው የእኛን እና የአባቶቻችን ኃጢአት መናዘዝ አለብን፡፡ የሚማልዱ ሰዎች ስለተደረገው በደል በጣም ግልፅ የሆነ መረዳት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ እውነታዎች በትክክል ተመርምረው መቅረብ እና ሁሉም በግልጥ ለመናዘዝ ፈቃደኛ መሆን አለባቸው፡፡ ስለሆነው /ስለተደረገው/ ነገር በመንፈሳቸው ጥልቀት ሀዘን ሊሰማቸው ይገባል፡፡

የሰው ልጆች ትልቁ ቁስል የሚፈጠርባቸው በግለሰብ ደረጃ የሚደርስባቸው በደል ብቻ ሳይሆን በህግ አካላት የሚፈፀሙ፤ በመንግስት አካላት፣ ባህል፣ በብሔር ቡድን፣ ተቋማት፣ አብያተ ክርስቲያናትና  በመሳሰሉት ሚፈፀሙ የሀጢያት ውጤቶች ነው፡፡ ችግሩ ያለው እኛ ምንም እንኳን የጋራ አካላት አንድ አባል ብንሆንም ብዙውን ጊዜ የግል ኃላፊነትን ከመውሰድ ራሳችን የማራቅ አዝማሚያ እናሳያለን፡፡ የጋራ /የቡድን/ ኃጢአት ፈፅሞ ተቀባይነት የሌለውና ግራ የሚያጋባ ሲሆን ውጤቱም የተጎዳውን አካል አይፈውስም፤ እንዲሁም ግጭቱ መፍትሔ የለውም፡፡ አደገኛ የመረቀዘ ጉዳት /ቁስለት/ ለብሔር ግጭት መነሳት ሰበብ ሊሆን እንደሚችል አስቀድመን ተመልክተናል፡፡

እኛ እንደ አንድ ግለሰብ ወደድንም ጠላንም አንድን ቡድን የምንወክል ሰዎች ነን። እራሳችንን ከማህበረሰቡ ኃጢአት ጋር አንድ አድርገን የምንመለከት ከሆነ በኃጢአት ተግባር ተሳታፊ የሆኑ ሰዎች ከኃጢአታቸው ወዲያውኑ ይነፃሉ ማለት አይደለም። በራሳቸው ስለ ኃጢአታቸው በእግዚአብሔር ፊት ንስሀ መግባት አለባቸው። ይሁን እንጂ የእኛን ኑዛዜ የሰሙ ሰዎች ከፍርድና ከመራርነት ተላቅቀው ለይቅርታ ጸጋን ማግኘት እንዲችሉ ያደርጋል። የእኛ ኑዛዜ የትላንትን ሁኔታ አይለውጥም፤ ነገር ግን የአሁኑን እና የወደፊት ሁኔታን ለመለወጥ ይረዳል።

ለፈውስ የእግዚአብሔር ተስፋ አማኞች ናቸው። የአደባባይ ንስሀ (ኑዛዜ) ማለት ቀመር አይደለም ወይም ተራ የአንደበት ንግግር አይደለም። ጥልቅ ከሆነ ከልባችን የሚወጣ መሆን አለበት። የአባቶቻችንን ኃጢአት ለይቶ በማወቅና ከእኛ ወገን ጋር ወደተለያዩ እርምጃዎች ሊመራን ይገባል። መናዘዝ፣ ንስሀ መግባትና እርቅን ማድረግ የህይወታችን መንገድ /መመሪያ/ ሊሆን ይገባል። የእርሱ ቤተክርስቲያንና የእርሱ ህዝብ ይህን የህይወት መመሪያ በህይወታቸው መለማመድ ይጠበቅባቸዋል ይሄም የእግዚአብሔር ዕቅድ ነው። እንዲሁም ለተጎዱት ህዝቦች የካህንነት አስታራቂ መሆን ይጠበቅብናል (2ኛ ዜና 7፡14)።

## 4) በፈረሰው ቅጥር ከመቆም የሚገኙ በረከቶች

- ለተጎዳው ልብ ዘላቂ ፈውስን የሚያመጣ ነው።
- የተበላሸን አዕምሮ ያነፃል።
- የአሁኑንና የወደፊቱን ህይወታችንን ይለውጣል (አድነትን እና ሠላምን ያመጣል)።
- ያሉት ሁሉም ነገሮች ተመሳሳይ ናቸው የሚለውን የፍረጃንና የፍርድን ሁኔታ ከሰዎች ህይወት ለመጣል ያግዛል።
- በሰዎች መካከል የሚፈጠር ግጭት የሚያለያይን ግድግዳ ይሰብረዋል።
- ምድር ሊፈውስ የሚችል ነው (ዘፍ 4፡10፣ ዘሌ 18፡ 24-25፣ 2ኛ ሳሙ 21፡1፣ 2 ዜና 7፡ 14፣ ሆሴዕ 4፡1-3)።
- በመጨረሻም ያለፈው ነገር ወደ ኋላ የሚጥል ማለት ነው።

- ፈውስን ሊያመጣ የሚችልና መንፈሳዊ ስልጣን የሚያድስ ሆኖ አንድ ጊዜ ከተናዘዝን በኋላ በማንነታቸው በሙላት ያለ ምንም ነቀፌታና የኃራ /የቡድን/ በደለኝነት እንዳይኖር የሚያስችል ነው፡፡
- ይህ የመንፈሳዊ ውጊያ አንዱ አካል ነው (2ኛ ቆሮ 10፡4)፡፡
- ፍርድ የሚገባቸውን የማህበረሰብ ክፍል ምናልባት ነፃ የሚያወጣ ነው (ህዝ 22፡30)፡፡
- ልጆች በአባቶቻቸው ኃጢአት ምንም ዓይነት መከራ ሊቀበሉ አይገባም (ኤር 31፡ 29)፡፡

## 5)በተግባር የሚገለጡ ግንዛቤዎች

**በመካከል መቆም ያለበት ማነው?**

- በመንፈስ ቅዱስ ውስጡ የተነካና ይህን ማድረግ የሚያስፈልጋቸው ሰዎች ናቸው፡፡
- የተጎዳን ሰው ታድሶ ለማየት ፍላጎት ያለው ሰው፤
- ለተደረገው በደል /ኃጢአት/ በተወሰነ ወይም በሙላት ሙሉ ኃላፊነትን ለመቀበል ፈቃደኛ የሆነ ሰው
- በእያንዳንዱ ክስተት ልባቸውን ለንስሀ ስጦታ ለመስጠት በእግዚአብሔር ላይ የሚደገፍ ሰዎች
- እርቅ እንዲሆን የውስጥ ቅናት /መነሳሳት/ ያለው ሰው

**ማሳሰቢያ፡** በአደባባይ /ብዙ ህዝብ/ ባለበትና የፖለቲካ ትኩሳት ባለበት ሥፍራ ንስሀ መግባታችን (መናዘዛችን) በትክክል (በተሻለ) ሁኔታ ለማከናወን እንዲቻል እግዚአብሔር ጥበብን እንዲሰጠን መፀለይ ያስፈልገናል፡፡ ይህን ስናደርግ ያለምንም ማመቻመች ወይም እውነት ሳይዛባና የሁኔታው (የጥቃቱ) አደገኛነት ሳይበረዝ ሊሆን ይገባል፡፡ ይህ ከመልካምነት ይልቅ የበለጠ ጎጂ ሊሆን ስለሚችል ነው፡፡

**በፈረሰው ቅጥር ስንቆም /ክፍተቶችን ስንሞላ/ አብሮ መታሰብ ያለበት ኃላፊነት፡-**

አመለካከትን በመለወጥ፣ ተግባራዊ እርምጃዎችን በመውሰድና ራስን በመስጠት ድጋፍ መስጠት ይጠበቅብናል፡

- የተጎዳውን ሰው ዋጋ መስጠት ወይም ማበረታታት
- ለእነሱ መታደስ/ማገገም አብሮ መሥራት
- ከራሳችን ወገን ጋር ከሚዛመዱ በተለየ (ይልቅ) ከሌሎች ጋር በመንፈስ መኖር
- የቡድናችን አመለካከት ለመቀየር በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ መጠቀም።

**ክፍተትን በመሙላት (በፈረሰው ቅጥር መቆም) ምን ያህል ጊዜ ሊወስድ ይችላል?**

ይህን እንደ ሸክም (ሀላፊነት) ልንመለከተው እንችላለን ወይም የተጎዳውን ሰው እንዲፈወስ ለመርዳት እኛ ያገኘነው ዕድል ሊሆን ይችላል።ከቡድናችን አንድ ሰው ኃጢአታችንን ሲናዘዝ እና ይቅርታ ሲጠይቅ ለመስማት እድል ያላገኙ የቆሰሉ ሰዎች እስካገኘን ድረስ ክፍተቱ መሀል በመቆም ዝግጁ መሆን አለብን። እንደ ሀላፊነት ወይም ለቆሰለ ሰው ፈውስ ለማምጣት እድል እንዳገኘን ልንቆጥረው እንችላለን።

**በፈረሰው ቅጥር በኩል መቆም የሚያስከፍለው ዋጋ**

በፈረሰው ቅጥር በኩል መቆም ዋጋ የሚያስከፍል ነው። ይህንን ጉዳይ ከልባችን የምናደርግ ከሆነ በስሜታችን ብዙ የሚሰማንና የምንከፍለው ዋጋ አለ። ምንም እንኳን አዎንታዊ ውጤት የሚያመጣ ቢሆንም እንዲህ ዓይነት ጉዳይ ሁልጊዜ ይመጣል ተብሎ መጠበቅ አይቻልም። በፈረሰው ቅጥር በኩል መቆም ማለት በመስቀሉ ጎዳና መራመድ ማለት ነው። ይህም «ከዓመፀኞች ጋር መቆጠር›› (ኢሳ 53፡12) አንድ መሆን ነው። ስለዚህ ተቃውሞ ወይም መገለል ሲያጋጥመን ምንም የሚያስደንቀን ሊሆን አይገባም።

በፈረሰው ቅጥር በኩል መቆም በራስ ወገን መገለልን ሊያደርስብን ይችላል፤ በተለይ እነርሱ በደል አድርገው (ስህተት ሰርተው) ስህተቱን (በደሉን) አምነው ካልተቀበሉ ሊያገሉን ይችላሉ። ሰዎች ራሳቸው እኛን በተሳሳተ መንገድ ሊረዱን ይችላሉ። በተሳሳተ መንገድም (አስተሳሰብም) ሊከሱን ይችላሉ። አንዳንዶች ሥነመለኮታዊ ተቃውሞዎች ሊያነሱ ይችላሉ። ምንም እንኳን በመስቀል መንገድ መሄድ ለአንዳንዶች ሞኝነት ለሌሎችም ማሰናከያ ቢሆንም

(1ኛ ቆሮንቶስ 1፡23-24) ኑዛዜን ለሚቀበሉ እና ልባቸው እንዲለወጥ ለሚፈቅዱ ሰዎች በጣም ወሳኝ ነገር ነው።

## ከራስ ጋር ማዛመድ

- ራስህ ከየትኛው (ምን) ወገን ጋር አገናኝተህ ታያለህ? (ብሔር፣ ሀገር፣ ፆታ፣ ቤተ-እምነት፣ ሙያና ወዘተ)
- አንተ ያለህበት ወገን ምን ዓይነት የኃጢአት (የበደለኝነት) አመለካከት ወይም ድርጊት ሲያደርግ ነበር?
- የራስህን ወገን ወክለህ በፈረሰው ቅጥር በኩል ለመቆም ወይም ክፍተትን ለመሙላት ካለው አጋጣሚ ምን ዓይነት ድርሻህን ተወጥተሃል?

## ቁልፍ ሀሳቦች

- መጽሐፍ ቅዱሳዊ ንስሀ መግባት የግልና የጋራ ድርጊት ነው።
- አማኞች የራሳቸውን ወገን ስህተት ለመናዘዝ በፈረሰው ቅጥር በኩል መቆም ወይም ክፍተትን መሙላት ይችላሉ።
- አንድ ሰው ቆሞ የተደረገውን በደል ሲናዘዝና ይቅርታ ሲጠይቅ መስማት የተጎዱትን ሰዎች ለመፈወስ የሚያግዝ ነው። እንዲሁም እርቀ ሰላምን ለማምጣት ወሳኝ መሣሪያ ነው።
- ነገሮቻችን ተዓማኒነት ያለው ለማድረግ በምንናዘዘው ኑዛዜአችን ውስጥ መኖር አለብን።

# ክፍል 4

# ቆርቆሮውን ማልበስ


ንስሀ መግባትና ይቅርታ ማድረግ በተከናወነ ጊዜ እርቀ ሠላም በዚያውም ሥፍራ መሆን ይጀምራል። ልባችን እርስ በርሳችን ክፍት እንደሆነ እና የተመለሰውን ማንነታችንን እንደ ቅድስት ሀገር ዜጎች ለማክበር ዝግጁ መሆናችንን ተገንዝበናል። ስለዚህ እንደ ቅዱስ ህዝብ ወደ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሃሳብ በመመለስ አንድነታችንን እና ልዩነታችንን በማክበር እንጨርሰዋለን። ሁላችንም እኩል ዋጋ አለን እና በማንነታችን የመኖር መብት አለን።



በግጭት ውስጥ ወይም ከግጭት በኋላ እንደተለያየ የብሔር ቡድን እርስ በርሳችን ለመስማማት እንድንችል ጊዜ መውሰድ እጅግ ወሳኝ ነገር ነው። እንዲሁም እርስ በርሳችን በረከትን ለመሰጣጣትና አብረን ለመፀለይ ያስችለናል። እርስ በርስ ከመፈራረድ (ከፍርጃ) ወደ እውቅና መስጣጡት (መስማማትና መበራረክ) ሊለወጥ ይችላል። ይህ ከሌላ ተቃዋሚ መንፈስ እየመጣ ላለው ለመንፈሳዊ ውጊያ እጅግ ጠቃሚ የሆነ  ነገር ነው  ቤተክርስቲያን አንዴ ከተፈወሰች፤ በማህበረሰቡ ውስጥ ለፈውስና ለእርቅ ማዕከል ሆና ለመገኘት ሚናውን ወደ ማወቅ ትመጣለች።



# እርቅ




# ትምህርት አስራ አራት

## በረከትን ማወጅ

### የሌሎችን ብሔር ወገኖችን እውቅና መስጠት እና መባረክን መማር

የአደባባይ ንስሀ ለንጉስ ካህናት ከአገልግሎት ሀብቶች መካከል አንዱ ገፅታ እንደሆነ ስንመለከት ቆይተናል። ሌላኛው የካህናት አገልግሎት ገጽታ ደግሞ በዘዳ. 10፡8 ላይ የምንመለከተው ነው፤ ይህም ካህናት በጌታ ስም በረከትን የሚያውጁ ናቸው። ስለዚህ እንደ ካህናት አገልግሎት መሠረት አንዱ ሌላውን እንዴት እንደሚባርክ ማወቅ እጅግ ጠቃሚ ጉዳይ ነው።

### 1) **የበረከት ኃይል (ስልጣን)**

ከዚህ ቀደም ብለን የቅድመ ፍረጃን አስፈሪ ኃይልና ሌላው ሰው ላይ የመፍረድን አደገኛነት አይተናል (ተመልክተናል) ። በየትኛውም *ሥፍራ* የብሔር (የዘር) ልዩነት ወይም ግጭት ካለ ፍርድን ያበዛል። ሰይጣንም ይህን በመጠቀም ግጭት እንዲቀጣጠል ያደርጋል። መጽሐፍ ቅዱስ የህይወትና የሞት ኃይል በአንደበት ላይ እንዳለ ይናገራል (ምሳ 18፡21) ። ፈውስን ሊያመጣ ወይም ልብን ሊወጋ ይችላል (ምሳ 12፡18) ። የህይወት ዛፍ ወይም መንፈስን የሚሰብር ሊሆን ይችላል (ምሳ 15፡4) እግዚአብሔር ህዝቡን የጠራው በረከትን እንዲናገሩ እንጂ ወደ እርግማን የሚያደርስ ፍርድን እንዲናገሩ አይድለም።

በዕብራውያን ባህል በረከትን እንደ ዋና ነገር በትኩረት የሚመለከቱት ጉዳይ ነው። የበረከት ቃላት ትልቅ ኃይል ይሰጣል ብለው ያምናሉ።እንዲሁም በረከትን ይዞ አለመልቀቅ (መከልከል) ትልቅ ሀዘን የሚፈጥር ነገር ነው። (ዘፍ 27) ከአይሁድ ባህል እና ወግ ልምምድ (ሥርዓት) በረከትን ስለመስጠትና ስለመቀበል ብዙ ነገሮች እንማራለን። ዛሬም ብዙዎቻችን እንደኤሳው *«ለእኔ የቀረ ሌላ በረከት የለህምን?* ›› የሚል ሀሳብ በልባችን ውስጥ እናጩሃለን። (ዘፍ 27፡36) ። ሁሉም የብሔረሰብ ወገኖች *«አባቴ ሆይ አንድ በረከት ብቻ ነው ያለህ? እኔንም ባርከኝ»* የሚል ጩኸት አላቸው!"(ዘፍጥረት 27:38)።

### 2) **በረከት ሁልጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስዊ ባህሪይ አለው።**

አባቶች ልጆቻቸውን ይባርካሉ፣ መሪዎች ህዝባቸውን ይባርካሉ፣ ነገስታት ተገዢዎቻቸውን ይባርካሉ። እንዲሁም ካህናት እንደግለሰብና እንደ ቡድን ህዝባቸውን ይባርካሉ። ኢየሱስ ይህን ሀሳብ በተጨማሪ ጠላቶቻችሁን ጭምር ባርኩ ብሎ ተናገሯል (ሉቃ 6፡ 28) ጳውሎስ ይህን ሀሳብ በሮሜ 12፡14 ላይ አስተማረ። አንዳንድ የበረከት ምሳሌ የሚሆኑን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መካከል ዘፍ 49፣ ዘዳ 33፣ ዘሁ 6፡24-26፣ መዝ 115፡14-15፣ 134፥3፤ 129-8.

## *የበረከት ስጦታ*

*ጋሪ ስማሌይ እና ጆን ትሬንት የሚባሉ «የበረከት ስጦታ»* በተሰኘው ግሩም መጽሐፋቸው የአይሁድ ልጆችን የመባረክ ባህል ምን እንደሆነ ፈትሸው አቅርበዋል። አምስት ዋና ዋና ነገሮችን ገልፀዋል።

1. ትርጉም ያለው መንካት (መነካካት)
2. የሚነገር መልዕክት
3. ለተባረከው ሰው ትልቅ ዋጋ መስጠት
4. ለተባረከው ሰው ልዩ የወደፊት ሁኔታን (ሂወትን) መሳል (ማሰብ) ።
5. በረከቱን ለመፈጸም ያለ ንቁ ቁርጠኝነት።

## 3) **ከሌላ የብሔር (የዘር) ቡድን ለመጡት ሰዎች በረከትን ማወጅ**

እኛ እርስ በርሳችን ለመከባበርና ሥፍራ ለመሰጣጣት ተጠርተናል። *«በወንድማማች መዋደድ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ እርስ በርሳችሁ ተከባበሩ››* (ሮሜ 12፡ 10) ። በመጽሐፍ ቅዱስ **ተከባበሩ** የሚለው ቃል ከፍተኛ አመለካከት ፣ መሸለም፣ ዋጋ መስጠት ማለት ነው። ፊሊ 2፡3 እንዲህ ብሎ ያዘናል። *«እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትህትና ይቁጠር»* (1ኛ ጴጥ 2፡17) በተጨማሪም “ለሰው ሁሉ ተገቢውን አክብሮት አሳዩ፤ የሚያምኑትን ወንድሞች ውደዱ” ይለናል።

የ እግዚአብሔር ቅዱስ ህዝብ እንደመሆናችን መጠን እንደ ንጉሳዊ ክህነት ኀላፊነታችንን ከተቀበልን እና ከሌሎች ቡድኖች የመጡትን በረከት ብንናገርባቸው ምንኛ ፈውስ ይሆናል! በሌላ ቡድን ውስጥ ያየነውን መልካም የሆነውን ነገር መናገር ። የእግዚአብሔር በረከት በእኛ ላይ እንዲመጣ መፀለይ እንችላለን። እንዲሁም በእኛ ላይ ለፍፃሜአችን የሚሆን ትንቢታዊ ቃላትን መናገር እንችላለን። ይህም መንፈስ ቅዱስ እንዲያነሳሳን ወይም መልእክትን እንዲሰጠን ይሆናል። ከዚህም በላይ ወደዚያ ፍፃሜ እንዲያደርሰን ራሳችንን መስጠት አለብን።

4) **ይህን እንዴት በተግባር ላይ እናውለዋለን።**

- የሌላ ብሔር የሆኑትን ሰዎች ምን ያህል እንደምናደንቃቸውና እንደምንቀበላቸው መናገር እንችላለን፤ እንዲሁም እግዚአብሔር እንዲባርካቸው ምን ያህል እንደምንፈልግ እና በሁሉም ንግግሮቻችንም ጭምር ለእነርሱ መንገር።

- የተለየ የስብሰባ ጊዜ /የቤተክርስቲያን ፕሮግራም ለማድረግ ጊዜ ወስደን ለሌላ ብሔር ምን ያህል አድናቆት ወይም ክብር እንዳለን መናገርና ምን ያህል ተባርከው ማየት እንደምንፈልግ ማሳየት።

- የሌለውን ብሔር ወገኖች ከማንኛውም ጥቃት ለመጠበቅ መከላከልና ስለ እነርሱ መልካም ነገሮችን መናገር፤ በተለይም በእኛ በራሳችን ብሔር ወገኖች ሲተቹና ሲፈረድባቸው በምንሰማበት ጊዜ ይህን ማድረግ አለብን።

**ከራስ ጋር ማዛመድ**

- ስለሌላው ብሔር ልትናገረው የምትችለው መልካም ነገሮች ምን እንደሆነ አስብ
- በእነሱ ላይ ምን አይነት በረከቶችን መጥራት/መጸለይ ትፈልጋለህ/ሽ?

**ቁልፍ ሀሳቦች**

- አንደበት ህይወትንም ሆነ ሞትን ለማምጣት ከፍተኛ ኃይል ያለው ነው።

- የንጉስ ካህናት እንደመሆናችን መጠን በእግዚአብሔር ስም በረከቶችን የምናውጅ ሰዎች ነን።
- የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች እርስ በርስ ሲከባበሩና እውቅና ሲሰጣጡ እርቅ ሠላም በህይወታቸው መተግበር ይጀምራል።

# ትምህርት አስራ አምስት

## ከዚህ ወዴት እንሄዳለን?

## የተፈወሰች ቤተክርስቲያን እንዴት የፈወሰና የእርቅ ማዕከል በመሆን በማህበረሰቡ ላይ ተፅዕኖ ታመጣለች፡፡

ይህ መጽሐፍ እግዚአብሔር ቤተክርስቲያኑን እየፈወሰ የእርሱም ህዝቦች ለሚኖሩበት ለራሳቸው ማህበረሰብ የፈውስና የእርቅ ማዕከል መሆን እንዲችሉ ለማሳየት ነው። ይህ ትምህርት ሰውን የሚያዘጋጅ የዝግጅት ትምህርት ነበር፣ አሁን ወደ ተግባር የምንለወጥበት ጊዜ ነው፤ እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያኑ ያለውን ፍላጎት የምናጠቃልልበትና ዳግም የምናጸናበት ሲሆን እንዲሁም ቤተክርስቲያን የዘር /ብሔር/ ልዩነቶችንና ግጭቶችን ቀዳድዳ በመጣል ለሀገር ፈውስ ልታመጣ የምትችልበትን ድርሻዋን መወጣት የምትችልበትን አንዳንድ መንገዶች እንዳስሳለን ፡፡

### 1) የእግዚአብሔር መሻት(ፍላጎት) ለቤተክርስቲያን ምንድን ነው?

ይህንን ስታነብ እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያኑ ያለው ፍላጎት በአንተ ሁኔታ ውስጥ እየተፈፀመ መሆኑን አስብ፡ ነገሮችን ለመለወጥ ምን ማድረግ ትችላለህ?

ሀ) በመጀመሪያ የእግዚአብሔር ህዝብ መፈወስ አለበት፡፡ እኛ መቀበል ያልቻልነውን ለሌሎች ሰዎች መስጠት አንችልም፡ (የሐዋ. 3፡6) ፡፡ የእግዚአብሔርን ማጽናናት ለራሳችን በተቀበልን ጊዜ እኛም ለሌሎች መስጠት እንችላለን (2ኛ ቆሮ 1፡3-4)

ለ) ኢየሱስ ከሁሉም የበለጠ የህክምና ባለሞያ ( ዶክተር) ነው። እርሱ የተሰበረውን ልብ እንዴት አድርጎ እንደሚፈውስ ያውቃል፡፡ እርሱ ወደ ምድር የመጣበት ዋናው ምክንያት ኃጢአታችንንና ህመማችንን በመስቀል ላይ ለመሸከም ነው (ኢሳ 61፡1-3፣ ኢሳ 53፡4-5፣ 2ኛ ቆሮ. 5፡17-19፣ 1ኛ ጴጥ. 2፡24)። እኛ ህመማችንን እንዲሁም ኃጢአታችንን ወደ እርሱ በማምጣት የእርሱን መጽናናት መቀበል አለብን (መዝ. 55፡22፣ 1ኛ ጴጥ. 5፡7)፡፡

ሐ) እግዚአብሔር ከምንኖርበት ማህበረሰብ የተለየን አድርጎ ሊሰራን ይፈልጋል (ዮሐ 17፡16) ። ምክንያቱም በተለየ ሁኔታ እንድናስብ ስለሚፈልግ (ሮሜ 12፡1-2) አእምሮአችንን በማደስ ህይወታችን መለወጥ ይፈልጋል (ፊሊ 2፡ 5፣ 2ኛ ቆሮ 10፡5) ።

መ) እግዚአብሔር ማንኛውንም ነገር በራሱ ህዝቦች መካከል የገባውን የሚለያይ ግድግዳ እንዲፈራርስ ይፈልጋል (ኤፌ 2፡14-14) ። እኛ የእርሱ ቅዱስ ህዝብ ዜጎች እንድንሆን ይጠራናል (1ኛ ጴጥ 2፡9) ። እንዲሁም ማንኛውንም ተፈጥሮአዊ እንቅፋቶችን (ክፍተቶችን) የሚያልፍ እውነተኛ የጠበቀ ህብረት እንድናሳይ ይጠራናል።

**ተስፋ ምንድ ነው?**

**ሰማያዊ ተስፍ፡**- ሕይወት ያለው ምድር ላይ ብቻ አይደለም፣ እኛ ከምንገምተው በላይ የከበረ ቦታን እግዚአብሔር ለልጆቹ አዘጋጅቶላቸዋል። 2 ቆሮንቶስ 4:17-18) ይህም ስለ ሕይወታችን እና ስለ መከራ ዘላለማዊ አመለካከት ይሰጠናል እናም በብዙ ችግሮች መካከል እንኳን ደስ እንዲለን ያስችለናል።

**ለመለወጥ ያለ ተስፋ ፡**- እግዚአብሔር ከቤተክርስቲያን የሚፈልገው መንግሥቱን (የእግዚአብሔርን አገዛዝ እና መመርያ ) በምድር ላይ ለማምጣት እንድንትተጋ፣ጽድቅንም አንድንለማመድ (እንድንኖር) ይፈልጋል (ማቴ. 6፡ 10)። ብዙ ጊዜ ቤተክርስቲያን የምታስበው ስለ መንግሥተ ሰማያት ብቻ ነው፣ የእግዚአብሔርን

መንግሥት፣ በምድር ላይ ለማምጣት ቾል ብላለች።

ሠ) አስፈላጊ በሆነበት ሥፍራ ሁሉ፣ ቤተክርስቲያን ለዓለም ብርሃን ለመሆን ሲገባት በወደቀችበት በማንኛውም መንገድና በዙሪያችን ላለው ዓለም ምንም ልዩነት ባላደረገችበት ንስሀ መግባት ይገባታል። እያንዳንዱ ሰው ስለራሱ የገዛ ድካሙ (ስህተቱ)ና ኃጢአቱ ንስሀ መግባት አለበት። ነገር ግን ቤተክርስቲያን በአጠቃላይ በካህናታዊ መታወቂያዋ (መለያዋ) ባልተገለጠችበት፤ እንዲሁም በስም ብቻ ቤተክርስቲያን በሆነችበት ጉዳይ በአዳባባይ ንስሀ የምትገባበት ሥፍራም ነው።

ረ) እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን በፍቅር ውስጥ እንድትሆን ይፈልጋል (ዩሐ 13፡ 34-35፣ ሮሜ 12፡9-21፣ ቆላ 3፡12-14፣ 1ኛ ተሰ 3፡12፣ 1 ጴጥ 1፡22) ። ፍቅር በዓለም ላይ ከሁሉም የበለጠ የፈውስ ኃይል ነው።

ሰ) እግዚአብሔር ቤተክርስቲያኑ የቤተሰብ ማዕከል እንድትሆን ይፈልጋል። ይህም በተለይ በማህበረሰቡ ውስጥ ዘመዶቻቸውን ያጡት ሰዎች ወይም በሰዎች የተካዱ ሰዎች የሚጠለሉበት እጅግ ወሳኝ የሆነ ሥፍራ ነው። በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለው ግንኙነት ሰዎች በህይወታቸው ያጡትን (አባት፣ እናት፣ ወንድ ልጆች፣ ሴት ልጆችና የመሳሰሉትን) ሰዎች ሚናቸውን መልሰው የሚያገኙበት ሥፍራ ነው (መዝ. 68፡6፣ ማቴ 12፡50፣ ዮሐ 19፡27፣ ኤፌ 2፡19፣ 3፡15፣ 1ኛ ጢሞ 6፡1-2፣ ዕብ 2፡11) ።

ሸ) እግዚአብሔር የተስፋ አምላክ ስለሆነ ቤተክርስቲያን የተስፋ መገኛ ሥፍራ መሆን አለባት (ሮሜ 15፡ 13) ። ሀገራት ወደ እርሱ ሲመለሱ እርሱ ተስፋን ይሰጣቸዋል (ማቴ 12፡21) ። ምክንያቱም የእርሱ እቅድ ለልጆቹ ሁልጊዜ መልካም ነውና (ኤር 29፡11) ።

ቀ) ቤተክርስቲያን ለሀገርም ሆነ ለማህበረሰብ የነብያት (ትንቢታዊ) ድምፅ መሆን አለባት። ይህም ማለት ቤተክርስቲያን ማንኛውንም ዓይነት ኢፍትሀዊነት ተቃውማ መናገርና የእግዚአብሔርን የልብን ሀሳብ ማወጅ አለባት።

በ) ቤተክርስቲያን በዓለም ውስጥ ከሚታየው የተለየ ዓይነት የአመራር ዓይነት ማሳየት አለባት፡፡ ይህም የአገልጋይ መሪነት ነው (ማቴ 20፡25-28፣ ዮሐ 13፡12-17፣ ፊሊ 2፡3-8) ። እንዲሁም በራስ ወዳድነት ምንም ማድረግ የሌለባት መሆን አለባት።

## 2) ቤተክርስቲያን የፈውስና የእርቅ ማዕከል መሆን እንድትችል የሚያደርጉ ተግባራዊ መንገዶች።

ከዚህ በታች ያለውን ተግባራዊ የሚሆኑ ሀሳቦችን በምታነብበት ጊዜ ቤተክርስቲያንህ እስካሁን እያደረገች ያልሆነውን ምልክት አድርግበት። እንቅፋቶቹንና የመፍትሔ ሀሳቦችን ለይተህ አስቀምጥ።

- ሰዎች ወደ ተግባር (ወደ እርምጃ) እንመዲጡ ለማነሳሳት ምን ማድረግ ትችላለህ?
- ሌሎች ልትጠቀምባቸው የሚገቡ መርሆዎች ምንድን ናቸው?

## *ፈውስ*

- በእምነታቸው ዋጋ የሚከፍሉትን፤ ብቸኝነት የሚሰማቸውን (ብቸኛ የሆኑትን) ፣ ሀዘን ያጠቃቸውን ፣ የተጎዱትን፤ ተስፋ የቆረጡትን መጎብኘት
- ሰዎች የራሳቸውን ችግር በግልጥነት እንዲናገሩ ማደፋፈር (የውስጥ ህመማቸውን፣ ጥርጣሬአቸውን፣ ጥያቄዎቻቸውንና፤ አስፈሪ ትዝታዎቻቸው ተመልሶ እንዳይመጣባቸው) በርህራሄ ልብና በሀዘኔታ ልብ ጊዜ ወስዶ በመስማት።
- ስለተጎዱት ሰዎች መፀለይና ህመማቸውን ወደ ኢየሱስ እንዲያመጡ ሰዎችን መረዳት።
- በመጋቢነት አገልግሎት ሊያገለግሉ የሚችሉትን ሰዎች (ወንዶችንና ሴቶችን) በግልፅ የርህራሄ ልብ ያላቸውን በማሰልጠን ለመንጋው እንክብካቤ ማድረግ እንዲችሉ መርዳት።
- የውስጥ ቁስላቸው እንዲፈውስ ለማድረግ የተለየ ጥናት ማካሔድ
- ሰዎች አንዱ ሌላውን መርዳት እንዲችሉ በትናንሽ ቡድን ፀሎት እንዲደርጉ ማበረታታት፣ አንዱ ሌላውን መስማትና የሌላውን ሰው ሸክም መሸከም እንዲችሉ (ገላ 6፡2)።
- በተመሳሳይ መንገድ የተጎዱትን የሚረዱ የድጋፍ ቡድኖችን ማቋቋም ሌሎችን በጥሩ( በወዳጅ) ልብ እንዲረዱ ማበረታታት።

## *ከዚህ በታች ስላሉት ሀሳቦች መስበክ*

- ለተጎዱት የእግዚአብሔር የርህራሄ ልብ እንዲመጣ
- ኢየሱስ አዳኝ፣ ፈዋሽ እና ሀጢያታችንን፣ ህመማችንን የሚሸከም መሆኑን
- ሁሉንም ሀዘናችንን፣ ልብ ስብራታችንንና ጭንቀታችንን ወደ መስቀሉ ማምጣትን በተመለከተ፤
- ስለ እውነተኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይቅርታን በተመለከተ፤
- የእግዚአብሔርን የይቅርታ መንገድ ፤

- ማንነቱ የታደሰለት የእግዚአብሔር ቅዱስ ህዝብ ዜጎች መሆንን በተመለከተ
- ግንኙነት/ ህብረትን እንደ ክርስቶስ አካል መውደድ የሚፈጠሩ ክፍፍሎችን እንዲያቀራርብ

***በማህበረሰቡ ውስጥ በድህነት ጠለል ያሉትን እና ችግረኛ የሆኑትን ለመርዳት ድጋፍ መስጠት***

- በተፈጠረው የግጭት (ውዝግብ) ሁኔታ የቁሳቁስ ድጋፍ መስጠት፤
- ማህበረሰቡ ለራሱ የማልማት እርምጃዎችን የሚወሰድበትን ፕሮግራሞች መምራት፤

***እርቅ ማካሄድ***

- በልዩነት መሀል ስላለው አንድነት እግዚአብሔር ለቅዱስ ህዝብ ያለውን አላማ ማስተማር
- ለሀገር መፀለይና ሌሎችም ይህን እንዲያደርጉ ማነሳሳት፤
- ያለፈውን ኃጢአት መናዘዝና ንስሀ መግባት እና ሁሉንም ዓይነት ፍረጃዎችን ለማስወገድ መፈለግ፤
- የቤተክርስቲያን አባላት ከሌላ ብሔር የሆኑትን ሰዎች በእንግድነት ለመቀበል እንዲችሉ ከእነርሱ ጋር ወዳጅነትን እንዲመሠርቱ ማደፋፈር፤
- የሌላን ብሔር (ተወላጅ) ሰው በችግሩ ጊዜ ለመርዳት የሚሠሩበትን መንገድ መፈለግ፤
- በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ማንኛውንም ዓመፅና ኢፍትሓዊነት ተቃውሞ መናገር የእግዚአብሔርን የጽድቅ ህይወት ዘይቤ ማሳየት።
- በማህበረሰቡና በማህበረ ምዕመናኑ (ጉባኤ) ውስጥ አንድነትና የእርቅ ሠላም ህይወት እንዲኖር መግለጥ
- ሌሎቹ ቡድን( ዎች) ሲበደሉ ወይም ሲፈርዱባቸው ( ሲተቿቸው) ሲሰሙ መከላከል (ድጋፍን ማሳየት)

- ❖ በብሔር ብሔረሰብ አባላት መካከል የጋብቻ ጥምረት እንዲኖር ማድረግና ጥበቃ ማድረግ፣
- ❖ የሌላ ብሔር ቋንቋ ለመማር ጥረት ማድረግ፤ የእነርሱን የአምልኮ ዝማሬዎች መማርና በእርሱም ማምለክ።

### 3) **ቤተክርስቲያን ማብራት አለባት**

ቤተክርስቲያን ተነስታ ብርሃኗን ለማብራት ጊዜው ነው። ተነስቶ ማብራትና ተልዕኮውን መፈፀም ለዓለም ብርሃንና ተስፋ ለመሆን ያስችላል፡፡ ከዚያም ሌሎች ወደ ብርሃኑ እንዲሳቡ ያደርጋል (ኢሳ 60፡ 1-3) ። እግዚአብሔር በእውነት በቤተክርስቲያኑ ውስጥ እንዳለ ያያሉ፤ እንዲሁም የእርሱ መንገድ ወደ ህይወት ይመራል (ዘካ 8፡23) ።

### **ከግል ህይወት ጋር ማዛመድ**

- ❖ ቤተክርስቲያን በሀገርህ ውስጥ የፈውስና የእርቅ ሠላም መካከል (ማዕከል) እንድትሆን አሁን ያላት ተስፋ ምንድን ነው?
- ❖ አንተ በዚህ ውስጥ የምትጫወተው ሚና ምንድን ነው?

### **ቁልፍ ነጥቦች**

- ❖ የተፈወሰችና የታደሰች ቤተክርስቲያን ለሀገር ትልቅ ተስፋ ናት፡፡
- ❖ ቤተክርስቲያን ሚናዋን (ተልዕኮዋን) ከተወጣች ማህበረሰቡ የተፈወሰ እና የታደሰ ይሆናል፡ ፡
- ❖ ሁሉም አባላት የራሳቸውን ድርሻ ለመውጣት ይችላሉ፡፡

# አባሪ

## ሀ/ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር እና መከራን በተመለከተ ተጨማሪ ሀሳቦች

የዚህ ክፍል ዋና ዓላማ በእግዚአብሔር ሉአላዊነት እና በሰዎች ነፃ ምርጫ ስላለው ግንኙነት የበለጠ ለመረዳት ቅዱሳን መጻህፍት በጥልቀት መመርመር ነው። በተጨማሪም በዚህ ትምህርት ላይ አንዳንድ የተለመዱ ተቃውሞዎች እና መፅሃፍ ቅዱስስ ስለእነሱ ምን ይላል የሚለውን እንመለከታለን።

***በዓለም ላይ የሚሆነው ማንኛውም ነገር የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው?***

በዘፍ 1 ና 2 እንደምንመለከተው ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር አምሳል በክብር እንደተፈጠረ እናያለን። እግዚአብሔር ሰውን ፈቃዱን እንዲያደርግ ባያስገድድም ፣ ምርጫው ግን ከእርሱ ጋር ህብረት እንዲኖረን ነው ።

መዝ 115፡16 እንዲህ ይላል *«የሰማያት ሰማይ ለእግዚአብሔር ነው። ምድርን ግን ለሰው ልጆች ሰጣት*‹‹እግዚአብሔር›› ይህቺን ምድር እንድናስተዳድር ኃላፊነትን ሰጠን በፍጥረት ሁሉ ላይ እንድንገዛና እንድናስተዳድር አደረገ። የእርሱ ዕቅዱ ለእርሱ በመታዘዝ እንድንኖር ነበር፣ የእርሱን ዓላማ በምድር ላይ እንድንፈፅምም ነበር። ነገር ግን ሰው አመፅንና ከእግዚአብሔር ተለይቶ መኖርን መረጠ። አስከፊውን ውጤት ለማየት ዘፍጥረት **3ን** እንመልከት እና እግዚአብሔር ምን ሊሰማው እንደሚችል እናስብ።

እግዚአብሔር ሁሉንም ዓይነት ኢ-ፍትሀዊነት ይጠላል። ስለዚህ እርሱ የኢፍትሀዊነት ምንጭ ሊሆን ፈፅሞ አይችልም (ምሳ 6፡16-19፣ ዘካ 8፡16-17፣ መዝ 5፡6፣ መዝ 50፡16-21)። እርሱ በሁሉም ዓይነት ሞት አይደሰትም (ህዝ 18፡ 32፣ ህዝ 33፡11)። እርሱ ክፋትን ይጠላል፤ እንዲሁም እርሱ ማንንም ሰው በክፉ አይፈትንም (ያዕ 1፡13)። የገዛ ራሳችን የኃጢአት ምኞት (መሻት) ወደ ክፋት ሁሉ ይመራናል፤ በመጨረሻም ወደ ሞት ይመራናል (ያዕ 1፡14፡15)።

ይህን ልንስት (ልንታለል) አይገባም።እግዚአብሔር በጎ ስጦታና ፍፁም በረከት ብቻ ለእኛ ሊሰጠን ይፈልጋል (ያዕ 1፡ 16-17) ። እርሱ በየዕለቱ አይለዋወጥም፤ የእርሱን ፈቃድ መታመን እንችላለን። እግዚአብሔር ቅዱስ ነው። በእርሱ ዘንድ ጨለማ ከቶ የለም (1 ዮሐ 1፡5፣ 2፡16) ።

ኤር 29፡11-13 ያለውን ክፍል ተመልከት። እግዚአብሔር ለአንተ ምን ይናገራል? ለቤተሰብህ፡ ለብሔርህስ ( ላለህበት ማህበረሰብ)? ለሀገርህስ ምን ይናገራል?

**በተለምዶ የሚነሱ ተቃውሞ**

በልባችን ውስጥ አንዳንድ ተቃውሞዎችና ጥያቄዎች አሁንም ሊኖሩ ይችላሉ።

***እግዚአብሔር እየተፈጠረ ያለውን ነገር ያውቃል፤ ስለዚህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነበር/ ነው?***

ብዙውን ጊዜ ሰዎች እንዲህ ይላሉ ነገር ግን እግዚአብሔር ሁሉን ያውቃል ማለት ክፋት እንዲሆን የእርሱ ፈቃድ ነው ማለት ነው? ብዙውን ጊዜ ትንቢቶች እንደማስጠንቀቂያ ይሰጡ ነበር፤ ይህም ሰዎች ንሰሀ እንዲገቡ ለመምከር ነበር (ኤር 18፡7-10 ተመልከት) ። ይህም ከዮናስ ስብከት በኋላ ነነዌ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው።

በሩዋንዳ የሆነውን ብንመለከት አንዳንድ ክርስቲያን መሪዎች እንዳረጋገጡት እግዚአብሔር *«የደም ጎርፍ» (የደም ወንዝ) እና ብዙ መከራ ይሆናል* ብሎ ህልምና ራዕይ ለሰዎች በሰጣቸው ጊዜ እነርሱ ግን በትክክል ለእርሱ መልስ አልሠጡም ነበር። ይህን እንደ እጣ ፈንታ በመቀበል እግዚአብሔር ከተናገረ ምንም የሚቀር እንደሌለ በማሰብ የሚፈጠረውን ነገር ተቀበሉት። አሁን ግን ሁኔታው ከሆነ በኋላ ለማረጋገጥ የቻሉት በሀገሪቱ መሪዎች ፍላጎት የሚሆነው

ከመሆኑ በፊት ስለ ሁኔታው እንዲማልዱና የሀገሪቱን መሪዎች የክፋትን ዓላማ በመቃወም እንዲነሱ እግዚአብሔር ማስጠንቀቂያ ሰጥቷቸው እንደነበር ነው።

በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የእግዚአብሔር ልብ ምን እንደሆነ በግልፅ እናያለን። በሉቃ 13፡ 34 ኢየሱስ ከተማይቱን አይቶ እንዲህ አለ ‹‹.... *ዶሮ ጫጩቶችዋን በክንፎችዋ በታች እንደምትሰበስብ ልጆችሽን እሰበስብ ዘንድ ስንት ጊዜ ወደድሁ እናተም አልወደዳችሁም*›› በግልፅ ይህ ክፍል የሚያሳየን የእግዚአብሔር ፈቃድ እነርሱን ለመውደድና ለመጠበቅ ነበር። ኢየሱስ ግን አለቀሰላት *«ለሰላምሽ የሚሆነውን በዚህ ቀን አንቺስ ስንኳ ብታውቂ... አሁን ግን ከዓይንሽ ተሰውሮአል*። (ሉቃ 19፡42)

ከዓይናቸው ፊት ማነው ነገሮችን የሰወረው? 2ኛ ቆሮ 4፡4 እንደሚነግረን ይህን ያደረገው ሰይጣን ነው፤ የዚህ ዓለም አምላክ የሆነው ማለት ነው። ኢየሱስ ለሰላማቸው የሚሆነው ምን እንደሆነ ነግሯቸዋል። ይህም ጠላቶቻቸውን መውደድና ለሚያሳድደዱአቸው መፀለይ ነበር። እነርሱ ግን ይህንን መልዕክት ተቃወሙና ለጦርነት ተዘጋጁ። እነርሱ የመረጡት ምርጫ አሳዛኝ መዘዝን ይዞ እንደሚመጣና ግልፅ የሆነ ሀዘን እንደሚያመጣ ኢየሱስ ያውቅ ነበር። ምንም እንኳን አስቀድሞ ትንቢት ተናግሮ ቢሆንም በግልፅነት የሚያሳየው የሆነው ነገር እርሱ የሚፈልገው ነገር አይደለም/አልነበረም።

በ70 ዓ/ም በሮም ላይ ዓመፅ ተነሳ። አይሁዶች ጠላታቸውን (ሮምን) ለመዋጋት ሞክረው ተሸንፈዋል (ጠፍተዋል)፤ እየሩሳሌም ሙሉ በሙሉ ፈፅማ ተደመሰሰች፣ ታላቅ መከራ ሆነ እና ምንም የማያውቁ ህፃናት በግፍ ተጨፈጨፉ። እግዚአብሔርም አዘነ ። በየትኛውም ጊዜ ቢሆን የሀገር መሪዎች የእግዚአብሔርን ድምፅ ለመስማት እምቢ (ፈቃደኛ ባልሆኑ) ጊዜ ብዙ ንፁሃን ሰዎች መከራ ውስጥ ይገባሉ፤ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም። እንዲያውም ከአመፀኛ መሪዎች የተነሳ የሚመጣውን መከራ እርሱን ያሳዝናል። የሀገራት መሪዎች የራሳቸውን ዜጎች ለመጠበቅ ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው።

***ስለኢዮብ ምን እንላለን?***

ብዙ ሰዎች በእዮብ ላይ የደረሰው ነገር የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ብለው ለመከራከር ኢዮብን ይጠቅሳሉ። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ግን ምን ማለት እንደሆነ ለማስረዳት ሌላ እይታ እንዳስሳለን። እዮብ መከራን እንዲቀበል የሰይጣን እንጂ የእግዚአብሔር ሀሳብ አልነበረም። እግዚአብሔር በኢዮብ ይመካ ነበር። ነገር ግን ሰይጣን የሚለው ኢዮብ እግዚአብሔርን የተከተለው እርሱ ስለባረከው ነው ይላል *«ያለውን ሁሉ ብንወስድበት እርሱ ከዚህ በኋላ ፈፅሞ እንደማይከተልህ እነግርሃለሁ»* አለ። እግዚአብሔር ከዚያ ሲመልስለት *«ፈፅሞ ይህ አይሆንም›* ሰይጣንም መለሰለት *«ማንም ሰው ካደረግህበት የበረከት ዋስትና ውጪ እንደማይከተልህ ታውቃለህ፡ እኔም የምናገረው ትክክል ስለሆነ አንተ ታፍራለህ እኔ እውነተኛ እሆናለሁ»* አለ።

ምንም እንኳን ይህ እግዚአብሔርን ባያስደስተውም (ቅር ቢያሰኘውም) ኢዮብን ይፈተን ዘንድ ለሰይጣን ፈቀደለት (ተወው) ። ይህን ሲያደርግ ኢዮብ ፈተናውን እንደሚያልፍና ፈፅሞም እንደማይክደው ስለሚያውቅ ነው። ስለነበረው ክስ ግን ማንም ሰው አያውቅም ነበር ። የኢዮብ ጓደኞች ኢዮብ ኃጢአትን እንደሰራ አድርገው ተናገሩት ኢዮብ ግን ተቃወማቸውና እርሱ ጻድቅ እንደሆነ ነገራቸው። የእርሱ ጓደኞች በመንፈሳዊው ዓለም ምን እየተደረገ እንደነበር ምንም የሚያውቁት ነገር አልነበረም።

በመጨረሻም እግዚአብሔር ለእዮብ ተገለጠ። ነገር ግን እግዚአብሔር ፈፅሞ ሁሉንም ነገር ለኢዮብ አላብራራለትም። እግዚአብሔር እዮብን *«ሰይጣን እየፈተነህ ነው ፀንተህ ቁም»* አላለውም። ምንም ዓይነት ማብራራት ሳይፈልግ እግዚአብሔርን መታመን የኢዮብ ምርጫ ነው። እግዚአብሔር እዮብን ያለው ነገር ቢኖር *እኔ እግዚአብሔር ነኝ ሁሉንም ነገር የፈጠርኩ ነኝ። እኔን ለማመን ፈቃደኛ ነህ?* እዮብ በመጨረሻ ያረጋገጠው ነገር ቢኖር እዮብ እግዚአብሔርን በእግዚአብሔርነቱ እንደሚወደውና ሰይጣን በኢዮብ አሸናፊነት ተሸንፎ ዝምታን እንደመረጠ እንመለከታለን።

***ስለፈርኦን ምን እንላለን?***

ሰዎች ብዙውን ጊዜ የሰውን ምርጫ የእግዚአብሔር ኃላፊነት ለማድረግ እንደ ምሳሌ አድርገው ፈርኦንን ይጠቅሳሉ። *«ነገር ግን እኔ ልቡን አደነደንኩ* (ዘፀ 7፡3-4)። ይሁንም እንጂ ቀጣይ ጥቅሶች ፈርአን ለወሰናቸው ውሳኔዎች ያለበትን ኃላፊነቶች ላይ ያተኩራል (ዘፀ 7፡14፣ 8፡ 32)። በመቅሰፍቶች ታሪክ ላይ አተኩረን ስንመረምር ለመጀመሪያ ጊዜ እግዚአብሔር የፈርኦንን ልብ ያደነደነበት ማሳያ በዘፀ 9፡12 ላይ ሲሆን ይህም ፈርኦን ደጋግሞ የራሱን ልብ ካደነደነ በኋላ ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔርን ጥያቄ ከተቃወመ በኋላ ነው። (መዝ 95፡8፣ በዕብ 3፡8፣ 4፡7 ላይ ተደጋግሟል) እንደሚያሳየን የልብ ደንዳናነት አደጋ ልባችን ከእግዚአብሔር ፀጋ ውጪ ያደርጋል። ምናልባት የፈርኦንን አጠቃላይ ሁኔታ በተሻለ መንገድ ለመረዳት እግዚአብሔር በመጨረሻ ያረጋገጠው ነገር በራሱ የገዛ ምርጫ ይህ እንደሆነና ሁኔታዎችን ተጠቅሞ ከግብፅ አማልክቶች በላይ ሉዓላዊ አምላክ መሆኑን አሳየ።

## *እንደ ኢሳ 45፡ 7 ያሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንዴት ልትረዳው ትችላለህ።*

ኢሳ 45፡ 7 እንዲህ ይላል *«እኔ ብርሃንን ሠራሁ፤ ጨለማውንም ፈጠርሁ» ደህንነትን እሠራለሁ ክፉትንም እፈጥራለው… እነዚህን ሁሉ ያደረግሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ*› አንዳንዶች በእጣ ፈንታ እንደሚያምኑ እንደ አቋም እንደሚይዙት ይህን የህይወት አካሄድ የሚያረጋግጥ ይመስላል ። እግዚአብሔር መልካምን ወይም ክፉን ሊልክ እንደሚችል ያምናሉ። ይህን እምነት ያለው በራሱ ለሚያደርገው እርምጃ ኃላፊነትን እንዳይወስድ የሚያሸሽ ነው።

ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በጥልቀት እንመልከት፤ ይህ በእውነት እግዚአብሔር የኃጢአታችን ምንጭ ነውን? ነገር ግን ኃጢአታችን የእርሱን ፈቃድ በመቃወም የመጣ እንደሆነ እናያለን። በአዳም አመፃ ምክንያት በዘፍ 2፡16-17 እንመልከት *«እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው ከገነት ዛፍ ሁሉ ትባላለህ። ነገር ግን መልካሙንና ክፉውን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና»*። ብርሃንና ጨለማ በትክክል ተለይቷል። ነገር ግን አዳም ጨለማውን መረጠ ከዚያም ጥፋት ተከተለ) ።

በአንድ ክፍል ውስጥ ጨለማ ለምን ይፈጠራል? ብርሀን ወደ ክፍል ውስጥ እንዳይገባ ብናግድም (ብንጋርድም) ብርሃን አሁንም ቢሆን አለ። ጨለማ የሚመጣበት ብቸኛው መንገድ

ብርሃንን በማስወገድ ነው። ጨለማ የብርሃን አለመኖር ውጤት ነው። እግዚአብሔር ብርሃንን ወደ ሰዎች ላከ ግን ከብርሃን ይልቅ ጨለማውን ወደዱ (ዮሐ 3፡19)። ሰው ብርሃንን በማይፈልግበት ጊዜ እግዚአብሔር ራሱን ከዚያ ያርቃል። ጨለማም በዚያው ሥፍራ ይቀራል። በተመሳሳይ እርሱ የሠላምንና የበረከትን መንገድ አሳይቶናል፤ ነገር ግን እኛ ላለመቀበል ከገፋነው እግዚአብሔር በረከቱን ከመስጠት ራሱን ያርቃል፤ እንዲሁም ውጤቱ ጥፋት ያመጣል። እኛ በጣም የከፋውን ፍርድ በህይወታችን የምንለማመደው እግዚአብሔር እኛን ህይወታችንን ከመጠበቅ እጁን በሚያነሳበት ጊዜ የሚሆን ነው። ይህን በሮሜ 1 ላይ በተደጋጋሚ እንመለከተዋለን። በኃጢአታቸው ምክንያት ያደረጉት ምርጫ በህይወታቸው አስፈሪ የሆነ ነገር እንዲለማመዱ *«እግዚአብሔር አሣልፎ ሰጣቸው»።* ኃጢአት አደገኛ የሆነ መዘዝ አለው *«የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና»* (ሮሜ 6፡23)።

በጠፋው (በአባካኙ) ልጅ ታሪክ ላይ እንደምንመለከተው፣ እግዚአብሔር በእኛ ህይወት እንዲሆን ከሚፈልገው ነገር በተቃራኒ የሆነው እንዲሆን ሊፈቅድ ይችላል። ስለዚህም የተሳሳተ ምርጫችን የሚያስከትለውን ውጤት አይተን ወደ እርሱ እንድንመለስ ለፈቃዳችን ሊተወን ይችላል።

## ***እግዚአብሔር በአንዳንድ ጉዳዮች ጣልቃ ገብቶ በሌሎች ግን ጣልቃ የማይገባው ለምንድን ነው?***

ፀሎት እጅግ ወሳኝ ነገር ነው። ስንፀልይ እግዚአብሔር በሁኔታዎች ውስጥ ጣልቃ እንዲገባ እየጋበዝነው ነው። የእግዚአብሔር ህዝብ ሲፀልይ እግዚአብሔር ጣልቃ ይገባል። (2ኛ ዜና 7፡14) ፡
፡

በዘፍ 1፡28 እግዚአብሔር ዓለምን እንድንገዛና እንድናስተዳድር ነግሮናል፡፡ *«ምድርን ለሰው ልጆች ሰጣት»* (መዝ 115፡16) እግዚአብሔር ወደ ሁኔታዎች ራሱን ለማስገባት አይመርጥም፡፡ ነገር ግን እኛ በፀሎታችን እርሱን ወደ እኛ ሁኔታ እንድንጋብዘው ይናፍቃል፡፡ እርሱ ከእኛ ተለይቶ ለብቻው መሥራት አይፈልግም፡፡ ከእኛ ጋር መሥራት ይፈልጋል፡፡ ፀሎት ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት አብረን እንደምንጓዝ ለመማር መልካም አጋጣሚ ይሰጠናል፡፡ በወንጌላት ውስጥ የተፃፉት አብዛኛው ተዓምራት ሰዎች በእምነት ወደ ኢየሱስ ሲቀርቡ ነው፡፡

ነገር ግን ብዙውን ጊዜ ሰዎች በሚፀልዩበት ጊዜ ተዓምራታዊ ጣልቃ ገብነት አልነበረም፡፡ ይህን ለመረዳት አስቸጋሪ ነው፤ ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ እያንዳንዱ ሰው ነፃ ሲወጣ አናይም፡፡ በሐዋ 12፡ 2-11 ያዕቆብ በእሥር ቤት ተገደለ፤ ነገር ግን ጴጥሮስ በተዓምራት ነፃ ወጣ፡፡ አንዳንዶች ይህ በእምነታችን መጠን ላይ የተመሠረተ ነው ይላሉ፤ ነገር ግን ዕብ 11 ይህንን አይደግፍም፡፡ ምንም እንኳን አብዛኞች የዕብ 11 ክፍል ስለተዓምራታዊ መዳን በእምነት መዳን ቢናገርም ከቁጥር 35 ጀምሮ ግን ሰዎች ያለምንም ተዓምራታዊ ድጋፍ  በአስፈሪ መከራ ውስጥ እንዳለፉ እናነባለን፡፡ ቁጥር 39 የእነርሱን እምነት ማጣት ማነስ ሲናገር አንመለከትም፡*«እነዚህ ሁሉ በእምነታቸው የተመሠከረላቸው ሲሆን*› ብሎ ይናገራል፡፡ የራዕይ መጽሐፍ ብዙ ሰማዕታት (ዋጋ የከፈሉ)እንዳሉ በግልጥ ይናገራል፡፡ አሁን ብዙ ምስጢር የሆኑና ብዙ መልስ ያልተሠጠባቸው ጥያቄዎች ሌላኛው የሰማይ ገጽታ ነው፡፡ እግዚአብሔር ለሁሉም ጥያቄዎቻችን ሁሉ መልስ አልሰጠንም፤ ነገር ግን በባህርይው ላይ ታምነን እንድንኖር ይጠይቀናል፡፡

አንድ እርግጠኛ ልንሆንበት የምንችለው ነገር አለ እሱም እግዚአብሔር ከችግር አምልጠው የተረፉትን ከችግር አምልጠው መትረፍ ካልቻሉት የበለጠ አይወድም፡፡ የቅዱሳኑ ደም በእርሱ ዓይኖች ፊት እጅግ የከበረ ነው (መዝ 72፡14፣ 116፡15) ፡፡ እግዚአብሔር የቅዱሳንን ሞት ኪሳራ እንዲሆን ፈፅሞ አይፈቅድም፡፡ (ዮሐ 12፡24-26)

# ለ/ አስደናቂውን ሰማያዊውን አባትህን ማወቅ

ኢየሱስ እንዲህ አለ *«እኔን ያየ አብን አይቷል»* (ዮሐ 8፡19፣ 14፡7-9) ። እርሱ የእግዚአብሔር ትክክለኛ ወኪል ነው (ዕብ 1፡3) ፣ እግዚአብሔር አብ በትክክል ኢየሱስን ይመስላል።

የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ስናጠና ፍፁም የሆነውን አባታችንን እንድናውቅ ይረዳናል

- ❖ እርሱ ይወደናል (ኤር 31፡3፣ ዮሐ 13፡1፣ 16፡27፣ ኤፌ 5፡1፣ 1 ዮሐ 3፡1)።
- ❖ ለእኛ ርህራሄ አለው (መዝ 103፡13፣ ማቴ 9፡36፣ ማቴ 14፡14፣ ሉቃ 15፡20፣ 2ኛ ቆሮ 1፡3)።
- ❖ በእኛ ይደሰታል (መዝ. 147፡11፣ 149፡4፣ ምሳ 8፡30-31፣ ሶፎ 3፡17)።
- ❖ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ይወደናል (ሮሜ 9፡16፣ 11፡6፣ ቲቶ 3፡4-7)።
- ❖ እኛን እስከሞት ድረስ ይወደናል (ዮሐ. 15፡13፣ ሮሜ 5፡8)።
- ❖ ለእኛ ያስባል (ዘዳ 32፡10-11፣ 1ኛ ጴጥ 5፡7)።
- ❖ የእርሱ ተወዳጅ ወዳጆች እንድንሆን ይጠራናል (ዘዳ 33፡12፣ ዮሐ 15፡13-15፣ ያዕ 2፡23
- ❖ ከእኛ ጋር የጠበቀ ህብረት ያደርጋል እንዲሁም በስማችን ይጠራናል (ኢዮብ 29፡4፣ ኢሳ 43፡1-2፣ ዮሐ 10፡14፣ 27)።
- ❖ ቀጣይነት ያለው ትኩረት ይሰጠናል (ዘዳ 31፡8፣ መዝ 34፡15፣ 139፡16፣ ማቴ 28፡20)
- ❖ ይመግበናል (መዝ 27፡10፣ ሆሴ 11፡1-4)።
- ❖ በችግር ውስጥ በምንሆንበት ጊዜ እርሱ ያፅናናናል (መዝ 23፡4፣ 71፡21፣ 94፡19፣ ኢሳ 51፡ 12፣ 2ኛቆሮ 1፡3-5)።
- ❖ ያበረታታናል፤ ይደግፈናል (ኢሳ 41፡8-12፣ ሉቃ 12፡32)።
- ❖ ታጋሽና ከእኛ ጋር በትህትና ይኖራል (መዝ 103፡8፣ ማቴ 11፡29፣ 2ኛ ቆሮ 10፡1፡1ኛ ጢሞ 1፡16፣ 2ኛ ጴጥ 3፡9)።
- ❖ የአካላዊ ፍላጎታችን ምን እንደሆነ ያውቃል (ዘዳ 33፡12፣ ኢሳ 40፡11፣ ማር 10፡16)።

- ❖ ይመራናል ያስተምረናል (መዝ 32፡8፣ ኢሳ 48፡17፣ ዮሐ 8፡12፣ 14፡26)።
- ❖ ሁሉን ያዘጋጅልናል (መዝ 23፡1፣ 34፡9-10፣ ፊሊ 4፡19፣ 1ኛ ጢሞ 6፡17)።
- ❖ መልካም (በጎ) ስጦታ ሲሰጠን ይደሰታል (ኤር 32፡ 40፣ ሉቃ 11፡13፣ ያዕ 1፡17)።
- ❖ ቸርና ይቅር ባይ ነው (መዝ 86፡5፣ ኤር 9፡24፣ ሚክ 7፡18-20፣ ኤፌ 2፡7)።
- ❖ ስለሚወደን በመልካም መንገድ እኛን ያርመናል (ኤር 46፡28፣ ዕብ 12፡5-11)።
- ❖ እናት ልጇን በምትወደው አይነት ፍቅር ይወደናል (ኢሳ 49፡ 15-16፣ 66፡13፣ መዝ 27፡ 10)።

**በእውነት እያንዳንዱ ሰው እንደዚህ ዓይነት ወላጅ ይናፍቃል።**

## ሐ) አሰቃቂ (አጋጣሚ) እና አሳዛኝ ሁኔታን መረዳት

***ዘርፉ ምሁራን ስለ አሰቃቂ አደጋ ( አጋጣሚ) እና ስለ ምልክቶቹ ምን ይላሉ።***

ለአሰቃቂ አጋጣሚ (አደጋ) የምንሰጠው ምላሽ፤ ምልክት በተመለከተ ያለን እውቀት በመላው ዓለም ከተሠራው ጥናት የተገኘ ነው። በተገኘው ውጤት መሠረት ሁሉም ሰዎች የስሜት ቀውስ ሲያጋጥማቸው

ተመሳሳይ ምላሽ እንደሚሰጡ ታውቋል። ምንም አይነት ነገር ተፈጥሮ ይሁን ምን፣ ተመሳሳይ የሆነ ምላሽ ይሰጣሉ፤ ሁሉም ሰው ላልተለመደ ሁኔታ የተለመደ መልስ ይሰጣል።

**በአሰቃቂ አጋጣሚ (የአዕምሮ ህመም) ችግር ውስጥ የሚያልፉ ሰዎች ወዲያውኑ የሚያሳዩት ምልክቶች**

**ሀ**) **አካላዊ**

- የልብ ምት ፍጥነት
- የሆድ ቁርጠት (ማስታወክና ተቅማጥ)
- የነርቭ መታወክ
- በላብ መጠመቅ
- የድካም ስሜት

**ለ**) **አዕምሮአዊ**

- የሀሳብ አለመረጋጋት
- የሀሳቦች መደጋገም ‹‹ምን እሆን ይሆን?›› የሚል ዓይነት
- በትክክል ለማሰብ አለመቻል በእንቅልፍ ብዛት ከነገሮች ለማምለጥ መሞከር

**ሐ**) **ስሜታዊ**

- ፍርሀትና ጭንቀት
- ሐዘን እና የልብ ስብራት
- ቁጣ
- ተስፋ መቁረጥ

**አሰቃቂ አደጋ** (**አጋጣሚ**) **የገጠማቸው ሰዎች ያለባቸው የረጅም ጊዜያት ተፅእኖ**

- አንድን ክስተት መላልሶ ማስታወስ
- የእንቅልፍ መረበሽ (ማጣት)ና ቅዠት
- በጣም ንቁ መሆንና የተጋነነ የፍርሃት ምላሾችን መስጠት
- በተደጋጋሚ የአዕምሮ መታወክ መግጠም (በአንድ ጉዳይ የተከሰተ የአሰቃቂ አደጋ ችግር በማስታወስ ለችግር መጋለጥ)
- አሰቃቂን አደጋውን የሚያስታውስ ማንኛውንም ነገር ለማስወገድ ጥረት ማድረግ
- ለምንም ነገር ፍላጎት ማጣትና አቅም ማጣት

- ሌላው ሰው ከአጠገብ ሲሞት (በሞት ሲለይ) ለመኖር ያለ የበደለኝነት ስሜት
- ምንም ነገር ተመልሶ ደስታ ሊሰጠኝ አይችልም የሚል ስሜት

ከላይ ያሉት ምልክቶች ውስጥ አንዱ መኖሩ በራሱ አንድ ሰው በአሰቃቂ (አደጋ) ችግር የመጠቃት ምልክት ሊሆን እንደሚችል ጠቋሚዎች ናቸው፡፡

**የአሰቃቂ ህመም ደረጃና እና ምልክት**

- ከላይ ያሉት ምልክቶች ምን ያህል ጊዜ ታይተዋል?
- በላይኛው ምልክት ተጎጂው በምን ያህል ጊዜ ተደጋግሞ ይታየዋል፡፡
- እንደዚህ ዓይነት ምልክቶች ምን ያህል በየዕለት ኑሮአችን ላይ ምስቅልቅል ፈጥሯል (ለምሳሌ፡ ራሳቸውን መንከባከብ ይችላሉን? የቤተሰባቸው ፍላጎት ያሟላሉን? ወደ ሥራ ገበታቸው ይሄዳሉን? ወዘተ ....)፡፡

## በአሰቃቂ አደጋ (አጋጣሚ) ውስጥ ያለ ሰው እንዲህ ይሆናል ለማለት የሚያስችሉ ምክንያቶች

### ውጪያዊ ምክንያቶች

- ለአስቸጋሪ (በአደገኛ፤አስጨናቂ) ሁኔታዎች ውስጥ ምን ያህል ተጋላጭነት አለ?
- ከቤተሰቦቻቸው ከጓደኞቻቸው ወይም ከሌላ ድርጅቶች በዚህ ችግር ውስጥ እያሉም ይሁን ካለፉ በኋላ ወዲያው ምን ያህል ድጋፍ አላቸው?

### ውስጣዊ ምክንያቶች

- መደበኛ የውስጥ መረጋጋት (ይህ ለስሜታዊ ፍላጎታችን እያደረግን ስንሄድ ምን ያህል ድጋፍ አግኝተናል በሚል ላይ የተመሠረተ ይሆናል)፡፡
- ማንነት (አንዳንድ ሰዎች ከሌሎች ሰዎች ቶሎ የሚጎዱ ናቸው)፡፡
- በእግዚአብሔር ማመን
- ከዚህ ቀደም የነበረ አሰቃቂ ህመም (አጋጣሚ) ካለ እና ምን ያህል እንደጎዳው መመልከት

- በአይምእሮ ህመም የተጋለጠ የቤተሰብ አካለ ካለ

## በአሰቃቂ አጋጣሚ (አደጋ) ውስጥ ያለን ሰው እንዴት መርዳት ይቻላል?

በአሰቃቂ አጋጣሚ (አደጋ) ውስጥ ያሉ ሰዎች በልባቸው ውስጥ ያለውን ህመም መናገር ያስፈልጋቸዋል፡፡ ነገር ግን እነርሱ መናገር እንዲችሉ የሚሰማቸው ሰው ያስፈልጋቸዋል፡፡

## ለማዳመጥ የሚረዱ ነጥቦች

- ሁሉንም ያጋጠማቸውን አጠቃላይ ሁኔታ እንዲናገሩ ማበረታታት በዚህ ጊዜ የሆኑትን ብቻ ሳይሆን ምን እንደተሰማቸውና ክስተቱ ምን እንዳደረጋቸው በዝርዝር እንዲናገሩ ማደፋፈር
- ለእነርሱ በቂ ጊዜና ሙሉ በሙሉ ትኩረትን መስጠት
- ትኩረት መስጠት እና በአይናችን እርህራሄን ማሳየት፡፡
- የሆነው ሁሉ ነገር ግልፅ እንዲሆንልህ ጥያቄዎችን መጠየቅ አለበለዚያ በመካከላችሁ ዝምታ ይፈጠራል፡፡
- ምን ዓይነት ማስተካከያ ወይም ማስተባበያ ሳትሰጣቸው ጥርጣሬአቸውንና ቁጣቸውን እንዲገልፁ ማድረግ፡፡
- ያለምንም እንቅፋት ወይም ያለምንም ማስተጓጎል እንዲያለቅሱ ፍቀድላቸው
- ወደ ሰዓት ፈፅሞ አትመልከት አታዛጋ/የተሰላቸ ሰው አትምሰል/ ወይም በመስኮት ወደ ውጪ አትመልከት
- ምንም ዓይነት ምክር አትስጥ
- ተናግረው ሲጨርሱ እንደሰማህ ለማሳየት ያሉትን ነገር ወይም የገባህን ነገር ጠቅለል አድርገህ ንገራቸው፡፡
- ህመማቸውን ወደ ኢየሱስ እንዲያመጡ አባረታቷቸው፡፡

## ሀዘን እና የሀዘን ሂደት

እንደ አሰቃቂ አጋጣሚ (አደጋ) ሁሉ ለሀዘን ምላሽ እንደየልምዳቸው ደረጃኛ መጠን የሚታወቁ ምላሾች አሉ። የጠለቀ ሀዘን ምላሽ የሚመሠረተው እንደ የ ሁኔታው ነው።

- ያልተጠበቀ ወይም ድንገተኛ ሞት ሲኖር
- የሞት ዓይነት በተለይም ጥቃት ሲኖር ወይም የጠለቀ መከራ ውስጥ ስናልፍ
- የግንኙነት ባህርይ (ለምሳሌ በጣም ጥገኛ ወይም ያልተፈታ ግጭት)
- ሌላ በጣም ወሳኝ ማጣት የነበረ ከነበረ በተለይ በህፃንነት ጊዜ
- የቀረው የህይወት ጊዜ አስጨናቂ ሲሆን።
- ተግባራዊ ድጋፍ ማጣት ከሆነ
- የሚቻል ከሆነ የቀብር ሥነሥርዓት አገልግሎት ማድረግ
- የሞተ ዘመድና ጓደኞች ቁጥር (ብዛት)

## ለሀዘን የታወቁ ምላሾች

***ድንጋጤ ፣ ክህደት፣ ድንዛዜነት***

### ድንገተኛና ያልተጠበቀ ሞት በህይወታችን ውስጥ ሲኖር የምንሰጠው ምላሽ

- ይህ መሆኑን በፍፁም ማመን አንችልም።
- ህልም ሊሆን ይችላል ብሎ ማሰብ (እስኪነቁ መጠበቅ ምክንያቱም መጥፎ ቅዠት ነው ብሎ በማሰብ)
- የሞተውን ሰው በሂወት እንዳለ መሰማት። (ምክንያቱም አይምሮአቸው የተፈጠረውን መቀበል ስለሚከብደው)

### እርግጠኛነት /ግንዛቤ መፍጠር

- የማጣት ወይም የመናቅ የጠለቀ ስሜት
- የሀብት ቁሳቁሶች (ንብረት) የሞተ ሰው ንብረት ናቸው
- ጥልቅ ሀዘን (ይህ ምናልባት ለዓመታት ጊዜ ሊወስድ ይችላል)

**ቁጣ**

- የሞት ምክንያት የሆኑት ላይ መቆጣት ። በመግደል ተሳትፎ የሆነ ከነበረ
- የበለጠ መሥራት አልቻሉም ብሎ ሀኪሞችንና ነርሶችን መቃወም
- ይህ እንዲሆን የፈቀደውን እግዚአብሔርን መቃወም
- በሞት የተለዩአቸውን ሰዎች መቃወም ምንም እንኳን ይህ አሳማኝ ሊሆን እንደማይችል ቢታወቅም
- ራስን መቃወም የበደለኝነት ስሜት ካለ

**የበደለኝነት ስሜትና ፀፀት**

ይህ ካለኝ ብቻ .....

- የበለጠ መሥራት (ብዙ መሥራት)
- ፈጥኖ ምላሽ መስጠት
- ነገሩ ሲፈጠር (በሆነበት ጊዜ) እዚያ ካለን
- የተሻለ አጋር ወንድ ልጅ፣ ሴት ልጅ፣ ወላጅ፣ ጓደኞችና ሌሎችም ቅርብ የሆኑ ከሆነ
- በትክክል ‹‹ሰላም ሁን›› ተብሎ መናገር የሚቻል ከሆነ
- ‹‹የአለመኖር ጥያቄ›› ለምን እኔ እስከ አሁን ድረስ ለምን እኖራለሁ፤ ሌሎች ሞተው?

**ጭንቀት**

- ሚች በሌለበት ምን ያህል መቋቋም እችላለሁ።
- ሚች በሌለበት በቁሳቁስ (ማቴሪያል) ምን ያህል መቋቋም እችላለሁ።
- ከሙት መንፈስ የሚመጣብኝ የበቀል መንፈስ (በተለይ ይህ የአድባር (ባህላዊ) ሀይማኖት ተከታይ ሲኮን)

**አካላዊ ምላሾች**

- ድካም/መዛል - ለማንኛውም ነገር አቅም ማጣት

- ❖ ትኩረት ለማድረግ መቸገር ወይም ለማስታወስ አለመቻል።
- ❖ በቀላሉ ለበሽታ መጋለጥ (በሀዘን ምክንያት የተነሳ በሽታ ለመቋቋም አቅም ማጣት

**መደንዘዝና ተስፋ ማጣት**

- ❖ ስለወደፊቱ ህይወት ያለ መጥፎ እይታ፡- ያለምንም ተስፋ ‹‹የማንኛውም ነገር ዋና ሀሳብ ምንድን ነው?››
- ❖ ለመነሳሳት መቸገር

**ተቀባይነት ማግኘትና እንደገና ማስተካከል**

በመጨረሻም ማጣት ወደሚለው ቃል እንመጣለን እንደገና የህይወትን ቅድመ ተከተል በማንሳት እንጀምራለን። እናም አስፈላጊ በሆነበት ሥፍራ ላይ እንደገና ማስተካከል አለብን።

በሀዘናችን ጊዜ እነዚህ ምላሾች ላንለማመድ እንችላለን። ብዙውን ጊዜ እኛ በተመሣሣይ ጊዜ ከአንድ ነገር በላይ ሊኖረን ይችላል። በህይወታችን ውስጥ ያለውን ማጣት (ኪሣራ) መቀበል እስከምንችልበት ጊዜ ድረስ በእነዚህ ምላሾቻችን መካከል ወደፊት ወደኋላ ወይም ማወላወል ውስጥ ስንገባ ራሳችንን ልናገኝ እንችላለን።

## በሀዘን የተሞላ ሰው (ሀዘንተኛ ሰው) ምን ያስፈልገዋል።

- ➢ ሊያለቅሱ (ሊጮህ)ና ሀዘናቸውን፣ ህመማቸውን ቁጣቸውንና ፀፀታቸውን ሊገልጡ ይችላሉ (አንዳንድ ባህሎች በዚህ ጉዳይ ከሌላው የተሻሉ ሊሆኑ ይችላሉ)።
- ➢ ምን እንደተከሰተ (እንደተፈጠረ) ስለሁኔታው ይናገራሉ። ስለሁኔታዎችና ስላጋጠማቸው የሞት ሁኔታ ደጋግመው ደጋግመው ሊናገሩ ይችላሉ።
- ➢ በሞት ያጡትን ሰው ‹‹ደህና ሁን›› ብለው ሊሰናበቱና በእግዚአብሔር ጥበቃ ስር ራሳቸውን እንዲያስተላልፉ ለመፍቀድ እንዲችሉ መርዳት፤ በተለይም ልጆች ዘመዶቻቸው በተሻለ ሁኔታ በኢየሱስ እንክብካቤ እየተደረገላቸው እንዳለ ማወቅ ይፈልጋሉ።

- የበደለኝነት ስሜታቸውንና ፀፀታቸውን ለኢየሱስ መስጠት እንዲችሉ እና ይቅር መባልን ለመቀበል መረዳት ይፈልጋሉ።
- ለሁኔታዎች የሚሰጡት ምላሽ ጤነኛ መሆኑንና ከጤነኝነት ውጪ እንዳልሆኑ  ማወቅ ይፈልጋሉ።
- ለወደፊት  ህይወታቸው  ድጋፍ ማድረግ እና እርግጠኝነት እንዲሰማቸው ማድረግ በተጨማሪም ተግባራዊ እርዳታ ማድረግ ያስፈልጋቸዋል።
- የቀብር ሥነሥርዓት ማድረግ የማይቻል ከነበረ የመታሰቢያ ፕሮግራም ማካሄድ መልካምና ተገቢ ነገር ነው። እንዲያውም በጣም አጠር ያለ የመታሰቢያ የአበባ ጉንጉን በትንሽ በተከመረ ድንጋይ ወይም መሬት ላይ ማስቀመጥ በጣም የሚረዳ ሊሆን ይችላል።

**እጅግ በጣም አሳዛኝ የሆኑ ሁኔታዎች መቋቋም**

አንድ ሰው በህይወት ይኑር ወይም ይሙት ባልታወቀ ነገር ወይም እርግጠኝነት በሌለበት ማዘን ወይም ተስፋ ለማድረግ  እርግጠኛ በማይኮንበት ጊዜ ማለት ነው። በስሜታችን ምላሽ መስጠት በማንችልበት ጊዜ ብቸኛው ይህን የምንቋቋምበት መንገድ ለእግዚአብሔር እጅ አደራ መስጠት ነው ። እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ያላቸው ሰዎች ሲያጋጥሙን የተለየ እንክብካቤ ማድረግና በቤተክርስቲያን መደገፍ አለባቸው።

## መ) የውስጥ ስብራትን /ቁስልን/ መፈወስ (*ካለብን የውስጥ ቁስል መዳን*)

እግዚአብሔር ልባቸው ለተሰበረ ያዝናል። እንዲሁም ከጉዳታቸው ከቁስላቸው ይፈውሳቸዋል (መዝ 34፡18፣ 147፡ 2-3፣ ኢሳ 61፡1-4፣ ሉቃ 4፡18) ። እርሱ በሚፈወስበት ጊዜ እርሱ መልካም ምክር ብቻ አይሰጥም። እርሱ ወደ እኛ በራሱ ይመጣል፣ ወደ እርሱ ክንድ ይወስደንና የህይወትን ቃልን ይናገረናል። ብዙውን ጊዜ ይህን ለብቻው አይሠራም። እርሱ የራሱን አካል የሆነችውን ቤተክርስቲያን በመጠቀም ‹‹.... *ትፈወሱ ዘንድ እንዲቻላችሁ አንዱ ስለአንዱ ይፀልይ››* (ያዕ 5፡16) ።

***ካለንበት አሳማሚ (ከሚያሳምም) ነገሮች እንዴት መፈወስ እንችላለን?***

- ህመምን መጋፈጥ። በመዝሙረ ዳዊት ላይ ዳዊት ስለሚሰማው ስሜት በጣም ታማኝ እንደነበረ ያሳያል ። ስለ ህመምህ ሁሉንም ለኢየሱስ መንገር (መዝ. 42፡ 3-4፣ 62፡8)
- ኢየሱስ ህመምን እንዲሸከም መፍቀድ እና በአንተ ፈንታ ለተጎዳው መስጠት። (ኢሳ 53፡ 4) በእግዚአብሔር ላይ የልባችንን እምባ ማፍሰስ (መዝ 56፡8) እርሱ ስለህመማችን ይሰማዋል እንዲሁም ያውቃል።
- የእግዚአብሔርን ድምፅ መስማት (ዮሐ 10፡27) እርሱን በህመምህ መካከል ፈልገው (ኢሳ 43፡1-2፣ 63፡9) የእርሱን የርህራሄ ልብ ተለማመደው (2ኛ ቆሮ 1፡3-4) የህይወትን ቃል ተቀበል እውነት አርነትን ያወጣሃል (ዮሐ 8፡32)
- በህይወታችን ለተጎዳንበት ነገር ላደረግነው ኃጢአታዊ ምላሽ ንስሀ መግባት፡- ለስህተት፤ ለፍርድ ፣ ለመራርነት፤ ለበቀል ፍላጎት፤ ለተሳሳተ እምነት ሁሉ ንስሀ መግባት። ለማንኛውም ዓይነት እሥራት መፀለይ (መዝ 51፡6፣ ሮሜ 6፡16፣ 14፡10-13፣ ዕብ 12፡ 15)
- ይቅርታ ለማድረግ የሚስችል ፀጋ በመቀበል ወደ እግዚአብሔር መቅረብ፡ ይቅርታ አለማድረግ በልብህ ዙሪያ ያለ እሥራት (ሰንሰለት) ነው። ይቅር ስትል ነፃ ትወጣለህ (ማቴ 5፡48-48፣ ማቲ 11፡25፣ ሉቃ 6፡27-37፣ ሮሜ 12፡14፣ 17-21፣ ኤፌ 4፡23፣ ቆላ 3፡13)
- በየቀኑ የህይወታችን አኗኗር የእግዚአብሔርን ፍቅር መቀበል የእርሱ ቃል የልብን መታደስ እንዲሰጥህ መፍቀድ (ኤር 31፡3፣ ሶፍ 3፡17፣ ዮሐ 14፡21፣ 2ኛ ቆሮ 4፡16)
- ፈውስን እንዲያገኙ ሌሎችን ለመባረክና ለመርዳት መፈለግ (ኢዮብ 42፡10፣ ፊሊ 2፡4፣ ያዕ 5፡16)
- እንደ ዮሴፍ እግዚአብሔር በመከራ ሥፍራ ውስጥ ፍሬማ ሊያደርግ ይችላል። (ዘፍ 41፡ 52)
- እንደ ኢዮብ ከፈተነህ በኋላ አንተንም እንደወርቅ ነጥሮ ፈትኖ ያወጣሃል (ኢዮብ 23፡10) ። ጌታ የተመሠገነ ይሁን!

## ***አፍረቶቻችን ላይ መስራት***

ምንም እንኳን ሰዎች ጥፋታቸውን እና ስቃያቸውን ለኢየሱስ ቢሰጡም, ነገር ግን አሁንም ድረስ በሀፍረት ስሜት ውስጥ ሊቀሩ ይችላሉ ይህም የተለየ ነገር ነው፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ነውርን ስለመቋቋም ምን እንደሚል ማየታችን አስፈላጊ ነው።

ከውድቀት በፊት ‹‹ምንም ሀፍረት አይሠማኝም›› የሚል የመጨረሻ ቃል ስለወንድና ስለሴት መኖሩ በጣም ወሳኝ ሀሳብ ነበር። (ዘፍ 2፡25) ራቁትነት ስለአካላዊ ራቁትነት ብቻ የሚናገር አይደለም። በተጨማሪ ስለግልፅነት፣ ስለመልካምነት፣ ስለግንኙነትና ስለ ህብረት የሚናገር ነው።

ሀፍረት ከኃጢአት ወይም ኃጢአተኛ ከመሆን የሚመጣ ነው። ከበደለኝነት ጋር ተመሣሣይ አይደለም። በደለኝነት ማለት ‹‹እኔ የሆነ ስህተት ሠርቻለው›› ማለት ሲሆን ሀፍረተኝት ማለት የሆነ ችግር (ስህተት) በህይወቴ ውስጥ አለ›› ማለት ነው። ይህም እንደ ሰው ልጅ ጉድለት አለብኝ ብሎ የሚሰማ ስሜት ነው።

በደለኝነት ከድርጊት ጋር የተያያዘ ሲሆን ሀፍረት ደግሞ ከማንነት ጋር የተያያዘ ነው። ሀፍረት ከእውቀት ጋር ተያያዥነት ያለው ሲሆን ይህም የጠበቀ የልብ ውስጥ ዕውቀት ነው። እግዚአብሔር ፈፅሞ እንድናውቀው የማይፈልገው አንዳንድ ነገሮች አሉ። ለዚህ ነው እርሱ መልካምና ክፉውን የሚየሳውቀውን ዛፍ እንዳንበላ የፈለገው።

### *ጤነኛ የሆነና ጤነኛ ያልሆነ ሀፍረት*

እግዚአብሔርን ስናሳዝን የሚሰማን ሀፍረት (ስሜት) ጤነኛ የሆነ ስሜት ነው ። ሰዎች ስላደረጉት ስህተት ምንም ሀፍረት የማይሰማቸው ሲሆን እርሱ ይደነቅ (ይገረምም) ነበር። (ኤር 8፡12) ። ነገር ግን ጤነኛ ያልሆነ ሀፍረት ደግሞ ብዙውን ጊዜ የሌላ ሰው ኃጢአት በእኛ ላይ ሲሆን ማለት ነው።

### *የሀፍረት ምንጭ*

- አካላዊ ገጽታዎች (አካላዊ ቁመና፣ የሰውነት ቅርፅ ወይም ተለይቶ የሚታወቅ ምልክት)

- የማህበራዊ ህይወት መገኛ ወይም ሁኔታ (ከተማ፣ ሀገር፣ ብሔረሰብ፣ የኢኮኖሚያዊ ሁኔታ የኋላ ታሪክ ድህነት)
- ሀገራዊ ታሪክ (የሉዓላዊነት ክብር ማጣት፤ በሌላ ሀገር መጨቆን ወይም መገዛት)
- መጠቃት (መገለል፣መደፈር፤ የህፃናት የወሲብ ጥቃት)
- የተደበቀ (ምስጢራዊ እውቀት) (ሚስጢር ጠባቂ መሆን በተለይ ለአካለ መጠን ያልደረሰ የወሲብ እውቀት፤ ህገወጥነት ድህረ ወንጀል ምልልስ፤ የቤተሰብ ሀፍረት)

## *የሀፍረት ውጤትና (ተፅዕኖና) የእኛ ያን ለማካካስ የምናደርገው ጥረት*

አዳምና ሔዋን ሀፍረታቸውን ለመደበቅ ያደረጉትን ጥረት እንመለከታለን፡፡

1. መሸፈን (መሰወር ፤መደበቅ) ራሳቸውን ለመደበቅ በቅጠሎች ለመደበቅ ያደረጉት ከንቱ ጥረት (ዘፍ 3፡7)
2. በዛፎች ውስጥ መደበቅ (መሸሸግ) እግዚአብሔር‹‹የት ነው ያለኸው?›› ብሎ ጠየቀ (ዘፍ. 3፡8) ይህ ጥያቄ ሰው ራሱን እንዲገልጥ የሚጋብዝ ነው፡፡ እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የጠየቀው የሆነውን ስለማያውቅ አይደለም፡፡ ነገር ግን እነርሱ ምን እንዳደረጉ ስለማያውቁ ነው፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሰው ልጅ በዛፎች (ቁጥቋጦዎች) መካከል እየተደበቀ ይገኛል፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት አልቻልንም ወይም እርስ በርሳችን ፊት ለፊት መገናኘት አልቻልንም፡፡
3. ራስን የማጋለጥ- ፍርሃት...›› ‹‹ፈራሁ....›› (ዘፍ 3፡10)
4. ጥፋትን ከራስ ማሸሽ ‹‹... እኔ አይደለሁም እርሷ ናት ...
5. ስለራስ ያለ የተሳሳተ እውቀት ‹‹ማን ነገረህ?›› ይህንን እግዚአብሔር አልነገራቸውም፡፡ ከተሳሳተ ቦታ (መልዕክት) የተቀበሉት ስለራስ ያለ ውሸት
6. ኩነኔ ወይም መራቅ - በማህበረሰቡ ውስጥ አልበቃም ብሎ ከማሰብ የሚመጣ፡፡ የሀፍረት ስሜት ብዙውን ጊዜ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየቀጠለ የሚሄድ ነው፡፡ ከእኛ የብሔር ወገን ጋርም ደግሞ የተጣበቀ ይሆናል፡፡

***የተሳሳተ ማንነትን መገንባት***

የሀፍረት ስሜትን ለመቋቋም ከምናደርጋቸው ነገሮች አንዱ በውሸት እራሳችንን መገንባት መፈለግ ነው ምክንያቱም ያለ ህመም እራሳችንን ማየት ስለማንችል ነው።

| | |
|---|---|
| ➢ የተሳሳተ ማንነት ከሰው ሁሉ የበለጥኩ ነኝ | ➢ ሌሎችን ዝቅ አድርጎ ፤ ራስን አግዝፎ መመልከት |
| ➢ የተሳሳተ ማንነት ከሰው ሁሉ አንሳለው | ➢ ራስን ዝቅ አድርጎ ፤ ሌሎችን አግዝፎ መመልከት |
| ➢ ትክክለኛ ማንነት ለራስ ያለ ትክክለኛ አመለካከት | ➢ ራስንም ሌሎችንም መቀበል |

ከሰው ሁሉ የበለጠ አድርጎና ከሰው ሁሉ ያነሰ አድርጎ ራስን መመልከት የትዕቢትና የጣኦት አምልኮ ህይወት ነው። እግዚአብሔር እኛ እንድንሆን አድርጎ የፈጠረንን ነገር ማዛባት ነው። ውጤቱም ያንን እንዳንመስል የተደረገነውን ነገር ማምለክ ይሆናል።

***ኢየሱስን መመልከት***

እርሱ ሀፍረት ተሰምቶት ያውቃል፤ሁሉንም በትክክል የሚሠራ ነው፤ እንደ ወንጀለኛ ተቆጥሮ ነበር፤ ስደተኛ ነበር፤ ከተናቀ ብሔረሰብ ወገን የመጣ ነው፤ በድሃ ቤተሰብ ውስጥ ያደገ ነበር እና ሌሎችም ጭምር፡ በእርሱ ማንነት ላይ ሀፍረት እንዲጣበቅበት ፈፅሞ አልፈቀደም እርሱ በማንነቱ ዘላለማዊ የሆነ ጥበቃ ያለው ነበር። የመጣውም ይህንኑ ለማድረግ ነው። (ዮሐ 13፡1-5)

በመስቀል ላይ እርሱ የሀጢአታችንና የህመማችንም ብቻ ሳይሆን የሀፍረታችንም ተሸካሚ ነበር። በመስቀል ላይ ራቁቱን በአደባባይ በህዝብ ፊት መሰቀል እጅግ ሀፍረትን የተሞላ

ነበር። ነገር ግን እርሱ በመስቀል ላይ መሰቀልን፣ በሀፍረት ውስጥ ማለፍ እንዲያስቆመው አልፈቀደም (ዕብ 12፡2) ወደ ነጻነት ስንመጣ ደስተኛ ሆኖ በመስቀል ላይ ታገሠ የእኛን ሀፍረት በመሸከም ጭምር ማለት ነው። በመስዋዕትነት (በሥርየት) ሞት እርሱ ሁሉንም የዓለም ኃጢአት መዘዝ በመስቀል ላይ ተሸከመ። መዝ 69፡7 የመስቀል ላይ መከራውን ከተናገሩት ትንቢታዊ መልዕክቶች መካከል አንዱ ነውና ፊቱን ስላሸነፈው ሀፍረት የሚናገረን ነው። ስለዚህ ይህ የእኛ ፊት ፈፅሞ በሀፍረት እንዳይሸፈን የሚያደርግ ነው። (መዝ 34፡5)

***ሀፍረትን እንዴት አድርገን እንታገለው?***

1. ችግሩን መቀበል ወይም የሚያታግለንን (የሚያሳፍረንን ነገር) ማወቅ (መቀበል)
2. ምን እንደሆነ እውቅና መስጠት ወይም  እግዚአብሔር እንድንሆን አድርጎ የፈጠረንን እውነታ ማመን  (መቀበል)
3. የሀፍረትን መነሻውን (ሥሩን )ማወቅ መንፈስ ቅዱስ በዚህ እንዲረዳን መፀለይ
4. ህመማችንን ለእግዚአብሔር መግለጥ፣ ወደ ኢየሱስ ወደ መስቀሉ መውሰድ
5. የእግዚአብሔርን መጎናፀፊያ መደረብ (ኢሳ 61፡10)
6. እግዚአብሔር እንዲያድሰን መፍቀድ (ኢሳ 54፡4፣ ኢዮኤል 2፡26-27)
7. እግዚአብሔር በደረሰብን ነገር ፈንታ ሊሰጠን የሚፈልገውን ሁለት እጥፍ ደስታና በረከት መቀበል (ኢሳ 61፡7)

## ቁጣ ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት

ቁጣ በመሠረታዊነት ኃጢአት ያልሆነ እግዚአብሔር የሰጠን ጤነኛ ስሜት ነው። እግዚአብሔር በኃጢአትና በኢ-ፍትሀዊነት ላይ ይቆጣል።  በኢ-ፍትሃዊነት ጉዳይ ላይ ተጋፍጠን የማንቆጣ ከሆነ ቆም ብለን እራሳችንን ማየት አለብን። የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አብረን እንመለከታለን።

***የእግዚአብሔር ቅዱስ ቁጣ፡***

ዘሁቁ 32፡ 10-13፣ ዘዳ 29፡27፣ ኢሳ 63፡3፣ ሶፎ 2፡2፣ ዘካ 10፡3፣ ሮሜ 1፡18፣ ኤፌ. 5፡6፣ ቆላ 3፡5-6

### *እግዚአብሔር ለቁጣ የዘገየና ቁጣው ለጥቂት ጊዜ ነው፡፡*

ዘፀ 34፡6፣ ዘሁ 14፡18፣ ነህ 9፡17፣ መዝ 30፡5፣ 78፡38፣ መዝ 86፡15፣ 103፡8፣ ኢሳ 54፡8፣ ኤር 3፡ 12፣ ሆሴ 14፡4፣ ኢዩኤል 2፡13፣ ዮናስ 3፡9፣ ሚክ 7፡18፣ ነህ 1፡3)

### *የጽድቅ (ቅዱስ) ቁጣ በኢፍትሀዊነትና በኃጢአት ላይ*

ነህ 5፡6፣ ኤር 6፡11፣ ማቴ 21፡12-13፣ 23፡13-36፣ ማር 3፡5፣ 10፡14፣ ሉቃ 11፡ 39-52፣ 13፡15-16፣ ዮሐ 2፡13-16፣ የሐዋ 5፡3፣ 4፣ 9፣ 8፡20-23፣ 13፡9-11፣ ገላ 2፡11-14

በኢፍትሃዊነት ላይ የሚደረግ ቁጣና መቃወም ተፈጥሮአዊና ጤነኝነት ነው፡፡ መቆጣት የተፈቀደ ነው፡፡ ነገር ግን ኃጢአት ማድረግ የለብንም (ኤፌ 4፡26-27) ። ይህን ከኢየሱስ መማር እንችላለን፡፡ በላይኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንደተመለከትነው እርሱ ሰዎች በኢፍትሀዊነት ተጎጂ ሲሆኑ ሲመለከት ተቆጥቶ ነበር። እርሱ ራሱ በኢፍትሓዊነት በተጎዳ ጊዜ ግን ተረጋግቶ ለፃድቅ ፈራጅ ራሱን አደራ ሰጠ (1ኛ ጴጥ 2፡23) ።

በመጽሐፍ ቅዱስ መንገድ የምንመለከተው ካልሆነ በስተቀር ቁጣ የሚጎዳ ሊሆን ይችላል፡፡ ቁጣን ይዘን የምንቆይ ከሆነ በልባችን ውስጥ ወደ መራርነት ፤ወደ ቅሬታ ይቀየርና ወደ ሀጢአት ይመራናል፡፡ በጣም የጠለቀ (መራር) ቁጣ ወደ አስፈሪ (አደገኛ) በሽታ የሚያመራ ይሆናል፡፡

### *ስለቁጣ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ*

መዝ 37፡8፣ ምሳ 29፡11፣ 22፣ 30፡33፣ መክ 7፡9፣ ማቴ 5፡22፣ ኤፌ 4፡26-27፣ 31፣ ቆላ 3፡ 8፣ 1ኛ ጢሞ 2፡8፣ ያዕ 1፡19-20 (በመጽሐፈ ምሳሌ ውስጥ ስለ በዛ ቁጣ የተሰጡ ማስጠንቀቂያዎች አሉ፡፡ ምሳ 14፡17፣ 29፡15፡18፣ 16፡32፣ 19፡19) ።

### *ቁጣን የምንቋቋምበት የተለመዱ መንገዶች*

- ማፈግፈግ (መተው) - በአካላዊ ከአካባቢው መራቅ አዕምሮአዊ ሥራ መሥራት፤ ቴሌቪዢን መመልከት፤ መጠጣት (መጠጥ) ፤ሀሺሽ መውሰድ...........
- በማስመሰል ማለፍ በውጪአዊ ህይወት ፈገግታ ማሳየት በውስጣዊ ልብ ውስጥ ግን የቁጣ (የበቀል) ስሜት መኖር
- መካድ፡ ይህ አካላዊ ህመም፤ ተስፋ መቁረጥ፣ ውጥረት፤ መራርነት፤ ቅሬታ ፤ ግልፍተኛ መሆን እና በትንሽ ጉዳዮች ጭምር ቁጡ መሆን
- ትካዜ /መተከዝ/ በአንድ ሰው አዕምሮ ውስጥ የተከሰተን ነገር ደጋግሞ ማሰብ በቀልንም ማሰብ በተጨማሪም ቅዠት ውስጥ መግባት
- መተካት /በሌላ ማካካስ/ ጉዳዩ ወደ ማይመለከተው ሰው ወስዶ ቁጣን በሌላ ሰው ላይ መግለጥ (ለምሳሌ ሚስት ላይ ወይም ልጆች ላይ)
- ግልፍተኝነት (መደንፋት) ከቁጥጥር ወጪ የሆነ ቁጣ
- ለመናገር አለመፈለግ ነገር ግን ዝምታን እንደ ማጥቂያ መሣሪያ መጠቀም።

እግዚአብሔር ከላይ ያሉትን አንዳቸውን እንድናደርግ አይፈልግም። እርሱ ቁጣችንን እንድክድ አይፈልግም ወይም በኃጢአታዊ መንገድ ምላሽ እንድንሰጥ አይፈልግም። ከእርሱ ጋር ሆነን እንድንጋፈጠው ይፈልጋል።

### *የቁጣ መከላከያ - ቁጣችንን በተግባራዊ መንገድ የምናውቅበት መንገድ*

ቁጣ ሁል ጊዜ ሌሎች ስሜቶችን ወይም ህመምን የሚደብቅ ስሜት ነው። ቁጣዬን እንደ ጋሻ እጠቀም ይሆናል። ይህ መሣሪያ በውስጣችሁ ምን እየተከናወነ እንዳለና ለኢየሱስ ምን መስጠት እንደምትችሉ ለማወቅ ይረዳችኋል።

በህይወትህ በመጨረሻ ስለነበረህ ስለተቆጣህበት ድርጊት (ክስተት) አስብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች ራስህን ጠይቅ።

- በአካላዊ ህይወቴ ላይ ምን ችግር ፈጠረ? በሥጋዬ (አካሌ) ላይ ምን ተሰማኝ? (ለምሳሌ፡ በሆዴ አካባቢ እሳት/የሚያቃጥል ነገር ተሰማኝ። በጀርባዬ በኩል ውጥረትና የህመም ስሜት ተሰማኝ በሆዴ (በጨጓራዬ) ውስጥ ቃር ተፈጠረ።
- ሌላ ምን ዓይነት ስሜት ተሰማኝ (ለምሳሌ ለልጆቼ በሰነዘርኩት የቁጣ ምላሽ ሀፍረት ተሰምቶኛል)
- ምን ሀሳብ እያሰብኩ ነበር? (ለምሳሌ ሁለተኛ እኔ እርሱን አላምነውም)
- ከእግዚአብሔር ጋር ባለኝ ግንኙነት ላይ ምን ተፅዕኖ ፈጠረብኝ? (ለምሳሌ፡ በህይወት ውስጥ እየሆነ ባለውና እኔም እያለፍኩበት ባለው ጉዳይ እግዚአብሔር ምንም ጉዳይ የለውም? ብዬ አምናለሁ። እኔ ከዚህ በላይ አልፀልይም!)
- ከሌሎች ሰዎች ጋር ባለኝ ግንኙነት ላይ ምን ተፅዕኖ ፈጠረብኝ?) (ለምሳሌ፡ ከሰው ጋር መኖር ፈፅሞ አይቻልም። አሁን ከሁሉም ሰው የመራቅ ስሜት ይሰማኛል። ባለቤቴ (ሚስቴ፣ ባሌ) አሳፍራኛለች (አስፈርታኛለች)። ከዚህ ሰው ጋር ከእንግዲህ ፈፅሞ መገናኘት አልፈልግም።)

ቁጣ ብዙውን ጊዜ አንድን ነገር ይፈልጋል። ምን እንደምትፈልግ ለመለየት የሚረዳህ ነው። (ለምሳሌ፡ ሰዎች እንዲሰሙህ መፈለግ (መስማት)፣ ሰዎች በትክክለኛው መንገድ እንዲያስተናግዱህ (እንዲቀበሉህ) መፈለግ ስለ አንድ ሁኔታ ያለውን እውነት የማወቅ ፍላጎት ስለሁኔታው ትክክለኛ የሆነ ፍትህ መፈለግ…)

***ቁጣን እንዴት እናስተናግደው?***

1. እግዚአብሔር አንድን ነገር ለይተህ እንድታውቅ እንዲረዳህ መፀለይ
    - የቁጣህን ምንጭ መለየት
    - ቁጣህን የቀሰቀሰው ስሜት ወይስ ህመም ምንድን ነው?
    - ሌባው ምንድን ነው የሰረቀብህ (ሰይጣን)?
    - በዚህ ሁኔታ ውስጥ በእውነት የምትፈልገው ነገር ምንድን ነው?

2. ከላይ ያሉትን ሁሉ በተመለከተ የሚሰማህን ስሜት ሁሉ ለእግዚአብሔር በትክክል ተናገር እንዲሁም ህመምህንና ቁጣህን በእርሱ ልብ ላይ አፍስሰው ኢየሱስ ሁሉንም በመስቀል ላይ እንደተሸከመልህ እመን።

3. እግዚአብሔር የልቡን ሀሳብ ይገልጥልህ ዘንድና እርሱ እንዴት አድርጎ ህይወትህን ሊያድስ እንደሚፈልግ ይናገርህ ዘንድ ፀልይ

4. የጎዱንን ሰዎች ሁሉ ይቅር ለማለት የምንችልበትን ፀጋ እንዲሰጠን የበረከትን ቃል እንድንናገራቸው ወደ እግዚአብሔር መፀለይ

5. አንድ ሰው በኢፍትሀዊነት የተጎዳ ከሆነ እግዚአብሔር በእርሱ ፈንታ አንተ እንድትወስደው የሚፈልገው የጽድቅ እርምጃ ካለ እንዲያሳይህ ፀልይ።

አንዳንድ ሰዎች ለምን እንደተቆጡ ትክክለኛውን ነገር ማስቀመጥ (ማግኘት) አስቸጋሪ ሊሆንባቸው ይችላል። በአጠቃላይ በህይወታቸው የሚቆጡት ብዙ ኢ-ፍትሃዊ ክስተቶችን በህይወታቸው አልፈው ከሆነ በዛ ምክንያት ሊሆን ይችላል። ሌባው የዘረፈባቸውን (የሰረቀባቸውን) ሁሉንም መንገዶች መዘርዘር (ሁሉንም በህይወታቸው የተለማመዱአቸው ያጡአቸውንና ኢፍትሃዊነቶችን ሁሉ) ሊረዱአቸው ይችላሉ። ከዚያም በኋላ ይህንን በእግዚአብሔር ልብ ላይ ማፍሰስ (መጣል) ያስፈልጋል። እነዚህ ሁሉ ነገሮች በክርስቶስ መስቀል መስዋዕትነት ውስጥ የተካተቱ በመሆናቸው ለማመን ድፍረት ያገኛሉ። በመጨረሻም፣ በዮሐንስ 10፡10 ሁለተኛ ክፍል መሰረት የተሰረቀባቸውን ሁሉንም ነገር ሊያድስላቸው የሚፈልገውን እየሱስን መጠየቅ ወደ እርሱ መፀለይ እንዴት የሙላት ሕይወት እንዲሚለማመዱ ኢየሱስን መጠየቅ አለባቸው። ይህ ፈውስ እና ነፃነትን ያመጣል።

## ፍርሃትን መቋቋም

### *ተፈጥሮአዊ ጤነኛ ፍርሃት*

አንድ አደጋ ሲያጋጥመን ‹‹የፍርሃት ስሜት ሲሰማን ይህ ፍርሃት ጤነኛ ፍርሃት ነው። ለዚያም የምንሰጠው ምላሽ ጭምር ጤነኛ ነው። በአደጋ ጊዜ የሚመጣው ፍርሃት ራሳችንን እንድንከላከል የሚያነቃን ነው። ለምሳሌ፡ ድቅድቅ ባለጨካ ውስጥ ወደ ቤቴ እንደተመለስኩ ሳለሁ ከቁጥቋጦ መካከል አንበሳ ዘሎ ወጣና ከፊት ለፊቴ ቆመ እንበል፤ ይህ ፍርሃት ጤነኛ ፍርሃት ነው። ከዚያ ለማምለጥና ራሴን ለማትረፍ ሁኔታ ውስጥ ሆንኩና ራሴን ለማዳን ፈለግሁ! ፍርሃት ጡንቻዎቼን አነሳስቸውና ለመሮጥ ተዘጋጀሁ (የዓለምን ሪከርድ ለመስበር!!)። ነገር ግን አንበሳው ተመልሶ ወደ ሌላ አቅጣጫ ተራመደ እኔን ፈፅሞ ረሳኝ። ይህ አደጋ ካለፈ በኋላ ፍርሃትም ጠፋና እኔም እየተረጋጋሁ መጣሁ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ።

በዚህ አስፈሪ ደቂቃዎች ውስጥ ፍርሃቴን ለማሸነፈ የረዳኝ የእግዚአብሔር ፀጋ ነው። በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ መለኮታዊ ብርታት፣ ሰላምና ጥበብ መለማመድ የሚያስፈልግባቸው ጊዜያት አሉ። በተጨማሪ በአስቸጋሪና ዋስትና በሌለው የየዕለት ኑሮአችን ሁኔታዎች ውስጥ ፍርሃትን ለማሸነፍ የእግዚአብሔር ፀጋ የሚያስፈልግበት ጊዜ አለ። የእርሱ ፀጋ እኛን እንደጋሻ በዙሪያችን ሊከበን የሚችል ሊሆን ይችላል (መዝ 5፡12) ።

## *ጤነኛ ያልሆነ ፍርሃት*

ከአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውጪ በምንሆንበት ጊዜ የሚሰማን ፍርሃት ካለ ይህ ፍርሃት እኛን ለመጉዳት የሚመጣ እንጂ ለመጥቀም የሚመጣ ፍርሃት አይደለም። በተጨማሪም ይህ ዓይነት ፍርሃት ወደ ህይወታችን አቅጣጫ ሁሉ ሊስፋፋ /ሊዛመት/ ይችላል። ይህም ሁልጊዜ በፍርሃት በተሞላ ስሜት ውስጥ እንድንሆን ወይም በቋሚነት የመጨነቅ ህይወት ውስጥ እንድንገባ ሊያደርግ ይችላል። ይህ ከውጭ በኩል ባለው አጋጣሚ ሁኔታ የሚመጣ አይደለም። ነገር ግን የልባችን ሁኔታ ነው። የእኛ ስሜታዊ አዕምሮአዊና መንፈሳዊ አቅሞች ሁሉ ለፍርሃትና ለጭንቀት ለሚያመጣው ጥቅም ሥር ይውላሉ። ምናልባትም የወደፊት ሂወታችንን ስለነገ በማሰብ ጭንቀት ሊያመጣብን ይችላል። እኛ እንዴት አድርገን እንኖራለን፣ እንሞታለን ወይም ስለ ቤተሰባችን ያለ ስጋት ፍርሃትን ይዞ ይመጣል፤ ምናልባትም ወደፊት እወድቃለሁ (እከሥራለሁ) ወይም በእግዚአብሔርና በሰዎች መገለል ወይም ፍርድ ሥር እወድቅ ይሆናል

ብሎ መፍራት። እነዚህ ሁሉ ነገሮች በጣም አጥፊዎችና ሁለንተናዊ ህይወታችንን የሚያጠቃ ነው ፤ አካላችንን፣ ስሜታችንንና አዕምሮአችንን የሚያጠቃ ነው ። በተጨማሪም በዙሪያችን ባሉ ሰዎች ላይም ተፅዕኖ ሊያመጣ የሚችል  እንደገናም እነርሱም እንደ እኛው በፍርሃት የተሞሉ እንዲሆኑ ሊያደርግ ይችላል።

## *የእግዚአብሔር መፍትሔ*

**«አትፍራ»** ይህ ትዕዛዝ በመጽሐፍ ቅዱስ ከሌሎች ሁሉ ይልቅ ምናልባት በብዛት (በተደጋጋሚ) የተጠቀሰ ነው። እግዚአብሔር በምን ሁኔታ በፍርሃት እንድንሞላ አይፈልግም። እግዚአብሔር የፍርሃትን መንፈስ አልሰጠንም ነገር ግን የኃይል፣ የፍቅርና ራስን የመግዛት መንፈስ ሰጥቶናል (2ኛ ጢሞ 1፡7) ። ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ብዙ ጊዜ አትፍሩ ብሎ ተናግሯቸዋል።

የሰው ልጆች በኃጢአት ወድቀዋል (ዘፍ 3፡7-9) ይህም በስሜቶቻችን ላይ ተፅዕኖ ፈጥሯል። ፍርሃት ሁልጊዜ ራሳችንን ለመደበቅ እንድንሞክርና የመከለያ ግድግዳ እንድንገነባ ያደርገናል (አስብን ብቻ ሳይሆን ሳናስበውም ጭምር ማለት ነው) ይህ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ላይ መለያየትን ያመጣል። ነገር ግን ኢየሱስን ወደ እኛ የጨለማ ሥፍራ (ፍርሃት) እንድንጋብዘውና እርሱ ብርሃንን ሊሰጠን ይፈልጋል። ከእርሱ ጋር ወደነዚህ አስፈሪ ሥፍራዎች እንድንጓዝ ይፈልጋል። በመስቀሉ ላይ ኢየሱስ አስፈሪ የሆነነ ፍፁም ድቅድቅ ጨለማን ስለተለማመደና ስላሸነፈው ዛሬ የፍርሃት ኃይል ፈፅሞ ያስረን ዘንድ አይችልም።

በፍርሃታችን ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘትና እርሱ ለልጆቹ ያለውን ፍቅርና ታማኝነት እንደገና ማወቅ ያስፈልጋል። የእርሱን ባህርይ መገለጥ የበለጠ ከተቀበልን በእርሱ መታመናችንም ያድጋል። ማቴ 6፡25-34 እኛ ለእግዚአብሔር ምን ያህል አስፈላጊዎች እንደሆንን ይናገራል። እንዲሁም በዚሁ ምንባብ ውስጥ በምንኖረው ኑሮ መጨነቅ እንደሌለብን ተናግሯል። እርሱ በራሳችን ላይ ምን ያህል ፀጉር እንዳለ እንኳን ያውቃል። (ማቴ 10፡30)

በዚህ ምድር ላይ ለምን እንደምንኖር የበለጠ ዕውቀት መጨበጥና እግዚአብሔር በእኛ ሊሠራ ያለውን ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። እኛ በዚህ ምድር ላይ የእርሱ ህልውና ወኪሎች (አምባሳደሮች) ነን። እኛ በእግዚአብሔር ዓላማና ማንነት በሙላት ስንኖር በእግዚአብሔር ማንነት በድፍረት እናድጋለን፤ የእርሱም ብርታት በእኛ ውስጥ ይሠራል።

እምነትና ፍርሃት በአንድነት አብረው አይኖሩም። ነገር ግን ፍርሃት ጠንካራ ስሜት ሲሆን ምክንያትን በመጠቀም ብቻ ፍርሃትን ማስወገድ አንችልም። የፍርሃት ሥር መሠረት ተለይቶ መታወቅ እና ከፍርሃት በስተጀርባ ያለው ጉዳት መፈወስ ያስፈልገዋል። ጉዳታችን ምን እንደሆነ ግልፅ ካልሆነልን መንፈስ ቅዱስ ለእኛ ይገለጥልን ዘንድ መፀለይ እንችላለን። ከዚያም በልባችን ውስጥ ያለውን በእግዚአብሔር ፊት ማፍሰስ እና ሁሉንም ህመምና ስሜቶቻችንን ወደ መስቀሉ ማምጣት እንችላለን።

### *ፍርሃትን እንዴት እናስተናግደዋለን?*

እኛም እንደ ገበሬ በልባችን ውስጥ የምንዘራው ዘር አለ ። በልባችን ውስጥ አዲስ ዘር ከመትከላችን በፊት የፍርሃት አረሞችን በማጥራት ከፍርሃት ነፃ መውጣት እንችላለን። ከፍርሃት ነፃ የምንወጣባቸው ነገሮች ከዚህ በታች ተቀምጠዋል።

1. በልባችን ውስጥ እያደገ ያለውን ፍሬ ምንነት መለየት። መልካም ዘፍ መልካም ፍሬ ያፈራል ክፉ ዘር ክፉ ፍሬ ያፈራል። (ማቴ 7፡17)።
2. እግዚአብሔር የዘፉን ሥር (መሠረት) ይገልጥልህ ዘንድ መፀለይ
3. የፍርሃት መሠረቱን ወደ እግዚአብሔር ማምጣት (ለምሳሌ፡ - አሰቃቂ የሆነ አጋጣሚን (አደጋን) ለምሳሌ እኔ ስለ እግዚአብሔር የተሣሣተ እምነት በውስጤ ሞልቶ ቢሆን፤ ስለራሴም ስለሌሎችም እንዲሁ ሞልቶ ቢሆን ፤ ከዚያም ያ ነገር ፍርሃትን ያመጣል። ስለዚህ ከጉዳቴ ያገኘሁትን ህመምና የተሳሳተውን እምነቴን ወደ እግዚአብሔር ማምጣት ያስፈልገኛል)።
4. ለፈውስ መፀለይ

*5.* እግዚአብሔር ቃል እንዲሰጠኝ መፀለይ

### *እሥራትን መስበር*

በሕይወታችን ውስጥ እድል ለማግኘት ሲል እኛን በባርነት ወይም በቀንበር ስር አስሮ ሊያቆየን የሚፈልገውን እና በጉድለታችን በኩል በቀላሉ የተገኘውን እድል( አጋጣሚ) የሚጠቀመውን ሰይጣንን መቃወም ያስፈልጋል። በሉቃ 10፡19 ላይ ኢየሱስ በእርሱ ላይ (በሰይጣን ላይ) ስልጣን እንደተሰጠን ተናገሯል። ከህይወታችን እርሱን ለማስወጣት (ለማባረር) ይህን ስልጣን መጠቀም እንችላለን። ይህን ከማድረጋችን በፊት የእግዚአብሔርን ፈውስ መቀበል አስፈላጊ ነው። እንዲሁም እንድንፈራ የሚያደርገንን (ይቅር ያላልነውን) ማንኛውንም ሰው ይቅር ማለት አለብን። ምክንያቱም ይቅር አለማለት ሰይጣን በህይወታችን መግቢያ ቀዳዳ እንዲያገኝ ያደርጋል። (ኤፌ 4፡26-27)።

### *ለአዲስ አመለካከት (እይታ) መፀለይ*

በአስፈሪ የህይወት አሳዛኝ አጋጣሚዎች ውስጥ ማለፍ እግዚአብሔር ወደፊት ከሁሉም ነገር ይጠብቀኛል ብሎ ለመታመን ከባድ ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም ጠላቶቻችን (ያጠቁንን) ጥሩ ደረጃ ላይ ደርሰው ስናይ እና ያላቸውን ነገር ሲናገሩ ስንመለከት በእግዚአብሔር መታመን ከባድ ሊሆን ይችላል። ይህ ጤነኛ ምላሽ ነው፤ አሁንም ለወደፊትም ህይወታችንም ተስፋ እንዳይኖረን የሚያደርግና ሽባ እንድንሆንም ሊያደርገን የሚችል ነው። ከተጎዳንበት ነገር ፈውስን ከተቀበልን በኋላ ህይወትን ከዚህ አቅጣጫ ለማየት እንድንችል እንዲረዳን ወደ እግዚአብሔር መፀለይ እንችላለን። በ2ኛ ነገ 6፡8-10 የኤልሳዕ አገልጋይ በጠላት ኃይል ዙሪያቸው እንደተከበበ ባየ ጊዜ እጅግ በጣም በፍርሃት እንደተሞላ የሚናገር ታሪክ አለ። ኤልሳዕም እግዚአብሔር መንፈሳዊ ዓይኖቹን እንዲከፈትለት ፀለየለት እናም ወዲያውኑ እነርሱ የሚጠብቁ የሰማይ ሠራዊት ለማየት ቻለ። እነርሱም ከጠላቶቻቸው በላይ እጅግ በጣም ብዙ እንደሆነ ተመለከተ።

እግዚአብሔር ህዝቡን እንደሚጠብቅ የሚናገሩ ብዙ ሌሎች ምሳሌዎች አሉ፡፡ መዝ 34፡7 እንዲህ ይላል፡፡ ‹‹የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሠፍራል ያድናቸውም››፡፡ መዝ 91 ከክፉ ስለመጠበቅና ከመከራ ስለመዳን አስፈላጊ ተስፋ ቃል ይሰጠናል፡፡ እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ በሚነደው እሳት ውስጥ በተጣሉ ጊዜ ሶስቱ ሰዎችን በአስደናቂ ተዓምራት ከሚነድደው እሳት ታደጋቸው (ዳን 3፡19-30)

## ሠ) ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ሰዎች ማገልገል

**ተደፍራ የነበረች ሴት**

በብሔር ግጭት ወቅት ብዙ ሴቶች በአሳዛኝ ሁኔታ ይደፈራሉ፡፡ ለእነርሱ ፍቅር መስጠትና የቤተክርስቲያንም ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ብዙውን ጊዜ የተደፈሩ ሴቶች የሚሰማቸው ስሜት፡፡

- ውርደት አልረባም (አልፈለግም) የሚል ስሜት
- የረከሱ በሌላ ሰው ቆሻሻ የረከሱ (የተበከሉ)
- የበደለኝነት ስሜት ምንም ስህተት የሰሩ ባይሆንም እንኳን፣ የተሳሳተ (ትክክል ያልሆነ) የጥፋተኝንት ስሜት መሰማት
- ጉዳትና በህመም የተሞላ ህይወት
- በአንዳንድ በሽታዎች በመያዝ የተነሳ የፍርሃት መንፈስ በተለይ ኤድስ
- ጥቃት ከደረሰባቸው መንገድ የተነሳ ቁጣ (ንዴት)
- ከደረሰባቸው ጥቃት የተነሳ ጥልቅ የሆን የሀፍረት ስሜት መሰማት ፡፡

በዮሐ 10፡10 ኢየሱስ እንዲህ ይላል *«ሌባው ሊሰርቅ፣ ሊያርድና ሊያጠፋ ይመጣል»* የተደፈረች ሴት በሰይጣን ብዙ ነገር ትዘረፋለች፡፡ ሠላሟን፣ ደስታዋን፣ ንፅህናዋን፤ ጨዋነቷን፣ ድንግልናዋን፣ ክብሯን ፣ ዋጋ ያላት መሆኗን፣ በሰውነቷ /በአካሏ/ ላይ መልካም ውሳኔ የመወሰን መብቷን ፣ መልካም ትዳር የመመስረት ተስፋዋን ፣ ጤንነቷን እና የመሳሰሉት ነገሮችን ታጣለች ፡፡ ኢየሱስ ግን እንዲህ ይላል፡፡ ‹‹እኔ ግን ህይወት እንዲሆንላችሁ እንዲበዛላችሁ መጣሁ›› እግዚአብሔር ይመስገን ኢየሱስ የመጣው ሁሉንም ሰይጣን

የዘረፈብንን ነገር ሁሉ ሊያድስልን ነው። እግዚአብሔር ለእኛ ሊያድሰው ያለውን መሻት የሚገልጡ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ።

- ኤር 30፡17 .... ‹‹እኔ ጤናህን እመልሳለሁ ቁስልህንም እፈውሳለሁ ይላል እግዚአብሔር››
- ኢዮ 2፡25 ..... ‹‹የሰደድሁባችሁ ታላቁ ሠራዊቴ አንበጣና ደጎብያ ኩብ ኩባ ተምች የበላቸውን ዓመታት እመልስላችኋለሁ።
- መዝ 23፡ 3 ‹‹... ነፍሴን መለሳት

በተጨማሪ መዝ. 71፡20-21፣ ኢሳ 51፡3፣ 57፡18-19፣ ህዝ 36፡34-36፣ ናሆም 2፡2 ሶፎ 3፡20፣ ዘካ 10፡6፣ 1ኛ ጴጥ. 5፡10

***ተደፍራ ለነበረች ሴት በምንፀልይበት ጊዜ ይህ ፀሎት በጣም አስፈላጊ ነው።***

- ለንጽህና /ለመታጠብ/ ይህም ከገዛ ራሳቸው ቆሻሻ የመጣ ሳይሆን በሌላ ሰው ሀጢአት ምክንያት በእነርሱ ላይ የተጨመረ ቆሻሻ ነው። እነርሱ ንስሀ ሊገቡ አያስፈልጋቸውም። በአካላቸው ፣ በአዕምሮአቸው ፣ በስሜታቸው ፣ በመንፈሳቸው ላይ የሚያነፃቸው የመንፈሱ የህይወት ውሃ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይመጣላቸው ዘንድ ወደ እግዚአብሔር መፀለይ እንችላለን። ህዝ 36፡26 ዓይነት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ከጣኦቶቻችሁ ሁሉ የሚለውን ከቃሉ ውስጥ ማውጣት ላለው ችግር ተዛማች እንዲሆንላቸው ተብሎ ማለት ነው። (በዚህ ጥቅስ ላይ ያለው ሁሉ ለተነሳንበት ሀሳብ ተዛማች ስለማይሆን ነው።)
- ከተሸከሙት ትክክል ካልሆነ የበደለኝነት ስሜት ነፃ እንዲወጡ ማድረግ። የሚጨነቁበት የበደለኝነት ስሜት የእነርሱ ጥፋት ስላልሆነ።
- ሃፍረታቸውን ለማስወገድ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሀፍርታቸውን እንደተሸከመ ሊያውቁ ያስፈልጋል። ፊቱ በሀፍረት የተሸፈነ ነበር (መዝ 69፡ 7-19) ስለዚህ እነርሱም ካለባቸው ሀፍረት ነፃ መውጣት ይችላሉ። (መዝ 34፡5)። ሌላ የሚያፅናና የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ከኢሳ 54፡4-5፣ 61፡7፣ ኢዮኤል 2፡27

ለእነዚህ አሉታዊ ነገሮች ስንፀልይ ሁሉም ይወገዳሉ። ስለዚህ በሰይጣን የተሰረቀው ሁሉም ነገር እንዲታደስ መጸለይ እንችላለን። እግዚአብሔር እንዲታደስ የሚፈልጋቸውን ሁሉንም ነገሮች በስም መጥራት በጣም አስፈላጊ ነው። እንዲሁም በተለይ ሊታደሱ ስለሚገባቸው እያንዳንዱ ገጽታዎች መፀለይ አለብን። በተጨማሪ እኛ ዋጋ እንደምንሰጣቸው እንደምንቀበላቸውና እንደምናከብራቸው ማወቅ ያስፈልጋቸዋል።

ዘዳ 10፡8 እንደሚነግረን አንዱ ከካህን ሥራዎች መካከል በእግዚአብሔር ስም መባረክ ነው። በአዲሱ ኪዳን ሁሉም አማኞች ካህናት ናቸው። (1ኛ ጴጥ 2፡9፣ ራዕ 5፡9-10) ስለዚህ እኛ በተጎዱ ሰዎች ህይወት ላይ በረከትን ለማወጅ ይህ ዕድል አለን። ተደፍረው የነበሩ ሰዎች በራሳቸው የወሲብ ፍላጎት በረከት መባረክና እንደገና የመቀደስ ህይወት ማግኘት ይፈልጋሉ። በነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንዳሉ 6፡24-26፣ መዝ 129፡8 (የመጀመሪያው ክፍል ሳይሆን ይህ ፅዮንን ለሚጠሉ ሰዎች ብቻ ላይ መዝ 115፡15፣ 134፡3 በሁሉም ህይወታቸው ላይ ማወጅ (መናገር እንችላለን) ።

ለእነርሱ እውቅና በመስጠት በራስ መተማመናቸውን መገንባት መልካም ነው (ለምሳሌ መሐ. መሐ 4፡7) እንደ ሰማያዊ አፍቃሪ አባት መልዕክት መውሰድ ይችላል) የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን በመመልከት በእግዚአብሔር ዘንድ እኛ ምን ያህል ዋጋ እንዳለን መመልክት እንችላለን።

ተስፋ አደርጋለሁ እንደዚህ ዓይነት አገልግሎትን መቀበል ሴቶች ራሳቸውን ይቅርታ ማድረግ የሚችሉ ሆነው ያገኛሉ። በተጨማሪም ፈውሳቸውን ይጨምራል።

### *የተደፈረችን ሴት ማማከርና መፀለይ የሚጠበቅበት ማነው?*

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ያለፉ ሰዎች ወንዶችን ማማን በጣም አስቸጋሪ ሊሆንባቸው ስለሚችል ሴቶች ይህን ሥራ ቢሰሩ ጥሩ ነው። የቤተክርስቲያኒቱ መሪ ወንድ ከሆነ ሴት የሆነችውን ለትብብር መጠየቅ አስተዋይነት ነው። ሌሎችን ለመርዳት (ለመንከባከብ) ልብ

ያላቸው የእግዚአብሔር ሴቶችን በቡድን በመጥራት እንዴት የተደፈሩ ሰዎችን ለመርዳት እንደሚችሉ ማሰልጠን መልካም ነገር ነው፡፡

በደረሰባቸው በደል  ምክንያት ለሌሎች ሰዎች ምንም ነገር ፈፅሞ መናገር ለማይችሉ የአዕምሮ መታወክ ላለባቸው ሴቶች ምን እናድርግ?   በልባቸው ውስጥ አስፈሪ ሚስጥሮችን የሚሸከሙ ሴቶችን ለመርዳት የሚያስችል መንገድ አለ? ለእነርሱ ሲሉ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በስብከታቸው ውስጥ እነዚህን ነገሮች በጥቅሉ መግለጻቸው አስፈላጊ ነው፡፡ አምላክ የውስጥ ቁስላችንን እንደሚፈውስ በሚሰብክበት ጊዜ፣ ሰባኪው መደፈር የሚያስከትለውን ቁስል ሊጨምር ይችላል፡፡ እየተሰቃዩ መሆናቸውን መረዳቱን እና አሳቢነትን እና ርህራሄን መግለጽ ይችላል፡፡ ማንኛዋም ሴት ተደፍራ የምትሰማ ሴት እንደገና ተስፋ እንዲኖራት የፈውስ መንገዱን መዘርዘር ይችላል፡፡

በእነዚህ ሴቶች ላይ ስለተፈፀመው ጉዳት ጥልቅ የሆነ ሐዘን በመግለጥ ይህ ስህተት (በደል) የእግዚአብሔር ልብ እንዳሳዘነ በመግለጥ የእግዚአብሔር ሰው ‹‹በፈረሰው ቅጥር በኩል ሲቆም ወይም ክፍተቱን ሲሞላ ውጤታማ ሊሆን ይችላል፡፡

በተጨማሪም ወንዶችን በመወከል እነዚያ ወንዶች በሁሉም መንገድ ሴቶች ላይ ጥቃት በማድረስ እና በማዋረድ ላደረጉት ይቅርታ መጠየቅ ይችላል፡፡ ይህም ሴቶች ከመደፈር የተነሳ በወንዶች ላይ ሊኖራቸው ስለሚችል ጥላቻና ፍርድ እንዲተው ሊረዳቸው ይችላል፡፡

### *ከመደፈራቸው የተነሳ ስለአረገዙ (ስለፀነሱ) ሴቶች ምን እናድርግ?*

እነዚህ ሴቶች የተወለደውን ልጅ ለመቀበልና ለመወደድ በጣም ከባድ ሆኖባቸው ራሳቸውን ሊያገኙት ይችላሉ፡፡ እንድ ሰው ፈፅሞ መውለድ እንደሌለባት፤  ከመገለል የተነሳ ደግሞ ይህ ልጅ ከባድ ስህተት እንደሆነ ሊሠማቸው ይችላል፡፡ ቤተክርስቲያን እንደነዚህ ዓይነት ልጆችን በእነዚህ ሁኔታ ውስጥ መወደድና በጥሩ ልብ በመቀበል ሊረዱአቸው ይችላሉ፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ስለሚወዳቸውና ስለሚቀበላቸው ነው፡፡ (እርሱ) እግዚአብሔር የተፀነሱበት መንገድ ከእርሱ ሀሳብ ጋር የሚጋጭ ቢሆንም እርሱ ሁኔታውን አይመለከተውም፡፡

እነርሱ ለዚህ ስህተት ተጠያቂ እንዳልሆኑ ያውቃል ። እርሱ አባት ለሌላቸው ለተረሱና ለተናቁ (ለተገፉ) የተለየ ፍቅር ሁልጊዜ አለው፡፡ (ዘዳ 10፡18፣ መዝ. 68፡5-6፣ 27፡10፣ ኢሳ 49፡15፣ 1ቆሮ 1፡ 26-29)፡፡ ኢየሱስ በሰው መናቅና መገለል ምን ማለት እንደሆነ ያውቃል (ኢሳ 53፡3)፡፡ ምንም እንኳን እርሱ በሰው የተገፋ ቢሆን እርሱ በእግዚአብሔር የተመረጠ ነበር፡፡ እርሱ ለእግዚአብሔር የከበረ የነበረ እና የመሠረት ድንጋይ ሆነ (1ኛ ጴጥ 2፡4፣ 7)፡፡ እግዚአብሔር እነዚህን አሳዛኝ ሁኔታዎች በመጠቀም እነዚህ ‹‹ያልተፈለገ›› ህፃናትን ወደ ትልቅ በረከት ሊያመጣ ይችላል፡፡ እንደ ቤተክርስቲያን ለእነዚህ ልጆችና ለእናቶቻቸው የተለየ ፍቅር ማሳየት እንችላለን፡፡

## በደረሰባቸው አሰቃቂ አደጋ (አጋጣሚ) ምክንያት ከአንዳንድ ሥፍራዎች ጋር በተገናኘ ጥሩ ያልሆነ ትውስታ ያላቸው ሰዎች

አስፈሪ (አሳዛኝ) የህይወት ማስታወሻዎች ከተፈፀሙባቸው ሥፍራዎች የተነሳ አንዳንድ ሰዎች እነዚህን ሥፍራዎች ለመጎብኘት የማይችሉ ሰዎች አሉ፡፡ እነርሱን እንዴት ልንረዳቸው እንችላለን?

ብዙውን ጊዜ ፈውስ የሚመጣው ነገሮችን ለማስወገድ ከመሞከር ይልቅ ነገሮችን ከእግዚአብሔር ጋር በመጋፈጥ ነው፡፡ እንደክርስቲያን መሪ እነዚህን የህመም ሥፍራዎች ከእነርሱ ጋር በመሆን ድጋሚ መጎብኘት ይችላል ። ወደ ሥፍራው እንደደረሰን እንደምንወዳቸውና ስለ እነሱ ግድ እንደሚለን ልናሳያቸው እንችላለን ፤ እንዲሁም በዚያ በሚያሳምም የህመም ሥፍራ በቀጥታ ከእነርሱ ጋር አብረን መፀለይ እንችላለን፡ በእግዚአብሔር ልብ ፊት ነገራቸውን እንዲያፈሱ እነርሱን መጠየቅና በእነዚህ ሥፍራዎች ስለተፈፀሙ ስለተከናወነው ጉዳይ ለእርሱ መንገር እንደሚገባ ማሳየት፡፡ (ይህን ማድረግ የማይቻላቸው ከሆነ የእነርሱን ባህርይ በቃላት እንዲገለፁ ማድረግ ይቻላል ሁሉንም ህመማቸውን ለኢየሱስ እንዲሰጡ አበረታቷቸው፡፡ እግዚአብሔር እነርሱ መከራውን በተቀበሉበት ጊዜ አብሮአቸው እንደነበረ ለእነርሱ ልታረጋግጡላቸው ትችላላችሁ (መዝ 139፡ 7-8፣ ኢሳ 63፡9) ስለሆነው ነገር እርሱ ያዝናል፡፡ ከዚያም እግዚአብሔር በመከራቸው ሰዓት ለእነርሱ ስላለው ፍቅርና ርህራሄ እንዲገለጥላቸው ልትፀልዩላቸው ትችላላችሁ፡፡ እነርሱ ባሉበት በዚያው

ሥፍራ የእግዚአብሔርን ፍቅር መለማመድ እንዲችሉ ፀለዩላቸው (ሮሜ 5፡5)። ይህ ከቁስላቸው የሚታገሱበት ነው። በመጨረሻም በእነዚያ ሥፍራ ጭምርም ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ የማወጅ ጊዜ ሊኖር ያስፈልጋል። ኢየሱስ በሰይጣን ላይ ስላለው ዘላለማዊ ድል የምስጋና ጊዜ ማድረግ ።

እነዚህን ሥፍራዎች ለመጎብኘት በጣም ሩቅ ከመሆኑ የተነሳ ለመጎብኘት የማይቻል ከሆነ ወይም ቦታው ደብዛው ጠፍቶ ከሆነ ወይም ከክልላችን /ከሀገራችን/ ውጪ ከሆነስ? ያንን ሥፍራ በፀሎት መጎብኘት ይቻላል: ይህም በሀሳባችን መሆን ይችላል። ያንን ትዕይንት በአዕምሮ እንዲስሉ መጠየቅና ከዚያም ከላይ እንደተጠቀሰው ከእነርሱ ጋር አብሮ መፀለይ።

## የተፈጠረውን መጥፎ አጋጣሚ በተደጋጋሚ ማስታወስ ( አንዳንድ ክስተቶችን በ ህልም ማየት)

በተጨማሪም እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ፍቅር፣ ህልውና መረዳት ያስፈልጋቸዋል። አዕምሮቸው ውስጥ ያለውን ለማስወገድ መሞከር ፈፅሞ ስኬታማ አያደርግም። እነዚህን የተወሰኑ ማስታወሻዎች በጌታ ፊት ማቅረብ እንዲሁም ሁሉንም ነገር ለእርሱ መንገር ያስፈልጋል። ለእርሱ ስንነግረው እውነታውን ብቻ ሳይሆን መናገር የሚገባንን ሁሉንም ነገር ፣ ስሜቱም እንዴት እንደነበረ እና ምን እንደተደረገ ጭምር መናገር እና ሁሉንም ህመም ለእርሱ መስጠት ይገባል። ከዚያም እርሱ እንዲናገራቸው መፀለይ አለብን። እግዚአብሔር በዚያን ጊዜ የት እንደነበረና ምን ዓይነት ስሜት እንደሚሰማው እንዲያሳያቸው መፀለይ እንችላለን። ብዙውን ጊዜ ይህን ፀሎት በዚህ መንገድ ከፀለይን በኋላ የተጎዳው ሰው በልቦናው ዓይን በተደረገው ትዕይንት መካከል ኢየሱስን ማየት ይችላል።

እግዚአብሔር በብዙ ዓይነት መንገድ ለእነርሱ ሊናገር ይችላል። በእግዚአብሔር ቃል፣ በራዕይ፣ በልባቸው በውስጠኛው ድምፅ፣ በክርስቲያኖች የመዋደድ ህይወት ይናገራል። ኢየሱስ እንዲህ ይላል *«እውነትን ታውቃላቸሁ (ለምሳሌ ስለእግዚአብሔር ርህራሄ) እውነትም አርነትን ያወጣችኋል።* (ዮሐ 8፡3)

# ረ/ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ስብስብ

## የእግዚአብሔር መገለጫ

### *እግዚአብሔር ሩህሩህ ነው።*

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዘፀ. 34፡6 | ዘዳ. 30፡3 | መሳ. 2፡18 | ነሀ. 9፡17-19 |
| ነሀ. 9፡27 | መዝ 86፡5 | መዝ. 103፡4፣8 | መዝ. 103፡13 |
| መዝ. 111፡4 | መዝ.116፡5 | መዝ. 119፡156 | መዝ. 135፡14 |
| መዝ. 145፡8 | ኢሳ. 30፡18 | ኢሳ 49፡10-13 | ኢሳ 49፡15 |
| ኢሳ 51፡3 | ኢሳ 54፡7፣10 | ኢሳ 63፡7 | ኤር 31፡20 |
| ሰቆ 3፡22-23 | ህዝ 39፡25 | ሆሴ 2፡19 | ሆሴ 11፡8 |
| ኢዮ 2፡13 | ሚክ. 7፡19 | ዘካ 10፡6 | ሚል 3፡17 |
| ማቴ 9፡36 | ማቴ 14፡14 | ማቴ 20፡34 | ማር 1፡41 |
| ሉቃ. 7፡13 | ሉቃ 15፡20 | 2ኛ ቆሮ 1፡3 | ያዕ 5፡11 |

### *እግዚአብሔር ምህረትን የተሞላ ነው።*

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዘፀ 33፡19 | ዘዳ 4፡ 31 | 1ኛ ዜና 21፡13 | ነሀ 9፡31 |
| መዝ 5፡7 | መዝ 6፡9 | መዝ 25፡6 | መዝ 28፡6 |
| መዝ 31፡22 | መዝ 78፡78 | መዝ 116፡1 | መዝ 142፡1 |
| ምሳ 28፡13 | ኢሳ 55፡7 | ኢሳ 63፡9 | ኤር 3፡12 |
| ዳን 9፡9፣ 18 | ሆሴ 6፡6 | ሚክ 6፡8 | ሚክ 7፡18 |
| ዕንባ 3፡2 | ዘካ 1፡16 | ዘካ 7፡9 | ማቴ 5፡7 |
| ማቴ 9፡13 | ማቴ 18፡33 | ማቴ 23፡23 | ማር 5፡19 |
| ሉቃ 1፡50 | ሉቃ 1፡78-79 | ሉቃ 6፡36 | ሉቃ 10፡ 36-37 |
| ሮሜ 9፡16 | ሮሜ 11፡32 | 2ኛ ቆሮ 4፡1 | ኤፌ 2፡4 |
| 1ጢሞ 1፡2 | 1 ጢሞ 1፡ 13-16 | ቲቶ 3፡5 | ዕብ 2፡17 |
| ዕብ 4፡16 | ያዕ 2፡13 | ያዕ 3፡17 | ያዕ 5፡11 |
| 1ኛ ጴጥ 1፡3 | 1ኛ ጴጥ 2፡10 | 2ዮሐ 1፡3 | ይሁዳ 21-23 |

***እግዚአብሔር ቸር ነው።***

ዘፍ 24፡ 27 ዘፍ 39፡21 2ኛ ሳሙ 9፡3 ዕዝ 9፡9

ኢዮ 10፡12 ምሳ 14፡21፣ 31 ምሳ 19፡17 ኢሳ 54፡8

ኤር 9፡24 ኤር 31፡3 ሆሴ 11፡4 ሉቃ 6፡35

ሐዋ 14፡17 ሮሜ 2፡4 ሮሜ 11፡22 2ኛ ቆሮ 13፡4

ገላ 5፡22 ኤፌ 2፡7 ቆላ 3፡12 ቲቶ 3፡4

**የእግዚአብሔር ፍቅር የማይለወጥ ነው።**

ዘጸ 15፡13 መዝ 13፡5 ዘጸ 21፡7 ዘጸ 32፡10

መዝ 33፡5፣ 18 መዝ 36፡7 መዝ 48፡9 ዘጸ 52፡8

መዝ 107፡8 መዝ 147፡11 ኢሳ 54፡10 ሰቆ 3፡32

ሆሴ 10፡12

**የሚያፅናና አምላክ**

መዝ 10፡17 መዝ 23፡4 መዝ 71፡21 መዝ 86፡17

መዝ 94፡ 19 መዝ 119፡ 50 መዝ 119፡52 መዝ 119፡76

ኢሳ 25፡8 ኢሳ 40፡1 ኢሳ 49፡13 ኢሳ 51፡3

ኢሳ 51፡ 2-3 ኢሳ 51፡9 ኢሳ 57፡18 ኢሳ 61፡2

ኢሳ 66፡13 ኤር 31፡ 13 ዘካ 1፡17 ማቴ 5፡4

ዩሐ 14፡ 18 2ኛ 1፡ 3-7 ፊሊ 1፡2 2ኛ ተሰ 2፡16-17

ራዕ 7፡17 ራዕ 21፡4

**የእግዚአብሔር ፍትህ**

ዘዳ 32፡4 2ኛ ዜና 19፡7 እዮ 37፡23 መዝ 9፡8

ዘዳ 9፡16 ዘዳ 11፡7 ዘዳ 33፡5 ዘዳ 36፡6

ዘዳ 45፡6 ዘዳ 89፡14 ዘዳ 97፡2 ዘዳ 99፡4

ዘዳ 101፡1 ዘዳ 103፡6 ዘዳ 111፡7 ዘዳ 140፡12

ምሳ 29፡26 ኢሳ 5፡16 ኢሳ 28፡17 ኢሳ 30፡18

| | | | |
|---|---|---|---|
| ኢሳ 33፡5 | ኢሳ 42፡1 | ኢሳ 51፡4 | ኢሳ 61፡8 |
| ኤር 9፡24 | ህዝ 18፡25 | ህዝ 33፡17 | ህዝ 34፡16 |
| ዳን 4፡37 | ሆሴ 2፡19 | ሶፎ 3፡5 | ማቴ 12፡18 |
| ሉቃ 18፡7 | ዩሐ 5፡30 | ሮሜ 2፡2 | ሮሜ 3፡25 |
| 2ኛ ተሰ 1፡6 | ራዕ 15፡3 | ራዕ 16፡5 | ራዕ 19፡2 |

**እግዚአብሔር የፍትህ መዳደልን ይፀየፋል**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዘፀ 23፡ 2፣ 6 | ዘዳ 24፡17 | ዘዳ 27፡19 | ኢሳ 5፡7 |
| ኢሳ 29፡21 | ኢሳ 58፡6 | ኢሳ 59፡15 | ኤር 22፡13 |
| ሰቆ 3፡34-36 | ህዝ 9፡9 | ህዝ 22፡29 | አሞፅ 5፡24 |
| አሞፅ 6፡12 | ሚክ 3፡1 | ዘካ 7፡9 | ዘካ 8፡16 |
| ሚል 3፡5 | ማቴ 23፡23 | | |

***እግዚአብሔር ስለ አድልዎ እና ጭፍን ጥላቻ ያለው አመለካከት***

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዘሌ 10፡18 | ዘዳ 16፡19 | 2ኛ ዜና 19፡7 | እዮ 13፡10 |
| እዮ 34፡19 | ሚል 2 ፡9-10 | ማቴ 5፡45 | ሐዋ 10፡28 |
| ሐዋ 10፡34-35 | ሐዋ 15፡7-9 | ሮሜ 2፡11 | ሮሜ 10፡12 |
| 1ኛ 5፡21 | ያቆ 2፡ 1፡9 | ማር 6፡2-3 | ዩሐ 1፡46 |

***እግዚአብሔር ለመበለቶች ወላጅ አልባ ለሆኑና ለጭቁኖች ያስባል።***

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዘዳ 10፡18 | ዘዳ 24፡19 | ዘዳ 26፡12 | ዘዳ 27፡19 |
| መዝ 9፡9 | መዝ 10፡14 | መዝ 10፡18 | መዝ 68፡5 |
| መዝ 82፡3-4 | መዝ 103፡6 | መዝ 146፡ 7፣ 9 | ኢሳ 1፡17 |
| ኢሳ 1፡23 | ኢሳ 58፡ 6፣ 10 | ኤር 5፡28 | ኤር 22፡ 3 |
| ኤር 49፡11 | ሆሴ 14፡3 | ሶፎ 3፡19 | ዘካ 7፡10 |
| ማር 12፡40 | ሉቃ 20፡47 | ዮሐ 14፡18 | 1ጢሞ 5፡3 |

1 ጢሞ 5፡16 ያዕ 1፡27

*እግዚአብሔር ለመበለቶች ባል ይሆናል፡፡*

ኢሳ 54፡5 ኢሳ 62፡4-5 ሆሴ 2፡16-20

## እኛ ለእግዚአብሔር ምን ያህል ዋጋ አለን፡፡

*እርሱ በእኛ ይደሰታል፡፡*

መዝ 147፡11 መዝ 149፡4 ኢሳ 62፡2-4 ሶፎ 3፡17

ኤር 31፡20 መዝ 35፡27 መዝ 37፡23-24 ምሳ 8፡30-31

*የእርሱ ሀብት (ገንዘቡ) ነን፡፡*

ዘፀ 19፡5-6 ዘዳ 7፡6 ዘዳ 14፡2 ዘዳ 26፡18

መዝ 135፡4 ሚል 3፡17

*የዓይኑ ብሌን ነን፡፡*

ዘዳ 32፡10 መዝ 17፡8 ዘካ 2፡8

*ለእርሱ የከበርን ነን፡፡*

ኢሳ 43፡4 ሰቆ 4፡2 መዝ 27፡14 መዝ 116፡15

*የእርሱ ሙሽራ ለእርሱ ቆንጆ ናት*

መሐ. 4፡7-10 ህዝ 16፡14 ዘካ 9፡16-17፣ ራዕ 21፡2 ራዕ 21፡ 9-11

*እኛ በእርሱ የተወደድን ወዳጆቹ ነን*

ዘዳ 33፡ 12 ኤር 31፡33 ኤፌ 1፡7-8 ኤፌ 5፡1-2 ኤፌ 5፡25-27 1ዮሐ 3፡1

*እርሱ ሊባርከን ይወዳል፡፡*

ዘዳ 23፡5 መዝ 24፡5 ኤር 32፡40-41 ሉቃ 11፡13 ሉቃ 12፡32

ሮሜ 10፡2

## የእግዚአብሔር ህዝብ – የተለያየ አመለካከት ያለው ህዝብ

*ክፋትን ለማሸነፍ (ለመግለጥ) ምንም ተስፋ የማይቆርጡ*

መዝ 37፡1 መዝ 37፡7-13 መዝ 73፡1-28

*መንፈሳዊ እይታ ያላቸውና ይህም ጥንካሬን የሚሰጣቸው*

ዕብ 11፡27፣ ዮሐ 14፡19፣ 2ኛ ቆሮ 4፡18፣ 2ኛ ነገስ 6፡17

*ይህንን ዓለም የማይመስሉ*

ሮሜ 12፡1-2 ዮሐ 17፡14-17 1ዮሐ 2፡15

*ከሰዎች ይልቅ እግዚአብሔርን የሚታዘዙ*

የሐዋ 4፡19፣ ዮሐ 12፡42-43

*የሰው ፍርሃት ወጥመድ እንደሆነ የሚያውቁ*

ምሳ 29፡25 ዮሐ 7፡13 ገላ 2፡12

*ክፉ ሰዎችን ከመታዘዝ ይልቅ ከክርስቶስ ጋር መከራን የሚቀበሉ*

ሐዋ 5፡41፣ ሮሜ 8፡17፣ ዕብ 11፡25፣ ያዕ 5፡10፣

1ኛ ጴጥ 2፡20፣ ሮሜ8፡18፣ 2ኛ ቆሮ 4፡17፣ 1ኛ ጴጥ 5፡10

*የእርሱ መንግስት ቅድሚያ የሚሰጠው መሆኑን የሚያውቁ*

ሉቃ 14፡26-27፣ ማቴ 6፡33

*ከራሳቸው ብሔር /ዘር/ ወይም ሀገር ይልቅ ለክርስቲያኖች ሁሉ ትልቅ የሆነ ታማኝነትን የሚያሳዩ*

ኤፌ 2፡19 ገላ 6፡10 ዮሐ 13፡34-35 ዮሐ 15፡12-13

ዩሐ 15፡17 ኤፌ 1፡15፣16 ቆላ 1፡4 1ኛ ተሰ 4፡9-10፣

ዕብ 6፡10 1ኛ ጴጥ 2፡17 1ዮሐ 2፡9-11 ገላ 3፡28

ቆላ 3፡11

*የክርስቲያን አመለካከት ለሚጠሉት (ለጠላቶች)*

ዘፀ 23፡4 ምሳ 24፡ 17 ምሳ 25፡21 ማቴ 5፡44

ሉቃ 6፡27 ሉቃ 6፡35 የሐዋ 7፡60 ሮሜ 12፡20

1ኛ ተሰ 5፡15

## መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ____________ ምን ይላል?

*ስለ ተስፋ*

መዝ9፡18 መዝ 25፡5፣21 መዝ 31፡24 መዝ 33፡18፣ 20

| | | | |
|---|---|---|---|
| መዝ 33፡22 | መዝ 37፡9 | መዝ 42፡ 5፣ 11 | መዝ 62፡ 5 |
| መዝ 71፡14 | መዝ 119፡114 | መዝ 130፡5-7 | መዝ 146፡5 |
| መዝ 147፡11 | ኢሳ 40፡31 | ኢሳ 49፡23 | ኤር 2911 |
| ሰቆ 3፡25 | ሚክ 7፡7 | ማቴ 12፡21 | ሮሜ 4፡18 |
| ሮሜ 5፡ 2፣ 5 | ሮሜ 8፡24-25 | ሮሜ 12፡12 | ሮሜ 15፡4፣ 13 |
| 1ኛ ቆሮ 15፡19 | 2ኛ ቆሮ 1፡10 | 2ኛ ቆሮ 3፡12 | ገላ 5፡5 |
| ኤፌ 1፡18 | ኤፌ 4፡4 | ቆላ 1፡27 | 1ኛ ተሰ 1፡3 |
| 1ኛ ተሰ 4፡13 | 1ኛ ተሰ 5፡8 | 2ኛ ተሰ 2፡16-17 | 1ኛ ጢሞ 6፡17 |
| ቲቶ 2፡13 | ቲቶ 3፡7 | ዕብ 3፡6 | ዕብ 6፡11 |
| ዕብ 6፡18-19 | ዕብ 10፡23 | ዕብ 11፡1 | 1ኛ ጴጥ 1፡3፣ 13 |
| 1ኛ ጴጥ 1፡21 | 1ኛ ጴጥ 3፡15 | 1 ዮሐ 3፡3 | |

### *ስለሀዘንና ስለ ለቅሶ*

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዘፍ 23፡2 | ዘፍ 37፡34 | ዘፍ 50፡10 | ዘሁቁ 20፡29 |
| ዘዳ 34፡8 | 1ኛ ሳሙ 30፡4 | 2ኛ ሳሙ 18፡33 | 2ኛ ሳሙ 19፡2 |
| 1ኛ ዜና 7፡22 | ዕዝ 9፡4 | መዝ 10፡14 | መዝ 31፡9 |
| መዝ 35፡14 | መዝ 38፡6 | መዝ 56፡8 | መዝ 88፡9 |
| መክ 3፡4 | ኢሳ 33፡7 | ኢሳ 61፡2 | ኤር 9፡1 |
| ሰቆ 1፡16 | ማቴ 2፡18 | ማቴ 5፡4 | ሉቃ 6፡21 |
| ዮሐ 11፡33 | ዮሐ 16፡20 | ዮሐ 16፡22 | 1ኛ ተሰ 4፡13 |
| ራዕ 21፡4 | | | |

### *በቀል የተከለከለ ነው። ለእግዚአብሔር አሳልፈህ ስጠው*

ዘሌ 19፡18 ዘዳ 32፡35 መዝ 94፡1 ምሳ 20፡22

ምሳ 24፡29 ህዝ 25፡17 ሚክ 5፡15 ናሆም 1፡2

ማቴ 5፡38-48 ሉቃ 6፡27-36 ሮሜ 12፡17-19 1ኛ ቆሮ 4፡12-13

1ኛ ቆሮ 2፡23 1ኛ ጴጥ 3፡9 2ኛ ተሰ 1፡ 5-10

## ህዝብን ወደዳነ ልብ ማሸጋገር

‹‹ይህ ከተስፋ መቁረጥ ወደ ተስፋ የመጓዝ ጉዞ ነበር፡፡ እግዚአብሔር በድጋሚ ተስፋ በውስጤ እንዲወለድ አደረገ›› (ደቡብ አፍሪካ)

‹‹ልቤ ተፈውሷል›› በተለይም በመስቀል ላይ ህመሜን ስቸነክር፡፡ ከዚህ አገልግሎት በፊት የእኔ ብሔር (ዘር)ቡድን ከሁሉ በላይ አስፈላጊ ነበር፡፡ እኔ ገጀራ አንስቼ አልነበረም፤ ነገር ግን በልቤ ውስጥ አሁንም ነፍሰ ገዳይነት ነበር፡፡ በመስቀል ላይ ሁሉንም ነገር ቸነከርኩት ልቤም ተፈወሰና እኔም ተለወጥኩኝ፡፡ ከዚያም በኋላ የእኔን ዘር (ብሔር) ከሌሎች ብሔሮች ቀዳሚ ነው ማለትን አቆምኩ፡፡ (ሩዋንዳ)



‹መኖሪያ ቤቴ ሙሉ በሙሉ ተቃጠለና አሁን ከተፈናቀሉ ሰዎች ጋር መጠለያ ውስጥ እየኖርኩ ነው፡፡ ከካሌንጂን ብሔር ከሆነ ከማንም ሰው ጋር ምንም ነገር ላለማውራት /ላለመነጋገር/ ወሰንኩ፡፡ እግዚአብሔር እንደጠላኝ ይስማኝ ነበር፣ ለመሞት ፈለኩ፡፡ በጣም ስለተቆጣሁና ተናድጄ ስለነበር አንድ ሰው ለመግደል እንድችል ብዬ ወደዚህ የመስቀል ልውውጥ መምጣትን ፈርቼ ነበር፡፡ ትናንትና ለካሌንጂን ሰው በትክክል ስለተሰማኝ ነገር ለመናገር ቻልኩኝ፡፡ ይህ ተዓምር /አስገራሚ/ ነበር፡፡ አሁን ይቅር ማለትን እና ዳግመኛ ሸክምንም አልተሸከምኩም፡፡ አሁን የካሌንጂን ሰው ለመጎብኘት እየሄድኩ ነው፡፡›› (ኬንያ)፡፡

‹‹በትናንትና ዕለት የተለያየ የሆነ ብሔር (ቡድን) በጋራ ሆነን በመስቀል ልውውጥ ላይ ስለነበረን ጊዜ እግዚአብሔር ይመስገን። ይህ እንደ ወንድማማቾች በአንድነት የቆምንበት ጊዜ ነው። ትናንትና የእኔ የፍቅር ህይወት (የነበረኝ ፍቅር) ስለታደሰ እግዚአብሔር ይመስገን። ሰይጣን ይህንን ከእኛ ሰርቆብን ነበር። በመስቀል ላይ ሁሉንም ነገር ሳደርግ የተሰማኝ ታላቅ ደስታ ከዚህ በፊት ፈፅሞ ተሰምቶኝ አያውቅም›› (ዲሞክራቱክ ሪፐብሊክ ኮንጎ)

‹‹ይህን የመስቀሉን ልውውጥ ከጨርስኩ በኋላ ሌሎችን ለመድረስ ይህን መማርያ መፅሀፍ ከመጠቀም ውጪ ሌላ ምንም ማድረግ አልቻልንም። ይህ መረጃ መስጠት ብቻ አልነበረም፤ ነገር ግን ልባችንንም የነካ ነው። ወደ እኛ ወሳኝ የህይወታችን ክፍል የገባም ነበር። በአንተ /በእናንተ/ ውስጥ እንዳደረገው በእኛም ውስጥ እሳት አንድዷል። አሁን እኛ ከዚህ ችግር ወጥተን ለሌሎች እንድንናገር እንደዚህ ዓይነት መሻት አለን›› (ዚምባብዌ)

‹‹እኔ የታሚል ታይገር ሽምቅ ተዋጊ ነበርኩ። እኛ በኢፍትሓዊነት መከራ የተቀበልን ብቸኛ ሰዎች ነበርን ብዬ አስብ ነበር። አሁን እኔ የሴሪላንካ ሀገር ቋንቋ ተምሬ ለሌሎች መጽናናት ለመሆን እፈልጋለሁ።›› (ሴሪላንካ)

## የጀርባ ሽፋን

ዶክተር ሪኺያኖን ሊዮይድ የቀድሞ የህክምናና የሥነልቦና ህክምና ዶክተር የነበሩ ከ1977/1985 ጀምሮ የሙሉ ጊዜ የክርስቲያን ሥራ ሠራተኛ በመሆንና በባህል ጉዳዮች ላይ በተጨማሪ የሚያገለግሉ ናቸው። ዶ/ር ሪህያኖን ለብዙ ዓመታት ክርስቲያን አገልጋዮችን በማስተማርና ስሜታቸው የተረበሹ ህይወታቸው በጥልቀት የተጎዱትን በማገልገል ላይ ይገኛሉ። ከ1987/1994 ዓ.ም ጀምሮ በሩዋንዳ በእርቅ ሰላም አገልግሎት በግንባር ቀደምትነት (ፈር ቀዳጅነት) ያገለገሉ ሲሆን በተለይም በአፍሪካ ኢንተርፕራይዝ በመነሻነት እያገለገሉ ይገኛሉ። በሺዎች ለሚቆጠሩ የቤተክርስቲያን መሪዎችን በመስቀሉ ወደሚገኘው ፈውስ በመምራትና በብሔረሰቦች መካከል እርቀ ሰላም ለማምጣት በማስተባበር ይሠራሉ። የፈውስና የእርቀ

ሠላም ቡድን በብዙ የተለያዩ ሀገራት ተቋቁሟል። በአሁኑ ሰዓት በዌልስ ውስጥ እየኖረ ሲሆን የህዝቦች ፈውስ በሚል ስም በሚታወቅ በይነ መረብ www.healingthenations.co.uk በሚባለው ድርጅት እየሠሩ ይገኛሉ።

መጋቢ ጆሴፍ ኒያሙቴራ የቀድሞ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህር የነበሩ ሲሆኑ በሩዋንዳ ፔንቲኮስታል ቤተክርስቲያን የክብር መጋቢ ይህንንም አገልግሎት በ1989/1997/ የተቀላቀሉ ናቸው። ምንም እንኳን ዋና ጣቢያው በሩዋንዳ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ዓለም አቀፍ አገልግሎት ነው። እርሱም እንደ አሰልጣኝ እንደ አማካሪ በተለየ ሁኔታ የተሰጠ አገልጋይ ሲሆን ለበረራና አገልግሎት ተብሎ የሚጠራ የራሱ ሀገር በቀል አገልግሎት በማቋቋም እያገለገሉ ያሉ ሲሆን www.rabagirana.org ከሜርሲ ዓለም አቀፍ አገልግሎት ጋር በአጋርነት እያገለገሉ ይገኛሉ።